# ቃል



ዳንኤል ስቲል

ትርጉም - ባሴ ሐበቴ

t.me/OLDBOOKSPDF

# ቃል

ዳንኤላ ስቴል

ትርጉም፡
ባሴ ሐብቴ

ጥቅምት 1984
አዲስ አበባ

እንደገና በ1990 ዓ·ም· ታተመ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

The Promise

by Danielle Steel

የተርጓሚው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው

የሽፋን ሥዕል ፦ ብርሃነ ሕይወት ጌታቸው

t.me/OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ አንድ

በሀርቫርድ ዩኒቨርስቲ ቅጥር ግቢ ፡፡ የኢሊየት ቤት እየተባለ "የሚጠራው ፊት ለፊት ፡፡ የማለዳ ፀሐይ ጀርባቸውን እየዳሰሰቻቸው ፣ ብስክሌቶቻቸውን ለጉዞ አዘጋጁ ፡፡ እና ሁለቱም ድንገት ቀና አሉ ፣ አንዳቸው ከአንዳቸው የሚፈነጠቀውን የፈገግታ ብርሃን በመሻት ፡፡ ወሩ ግንቦት ነበር—የጸደይ ወራት መዳፊያ፣ የወጣትነት ፣ የአበባነት ተምሳሌት ፣ ግንቦት ፡፡ እነሱም እፍላ ወጣቶች ነበሩ ፡፡ በጥቁር ሀጉሯ ላይ የማለዳዋ ፀሐይ ጨረሮቿን ስላሳረፈችበት እንደንፁህ ጥቁር ሀር ሲያንጸባርቅ ይታያል ፡፡ ዓይኖቹ ላይ ያረፉ አይኖቿም በደስታ ብርሃን ይረጫሉ ፡፡ እንዲያ ብርሃንን በሚረጩ ዓይኖቿ እያየችው ፍንድቅ ፣ ፍልቅልቅ ብላ ሳቀች ፡፡

« እሺ የኛ ዶክተር ለመሆኑ ምን ይሰማሃል ? » ስትል ጠየቀች ፣ ፍልቅልቅ ሳቋን እቁማ ፣ በፈገግታ ጉልታ ፡፡

« የሚሰማኝን እንድነግርሽ ከፈለግሽ ሁለት ሳምንት ያህል መታገስ ይኖርብሻል ፡፡ ዲግሪየን እስክቀበል ማለቴ ነው » አለ ፡፡ እሱም እንደሷው በፈገግታ በርቶ ፣ በግንባሩ ላይ ዘፍ ያለውን ነጣ ያለ ወርቅማ የጸጉር ቁባ ራሱን ነቅንቆ ወደ ኋላ እየመለሰ ፡፡

« ዲግሪ ! ? » አለች « ብትፈልግ ከዲግሪህ ጋር እንጦሮጦስ ውረድ ! — እኔ ያልኩህ ስላለፈው ሌሊት ምን ይሰማሃል ነው »

ይሆን ብላ እንደገና በፈገግታ ተበረገደች ፡፡ ምን እንደሚሰማው ለጠየቀችው ጥያቄ መልስ ከመስጠቱ በፊት ኋላዋን በመዳበጥ መልከ ቾፍ አደረጋት ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

« ወደር የለሽ ነው » አለ ኋላዋን እየተመለከተ ። ቀጥሎም «የአንተስ ስሜት እንዴት ነው ? ለመሆኑ ለሽርሽር የተረፈ አቅም አለሽ ? »

ይህ ሲሆን ብስክሌቶቻቸው ላይ ወጥተው በየፊናቸው ፔዳል አስተካክለው በመርገጥ ላይ ነበሩ ።

« አንተስ ፣ አቅሙ የተረፈህ ይመስልሃል ? » አለች ።

ይህን ተናግራ ብስክሌቷን አስነስታ ጥላው ነጐደች ። ትን ሿን ብስክሌት—ከጥቂት ወራት በፊት የተወለደችበትን ቀን ሲያከ ብሩ የገዛላትን ቢስክሌት—አስነስታ ጥላው ነጐደች ። ከልቡ ያፈቅራታል ። ሕይወቱን በሙሉ እሷኑ ሲያፈቅር ነው የኖረው። እሷን የመሰለች ልጅ ጸንሶ ፣ እሷኑ ሲያልም ፣ እሷኑ ሲያፈቅር ኖሯል ። በልቡ ቢጸንሳትም በግዘፈ አካል ካገኛት ፣ ከተዋወቁ ግን ይኸው ሁለት ዓመት ሞላ ።

ከመገናኘታቸው በፊት የእሱም የእሷም ኑሮ የብቸኝነት ኑሮ ነበር ። በእርግጥ ድንግል ሆኖ ኖረ ልንል አንችልም ። ግን የሚ ያገኛቸው ሴቶች ደግሞ ያችን በልቡ የቀረፃትን ፣ ሙሉ ብሎ የሚያስባትን ሴት ሆነው አላገኛቸውም ።

በሀርቫርድ ዩኒቨርስቲ የከፍተኛ ትምህርቱን ለመከታተል ከኒውዮርክ ስቴትስ ወደ ማሳቹሴትስ ስቴት ከመጣበት ጊዜ ጀምሮ ያለውን ብናስብ እንኳ በዚህ ጊዜ ውስጥ ከተለያዩ ከተ ሞች ከመጡ ልጃገረዶች ለዓይኑ የገቡለትን ቀርቦ ከማነጋገር አል ተቆጠበም ። ግን ገና የመጀመሪያ ዲግሪውን ሳያገኝ ተስፋ ቆረጠ ። የመጀመሪያ ዲግሪውን ይዞ የማስተርስና የዶክትሬት ዲግሪውን ለመቀበል በዚያው በሀርቫርድ ዩኒቨርስቲ ትምህርቱን ቀጠለ ። በዚህ ጊዜ ግን ተስፋ ቆርጦ ነበርና ማንኛዋንም ሴት አይሞክርም ነበር ። እነዚያ ከተለያዩ ከተሞች የሚመጡ ልጃገረ ዶች ወይ ዕውቀት ወይ ንጹህ ነፍስ ወይ ታማኝነት ይጐድላ ቸው ነበረና ደጋግሞ መሞከሩን ከንቱ ነገር ብሎ ተወው ፣ የድ



t.me/OLDBOOKSPDF

ናንሲ ማክአሊስተር ማይክል ሂልያርድን እስከታገኝ በነ ፍቧ ውስጥ አንድ ትልቅ ክፍት ቦታ እንዳለ አዘውትራ ታስብ ነበር። ያን ክፍት ቦታ ሊሞላ የሚችል ሰው አገኛለሁ የሚል ሕልም እንኳን አልነበራትም ።

ግን አገኘች ። ዛሬ ያንን ባዶ ማይክል ሞልቶታል ። ዛሬ ያ ባዶ የለም ። የኔ እምትለው ሰው አላት ።

የማይክልና የናንሲ ፍቅር የአንድ ሰሞን ሽርሽብንን ፣ የአ ንድ ሰሞን የስጋን ትኩሳት ለማብረድ የታለመ ተራ ፍቅር አልነበረም—አይደለም ። ነዚህ የሁለቱ ፍቅር በጠንካራ ስሜት ላይ የተመሰረተ ፍቅር ነው ። ይህ ፍቅር ስላለም እሷ በሱ የተ ጓላና የትደላደለ አስተዳደግ የበታችነት አይሰማትም። እሱ የሷን ተራ አስተዳደግ ተመልክቶ እንደ ዝቅተኛ አያያትም ። በዚህ ፈንታ አንዳቸው ከንዳቸው አስተዳደግ እየተማሩ—የኖሩትንና ከዚያ ኑሮ ያገኙትን ልምድ አዋጥተው በመቀየጥ ውብና እጹብ ድንቅ የሆነ አዲስ ኑሮ ፈጠሩ ። ስለዚህ እሷ ለሱ አዲስ አይደለ ችም ፤ እሱም ለሷ አዲስ አይደለም ።

የማይክል እናት ማሪዮን ሂልያርድ የማይክልና የናንሲን ፍቅር ስትሰማ «ለየት ካለ ሰው ጋር ፍቅር ሲይዝህ ደግ አይደ ለም» ስትል ለልጅዋ እንደማስጠንቀቂያም እንደምክርም አድርጋ ነግራው ነበር ። ማሪዮን ነገሯን የጀመረችው «ከሆንች ሰዓሊ ጋር ፍቅር ያዘኝ ብሎ ይንዘላዘላል ብለው ነገሩኝ» በማለት ነበር ።

ማሪዮን ያለችውን ትበል እንጂ ማይክል ናንሲን ያውቃ ታል ። ናንሲን ከማፍቀር የበለጠ ነገር እንደሌለ ያውቃል ። ናንሲ እፈቀረችው መባል ደግሞ ራሱን የቻለ ጽድቅ እንደሆነ ያም ናል ።

ማይክል ልጅም ጅልም ስላይደለ መጥፎና ጥሩን ለራሱ አሳምር ያውቃል ። እናቱ ልዩ ስላለችውም ቢሆን ናንሲ ከሱ የተለየች ፍጡር አይደለችም ። ልዩ የሚያደርጋት ነገር



t.me/OLDBOOKSPDF

ይጥሳትና ከዚያ በኋላ ልክ እንደትናንት ማታ ! . . . እንደ ማታው ! ልክ እንደ . . .

ይህን ሐሳብ በግድ አስወጣው ፤ ከአእምሮው ውስጥ ። ሐሳቡ ሊመለስ ሲታገለው ፤ ብስክሌቱን በኃይል እየነዳ በጥሪ ድምፅ እንዲህ አለ ፤

« የኛ ሐሳብ ቢስ . . . ይህን ያህል . . . » አለ

ዞራ ሳቀችና ፍጥነት ጨመረች ። እሱም ፍጥነት እየጨመረ:

« ጠብቂኝ እንጂ ! ጅል» አለ ።

ብዙ ጊዜ ሳይፈጅ ደረሰባት ። ሁለቱም በጣም ደክመው ነበረና መነጋገር አልቻሉም ። ስለዚህም ፍጥነት ቀንሰው ፤ ጸጥ ብለው ጎን ለጎን በመሆን ጉዟቸውን ቀጠሉ ። በዚህ ሁኔታ ሲጓዙ ሳለ ድንገት ተያዩ ። እጁን ዘረጋላት — እጅዋን ዘርግታ ጣቱን ነካ አድርጋ ለቀቀችው ። ትኩር ብሎ እያያት የደስታና የአድናቆት ሲቃ በተሞላ ድምፅ :—

«ናንሲ» አላት «ናንሲ ዛሬ ደሞ እንዴት ቆንጆዬ ልጅ የሆንሽ መሰለሽ ? » አላት ።

ድምጹ ነፋሻውን የመጸው ወራት አየር እየሰነጠቀ ሲደ ርሳት የሰራ አካላቷ ተፍነከነከ ። በአካባቢያቸው ያለው አለም ምንም ነገር ያልበከለው ፤ ንጹህ ወላንሳ በመሆን ደስታዋን ፤ ደስታውን ፤ ደስታቸውን አደመቀው ።

«ናንሲ !» አላት በዚያው ድምፅ «ናንሲ ! ምን ያህል እን ደምወድሽ ብታውቂ !»

«አይጠፋኝም ! አይጠፋኝም ሚስተር ሂልያርድ» አለች ናንሲ በውሸት — ጠብ ድምፅ ፤ ማይክል በማለት ፋንታ እንደ ሩቅ ሰው ሚስተር ሂልያርድ እያለችው ።

«አይጠፋኝም ! ግን ፍቅርህ የኔን ፍቅር ከፊሉን እንኳ አይሆንም» አለች ።

የውሸት ብሽቀት በሽቆ ፤



t.me/OLDBOOKSPDF

«ባትናገሪ ይሻልሽ ነበር ። ስትናገሪ ነገር የማይገባሽ መሆንሽ ቁልጭ ብሎ ይታያል» ሲል ተናገረ ።

ይህን የብሽሽቅ ጨዋታ በመሻት ነበር ያን መልስ የሰጠችው እንጂ እንደሚወዳትማ ታውቃለች ። ምን ያህል እንደሚወዳት ያወቀችው ፣ ወደኋላ ስታስበው ፣ በመጀመሪያ የተገናኙ እለት ነበር ። . . . ያን ለት «ወይ ለእግዚብሽን ያቀረብሻቸውን ስዕሎች ሁሉ ሽጭልኝ ፣ እምቢ እምትይኝ ከሆነ ደግሞ የለበስ ኩትን ልብስ ሁሉ አውልቂ ጥየ ባደባባይ በጸሐይ ራቁቱን እሄዳለሁ» ሲል ኩስተር ብሎ የዛተው ትዝ አላት ። እንዲያ ያላት እለት ነበር እንደሚወዳት የተረዳችው ።

«ብስል ሰው ብትሆኚ ፍቅሬ ያንችን ሰባት እጥፍ እንደሆነ ይገባሽ ነበር» አለ ።

«ሰባት እጥፍ ? »

«አዎ ! »

«እትዋሽ ! በጭራሽ የሌለ ነገር ! »

«ያንችን . . . »

ነገሩን ሳይጨርስ ፍጥነት ጨምራ ፈትለክ አለችና ዞራ ከሳቀች በኋላ ኩስተር በማለት «ማይክል ! ያንተ ፍቅር መጠን አለው ። የኔ ግን መጠን ስለሌለው ፣ ሰባት ጊዜ ፣ መቶ ጊዜ ተብሎ አይለካም» አለች ። «እንዴት አወቅሽ ? » አላት ፣ እሱም ቢስክሌቱን በኃይል እየነዳ — ሊደርስባት እየተቃረበ ።

ዞራ አየችውና፡—

«ዛር ነገረኝ !» ብላው እንደገና ፍጥነት ጨምራ ራቀችው።

ርቀታቸው ሳይቀንስም ሳይጨምርም ፈትና ኋላ ሆነው ጉዞ ጀመሩ ። በመካከላቸው ያለው ርቀት አካሏን ለሁለተኛ ጊዜ እንዲማትር አደረገው ። እንደገና ሰውነቱ በደስታ ተሞላ ። ሆኖም አሁን እመስኩ ላይ ሊጥላትና . . . አላሰበም ። ለዘለአ



t.me/OLDBOOKSPDF

የለም ከመወሰኑ በፊት ቢያንስ ቢያንስ ከእናቴ ጋር መመካከር አለበት አለች በሐሳቧ ።

«እሰብኩበት ። ወሰንኩ ። ናንሲ በጣም ታስፈልጊኛለሽ» አለ ።

ማይክል ይህን ቢል አዲስ ነገር አልተናገረም ። ሁለቱማ እንደሚጋቡ ከወሰኑ ቆይተዋል ። የሰርጉን እቅድ ሁሉ አውጥተዋል ። ይህ የታወቀ ነገር ነው ። የናንሲ ሐሳብ ቀጠለ ።

«የሰርጋችን ቀንም» አለ ማይክል «የዛሬ አስራአምስት ቀን እንዲሆን ወስኛለሁ ። ያም ማለት ዲግሪየን የምቀበልበት ቀን መሆኑ ነው »

እሷ ቤተሰብ ስለሌላት ድግሱ የአንድ ወገን ብቻ እንደሚሆን ካሰበበት በኋላ የሱ ድግስም ቻቻታ የሌለበት ፣ የልብ ጓደኞቹ ብቻ የሚገኙበት እጥር ምጥን ያለ ሰርግ እንደሚሆን ነገራት ።

«ለምን ማይክ ?» አለችው ።

«ምክንያቱም በጫጫታ የምናሳልፈው ጊዜ የለንም ። ብቻ ችንን መሆን ያስፈልገናል ።» ብሎ መለሰላት ።

ሁለቱም ዝም አሉ ።

«ዛሬ ጧት አንድ ነገር እነግርሻለሁ ብዬ ረሳሁትና እስ ካሁን ሳልነግርሽ ቆየሁ ። . . . ኒው ዮርክ ልሄድ እስቤአለሁ ። ከግሪየን ጋር ስለሰርጋችን ለመመካከር » አለ ፤ ድንገት ።

ናንሲ ዝም አለች ።

«ዛሬውኑ ልሄድ ነው የወሰንኩት »

«ዛሬውኑ ? »

«አዎ ! —ዛሬ ማታ ። እደርሳለሁ »



t.me/OLDBOOKSPDF

ይህን ሲል የብስክሌቷን ፍሬን ያዘች ። በአላምንህም አስተያየት እያየችው ፣

«ዛሬ ?. . . ዛሬ ማታ ! ዛሬ ማታ ?» አለች ።

ራሱን በአዎንታ ነቀነቀ ። ሁለቱም ቆሙ ።

«ማሪዮን እምትስማማ . . . ይመስልሃል ?» አለች በመጠራጠር—መልሱን ለመስማት በመፍራት ።

« አትጠራጠሪ ። ትስማማለች » አለ ።

በጥርጣሬ አይን አየችው።የተናገረውን እሱም እራሱ ያመነበት አልመሰላትም ።

«ጋብቻውን ላትፈቅደው ትችላለች ። ግን ደሞ ሚስት ልም ረጥልህ ለማለትም አትደፍርም ። ይህን ያህል አውቃታለሁ ። ስለ ዚህ አታስቢ ።»

ነገሩ እንኳ እሷን ብቻ አይደለም ራሱን ማይክልንም ያሳ ስበዋል ። ቤትዮዋ ማሪዮን ሂልያርድ ናት ! ማሪዮን የማይክልንና የናንሲን ጋብቻ ካልፈቀደችው እንዳይጋቡ ከመከልከል አትመ ለስም ። ምክንያቱም ለማሪዮን ከራሷ እምነት ውጪ ምንም ነገር የለም ። ይህንን ደግሞ ከናንሲ ይበልጥ የሚያውቀው ማይክል ነው ።

ማሪዮን ሲጀመር ጀምሮ የሁለቱን በፍቅር መተሳሰር አልወ ደደችውም ።

ለረጅም ጊዜ ማሪዮን ያችን ሰአሊ ካልተውክ እረግምሃ ለሁ ፣ እከድሃለሁ ፣ ውርስህን አፈርሳለሁ ስትልና ስታስፈራራው፣ ማይክል የመጣው ፣ ይምጣ የቻልሽውን ሁሉ አድርጊ ናንሲን ግን አልተውም ፣ ሲል ደብዳቤም መፃፍ፣ ስልክም መደወል ሲያቆም ! ጠርታ ስታባብለው ፣ የተለያዩ ምርጫዎች ስታቀርብለት ፣ ቆንጆ ከሚባሉት የደህና ቤተሰብ ቤቶች ልጆች ጋር ስታስተዋውቀው ማይክል ግን ሁሉን ችላ ብሎ ወደናንሲ ሲመለስ ፣ ናንሲን እንደሚ ወድ ደጋግሞ ሲነግራት ስታስፈራራው . . .



t.me/OLDBOOKSPDF

ጨረሱ። ለድህረ ምረቃ ፕሮግራም ሁለቱም ቀጠሉ። በነዚህ ዓመታት ውስጥ ባህሪ ለባህሪ ተዋውቀዋል። ዛሬ እንደወንድማማች እንጂ እንደጓደኛ አይደሉም።

ቤንጃሚን (ቤን) አቭሪን ከማሪዮን ጋር ካስተዋወቀው ቆይቷል። ትምህርቱን ጨርሶ ሲመረቅ ቤን ለማሪዮን ማመልከቻ እንዲያስገባ ነገረው። ቤን እንደተባለው አደረገ። ማይክ ስለቤን ጉብዝና ለእናቱ ተናገረ። በመጨረሻ ማሪዮን ቤንን እንደተቀበለችው ለማይክል አስታወቀች።

«ቤን ስራውን እን· ነኝ አውቋል?» አለች ናንሲ።

ማይክ በአሉታ ራሱን ነቀነቀና—

«ከአሁኑ ቢያውቅ ደስታው ይበላሽበታል ብዬ አልነገርኩትም። በድንገት ነገሬ ላስፈነድቀው አስቤአለሁ»

ናንሲ ገረማት።

«ምን አይነት ሰው ነህ ማይክ? በጣም ደግ ነህ።
አንተን ስለወደድኩ ምን ያህል የታደልኩ ሰው ነኝ እላለሁ»

«አመሰግናለሁ ሚስዝ ሂልያርድ»

«አባክህ እንዲያ ብለህ አትጥራኝ ማይ ክ?»

«ለምንድነው እንዲያ ብዬ የማልጠራሽ? ምክንያቱን ልትነግሪኝ ትችያለሽ? ይልቅስ ካሁኑ ተላመጅው። አዲስ ስምኮ በቀላሉ አይለመድም»

«ሁሉም ነገር ቢሆን ይለመዳል። ሲሆን የማይለመድ ነገር የለም» አለች። ቀጥላም «ለጊዜው ግን ናንሲ ማክአሊስተር ነኝ። ሚስ ማክአሊስተር ብትለኝ በቂ ነው» ስትል ጨመረች።

« ጊዜ የለንም’ኮ የኔ እመቤት። ለአሥራ አምስት ቀን
እድሜ ማክአሊስተር ብልሽ ግፍ አይሆንም!»

ይህን ብሎ ድምጹን ወደ ጨዋታ ቅኝት ቀየረና—



t.me/OLDBOOKSPDF

«አሁን ወንድና ሴቱ ይለይ!—ባዛሩ በር ድረስ እሽቅድምድም እንገጥማለን። ይለይ!» አለ ።

«ይለይ!» አለች።

ትንፋሽ እስኪያጥራቸው ድረስ በፍጥነት መንዳት ጀመሩ። ለረጅም ጊዜ ማንም አልቀደመም ።

በመጨረሻ ማይክል ከናንሲ ግማሽ ደቂቃ ቀድሞ ደረሰ። ሁለቱም ከላይ የተንጋገሩትን ረስተው ድንገት በተፈጠረው ደስታ ታጥበው ፥ ፀድተው ነበር ።

ቢስኪሌታቸውን ዛፍ አስደግፈው ወደ ባዛሩ ቅጥር ሄዱ። በዚህ ጭር ባለ ገጠር ማንም ቢስክሌት እንደማይሰርቅ እርግጠኛ ነበሩ ።

ይህ ሁሉ ከሆነ ከጥቂት ደቂቃ በኋላ ኮርን (ከንቅረቀንዳው ተቀትሎ በቅቤ የተዘፈዘፈ በቆሎ) ይዘው መጋጥ ጀመሩ ። ቅቤው እጃቸውን እረስርሶ ሲንጠባጠብ ይታይ ነበር ። በቆሎ ቅቅል በቅቤ አቸውን ካስገቡ በኋላ « ሆት ዶግ » በብዛት ጎስጎሱ ። በላዩ ላይም ቀዝቃዛ ቢራ ቸለሱበት ። ናንሲ በዚህ አላበቃችም ። ጣፍጭ የሆነና እንደ ጀላቲ መያዣ እንጨት ያለው ግን ጠንከር ያለ ሳይሆን ጥጥ የሚመስል ካንዲ ፍሎስ የሚሉት ጣፍጭ ነገር፣ መብላት ቀጠለች። ካንዲ ፍሎሱን ስትልስ ፊቷና ጉንጯ ፥ ከንፈሯና አፍንጫዋ ተቀባብተው ነበር ።

«ልጅ መሆንሽ ነው?—አይቀፍሽም?» አላት ማይክል

«ይጣፍጠኛል' ንጂ ለምን ይቀፈኛል ! ትንሽ ብትቀምስ እስሩን ትረሽነው ነበር» አለች ካንዲ ፍሎሱን አፏ ውስጥ እንደ ያዘች። ስለዚህም ቃላቷ ሁሉ የህፃን ልጅ ይመስሉ ነበር። ሁኔታዋም የህፃን ልጅ ነበር።

«ምን አይነት ፍጡር እንደሆንሽ አይገባኝም ! ባየሁሽ ቁጥር የበለጠ ቆንጆ የምትሆኚው ለምንድነው?» አለ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ሰፊ ፈገግታ ለገሰችው። ፊቷ በካንዲ ፍሎሱ ተበካክቷል። መሀረብ አውጥና ጉንጯን ጠረገላት ። ከዚያም ፣

«ፊትሽ እንዲህ ባይበካከል' ኮ ፎቶ እንነሳ ነበር» አላት ።

«ፎቶ!» አለች እንደእምቦሳት ግመት ሆዋን እየፈነጠዘች «የት የት ነው እምንነሳው?»

ይህን እያለች ሌላ ካንዲ ፍሎስ አነሳች ። እንስታ ስትልስ ጥጥ መሰሉ ጣፋጭ ነገር ፊቷን ሸፈናት ።

«ምንም ማድረግ አይቻልም። ለምን አይበቃሽም ይኸ ነገር?»
«የት ነው ፎቶ እምንነሳው? የት ነው?»

«ፏዚያ ጋ»

ፎቶግራፍ ተነሱ ። ፎቶግራፍ አንሺዎቹ የተለያዩ ልብሶች ይሰጣሉ ። ማይክና ናንሲ የርሄት በትለርን የስካርለት ኦ ሀራን አለባበስ መረጡ ። (ርሄት በትለርና ስካርለት ኦ ሀራን (Gone with the Wind) በሚል ርእስ አሜሪካዊቷ ማርጋሬት ሚቸል በፃፈችው ዝነኛ ልብወለድ መፅሐፍ ውስጥ ዋናዎቹ ገፀ ባህርያት ናቸው።) እንደርሄት በትለርና እንደ ስካርለት ኦ ሀራ ለብሰው የተነሱትን ፎቶግራፍ ሲያዩ ተገረሙ ። ናንሲ የደቡባዊ ዩናይትድ ስቴትስን ቆንጃጅት ልብስ ስትለብስ ውብቷ ጎላ። ማይክልም ኮስታራ ወንድ ሆኖ ቁጭ አለ ።

ይህን ያየው ፎቶግራፍ አንሺ ሳይቀር ገንዘቡን ተቀብሎ ፎቶግራፉን ሲሰጣቸው—

«ይህን ፎቶ መስጠት አልነበረብኝም ። አንድ የተለየ ደስ የሚል ነገር አላችሁ ። ይህን ካየሁ ደግሞ ቆየሁ። ስለዚህ ቢያንስ ፎቶግራፋችሁን እያየሁ ደስ እንዲለኝ ማስቀረት ነበረብኝ» አላቸው ።

ናንሲ ይህን ስትሰማ ደስ አላት ። ማይክልም ፈገግ አለ ። ያን ያህል ግን አልተደሰተም። ምክንያቱም አይቶ እማያደንቃት



t.me/OLDBOOKSPDF

እንደሌለ ያውቃል። ግን የሱ ናት ። ሙሉ በሙሉ የሱ ትሆናለች። ሁለት ሳምንት . . . የናንሲ ጉትጎታ ከሃሣብ መለሰው።

«ተመልከት. . . እዚያ ጋ. . . ቀለበት በጠርሙስ አንገት ማስገባት ጨዋታ አለ» አለች።

ይህን ጨዋታ ለመጫወት ከልጅነቷ ጀምሮ ትልቅ ጉጉት ነበራት ። ሆኖም እድሉ አጋጥሟት አያውቅም ። ከእንስሳ ማውታን ማሳደጊያው ውስጥ የነበሩ መነኩሴ ሞግዚቶቿን ስትጠይቅ ከፍተኛ ገንዘብን የሚያባክን ጥቅም የሌለው ጨዋታ ስለሆነ አይቻልም ይሏት ነበር ።

«መጫወት እንችላለን ? » አለች ገንዘብ ይባክናል እንዳይላት እየፈራች ።

«ከፈለግን ደግሞ ማን ይከለክለናል ? ያውም አንች ብለሽ!» አለና በትያትር ደንብ ለጥ ብሎ እጅ ነሳት ። ከዚያም ክንዱን በክንዷ ታስገባ ዘንድ አዘጋጀላት ። ጅንን እያለ ለመሄድ ሞከረ ። ናንሲ ግን በዚያ የመጀነን ጉዞ ተካፋይ ልትሆን አልተቻላትም። ልክ እንደ እንቦሳ መፈንጠዝ ጀምራ ነበርና ። ይህ ፈንጠዚያ ደግሞ ይበልጥ ደስ አሰኘው።

«አሁኑኑ መጫወት እንችላለን?»

«አሳምረን ነዋ ፍቅሬ»

አንድ ዶላር አወጣና ለአጫዋቹ ሰጠ። አጫዋቹም ከተለመደው አራት እጥፍ የሆነ ቁጥር ያላቸው ቀለበቶች ሰጣት ። ሩቡ በቂ ነበር። እሷ ግን ልምድ ስለሌላት ያን ሁሉ ቀለበት ተቀብላ ወደ ጠርሙሶቹ ብትወረውርም ጉዳዩ ፍየል ወዲህ ቅዝምዝም ወዲያ ነበር ። ማይክል ደስ ብሎት ሲያስተውላት ከቆየ በኋላ ፣

«ምን ማግኘት ነው እምትፈልጊው?» ሲል ጠየቃት ።

«ያንገት ጌጠቹን ! መቁጠሪያ መሰል ጌጠችን» አለች።

በጣም እንደጓጓች ድምጿም አይኗም ጠቅላላ አካላቷም ይናገር ነበር ። «እንደዚያ አይነት ውብ ጌጥ አጥልቄ አላውቅም» አለች።



t.me/OLDBOOKSPDF

«እኔም አንዳንዴ እንደሱ ይመስለኛል» አለች ናንሲ «ግን አላምንም ።»

«አልፈቅድም ብላ ምን ትፈይዳለች ?» አላት ማይክ እያቋረጣት ።

«ካልፈቀደች ልንጋባ አንችልም !»

«ለምን ? ልትነግሪኝ ትችያለሽ ? ለምን ?»

«ካልፈቀደች !...» ብላ ምን ማድረግ ይቻላልን ትከሻዋን ነቀንቅ በማድረግ ገለፀችለት ። «ሞኝ አትሁኝ ናንሲ» አላት ። «እኔም አንችም ለአካለ መጠን ደርሰናል ። ሕጋዊ የሆነ ነገር ሁሉ በፈቃዳችን ልንፈጽም መብት ያለን ሰዎች ነን ። ስለዚህ አይሆንም ካለች መኪናችን ውስጥ ገብተን ወዳንድ ፍርድ ቤት መንዝ ነው ። በሕግ እንጋባለን እየሽ ?»

ያንለት ያነጋገሩን ገራገርነት በማጤን ብቻ ሳቀች። ይህ እን ዲህ ቀላል አድርጎ ያቀረበው ሃሳብ ግን ከማንኛውም ሰው ይበ ልጥ አስቸጋሪ ሆኖ የሚታየው ለሱ ለራሱ ለማይክል ነበር ። ለማ ይክል ግማሽ ሕይወቱ «ኮተር ሂልያርድ» አይደለምን ።

እጅዋን ያዘ ሲያደርጋት ከሐሳቧ ተመለሰች ።

«እንዴት ቆንጆ ነሽ!» አላት ፣ አይን አይኗን እየተመለከተ። ደካማ ፈገግታ አሳየችው ።

«በጣም እወድሻለሁ !... የኔ እመቤት !» አለ ።

«ማይክ ... በጣም እወድሀለሁ» አለችው ።

ከብስክሌቷ ወርዳ ቆመች ። እሱም ወረደ ።

ገጽታዋም ፣ አይኗም ጥያቄ ይታይባቸዋል ። ጭንቀት ይነበ ብባቸዋል ። አቅፎ ሳማት ። የገፅታዋና የዓይኖቿ ጥያቄ ተሰረዘ ። በሁለቱም ልብ ውስጥ የሰፈረው ጥያቄና ጭንቀትም በልባቸው ውስጥ ተዳፈነ ። ያን ጥያቄ ሊያጠፉ የሚችል የለም—ካላንድ



t.me/OLDBOOKSPDF

ሰው ፣ ካለማሪዮን ሂልያርድ ። ያች ሴት ካልራራች የሁለቱም ልብ በተጻፈነው ጥያቄ ይግባል ። ከብስክሌቷ ወርዳ ብስክሌቷን ለቅቃ እቅፉ ላይ አረፈች ።

« ማይክል የማሪዮንን ሆድ ቢያራራልን . . . ቢረዳን » አለች ። «አይዞሽ ! ይረዳናል ። ሁሉ ነገር ቀላል ሆኖ ነው የም ናገኘው ፣ እመኚኝ» አላት ።

ይህን ብሎ በቀልድ ቁጣ፣

«ምንድነው ነገሩ ፣ አሁን ጉዞ እንቀጥላለን ፣ ወይስ እዚህ ቆመን ማደር ሊኖርብን ነው ? » አለ ።

ጉዞአቸውን ሲቀጥሉ ማሪዮን ሂልያርድን የረሷት ይመስ ላሉ ። ሆኖም ማሪዮን ከነፍሳቸው አልተሰረዘችም ። ማሪዮን አንድ ሰው ብትሆንም ትልቅ ተጻምም ናት ። በቀላሉ አትሰረዝም ። ማሪዮን በማይክል ሕይወት ውስጥ የቆመች ትልቅ ምሶሶ ናት ። ዛሬ ዛሬ ደግሞ በናንሲ ሕይወት ውስጥም ጎልታ መታየት ጀመረች ።

በብስክሌታቸው ላይ ሆነው ለሙን መሬት እያጻረጡ እሽቅ ድምድሙን ተያያዙት ። እንዴ ስትቀድመው ወዲያው ሲደርስባት ጎን ለጎን ሲጓዙ እንደገና ስትቀድመው ዞራ ስታሾፍበት ሊደር ስባት ሲያባርራት . . . እንደለቆ ጥጃ ሲፈነጥዙ . . . በሌላ ጊዜ ፀጥ ብለው ጎን ለጎን ሲጓዙ . . . እነሱም ገሰገሱ፣ ፀሐ ይም የሰማዩን ዳገት እየተንፏቀቀች ወጣች ።

ወደ ሪቨር ቢች ሲቃረቡ ተሲያት ተቃርቦ ነበር ።

ከፊት ለፊታቸው የመጣው መኪና ፍጥነቱን ሲቀንስ ቤን አብሪ መሆኑን ተመለከቱ ። « ታዲያስ ? » አለ ቤን ።

«ሃይ ቤን ! » አለች ናንሲ ።

ሰላምታ ተለዋወጡ ። ከቤን አብሪ ጎን አንዲት ልጅ ተቀምጣ ለች ። ናንሲም ሆነች ማይክል ይህችኛዋን ልጅ አይተዋት አያ ውቁም ። ግን ከየት አገኛት ? ብለው አልተደነቁም ። ቤን አብሪ



t.me/OLDBOOKSPDF

ዛሬ አብሯት ከወጣች ልጅ ጋር ነገ ተመልሶ አይወጣም ። ይሆን ባህሪውን ናንሲም ማይክልም ያውቃሉ ።

«ወዷት ነው ? ወደ ባዛሩ የምትሔዱ ይመስላል» አለ ቤን።

ሁለቱም ዝም አሉ ። ሀሳባቸው እልጅቷ ላይ ነበር ። ይሆን የተገነዘበው ቤን ቶሎ ብሎ አስተዋወቃቸው ።

«ጃኒት ትባላለች — ናንሲና ማይክል ይባላሉ » አለ ።

«ባዛሩ እንዴት ነው ? » አለ ማይክል ከትውውቁ በኋላ።

«እንግዲህ እንደየሰዉ ነው ። ግን » አለና እባዛሩ ውስጥ ያለውን ነገር ይዘረዝርላቸው ጀመር ። በሚወ... አሸንፈው ያመጧቸውን ዕቃዎች፣የገዟቸውን ምግቦችና መጠ...ችም ነገራቸው ። ንለግውን ሳይጨርስ፣—«በቃ በቃ . . . እንሔዳለን ። በቂ አድርገህ እንድንሔድ ገፋፍተኸናል » አለ ማይክል ። ከዚያም ወደ ናንሲ ዞሮ « ምን ይመስልሻል ደረስ ብለን ብንመለስ ? » ሲል ጥያቄ አቀረበላት ።

«በጣም ደስ ይለኛል » አለች ናንሲ ። « እናንተስ አብራችሁን አትመለሱም ቤን ? »

እንደጠየቀች መልሱን አገኘች ። ቤን አብሮ ጎምዥቷል ። ጃኒትም ብትሆን ረሀቡን ለማርካት የጓጓች ትመስላለች ። የሁለቱን ሰዎች በሥጋ የመፈላለግ ችኮላ ስትገነዘብ ናንሲ ማክእሊ ስተር እንደመሳቅ ቃጣት ። ቢሆንም ሳቋ አካሏን ዘልቆ ሳይታይ አፍና አስቀረችው ።

«እኛ እንኳ አረፈድንበት » አለ ቤን « አሁን ወደ ቤት ! ደክመናል ። በስንት ሰዓት የወጣን መሰላችሁ —ቢት ፣ በአሥራ ሁለት ሰዓት »

ይሆን ብሎ !

« ግን ማታ ፒሳ መብላት የሚፈልግ ካለ ቤት ድረስ ብቅ ማለት ይችላል » ሲል ጨመረ ።

ማይክልና ቤን ጎረቤት ናቸው ።



t.me/OLDBOOKSPDF

«ለመሆኑሳ እራት የምትበሉት የት ነው ዛሬ ?»

ቤን ይህን ሲጠይቅ ናንሲ፡—

«ሲኛር፤ ዛሬ እራት የምንበላው የት ነው ?» ስትል ማይክልን ጠየቀች ። ማይክል ራሱን በአሉታ ነቅንቀና፡—

«ጉዳይ አለኝ . . . እራት ላይ አንገናኝም» ሲል በደፈናው መልስ ሰጠ ። «ሆናም» አለ ቀጠለና « በሌላ ቀን ለፒሳው ፕሮግራም ልንይዝ እንችላለን »

ጉዳይ አለኝ ? ቀርጦ ማሪዮንን ሊያነጋግራት አስቧል ማለት ነው ።

«እሺ እንግዲያ . . . እንዳያ ከሆነ በቸር ይግጠመን » አለ ቤን።ጄኒትና ቤን ለስንብት እጃቸውን አወዛወዙ ። ከሄዱ በኋላ፡—

«እውነት ዛሬ ማታ ልትሔድ አስበሀል ?» አለች ናንሲ።

«እንዲህ አይነት ፊዝ የምሞክር ይመስልሻል ባንቸ ላይ?» አላት ጥያቄዋን በጥያቄ እየመለሰ።

«አይመስለኝም፤ ሆኖም- -»

«የኔ እመቤት ምንም የሚያስጨንቅሽ ነገር የለም ። እርግጠኛ ነኝ ማሪዮን ትስማማለች። እርግጠኛ ነኝ ሁሉ ነገር እንዳሰብነው ይሆናል» አለና ድምጹን ወደ ደስታ ቅኝት ለውጦ « በነገራችን ላይ ማሪዮን ቤንን ልትቀበለው ነው፤ ስራ ለመግባት አመልክቶ እንደነበር ነግሬሻለሁ አይደል ?»

«ነግረኸኛል።»

«በጣም ጥሩ ሆነ እየሽ ። ስራውን የምንጀምረው ባንድ ቀን ነው። የምንሰራበት ቦታ ግን ይለያያል»

ማይክ ይህን ለናንሲ ሲነግር ጉዳዩ ለራሱ እንጂ ለአንድ ሌላ ሰው የተፈፀመለት አይመስልም ነበር ።

ቤንና ማይክ የተዋወቁት እዚሁ ሀርቫርድ ውስጥ ነበር—የመጀመሪያ አመት ተማሪ ሆነው ። የኮሌጅ ትምህርታቸውን አብረው



t.me/OLDBOOKSPDF

በህፃንነቷ የምትመኘው አንዱ ትልቅ ነገር ይኸ የአንገት ጌጥ ነበር ። የሚያብረቀርቅ ፣ የሚያምር ጌጥ ስታይ እንደጓጓች ነበር ያደገችው ። «የምትፈልጊው ነገር ቀለል ያለውን ነውና ውዴ ። ሌላ ! ለምሳሌ ጃኒት የያዘችውን አይነት አትፈልጊም ?» አላት ።

አንገቷን በአሉታ ነቀነቀች።

«እሺ ተይው። የፈለግሽውን ለማድረግ ታዛዥሽ ነኝ» አለና ወረ ወረ። ሶስቱም ኢላማቸውን መቱ ። የአንገት ጌጡን ተቀብሎ ለናንሲ አጠለቀላት ። «ይኸው ወጣቷ እመቤት። የፈለግሽውን አምጥቻለሁ። ያንችው ነው። ኢንሹራንስ ልንገባለት ይገባል ብለሽ ትገምቻለሽ?»

«አይ ! እንግዲህ በአንገት ጌጤ ላይ ማሾፍህን አቁም ። ደስ አይልም?» ቀስ ብላ ነካ ነካ አደረገቻቸው ። እያንዳንዳቸውን ነቅንቅ ነቅንቅ —ሲያንፀባርቁ ለማየት ።

«ጌጡ ሳይሆን ውበና ደስ እምትይ አንቺ ብቻ ነሽ። ስለዚህ ሌላ ልብሽ የሚሻው ነገር ቢኖር ታዛዥሽ እሆናለሁ»

የደስደስ የተሞላ ፈገግታዋን አሳየችውና !

«ሌላ ካንዲ ፍሎስ ግዛልኝ» አለችው ።

ገዛላት ።

ከባዛሩ ወጡ። ቢስክሌቶቻቸውን ወዳቆሙበት ቦታ ሲያመሩ ማይክል፣—«እንዴት ነው! ደከሞሻል?» ሲል ጠየቃት ።

«በጣምም አልደከመኝም »

«ወደ ቤታችን እንመለስ ወይስ ወደ ፊት እንቀጥል ?»

«ምን ያህል እንቀጥል ? »

«ቅርብ ነው ! ላሳይሽ የምፈልገው ቦታ አለ ። እባህሩ ዳር አካባቢ አንድ ደስ እምትለኝ ቦታ አለች »

«ደስ ይለኛል እንሂዳ»



t.me/OLDBOOKSPDF

ቀስ ብለው ፣ ፀጥ ብለው ጉዟቸውን ቀጠሉ ። ድንገት ሁለቱም በየግል ሀሳባቸው ተዋጡ ። የቅድሙ መቃበጥና መቧረቅ ጥጋቸው የሸሸ ይመስል ነበር ። ወደ ባህሩ ዳር ሲደርሱ—ገና ይህ ነው ሳይላት ሊያሳያት የፈለገውን ቦታ አወቀችው። በትላልቅ ዛፎች የተከበበ ፣ ለመፋቀርና ትዝታን ለዘላለም አጥምዶ ለማስቀረት ተብሎ የተሰራ የመሰለ ቦታ ነበረ ። ይህን ቦታ እንዳየች ናንሲ እየፈነደቀች ፡—

« እንዴት ደስ ይላል ! እንኳን መጣን» አለች ።

«በጣም ደስ ይላል ፤አይደለም ?» አለ ፤ ደስ ሲላት ስላዩ እየ ተደሰተ ።

«በጣም በጣም» አለች እየፈነጠዘች ።

« ብዙ ጊዜ አስባለሁ ፤ ላሳይሽ »

«ዛሬ እንኳን ይዘኸኝ መጣህ ። እንኳን አላመለጠኝ»

እጅ ለጅ ተያይዘው በፀጥታ ተቀመጡ ። ለተወሰነ ጊዜ በዚህ ሁኔታ ቆዩ ። ከዚያም ናንሲ ድንገት ብድግ አለች ።

«ምነው ?... ስለቸሽ ?» አለ ማይክል ።

«አይ . . . አልሰለቸኝም »

«ታዲያ የት መሄድ ፈለግሽ ?»

«አንድ ጉዳይ አለኝ . . .»

«ነው? ቀላል ነው ። ወደጥሻው ገባ ብለሽ . . . »

«ግን እኔ ያሰብኩት ሌላ ነው »

ይህን ብላ ጥላው ሮጠች ። ቀስ እያለ ተከተላት ። በልቡ ምን ይሆን ደግሞ አሁን ያሰበችው ? የሚል ጥያቄ እየጠየቀ ። ጐንበስ ብላ አንድ ትልቅ ድንጋይ ለመፈንቀል ትታገል ጀመር። ድንጋዩ ግን ንቅንቅም አላለ ።

« ቲል ፣ ከድንጋይ ጋር ትታገላለች ?» አለ የቀልድ አየናቃት። ቀና አላለችም። ትግሏን ቀጠለች ።



t.me/OLDBOOKSPDF

«ቦታ ቦታ ። ይህን ያህል ካስፈለገሽ እንዲ ዞር በይልኝ ፤ ልሞክረው» አለ ።

ደካከማ ቀና አለች ።

«ግን ለምንድነው የፈለግሽው ?» አላት ፤ ድካሟን በፊቷ ላይ ሲያይ ግራ ተጋብቶ ።

«ለሆነ ጉዳይ . . . ትንሽ ብቻ ብድግ ካለ ይበቃል» አለች ።

ማይክ ሲሞክረው ድንጋዩ በመጠኑ ተነሳ ።

«በቃ ! እንደሱ ያዘው» አለች ናንሲ ።

ከዚያም እባዛሩ ላይ ማይክል ትሟውቶ በማሸንፍ የሸለማትን የጌጥ መቁጠሪያ አውልቃ እድንጋዩ ሥር ከተተችው ። ይህን ካደረገች በኋላ ፤

«አሁን ልቀቀው» አለች ።

«ምን ? የአንገት ጌጥሽን መቅበር ፈለግሽ ?»

«አዎ ! ልቀቀው»

ድንጋዩ ወደ ቦታው ተመለሰ ። መቁጠሪያ መሰሉ ጌጥ ተቀበረ ። ከዚያም መቁጠሪያው የተቀበረበትን ቦታ እየተመለከተች ፤

«ይህ የአንገት ጌጥ በቃል ኪዳን የመተሳሰራችን ቋሚ ምስክር ነው ። ይህ ምስክርም ይህ ድንጋይ ፤ ይህ ወይብና እነዚህ አድባር መሳይ ዛፎች በዚህ ቦታ ላይ እስከ ኖሩ ድረስ ይኖራል ። ትስማማለህ ?» አለች ።

«እስማማለሁ ግን...» አለ ፈገግ እያለ « ግን ፍቅራችን የጀማሪ ፍቅር አልሆነም ?»

«ምን ነውር አለበት ? ...ከፍቅር ሁሉ የጀማሪ ፍቅር ንጹህ ፍቅር መሆኑን አታውቅም ? ስለዚህ እንዲያ አይነት ፍቅር ሲያጋጥምህ በደንብ መያዝ ፡ መንከባከብ ፡ መጠለያ ማበጀት አለብህ » አለች ።

«ልክ ነሽ ። በጣም ልክ ነሽ ፍቅሬ ። አሁን ፍቅራችን እዚህ ቦታ ላይ መጠለያ ይኖረዋል» አለ ማይክል ፡ ደስ እያለው ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ምቹ የቤት ዕቃ ሊኖራት አይችልም ። ሆኖም ሰላም በዕቃ ዓይነት ወይም በቤት ስፋት አይገኝም ። ሰላም በዚህ ሁኔታ ቢገኝ ኖሮ እጅግ ሰፊ የሆነው የእናቱ መኖሪያ ይሆን ነበር ለማይክል ሰላምና ዕረፍትን የሚሰጠው ። ያ ያደገበት ቤት ለሱ ምንም አልነበረም ።

የናንሲ ጠባብ ቤትና በውስጧ ያሉት ትናንሽ ዕቃዎች ግን ከላይ እንደተገለጠው ሰላምና ዕረፍት ይሰጡታል ። ናንሲ ሰዓሊ ናትና ውበትን የሚያደንቅ ዓይን አላት ። ይህ ስለሆነ ከሰፋፊና ግዙፍ ውድ የእናቱ መኖሪያ ቤት ዕቃዎች ይልቅ የናንሲ የቤት ዕቃዎች ያስደስቱታል ።

ግድግዳው የተቀባው ቀለም ፣ የወለሉ ምንጣፎች ለማይክ ደስታ ይሰጡታል ። በዚህ ሁሉ ላይ ናንሲ በሕይወት ተከብባ የምትኖር ፍጡር ናት ። የተጀመሩም ሆኑ ያለቁ ሥዕሎቿ ለሱ ሕያው ናቸው ። በመጀመሪያ በእግዚብሔር አዳራሽ ውስጥ ሲያያቸው ያየባቸው ሕያውነት ይበልጥ እውን እየሆነ ሄዶ ነበር ።

በዚህ ሁሉ ላይ በናቱ ግዙፍ አዳራሾችም ውስጥ ሆነ የትም ቦታ የማያገኘው ፣ እንደልቡ ሆኖ እየተዝናና የሚያጣጥመው ያ የቀለም ሽታ ለሱ የሱስ ያህል ነበር ።

« እዚህ ቤት ስሆን ምን ያህል ደስ እንደሚለኝ ታውቂያ ልሽ ፣ ናንሲ ? » አለ ማይክል ።

« አዎ . . . አውቃለሁ » አለችና ዞር ብላ በናፍቆት ተመለከተችው ። ከዚያም ቤቷን በፍቅር እየቃኘች ፣—

«እኔም እንደዚች ቤት ደስ የሚለኝ ቦታ የለም ። ለመሆኑ ከተጋባን በኋላ እንዴት ነው እምናደርገው ? »

«ቀላል ነው ። እነዚህን ውብ ነገሮች ጥርግ አድርገን እንወስዳለን ። ኒውዮርክ ውስጥ ሽክ ያለ አፓርታማ እንከራያለን ። ዕቃዎቹ ሲገቡ ቤቱ እንደዚሁ ደስ ይለናል ። አይመስልሽም ? » አለ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

እንዲህ እያለ በቤቱ ውስጥ ያሉትን ውብ ነገሮች ሲቃኝ ድንገት ዓይኑ አንድ ነገር ላይ አረፈ፤

«እንዴ! ያ ምንድን ነው?» አለ ወደ ሸራ መወጠሪያ አትሮኖሷ እያመለከተ «አዲስ ሥዕል ነው?»

ብድግ ብሎ ወደ አትሮኑሱ እየሄደ፤

«መቼ ነው የሠራሽው? የጀመርሽው?» አለ።

ሥዕሉ ገና ጅምር ቢሆንም የመሳብ ምስጢራዊ ኃይሉ እሚከሰትበት ደረጃ ላይ ደርሷል። ሥዕሉ የገጸ ምድርን ምስል የያዘ ሲሆን የተፈጠረው ገጸ ምስልም ዛፎች የሚገኙበት አንድ ሜዳን ያሳያል።

ማይክል ወደ ሥዕሉ ተጠጋ።

በዚህ ጊዜ ሌላ ነገር አጋጠመው። በሥዕሉ ውስጥ ከሚገኙት ዛፎች ባንደኛው ላይ የተደበቀ ልጅ አየ። የልጁ እግሮች ተንጠልጥለው እሱም ላለመውደቅ ሽምቅቅ ብሎ ታየው።

ሥዕሉን በተመስጦ ሲመለከት ከቆየ በኋላ ወደ ልጁ እያመለከተ፤

«ሥዕሉ ተስሎ ሲያበቃ ልጁ እንዲህ እንዳለ ይታያል? ማለት የዛፍ ቅጠልም ሆነ ቅርንጫፍ አይሸፍነውም?» ሲል ጠየቃት።

«እንዲህ እንዳለ ማለት አይቻልም። ሆኖም በሆነ መንገድ ልጁ መኖሩ አይቀርም» አለችው። ቀጥላም «እንዴት ነው? ወደድከው?» ስትል ጠየቀችው።

ጠየቀችው እንጂ እንደወደደው፤ እንዳደነቀው ከፊቱ ላይ አንብባለች። ሥዕሎቿን እንደሱ የሚወዳቸው ሰው እጋጥሟት አያውቅም። ሐሳቧን እንደሱ የሚረዳላት ሰው የለም።

«ወደድከው ወይ?! አፈቀርከት እንጂ!» አላት።

«ነው?»



t.me/OLDBOOKSPDF

«አትጠራጠሪ »

«እንግዲያስ ይህ ሥዕል የግልህ ነው ። ለሠርግህ ዕለት የግ በረከትልህ ስጦታ ነው » አለች ።

« ተስማምቻለሁ ። የሠርግ ወሬ ብታነሺ » አለና ሰዓቱን ዐዩ ፤ «አሁን መሄድ አለብኝ »

«ምንድነው እሱ ? ግድ ዛሬ መሔድ አለብህ ማለት ነው ? »

«አዎ መሄድ አለብኝ ። ከምሽቱ አንድ ሰዓት ኒውዮርክ ብደርስ ፣ እንደበረራው ትራፊክ ሁኔታ እቤት አንድ ሰዓት ተኩል ብደርስ ፣ ማሪዮንን አነጋግሬ የሠርጋችንን ጉዳይ አዘጋ ጅቼ ከጨረስኩ በኋላ ወደዚህ ለመመለስ ቢያንስ የመጨረሻዋን አውሮፕላን አገኛለሁ። ተመልሼ እዚሁ ነው እማድረው ። ገቢቶ ? »

«ገቢቶ » አለች ። ሆኖም ለምን እንደሆነ አትወቅ እንጂ የዚ ያን ዕለት አካሄዱ በምንም መንገድ ደስ አላላትም ። የሆነ ነገር ቅር ይላታል ። ባይሔድ . . . ባይሔድ የሚል ሐሳብ ይሰማታል።

«ሁሉም ነገር እንዲሳካ እመኛለሁ » አለች ።

«አትጠራጠሪ ፣ ይሳካል » አላት ።

ሆኖም ራሱ የተናገረውን እንደማይተማመንበት ሁለቱም ያውቃሉ ። ማሪዮንን ያውቋታላ ።

ተቃቅፈው ለረጅም ጊዜ ቆዩ ።

ከዚያም ተሰናብቷት ሲወጣ ሲዘጋጅ ፣

«እንግዲህ ይቅናህ አለችው »

«ናንሲ በጣም እወድሻለሁ » ሲል መለሰላት ።

ሔደ ።

ለረጅም ጊዜ ብቻዋን ቁጭ ብላ እባዛሩ ላይ የተነሱትን ፎቶ ግራፍ ተመለከተች ። ማይክል ሂልያርድና ናንሲ ማክአሊስተር —እይደለም ፤ ርሄት በትለርና ስካርለት ኦሀራ—እንዚህ ሁለቱ ዘለ ኣለም በፍቅር ሲነሱ ይኖራሉ ። ማይክና ናንሲ የርሄትንና የስካ



t.me/OLDBOOKSPDF

ርስትን ልብስ ለብሰው ሲታዩ የዚያ አለባበስ ዘመኑ አልፏልና ትንሽ ምኝ አስመስሏቸዋል ። ሆኖም ደስ ብሏቸዋል ። ዋናው ደስታ ነው ።

እዎ ፍቅር ደስታ ነው ። ምነው ማሪዮን ሂልያርድ ይህን መገንዘብ ብትችል ! ምኝነትና ደስታ እንደሚለያዩ ብታውቅ! የተለያየ ሰው ነው እንጂ ምኝ እንደሌለ ቢገባት ። ደስታ ግን ደስታ ነው ። ምነው ማሪዮን በሐሳብና በኑሮ መካከል ያለውን ልዩነት ብታውቅ !

ናኒስ ብቻዋን በሐሳብ . . .



t.me/OLDBOOKSPDF

## ምዕራፍ ሁለት

የመመገቢያ ቤቱ ጠረጴዛ እንደ አንድ ፀጥተኛ ሃይቅ ተን ጣለ ። ያብረቀርቃል ። ከዳር እስከዳር ያብረቀርቃል እንዳንል ከወደ አንድ ወገን የሆነ ነገር አርፎበታል ። ይለያል ማለት እንጂ ውበቱን ይቀንሳል ማለት አይደለም ። እጅግ ውብ በሆነ የኪነጥበብ ሥራ የተጌጠው የጠረጴዛ ልብስ ፣ በሱ ላይ ያረፈው በሰማያዊና በወርቅማ ቀለም ያጌጠ ሳህንና ባጠገቡ የተቀመጠው የቡና ዕቃዎችን የያዘ ሰርቪስ— ሁሉም ውብት ናቸው ። ከነዚህ አጠገብ የመጥሪያ ደወል ይታያል ። ይህም ደወል ከንጹህ ብር የተሠራ ነው ።

ማሪዮን ሂልያርድ ብቻዋን ተቀምጣለች ። ሲጋራዋን ለኩሳ ጭሱን ስባ ወደ ውጭ ካስወጣች በኋላ በረጅሙ ተነፈሰች ። በጣም እንደደከማት ይታወቅባታል ። እሁድ ሲባል ሁል ጊዜም ቢሆን ለሷ አድካሚ ቀን ነው ። አንዳንድ ጊዜ ከሥራ ቀኖች ይልቅ እሁድ ሥራ ይበዛብኛል ብላ ታስባለች ። እውነት ነው ። እሁድ ለሷ ሥራ የበዛበት አድካሚ ቀን ነው ።

ለሚደርሷት ደብዳቤዎች መልስ መስጠት አለባት ። የቤተ ሰቡን አስተዳደር የምትከታተለውም እራሷ ናት ። ለቅመም ስንት ወጣ ? ምን ያህል ሥጋ ተገዛ ? የቤት መወልወያ ሰም ወዘተ —ሁሉን መቆጣጠር አለባት ። ይህን ደግሞ በሌላ ቀን ልታከ ናውነው አትችልም ። ማሪዮን የኮተር ሂልያርድ ሥራ አስኪያጅ ናት ። ኮተር ሂልያርድ ደግሞ ካንድ መንግሥት የሚስተካከል ግዙፍ የአርኪቴክቸር ድርጅት ነው ።

የቤቱን አያያዝ እሁድ እሁድ ነው የምትቆጣጠረው ። ሥራው አሰልቺና አድካሚ ነው ። እንኳን ዛሬ ባለቤቷ ሞቶ ፣ የሰውን ሥራ ደርባ በምትሠራበት ጊዜ ያኔም ሥራዋ ይኸው የቤት



t.me/OLDBOOKSPDF

አስተዳደር በነበረበት ጊዜም ቢሆን የቤት ለቤት ሥራ ለማሪዮን አሰልቺ ነበረ ። ሆኖም ሥራ ሥራ ነው ። ኃላፊነት ኃላፊነት ነው ። ስለዚህም ማሪዮን ሥራዋን ትሰራለች ። ዛሬም ያኔም።

ብቻ ያኔ ማሪዮን አንድ ደስታ ነበራት ። ያኔ ማንም ማን ሳይ ሻማት ማይክልን ታቅፈው ፣ ታጫውተው ነበር ። ማንም ማን ሳይሻማት ማይክልን ይዛ ሽርሽር ትሔድ ነበር . . .

ከማይክል ጋር ታሳልፍ የነበረውን ጊዜ ስታስታውስ እት ዝታ ውስጥ ትነከራ ሳታስበው አይኗን እንቅልፍ እንደያዛት አድርጋ ጨፈነች ። ያ ደስ የሚል ጊዜ ነበር ። እነዚያ እሁዶች ልዩ ነበሩ ። ያለፈ ጊዜ ተመልሶ እማይመጣ ።

ዛሬም ማይክልን ትወደዋለች ። ዛሬም ሁሉን ነገር የምታ ስበው ለማይክል ነው ። የወንዱንም የሴቱንም ሥራ አጣምራ እምትሰራው ፣ ከሰኞ እስከ ሰኞ ያለ እረፍት እምትደክመው ለማይ ክል ነው ። ደግሞም ልፋቷ ከንቱ አይደለም ። ይኸውና ይህን ግዙፍ ድርጅት እንደሰፋ ፣ እንደተንሰራፋ እንዲደርሰው አድርጋለች ። ከዚህ የበለጠ ቅርስ ፣ ከዚህ የላቀ ውርስ ከየት ሊመጣ ይችላል ?

ድንገት ትዝ አላት ፣ በሁለት አመቱ ድክ ድክ ሲል ፣ ያ ረጂም ዘመን ። ማይክል ታያት ። ህፃኑ ማይክል ! ውስጧ በትዝታው በራ . . .

«እንዴት ውብ ሆነሃል ፤ አምረሃል እማዬ!»

ይህን ድምፅ ስትሰማ በቅጽበት አይኗን ገለጠች ። ስታስ በው የነበረው ማይክል ልጅዋን ፣ ባላሰበችው ጊዜ እፊቷ ቆሞ ስታየው አይኗን ማመን አቃታት ። ሆኖም እውነት ነውና ነገሩ አስደነቃት ። ተነስታ ልክ እንደህፃንነቱ እቅፏ ልትስመው ፈለ ገች ። ግን አስፈላጊ አይደለም ። የዚያ አይነቱ ስሜታዊ ነገር እጉል ልቡን ያለሰልሰዋል ስትል አሰበች ። ስለዚህም ስሜ ቷን አምቃ ቀዝቀዝ ባለ አነጋገር ፦



t.me/OLDBOOKSPDF

«ስትገባ እንዴት ሳልሰማህ ቀረሁ በል?» ስትል ጠየቀችው ።

«ቁልፍ አለኝ አይደል ፣ በሱ ነው የተጠቀምኩት » አላት። «ልቀመጥ እችላለሁ?»

«መጠርጠሩስ !... እሚበላ ነገር ያስፈልግሃል ? »

ሚካኤል ረጋ ብሎ ሄደና አጠረቤዛው ላይ የተቀመጠውን ሣህን ጎንበስ ብሎ አያዩና እሣህኑ ላይ የቀረውን ምግብ እሚ መረምር እየመሰለ ፣

«እሃ !... ምንድን ነበር የተበላው ? ቸኮላት ነው?» ሲል እናቱን ጠየቀ ።

ማሪዮን ይህን ስታይ ደስ አላት ። ሆኖም ደስታዋን መግረም በመሰለ ሳቅ ገታችው ። በልቧ ግን አንዳንዴ ልጅ ይመስለኛል ። ደሞም ልጅ ነው ። አሁን የጠየቀው የልጅ ጥያቄ ነውኮ ስትል አሰበች ።

የበላችውን ምግብ ነገረችውና እንዲመጣለት ይፈልግ እን ደሆነ ከጠየቀችው በኋላ ፣

«ከፈለግህ ይምጣልህ ። ማንንም አስቸግራለሁ ብለህ አታ ስብ ። ማቲስ አሁንም እማድቤት ነው ያለችው » አለች ።

«ምናልባት የቀረውን እየጎራረሰች ይሆናል!» ብሎ ሳቀ ።

ይህን እውነት ሊሆን የሚችል ቀልድ ስትሰማ ማሪዮን ሳቅ አለች ። እና የመጥሪያ ደወሏን እንቃጨለች ።

እፍታ ሳትቆይ ማቲስ መጣች ። ጥቁር በወርቃማ ሀር የተ ዘመዘመ ልብስ ለብሳ ፊቷ በፈገግታ ተበርግዶ ። ማቲስ ሁሌም ስትጠራ እንዲህ ሆና ነው እምትቀርበው ። አድሜ ልኳን ሀብ ታሞችን ስታገለግል በመኖሯ የሚያስደስታቸውን ነገሮች አሳ ምሯ ታውቃለች ።

«አቤት እሜቤቴ» አለች ማቲስ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

«ማቲስ ለሚስትር ሂልያርድ ቡና አምጪለት እስኪ» አለችና ወደ ማይክል ዞራ «የሚበላ ነገርስ ምን ይሁንልህ የኔ ውድ ?» ስትል ጠየቀችው ።

ራሱን በአሉታ እየነቀነቀ ፦

«ቡና ... ቡና ብቻ ይበቃል» አላት ።

«እሺ እመቤቴ» አለች ማቲስ ።

ማሪዮን ምንም መልስ አልሰጠችም ። ይህም ለቅሰበት ያህል በማይክል አእምሮ ውስጥ ጥያቄ አመጣበት ። ይህ ጥያቄ ድንገት የተፈጠረ አልነበረም ። ይህን ያህል ጊዜ አብሯት ሲኖር እናቱ አንድም ቀን ለአሽከሮችና ለቤት አገልጋዮች «ኣሰይ» ወይም «አበጀህ» ወይም ሌላ ይህን የመሰለ የምስጋና ቃል ስትናገር ሰምቷት አያውቅም ። ለምንድነው እንዲህ እማታደርገው? ይላል ። ምናልባት በቢ ቤት አገልጋይ ሁሉ ገና ሲፈጠር እቧን ሊያገለግል እንደተፈጠረ አድርጋ ስለምትቆጥር ይሆን ? ይህንና ይህን የመሳሰሉ ጥያቄዎች መጡበት ። ከዚያም ፣ ምናልባትም ... ይልና መልስ ሊሰጥ ይሞክራል ። ስለአስተዳደጓ የሰማውን ፣ ስለአኗኗሯ ያየውን ማሰብ ይሞክራል ።

ማሪዮን ሂልያርድ የተወለደችው ትጅግ ሀብታም ከሆነ ቤተሰብ ነው ። ስለዚህ ከተወለደችበት ጊዜ ጀምሮ ባካባቢዋ አሽከሮችንና አገልጋዮችን ስታይ ነው ያደገችው ። ምንም እንኳ ገና በሶስት አመቷ እናቷና ታላቅ ወንድሟ በመኪና አደጋ ቢሞቱባትና ብቸኛ ህፃን ሆና ያደገች ቢመስል ማሪዮን ግን ብትወድቅ በሚያነሱ ፣ ብታለቅስ በሚያባብሉ አገልጋዮች ቶክበ ነው ያደገችው ።

የወንድሟ መሞትም ጎዶት ሊባል አይችልም ። ቢኖር የቅትር የአርኪቴክቸር ድርጅት ወራሽ እሱ ነበር የሚሆነው ። የሱ ሞት ግን የዚህ ግዙፍ ድርጅት ብቸኛ ወራሽ ለመሆን አበቃት ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ዣሬም ቢሆን በፀሀፊዎችና በአማካሪዎች ተከባ ሲያዘጠዝ ጡሳት ነው እምትታየው ። ስለዚህ አንድ ሰው ለፈጸመው ግል ጋሎት ምን ብላ በምን መንገድ ጥቅሙን ተገንዝባ ምስጋና ልት ሰጥ ትችላለች?

«ትምህርቱስ ፤ ኮሌጅ እንዴት ነው?» አለች እናቱ ከሀሳቡ እያናጠበችው ።

«ለአምላክ ምስጋና ይድረሰውና ልንገላገለው ነው ። ሁለት ሳምንት ያህል ። በቃ ! » አለ ማይክል ።

«ይገባኛል ፤ መቼም የምታኮራ ልጅ ነህ ። የዶክትሬት ዲግሪን ማግኘት የሚያስከብር ነገር ነው ። በተለይ በአርኪቴ ክቸር መሆኑ በጣም ያኮራኛል ። የልብ ልብ ይሰጠኛል» ።

ምስጋናውን ሲሰማ ልክ እንደልጅነቱ ደስታና ሀፍረት የተቀላቀለበት ስሜት ተሰማው ።

« ቤን አብሪስ ደህና ነው ? »

«ደህና ነው» አለ ከእፍረቱ ለመውጣት እየሞከረ ።

«ደግ ፤ በዚህ ሳምንት ውስጥ ልናነጋግረው እንሞክራለን— ስለሥራው ጉዳይ ማለት ነው ። ያው እስካሁን አልተነገረውም አይደለም?» አለች ማሪዮን ጉዳዩ ሚስጥር ሆና ይቆይ በማለቱ ማይክልን በልቧ ገና ልጅ ነው እንጂ ሥራውን እናቱ ፈቅዳ ልሀለች ማለት እየቻለ ፣ ድንገት መንገሩ ጥቅሙ ምንድነው? እን ድትለው አድርጓታል ።

«አልሰማም ። ማንም አልነገረውም» አለ ማይክል ።

«እዎ ሳይሰማ መቆየቱ ጥሩ ነው » አለች ። «ደግሞም የያዝ ንለት ቦታም ኮ በቀላሉ የሚታይ አይደለም ። ትልቅ ቦታ ነው ። »

«ለሱ ችሎታ ያ ቦታ አይበዛበትም»

«ያ እንዲሆን ተስፋ አደርጋለሁ ። » ድንገት አየት አድርጋው ፣ «አንተስ እንዴት ነው ? ተዘጋጅተሀል ። በንግዳችን ላይ ቢሮህ ተዘጋጅቶ ወደ ማለቱ ነው ። »



t.me/OLDBOOKSPDF

ስለ ቢሮው ሲያስብ አይኖቹ በደስታ ሲያንፀባርቁ ይታዩ ነበር ። ቢሮውን አይቶታል ፤ ወዶታል ። አሰራሩ ዱሮ የአባቱ ቢሮ የነበረውን ሲመስል ፣ የውስጥ ድርጅቱ ፣ መቀመጫው፣ጠረ ቤዛውና የመሳሰለው ሁሉ ከለንደን የመጣ ነው ። ራሷ እና ትየው ናት ባለፈው ለእረፍት ሄዳ በነበረበት ጊዜ አስርታ ያመጣችው ።

«እኔ ዝግጁ ነኝ ፤ ቢሮው ማለቱ ደግሞ ጥሩ ነው ።ብቻ የው ስጡን ዝግጅት በሚመለከት አንዳንድ ነገሮች አሉ ። በመጀመ ሪያ የግድግዳውን ቀለም ልየው ብዬ ነው» አለ ።

«ምንም መጨነቅ አያሻህም ፣ ግድግዳው ላይ ስለሚሰቀሉ ስእሎችና ስለሌላውም እኔው ራሴ እስቤበት አዘጋጅቼልሀለሁ » አለች ማሪዮን ።

እሱም ይሀንኑ አድርጓል ። ናንሲ ንድፎችን መራርጣለት የሚ ሆኑትን ለይቶ አስቀምጧል ። ናንሲ ትዝ ስትለው ማሪዮን ደግሞ ስለግድግዳው ንድፎች ዝግጅት ስትነግረው ደርሶ ደሙ ልውጥ አለ ። ይህ እንደሆነ እናትዮዋም ወዲያው ገባት ።

«እማዬ» አለ አጠገቧ እየተቀመጠና በረጅሙ የመከፋት ትንፋሽ እየተነፈሰ ። በዚህ ጊዜ ማቲስ ቡናውን ይዛለት ገባች። ቡናውን ስታቀርብለት ፣

«አመሰግናለሁ ፣ ማቲስ » አለ ማይክል ።

«ምን አድርጌ ምስጋና ሚስተር ሂልያርድ» አለች ማቲስ በጣም ደስ ተሰኝታ ።

ማይክልን ትወደዋለች ። ሁኔታው ሁሉ ሰብዓዊነት የተቀላ ቀለበት ነው እንጂ እንደጌታ አይደለም ። አለችንጂ . . .

«ሌላ እሚያስፈልግ ነገር አለ ፣ እመይቴ?» አለች ማቲስ በምታውቅበት ትህትና ።

«ምንም አያስፈልግም ። እንዲያውም ማይክ ቡናሀን ያዝና እቤተ መጻሀፍታችን ብንገባ ይሻላል» አለች ማሪዮን ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ገጭቶ ገደለ ? ይህን የመሳሰሉ ጥያቄዎች ። ርግጥ ችግር የለውም ።
እሱ ደህና ይሁን እንጂ ሁሉም ነገር መፍትሄ ያገኛል ። እሷ
እያለች ችግር ሊያስጨንቀው አይችልም ።

« ችግር . . . ችግርስ አላጋጠመኝም ። ግን አንድ ልንመ
ካከርበት የምፈልገው ነገር አለ ። »

«ልንመካከርበት» ማለቱ ደስ አላለውም « ልንገርሽ» ማለት
ነበረበት ። ተሳሳትኩ አለ በሀሳቡ ።

«ካሰብኩበት በኋላ » አለ «እንግዲህ ሁለታችንም የልባ
ችንን መነጋገር ይኖርብናል ።

«እንዳባባልህኮ አብዛኛውን ጊዜ ከልብ የማንነጋገር ነው
ያስመሰልከው ። »

«ነው ። አሁንም ቢሆን እሉ አንዳንድ ነገሮች ፣ እኔም የል
ቤን የማልነግርሽ ፣ አንቺም የልብሽን አማትነግሪኝ ። ስለናንሲ
የየልባችንን በልባችን እንጂ የልባችንን አውጥተን ተነጋግረን
አናውቅም ፤ አይደለም እማዬ ? »

«ናንሲ ? ናንሲ አልከኝ?» አለች ድምጽዋ ባዶ ነበር ። ንቀ
ቷን ግን ሰምቶታል ። ብድግ ብለህ በጥፊ አልሳት የሚል ስሜት
ተናነቀው ።

«አዎ ናንሲ ። ናንሲ ማክአሊስተር ። ጓደኛዬ»

«አ . . . ትዝ አለችኝ» አለችና ስኒና ማንኪያ እያጫወተች
ትንሽ ዝም ካለች በኋላ « ታዲያ ስለናንሲ የልባችንን ያልተነ
ጋገርነው መቼ ነው ? » ስትል ጠየቀች ።

«ምን ጊዜም ። አንድም ቀን የልባችንን ተነጋግረን አናው
ቅም ። አንች ሁልጊዜ ናንሲ እንደሌለች ፣ እንዳልተፈጠረች ለማ
ድረግ ስትሞክሪ አይሻለሁ ። እኔ ደግሞ ስለናንሲ እንዳልነግርሽ
ድንገት እንዳትበሳጪ እያልኩ እሰጋለሁ ። ስለዚህ ተነጋግረን
አናውቅም ። አሁን ግን ግድ መነጋገር አለብን ። ናንሲን ለማ
ግባት ወስኛለሁ ። በዚህ በአስራ አምስት ቀን ውስጥ ጋብቻ



t.me/OLDBOOKSPDF

ችንን እንፈጽማለን» አለና በኃይል ተነፈሰ ። ወደ ኋላው ተለጠ ጠና ተቀመጠ ።

«ነገሩ እንዲያ ነው?» አለች ማሪዮን ቀዝቀዝ ብላ ። «ግባኝ፤ ግን ምንው ተጣደፋችሁ ? ምን ተፈጠረ? አረገዘች ወይስ»

«እርግዝና? አላረገዘችም»

«ኢድለኛ ነን አትለኝም ። ግን እንዲያ ካልሆነ ለምንድነው እምትጋቡት? ማለት ለምንድነው ጋብቻው በድንገት በዚህ ባሥራ አምስት ቀን ውስጥ መፈጸም አለበት ብላችሁ የወሰና ችሁት ? »

« ምክንያቱም ያኔ ትምህርቴን እጨርሳለሁ ። ምክንያቱም ያኔ ወደኒውዮርክ መመለሴና እዚህ መኖሬ ስለሆነ መጋባታችን አስፈላጊ ስለሆነ . . . »

« አስፈላጊ ስትል ለማን ? » አለች ማሪዮን እንደበረዶ በሚ ቀዘቅዝ ድምፅ ። ያ ድምፅዋ ማንንም ሰው ተስፋ ሊያስቆርጥ ይችላል ።

« ለኛ ... ለኛ ስለሚያስፈልግ ፥ ለሁላችን »

« ለኔ ግን አስፈላጊ አይደለም ። ጋብቻችሁ አያስፈልገ ኝም ። » አለች ። ትንሽ ለስለስ ያለች በመምሰል እንዲህ ስትል ቀጠለች ፥

« በነገራችን ላይ ከዚህ በፊት የፎርድን ማዕከል ስንሰራ ድርጅታችን ምን ያህል ትርፍ እንዳገኘ ታውቃለህ ። ያንን ማዕከል ያሰሩት ሰዎች በሽፋንም ቢሆን የሚሳተፉበት አንድ የህክምና ማዕከል ሳንፍራንሲስኮ ውስጥ ለማሰራት ኮንትራቱን ወስደን ጨር ሰናል ። ለዚያ ሥራ ሌላ ሰው የለኝም ። እምነቱን ሁሉ የጣልኩት ባንተ ላይ ነው ስለዚህ አትችልም ። ለሚስት ጊዜ ያለህ አይመስለኝም ። ሚስት በኋላ ሰርተህ ጠንክር ካልክ በኋላ ታገ ባለህ ። እውነቱን ለመናገር ማንም ትሁን ማን፥ እንዲህ ተቻ ኩለህ እንድታገባ አልፈልግም ። እንድትቆይ እፈልጋለሁ »



t.me/OLDBOOKSPDF

« ግን ኮ እማዬ ፤ ናንሲ ሥራ እምትከለክለኝ ሳትሆን እም ትረዳኝ ልጅ ናት— ለሁላችንም ትልቅ ስጦታ ናት እኮ »

« ትሆን ይሆናል ። ምናልባትም ደህና ስጦታ ! . . . ለመሆኑ ግን የሚፈጠረውን አጉል ወሬ አስበህበታል ? »

« የምን አጉል ወሬ ? »

« ማንነቷን አውቀሃል፤ ስለአስተዳደጓስ ነግራሃለች ? »

« ማን እንደሆነች ስትይ ምን ማለትሽ ነው ? »

« ታገሰኝና ሁሉን ነገር ግልፅ አደርግልሃለሁ ። »

ይህን ብላ የቡና ሲኒዋን አስቀምጣ ተነሳችና ከጽሕፈት ጠረጴዛዋ ኪስ አንድ ፋይል አውጥታ ሰጠችው ።

«ምንድነው ይኼ ደሞ ? »

«ሪፖርት ነው ፤ አንብበው ። ማንነቷን ፤ ማለት የስአሊዋን ጓደኛህን ማንነት አጥንቶ የሚነግረኝ ሰው በግል ቀጥሬ ያገኘሁት ሪፖርት ነው ። ይህን አይቼ ካወቅኳት በኋላ ነገሩ ሁሉ የማይሆን መሆኑ ገባኝ ። ቁጭ በል እባክህ ። እና አንብበህ ራስህ ተረዳ »

አልተቀመጠም እንደቆመ ማንበብ ቀጠለ። ሪፖርቱ ስለናንሲ ማክአሊስተር ወላጆች ይናገራል ።

የናንሲ አባት የሞተው ናንሲ ገና ሕፃን እያለች ሲሆን ያረፈበት ቦታም በእስር ቤት ውስጥ እንደሆነ ይናገራል ።

የናንሲ እናት አባትየው በሞት በሁለተኛው ዓመት ላይ እንዳረፈች ሪፖርቱ ይገልፃል ።

አባትዬው እስር ቤት የገባበት ምክንያት መሳሪያ ታጥቆ ዝርፊያ በመፈጸሙ እንደነበረ በሪፖርቱ ላይ ተገልጿል ።

እንዲሁም እናትዮዋ የሞተችው መጠጥ ታበዛ ስለነበረ በዚሁ ጠንቅ እንደሆነ ተዘግቧል ። ወዘተ



t.me/OLDBOOKSPDF

ማይክል ከዚህ በላይ ሊያነብ አልቻለም። በዚያ ላይ ደግሞ፣

«እንዴት ዓይነት ጥሩ ሰው እንደመረጥክ ታየህ የኔ ልጅ!» የሚለው የማሪዮን ድምፅ በጣም አናደደው። ማሪዮን ይህን ስትል ፋይሉን አሽቀንጥሮ ጣለና፣

«እንዲህ ዓይነት ትርኪ ምርኪ አላነብም!» አለ።

«ሚስትህ ስትሆን ግን አይቀፍህም» አለች ማሪዮን።

«እሷ እንዲህ አይደለችም። ወላጆችዋ ምንም ይሁኑ ምን እሷ አይደለችም! አባቷ ቀማኛ ቢሆን፣ እናቷ ሰካራም ብትሆን የናንሲ ጥፋት እምኑ ላይ ነው?»

«ጥፋት አልከኝ? ጥፋት የለባትም ግን ከነዚህ ሰዎች ስለተ ወለደች አልታደለችም። አልተባረከችም። አንተም እሷን ስታገባ ያው ነው ልጄ! ምን ነካህ? እደግ እንጂ። ይህ ሀብትኮ በቀላሉ አልተገኘም። በንት ጥረት ተደርጐበታል። እና በአጉል ወሬ ለአጉል ሴት ስንል ይፈታ ነው እምትል እንዴ። ዛሬ ትልቅ ሰው ነህ ኮለኑር አስብ። በኔ በኩል ነገሩን መርሳት አለብህ ከሚለው የተለየ ምንም አማራጭ አይታየኝም» አለች ማሪዮን።

«ርሳው? ይረሳዋል ብለሽ አሰቢ!» ድንገት ነበር እንደብራቅ የጮኸው። «ዘላለም አለሚን ያንችን ግንባር ሳይና ያንችን ፈቃድ ስፈጽም መኖር እንደማልችል አታውቂም እንዴ እናት አለም! የለም አልችልም! እንደፈረስ ገርተሽ፣ ሰንገሽ ድርጅት የምትይውን ጋሪ የሚጐትት እንሰሳ ልታደርጊኝ ነው እንዴ እምትፈልጊው? ቢፈልግ ውርስ የምትይው ነገር እንጦርጦስ ይውረድ። እኔ ምፈልገው ስራ ነው። እድርጅት ውስጥ ተቀጥሬ እሰራለሁ። ከዚያ በላይ ምንም አልፈልግም። ከዚያ በላይ ምንም አትፈልጊብኝ። ተቀ ማሪሽ ስሆን ስራዬን እንጂ ሕይወቴን በሙሉ ያንቺ ልታደርጊው



t.me/OLDBOOKSPDF

አትችይም ። ስለዚህ በሌላ በኩል ያሻኝን የማድረግ መብት አለኝ ። የወደድኳትን የማግባት መብት አለኝ ። »

«ማይክል !»

በዚህ ጊዜ ጆርጅ ኮሎዌይ ገባና አቋረጣቸው ። ጆርጅ ኮሎዌይ የማሪዮን ሂልያርድ ቀኝ እጅ ነው ። የማይክል አባት ሲሞትና ማሪዮን ሂልያርድ ስራ አስኪያጅነቱን ስትረከብ ስሙ የስዋ ይሁን እንጂ የኮተር ሂልያርድ ስራ አስኪያጅ ጆርጅ ነበር ። ጆርጅ እድሜው በሃምሳና በስድሳ መካከል የሚገኝ ግርማ ሞገስ ያለው ሰው ነው ። በነገሩ ዝግተኛ ሲሆን ፍርዱና ውሣኔውም ማመዛዘን የተሞላ ነው ።

ጆርጅ ኮሎዌይ የማሪዮን ሂልያርድ የቅርብ አማካሪና የሚስጢሯም ተካፋይ ነው ። ጆርጅ የማያውቀው ነገር የለም ።

ለዚህ ነው ሲገባ የፊቷን መገርጣትና ጠቅላላ ሁኔታዋን ሲያይ ጮክ ብሎ «ማይክል !» ያለው ። ግን በኋላ ለስለስ ብሎ ፤

«ማሪዮን ደህና ነሽ ?» አለ ። ይህን የጠየቀው በከንቱ አልነበረም ። ማሪዮን ሂልያርድ አከፍተኛ ደረጃ የደረሰ የደም ግፊት ከያዛት ቆይቷል። ይህን ግን ሐኪሟና ጆርጅ ኮሎዌይ ካልሆነ ሌላ ማንም ሰው አያውቀውም ። በተጨማሪ የልብ ድካምም አለባት ።

«ደህና ነሽ ወይስ ?»

«ደህና ነኝ ። አዎ ደህና ነኝ» አለች «ደህና አመሸህ ጆርጅ?»

«ደህና ደህና . . . ጥሩ ጊዜ አይደለም የደረስኩት መሰለኝ ? ንግግራችሁን ሳትጨርሱ ።»

«አይ ደህና... እንዲያውም ጥሩ ጊዜ ነው የደረስከው ። እኔ መውጣቴ ነበር » አለ ማይክል ። « ደህና እደሪ » ብሎ ወጣ ።

«ማይክል ነገ ስልክ ደውዬ እነግርሃለሁ ሁሉንም በስልክ እንጨርሳለን ። » አንድ አንጀቱ የሚቆርጥ ነገር ሊናገራት ፈለገና ተወው ። ምን ጥቅም አለው ብሎ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

«ማይክል . . . »

መልስ አልሰጣችም ። ዝም ብሎ ጆርጅን ጨብጦ ወጣ ። ዞር ብሎም አላየ ። ዞር ብሎ ቢያይ ኖሮ በጆርጅ ፊት ላይ የሚታየው መጩነትና የእናቱን ድክምክም ማለት ማየት ይችል ነበር ።

«ምን ተፈጠረ ? » አለ ጆርጅ

«የሆነ እብደት ይዞታል ፤ የእብድ ስራ ታልሰራሁ እያለ ነው»

«አደርጋለሁ ስላለ ብቻ ላያደርገው ይችላል። ሁላችንም ይህን አደርጋለሁ ፤ ያን አያልን አንዳንዴ መፎከራችን ያለ ነው »

«ድሮ እዎ ። በኛ ጊዜ መፎከር ነበር ፤ የዛሬ ልጆች ግን ግድ ፊን ነው » አለች ማሪዮን ። በጣም ደከማለች ።

«መድሐኒት ወሰደሻል ዛሬ ? »

እንገቷን በአሉታ ነቅንቀች ።

«የት ነው ያለው ? »

«ኢቦርሳዬ ውስጥ»

መድሐኒቱን መርጦ ሰጣት። ቀስ እያለ ሰልብ አድርጋት ኖር ውሀውን አስጠግቶ ሲያስውጣት አይኗ ተገለጠ ።

«ጆርጅ ፣ አንተ ባትኖር ምን ይውጠኝ ነበር ? » አለች ፈገግ ብላ ።

«እኔስ ያላንቺ ምን ይውጠኝ ነበር ማሪዮን። ላስበው እንኳ እጨነቃለሁ ። አሁን ልሂድ ትንሽ አረፍ ትይ ?»

«ብቻዬን ከሆንኩ ስለማይክል እያሰብኩ ብሰጭት ብቻ ነው እሚተርፈው'»

«ምንድነው ? ሊድርጅ ስ ሲሰራም ሳለም አይደል ? ነው ወይስ . . . ? »

«አላለም ፤ ነገሩ ሌላ ነው»


t.me/OLDBOOKSPDF

ያ ከሆነ ስለልጅቱ ጉዳይ መሆን አለበት ፤ አለ ጆርጅ ኮሎ ዌይ በሃሳቡ ።

★ ★ ★

ማይክ ከኒውዮርክ ከመነሳቱ በፊት ወደ ናንሲ ስልክ ደውሎ በዘጠኝ ደቂቃ ውስጥ እንደሚደርስና ተዘጋጅታ እንድትጠብቀው ነገራት ። ከጥቂት ምልልሶች በኋላ የምትዘጋጀው በሰርግ ሊጋቡ እንደሆነ ሲገልፅላት ፤

«ለምን ዛሬ ማታ ? ለምን ?» አለችው

«ያ.መነፍሴ የሆነ ነገር ነገረኝ ። ብቻ ነገሩ የተገባ ነው » አላት ።

በቃ ልታገባ ነው ። ትዳር ልትመሰርት !

ማይክልና እሷ የሕግ ባልና ሚስት ሊሆኑ ! በፈገግታ ተመላች።

«መጣሁ ፤ ዘጠኝ ደቂቃ ብቻ . . . እና ደሞ ናንሲ ! »

«እ ?»

«በጣም እወድሻለሁ !»

ይ ነን ብሎ ስልኩን ዘጋውና እየሮጠ አውሮፕላኑ ላይ ተሳፈረ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ ሦስት

ግው! ግው ! ግው !

እየደጋገመ በሩን ይጠልዘው ገባ ። ይህን በር ሲደበድብ ሶስት ደቂቃ ያህል አልፏል ። ግን ተስፋ ቆርጦ ሊሄድ አልፈለ ገም ። የቤን አብሬን ጠባይ ያውቃል ። እቤት ውስጥ እንዳለም በደንብ ይገባዋል ።

«ቤን ! ስማ ፤ ቤን !»

ግው! ግው ! ግው !

« ቤን ! በስላሴ ስማኝ ! ትሰማኛለህ ሰውዬው ! ...»

ግው! ግው! ግው! ..ግው ግው! ግው! .....

«ቤን ....»

ግው! ግው! ግው! ...

በመጨረሻ ኮቴ ተሰማው ፤ የተደናበረ ኮቴ ። ቀጥሎ አንድ ነገር መታና ተንኳኳ ። የመደነቃቀፍ ድምፅ ተሰማው ።

በሩ ሲከፈት እንቅልፍ ያናወዘው ቤን አብሬ ብቅ አለ ፤ ግራ ተጋብቶ ፡ በከነቴራና ሙታንታ ብቻ ።

«ገና በአምስት ሰዓት የተኛኸው ምን ነካኝ ብለህ ነው ፤ በክርስቶስ ?» አለ ማይክል ።

ቤን ግን አልመለሰለትም ። ማይክ ፊቱን ሲመለከት ነገሩ ሁሉ ገባው ።

«ኧረ በስላሴ ! ቤን ፤ ጥምብዝ ብለህ ሰክረሃልና !»

«ከራስ ፀጉሬ እስከ እግር ጥፍሬ » አለ ቤን ቁልቁል እግሩን እየተመለከተ ፤ የሰካር ፈገግታ ፈገግ ብሎ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

እግሩ ሲብረከረክ ይታይ ነበር።

«ስካርህን በቶሎ ማብረድ አለብኝ። ለብርቱ ጉዳይ እፈል ግሀለሁ »

«ተባለ እንዴ! ስድስት ቢፍ ኢተር ጂን ቶኒክ ውሀ ሲበ ላው ታየኝ ከ! ፆን ሁሉ ስጠጣ ያመሸሁት ፤ ባንተ መምጣት ብቻ ላበላሸው ነዋ! ቡልሽት »

« ስድቡም ይቆይ ፤ ስካሩም ቢበላሽ አይጐዳ ። ይልቅስ ቶሎ ነቃ በልና ልብስህን ለባብስ»

«የለበስኩት በቃኝ! »

ቤን ይህን ሲል ማይክል አልጋት ገብቶ ነበረና መብራቱን አበራው ። ቤን አቭሪ ግን አይኑን ሲገልጥ ተቸግሮ ሙጭጭናበስ ጀመረ ።

«ሄይ ! ... ምን ማድረግህ ነው ?» አለ ቤን ።

ማይክል ግን ፈገግ አለ እንጂ ምንም መልስ አልሰጠውም ። መብራቱን አብርቶ ወደ ኩሽና መንገዱን ቀጠለ ።

«ምን እያደረክ ነው ?» አለ ቤን ።

«አንተ ብትሆን አኩሽና ውስጥ ምንድነው እምታደርገው ? የቦምብ ከምሱር ትንቅላለህ ?» አለ ማይክል ።

«አትጠራጠር ። እንቅልና እወረውር ... »

«ይልቅ ወሬውን ተውና አንድ ትልቅ ፌስታ ለማድረግ ዝግጁ ሁን » አለ ማይክ ፈገግ ብሎ ። ቤን ነቃ አለ ። እፊቱም ላይ አንድ ነገር ለማግኘት ተስፋ የማድረግ ስሜት ታየበት ።

«ፌስታው ምንድነው ? ልንጠጣ ያስችለናል ? »

«የፈለግነውን ማድረግ እንችላለን ። ግን አሁን አይደለም ። ሁሉም በኋላ ያደርሰናል»

«ባይ ተስፋ ፤ ጅልህን ብሳ » አለና እወንበሩ ላይ ሄዶ ተወ ዘፈ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

«ጉዳዩ ምን እንደሆነ አውቀሃል ?» አለ ማይክ ።

«አሚያስጠጣ ጉዳይ ካልሆነ ላውቀውም አልፈልግ ፤ ልትነግረኝም አልሻ ። እኔ ጌታዬ ፣ ዶክትሬቴን ልቀበል ነው ። ሌላ ባጣ እሱን እያሰብኩ መጠጣት እችላለሁ ።

«እኔ ደግሞ ዛሬ እሱኑ አሳብቤ ሚስት ላገባ ነው»

«እሱም አይከፋም » አለ ቤን። እና ድንገት ቀና ፣ ነቃ ብሎ « ምናልክ ? ምን መሆኔ ነው አልክ ?» አለ ።

«ሰምተኸኛል ፤ ምን ትጠይቀኛለህ !--- ናንሲ እና እኔ ልንጋባ ነው አልኩህ »

ማይክል ይህን ሲናገር በኩራትና ያለው ነገር እንደሚፈፀም በተማመነ ድምፅ ነበር ።

«የቀለበት ማሰሪያ ፌስታ መሆኑ ነዋ!» አለ ቤን በጣም ነቃ ብሎ ።« ይኸ ከሆነማ ብዙ ቢፍ-ኢተር ጂን ሊያስጨምር ይችላል ። ቢያንስ ሌላ ስድስት ወይም ሰባት — ስምንትም ያስጨምራል አትለኝም !»

«ቀለበት አይደለም ፤ ሰርግ ። ሰርግ አልኩህ ። ሰርግ ታውቃለህ ? ቤን »

«ዛሬ ? ሰርግ ?» አለ ቤን ግራ ተጋብቶ «ለምን ዛሬ ? ለምን ?»

«ምክንያቱም ዛሬውኑ እንዲሆን ፈለግና ። ዛሬ መጋባት ደስ አለና !» አለ ማይክል ። «ያም ሆነ ያ እንዲህ ደንዝዘህ ቢነግሩህም ስለማይገባህ ይቅር ። ግን ሚዜ—አንደኛ ሚዜው አንተ ነህ ብልህ ያን ያህል ሰምተህ መረዳት ትችላለህ ?»

«በደንብ ነዋ! የውሻ ልጅ ። ደሞ ይኸን ልጣ ! ግን እውነት ዛሬ ልትጋቡ ነው?»

ብድግ ብሎ ከወንበሩ ላይ ዘሎ ሲወርድ አደናቀፈውና ጀበናውን በእግሩ መታው ።

«የተረገመ እንቅፋት»



t.me/OLDBOOKSPDF

«እየው። እንዲህ ከሆንክ ራስህን ታጠፋለህ ። ስለዚህ ቀስ ብለህ ሂድና የሆነ ልብስ . . . » አለ ማይክል ።

«ልክ ብለሃል . . . »

እያጉተመተመ ወደ መኝታ ቤቱ ገባ ። ሲመለስ ትንሽ ሰውነቱን ሰብሰብ ለማድረግ ሞክሮ ነበር ። ትንሽ ነቃ ብሎ ልብሱንም ለብሶ ነበር ። እንዲያውም ሰማያዊና ነጭ ነጠብጣብ ባለው ቲ ሸርት ላይ ከራቫት አስሮ ነበር ። ማይክል ሁኔታውን ካዬ በኋላ ፈገግ ብሎና ራሱን ነቅንቆ ፣

«ምናለበት ባይሆን ቀለሙ ወደ ቲ ሸርቱ የሚጠጋ ከራቫት ብታስር !—መቼም ቲ ሸርቱ ይሁን እንበል» አለ ። ከራቫቱ ጥቁር ሲሆን አልፎ አልፎ ቢጫ ጣልጣል ያለበት ነበር ።

«ለመሆኑ ከራቫት ያስፈልገኛል እንዴ ? » አለ ቤን ። «ለዚህ ቲ ሸርት የሚሆን ቀለም ያለው የማገኝ አይመስለኝም» ሲል ጨመረ እየተጨነቀ ።

«ትወው አትጨነቅ ፤ ይቅር ። ግን ለጊዜው ሱሪህን ቀልፍ። ከዚያ አለቀ። እንሄዳለን ። ደሞ ጫማ ያደረግከው ባንድ እግርህ ነው፤ ያኛው እግርህም ጫማ ሳያስፈልገው አይቀርምና በል አንደኛውን ጫማ ፈልገው»

ቤን እግሩን አየና ባንድ እግሩ ብቻ ጫማ እንዳደረገ ሲገነዘብ ሳቁን ለቀቀው ።

«እሺ ፤ እሺ ። በቃ ዞርብኛል ። ምንም ማድረግ አልችልም ። ወይ አስቀድመህ ዛሬ ማታ እፈልግሃለሁ ብትለኝ ደግ ። ዛሬ ጧት ትገናኝተን ነበር ፤ አይደለም ? ያኔ ልትነግረኝ ትችል ነበር ቢያን ስ» አለ ቤን አቭሪ ፤ እየሳቀ ጀምሮ ወደ መጨረሻው ግን ከምር በሆነ አነጋገር ።

«ጧት አላሰብኩትማ! ይህ እንደሚሆን አላወቅኩም ነበር’ ኮ»

«አላወቅኩም ነበር?»



t.me/OLDBOOKSPDF

ቤን ይህን ጥያቄ የጠየቀው ስካር የሚባል ነገር በማይሰማ በት ድምፅና በቁም ነገር ነበር ።

«በፍጹም ስልህ!»

«እውነትህን ነው? ወይስ ታሾፋለህ?»

«ምንም አላሾፍኩም ። አሁን በቃ ። እንዴት አላወክም ፣ ጭቅ ጭቅ ፣ ስብከት አልፈልግም ፡ አሁን ካንተ የምፈልገው የረሳኸ ውን ሁሉ አስተካክለህ እንድንሄድ ነው ። ናንሲ ትጠብቀናለች ።

ማይክል ይህን ሲል ቤን እቫሪ ግራ በመጋባት ይመለከተው ነበር ። ይኸኔ ማይክል ፦«ስካሩ ትንሽ ለቀቅ እንዲያደርግህ ይህን ጠጣበት» ብሎ ቡና ሰጠው።

ቤን ቡናውን ተቀብሎ ፉ . . . ት አድርጎ ከጠጣለት በኋላ ፊቱን አኮፋተረና በመዐፀት ድምፅ—

«ያን የመሰለ ጂን እንዲህ ብላሽ ሆና ይቅር» አለ ።

«ግዴለህም ፤ ከሰርጉ ፍጥምጥም በኋላ ትተካበታለህ»

«በነገራችን ላይ የት ነው ፍጥምጥሙን የምታደርጉት?»

«ልታየው አይደለም ? አይዞህ ምንም ችግር የለም ። ሁል ጊዜም የማትረሳኝ አንዲት ትንሽ ከተማ አለች ። ከዚህ የአንድ ሰዓት መንገድ ያህል ብትሆን ነው ። በልጅነቴ አንድ ጊዜ ለእረፍት ወስደውኝ አይቻት እንደ ወደድኳት ቀረሁ ። ለሰርግ የምትስ ማማ ናት »

«እንዴት ነው ፤ የጋብቻ ፈቃድስ ? » አለ ቤን ።

(ያገባ ሰው በጋብቻ ላይ ጋብቻ እንዳይፈጽም በማሰብ ማንም ሰው አገሌ የተባለው ሰው ያላገባ ወይም ወዘተ ስለሆነ ሊያገባ ይችላል የሚል ፈቃድ ያስፈልገዋል ።)

«አያስፈልገኝም ። ከተማዋ ከዚህ አይነቱ ጣጣ ነፃ ናት ። የፈለግከውን በፈለግከው ሰዓት ብታደርግ ማንም አይጠይቅህም ። ገለፃው ይበቃ መሰለኝ ። አሁን ዝግጁ ከሆንክ እንሂድ»

ቤን ቡናውን ጨለጠና፣



t.me/OLDBOOKSPDF

«እዎ መሄዱ ይሻላል ። ኧረ በእግዚአብሔር ፣ ሁሉ ነገር እን ግዳ ሆነብኝ አይደለም እንዴ ? ተደነጋገርኩኩ ! ፍርሃት ፣ ፍርሃት አይልህም ? »

«ቅንጣት ታህል!»

«ምናልባት ነገሩን ደህና አርገህ ባታላምጠው ይሆናል ። እኔ እንጃ ... ሠርግ ፣ ጋብቻ ሲሉኝ . . . ህእ ! »

ቤን ይህን ተናግሮ ራሱን በትግርምት እየነቅነቀ እንደገና ባንድ እግሩ ጫማ እንዳላደረገ አየ ። ጫማውን ሲፈልግ እየተነሳ ፣

«ምንም እንኳ ናንሲ ግሩም ልጅ ብትሆን!» አለ ስለጋብቻ እንደማይገባው የተናገረውን በመቀጠል ።

«ከግሩምም በላይ ናት» አለ ማይክል ። ቤን ይነሳ እንጂ ጫማ ውን ለመፈለግ አልሄደም ነበረና ማይክል ፈልጎ አመጣለት ። ከዚያም በአክብሮት ጎንበስ ብሎ በሁለት እጁ ጫማውን ለቤን አቀረበለት ።

«ትባረክ» አለ ቤንም ቀልዱን በመቀበል ።

ደርሰው ለመሄድ አቆበቆቡ ። ከዚህ ዓይነቱ ጭቅጭቅ ሊወጡ የሚችሉት ቤቱን ሲለቁ መሆኑን የተገነዘቡ ይመስሉ ነበር—ከዚህ የቁም ነገር ምልልስ ለመላቀቅ ፣ ለመፈንጠዝ ፣ በደስታ ተሞልቶ ለመሳቅ ።

«እንዴት ነው አሁን ? ምንም የሚያሳፍር ነገር የለም ? » አለ ቤን ጫማውን ካደረገ በኋላ እሱሪው ኪስ እየገባ ።

«የምን ማሳፈር፣ ዝንጥ ብለህልንጂ ! »

«እሱን ተወው ! ያ የተረገመ ቁልፍ መያዣዬን ደሞ የት ጣልኩት ይባላል ! »

ማይክል እያየው ሲስቅ ግራ ተጋብቶ የተቀመጠበትን ቦታ እና አካባቢውን መቃኘት ጀመረ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ቁልፍ መያዣው እሱሪው የጎን የቀበቶ ማስገቢያ ጥብጣብ ላይ ተንጠልጥሎ ነበር ። «ያውልህ ቁልፉ ፣ ቶሎ በል ። ቤቱ እንሂድ »

ከዚያም ከንድ ለከንድ ተያይዘው ድምፃቸውን ከፍ አድርገው የመጠጥ ቤት ዘፈን እየዘፈኑ ወጡ ። እየዘፈኑ ጉዞኣቸውን ቀጠሉ ። ማንም ሰው ወጥቶ አትረብሹን አላላቸውም ። ያ አካባቢ በጠቅላላ የሀርቫርድ ተመላላሽ ተማሪዎች ተከራይተው የሚኖሩበት አካባቢ ስለሆነ በተለይ እንዲህ ትምህርት ቤት ለእረፍት ሲዘጋ አካባቢ ፣ ማለትም ከፈተና በኋላ ሁሉም የሚያደርገው በመሆኑ ማንም ማንን ረበሽከኝ ሊል አይችልም ። ወቅቱ የነፃነትና የመቦረቅ ነበር ።

★ ★ ★

እናንሲ ቤት አጠገብ ሲደርሱ መኪናቸውን አቆሙ ። ከዚያም ማይክል ጥሩምባውን አንዴ አምባረቀው።

ናንሲ ዝግጁ ሆና ስትጠብቅ ዓመታት ያለፉ ሲመስላት ነበርና ጥሩንባውን ሲያንባርቀው ተንደርድራ ወጥታ በአናቷ አጠገባቸው ገጭ አለች ።

ናንሲን ሲያዩ ሁለቱ ወንዶች መብረቅ የመታቸውን ያህል ደነገጡ ። ፀጥ አሉ ።

«የስላሴ ያለህ ናንሲ። እንዴት ነው እንደዚህ ቁንጅት ያልሽው በይ ! . . . ደግሞ ይሽን ቀሚስ ከየት አመጣሽው?» አለ ማይክል ፀጥታውን እየገሰሰ።

«ነበረኝ!» አለች ናንሲ ።

ሁለቱም የፍቅርና የመነፋፋቅ ፈገግታን ተላበሱ ። በዚህ ሁኔታ ላይ እንዳሉ ስሜቷ ሲራወጥ ተሰማት ። ድንገት ሁለን ተናዋ የሙሽራ የሆነ መሰላት ። ላሱም ። ከእግር እስከራሷ ሙሽራ ሆና ታየችው ።


t.me/OLDBOOKSPDF

አንገትጌው በሐር ጥልፍ የተጌጠ ነጭ ረጂም ቀሚስ ለብሳ ፣ ጥቁር ሐር ምስጋን ይንሳው በሚያስኘው ፀጉሯ ላይ ስማያዊ የሐር ኮፍያ አድርጋለች ። ነጭ ስንደል ተጫምታ ፣ በእጅ ቀም ጥንታዊነት ያለው የሚመስል እጅግ የሚያምር የተጠለፈ መሀረብ ይዛለች ።

ቃላት ሊገልጿት በማይደፍሩት መጠን ተውባ ፣ ቆንጅታ ነበረና ለተወሰነ ጊዜ ማይክል ምንም ቃል ትንፍሽ ሊል አልቻለም ። ቤን አብሪ እንኳ እንዲያ ሆና ሲያያት ስካሩ ፈፅሞ ጥሎት የበረረ ይመስል ነበር ።

«ታያላችሁ ይህንን ? በጣም ውብ ! በጣም ጥንታዊ ነው » አለች መሀረቡን እያሳየቻቸው ፤ «ከሴት አያቴ ያገኘሁት የውርስ እቃ ነው»

«ልእልት መስለሻል ኮ ናንሲ» አለ ቤን አብሪ ።

«እግዜር ይስጥልኝ ቤን»

«እንዴ!... ቆይ ...ስሚ ናንሲ ። በውለት የወሰድሽው አንድ እቃ ይዘሽ የል? »

«ምን ማለትህ ነው ቤን?»

«ውብ... ጥንታዊ የሆነ መሀረብ ይዘሻል! አይደለም ? ጥሩ ። አሁን ደግሞ አዲስ የሆነ ውብ እቃ መዋስ ያስፈልግሻል » አለ ቤን ፤ « ያ እቃ አለሽ?»

«የለኝም» አለች እየሳቀች ።

«ደግ » አለና ካንገቱ አንድ ነገር ለማውለቅ መታገል ጀመረ። ቆንጆ የወርቅ ሀብል አወለቀና ፣

«ያዥ ። ይኸ ግን ስጦታ አይደለም ። ውሰት ነው ። ለምሪቃ በአል የደስ ደስ እህቴ የላከችልኝ ስጦታ ነው። ችኩል አይደለሁ ?



t.me/OLDBOOKSPDF

ከምረቃው በፊት አደረግሁት ። ስለዚህ ለሰርግሽ እለት ላውስሽ እችላለሁ» አለና ከመኪናው ወጥቶ አንገቷ ላይ አጠለቀላት ። የወርቁ ሃብል ከአብረቅራቂው የቀሚስ ጥልፍ ጋር በጣም አደ መቃት።

«አሁን ሁሉ ነገር ድንቅ ሆነ» አለች ወርቁን እያየች ።

«አንችም ድንቅ ልጅ ነሽ» አለ ማይክ እየወጣና የመኪና ውን በር እየከፈተ ። «በል ቤን ወደ ኋላ እለፍ . . .የኔ እመቤት ፣ አንች ጋቢና ግቢ »

«ለምንድነው ኋላ እምሄደው ? ለምን ? እጭኔ ላይ መቀመጥ አትችልም?» አለ ቤን እንደ ህፃን ልጅ እየተነጫነጨ ። ማይክል በቁጣ አፈጠጠበት ። በዚህ ጊዜ ቤን ወደኋላ ወንበር እየተሸጋገረ ፣

«እሺ ፣ በቃ አትቆጣ ! እኔ ደሞ አንደኛ ሚዜ ስለሆንኩ ምንም አይደል ... »

«ይህን ጠባይህን በጊዜ ካላረምክና ካልተጠንቀቅክ ... ዋ ! ለነፍስህ ብታዝናላት ይሻልሀል »

እንዲህ እየተቀላለዱ ቦታ ቦታቸውን ያዙ ። ናንሲ ማይክልን በጉጉት እየት አደረገችው። ወዲያው ማሪዮን ምን ብላው ይሆን ? የሚል ጥያቄ መጣባት ። ግን በሀሳቧ አልገፋችበትም ። አሁን ስለ ቧና ስለማይክል ብቻ ማሰብ ያለባት ጊዜ ነው ።

«ምን አይነቱ ሌሊት ነው ? ምስቅልቅሉ የወጣ ! ጅል የሚ ያደርግ ! ግን ደስ ይላል» አለች ።

ከዚያም እየቀለዱ ፣ እየተበሻሸቁ ፣ የውሸት እየተጣሉ ጉዟ ቸውን ቀጠሉ ። ከጊዜ በኋላ ድንገት ጸጥ አሉ ። ሁሉም በየ ግል ሐሳባቸው ውስጥ ሰመጡ ። ማይክል ከእናቱ ጋር ስለተለ ዋወጣቸው ንግግሮች ሲያሰላስል ፣ ናንሲ ደግሞ ይህች ዕለት



t.me/OLDBOOKSPDF

በሕይወቷ ውስጥ ተመዝግባ ለዘለዓለም የምትኖር ልዩ ሌሊት እንደሆነች ታስብ ነበር ።

በዚህ ሁኔታ ብዙ ተጓዙ ።

« ገና ብዙ መንገድ ቀረን ፣ ማይክ ? » አለች ናንሲ ። ደርሰ ጭንቅ ፣ ጭንቅ ይላት ጀምር ነበር ። መሐረቧም መጨማደድ ጀምሯል ።

« ደርሰናል ። አምስት ማይል ያህል ቢቀረን ነው » አለ ማይክል አንድ እጁን ሰደድ አድርጐ የናንሲን እጅ ጭብጥ እያደረገ ።

እጅዋን እንደያዘ ፣ —

« በቃ ፣ ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ የሕግ ባልና ሚስት ነን ። ሚስ ማክአሊስትር ሚስዝ ሂልያርድ ትሆናለች » አለ ።

« እንደሱ ካልክ ታዲያ ምን ትንቆራዘዛለህ ። ቤንዚን ስጠው ለመኪናው ። እኔ 'ኮ እዚህ ብቻየን ተቆራምጄ ብርድ ወደ በረዶነት ሊቀይረኝ ምንም ያህል አልቀረኝ » አለ ቤንዟሚን አብሪ ከኋላ ወንበር በቀልድ የእሮሮ ድምፅ ።

በዚህ ጊዜ ሦስቱም አንዴ ሳቁ፣ አወኩ ።

እየሳቁ —

ማይክል የቤንዚን መስጫውን ረግጦ መኪናው ፍጥነት እንደጨመረ ኩርኛ አጋጠመው ። ፍጥነቱን ሳይቀንስ መሪውን ሊጠመዝዝ መኪናው ተወንጭፎ ሲዞር ፣

ሳቁ ባንዴ ቀጥ አለ — ወደ ፍርሃት ትንፋሽ ተቀይሮ ። አንድ የጭነት መኪና መንገዱን ግጥም አድርጎ ያላንዳች ማመንታት ወደነሱ ሲምዘገዘግ ያየው ማይክል በሆነ መንገድ ሾልኮ ለማምለጥ ከመሪው ጋር በብዙ ታገለ ። ሆኖም የመጣባቸው ካምዮን ፍጥነት ከፍተኛ ከመሆኑም በላይ ፍሬኑ የተበጠሰ ይመ



t.me/OLDBOOKSPDF

ስል ነበር ። ወይም ነጂው እንቅልፍ ተጭኖት ሊሆን ይችላል ። አይታወቅም ።

ሁሉ ነገር ባዶ ሆነ ። በዚያች ቅፅበት ናንሲ የሰማችው ድምፅ ቢኖር « አሀ ! አምላኬ ! » የሚለውን የቤን አብሪን ድምፅና የራሷን ጭርር ያለ ጩኸት ነበር ። ከዚያ ቀጠለ ፣ የመስታወት መሰበር ድምፅ . . . ከሽ . . ጥርቁስ . . . ከሽ . . ቃቃ . . ከሽ ከሽ . . . ብረት ፣ ቋ ድቅቅ . . . ጥርምስ . . . ጥርምስምስምስ . . . የሞተር ማጓራት ፣ ድርርር ጥዝርር . . . .

እጅ ሲወናጨፍ ፣ እግር ሽቅብ ሲነሳ ፣ የመቀመጫው ሶፋ ቆዳ ሲሰረጠጥ . . . ፕላስቲክ ሲቀረደድ ታያት ። ቀጥሎም ሁሉ ነገር የመስታወት አቧራ ሆና ታያት ።

በመጨረሻ ሁሉም ነገር ፀጥ ፣ ቀጥ አለ ። እሰም ባዶ ሆነች ። ጨለማ ሆነች ።

★ ★ ★

ቤን አብሪ ነፍሱ መለስ ስትልና ሲነቃ አያሌ ዓመታት ያለፉ መሰለው ። ራሱን እንደ ታምቡር ይወቅጠዋል ። ሁሉ ነገር ጨለማ መሰለው ። አፉ ውስጥ እፍኝ አሸዋ የተጠቀጠቀ መስሎ ተሰማው ።

ካያሌ ዓመታት በኋላ ነቃ ። ዓይኑን የገለጠው ደግሞ ከበርካታ ሰዓቶች በኋላ ሆኖ ተሰማው ። በዚህ ረጂም ጊዜ ውስጥ ዓይኑን ለመግለጥ ያደረገው ትግል ከማድከም አልፎ የሕመም ስሜት አሳደረበት ። ዓይኑን እንደገለጠ ያየውን ነገር ምንነት ለመገንዘብ አልቻለም ። እየቆየ የሚያየው ነገር ዓይን መሆኑን ተገነዘበ ። ቆይቶ ግድግዳ መሆኑን አወቀ ። በመጀመሪያ ያየው የግ



t.me/OLDBOOKSPDF

ይከል በኩል ያለው በር ተገንጥሏል ። ይህን ጊዜ አንድ ነገር ትዝ አለው ። ምን ? ምን ? አዎ አንድ ሰው አብሯቸው ነበር። አዎ ነበረ ። ማን ?.... ናንሲ !.... ናንሲ አብራን ነበ ረች !.... የት ነበር የሚሄዱት ? የት ....? ሊያስታውስ አል ቻለም ። ከባድ ራስ ምታት ይወቅረዋል ። ናንሲ !

ተገላበጠ ። ጠቅ አደረገው ራሱን ። ተንቀሳቀሰ ። እንደ ጦር የሚወጋ የሕመም ስሜት በአካሉ ዳር እስከ ዳር የተሰ መጠጠ መሰለው ። ያ ሕመም ሽቅብ ወገቡ ድረስ ዘልቆ ተገ ላበጠ ። ከሕመሙ ለመሸሽ ተንቀሳቀሰ ። ,ዓይኔ አያት ናንሲን ። የሆነ ነጭና ቀይ ቀለም ያለው ዝንጉርጉር ቀሚስ ለብሳ ፣ የፊት መስታወት በነበረበት በኩል ዘልቃ ፣ እኮፈኑ ላይ በፊቷ ተደ ፍታ ። ናንሲ ! ሞታለች ማለት ነው ! አሁን ስለሕመሙ አልተጨነቀም ። እግሩ እንደጦር ቢወጋውም አልተሰማ ውም ። ወዳለችበት እንደምንም ተገላብጦ እየተንተተ ሄደና ወጣ ። አዎ መሄድ አለበት ። .....እንደምንም ብሎ መገልበጥ አለበት ። ናንሲ...ወይኔ ናንሲ !.. ሲጠጋ ፀጉሯ ላይ የተበተ ነው የደቀቀ መስታወት ታየው ። ለብሳዋለች ። የፊት መስ ታወቱን በጠቅላላ አካሏ ለብሳዋለች ። ደቃቅ ዱቄት ሆኖ ልብስ ሆኗታል ። ፀጉሯ ፣ ልብሷ ፣ ጠቅላላ አካላቷ.. አምላኬ ምነው!.. ምነው !.. ያለውን ኃይል አጠራቅሞ ቀስ ብሎ ገለበጣት ። ከዚህ በኋላ በሚያሳዝን ሁኔታ በጩለማ ብቻውን እንደተዉትና እንደፈራ ልጅ ያምጧቅስ ጀመረ ።

«ምነው አምላኬ !..ምነው !»

ፊቷ !..ወይኔ ናንሲ !...ፊቷ ፈፅሞ ጠፍቶ ነበረ ። ሞታ ይሆን !? ርግጠኛ መሆን አልቻለም ። ሆኖም ላንዲት አስፈሪ ቅፅበትም ቢሆን ብትሞት ሲል ተመኘ ። ጭካኔ አልነ



t.me/OLDBOOKSPDF

በረም ይህን ያስመኘው ። ተርፋም ሰው እንደማትሆን ስለተገ
ነዘበ ነበር ። ድንገት ስለገባው ነበር ።

ውብ ፊቷ ምንም ቅሬታ ሳይተው ሞቷል ። ሌላ የተተረ
ተረ ፡ የተጠቀጠቀ ፡ የተተለተለ ፊት ሆኗል። ናንሲ አልነበረችም።
ናንሲ የለችም ። ይህን ሲያስብ መንፈሱ እጅግ ተጨነቀ ። ከዚ
ያም ምህረት ወረደለት ። በሷ ደምና በሱ እምባ እንደራስ ተዝለ
ፈለፈና አሸለበ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ አራት

እንዲያ ደሙ ምጥጥ ብሎ እሆስፒታል አልጋ ላይ ስታየው የእናት ልቧ በሐዘን ፍላፃ ተወጋ ። እሆስፒታሉ የደረሰችው ከሌሊቱ አሥራ አንድ ሰዓት ላይ ነበር ። አደጋው መድረሱን እንደ ሰማች ባለው መንገድ በርራ ደረሰች ። መጓጓዣ ቢጠፋ በእግሯም ቢሆን መንገድ መቀጠሏ አይቀርም ነበር ።

ግን ደግሞ ችግር አልነበረም ፤ ቢሆን ለማለት እንጂ ። በዚች ዓለም ያለሱ ማን አላት ። ያለሱና ያለ ድርጅቱ ኑሮ ለሷ ምኗም አይደለም ። ድርጅቱን የምትንከባከበው ይበልጥ እንዲ ደረጅ ፤ እንዲበለፅግ ያላንዳች ዕረፍት የምትደክመው ደግሞ ለሱ ለማውረስ ነው ። አንድ ያላት እሱ ነው ። ለሱ ደግሞ ተራ ነገር ልትሰጠው ፤ ተራ ነገር ልታበረክትለት አትፈልግም ። ያዘጋጀ ችለት በረከት ኮተር ሂልያርድን ያህል ግዙፍ ድርጅት ነው ። ይህን ስጦታዋን ታዲያ እንደቀላል ነገር ወርውሮላት ሊሄድ ! ሊሞት ! . . . የክርስቶስ ያለህ ! ዘንገናት ። . . . ያች መናጢ ናት ይኸን ሁሉ ችግር ያመጣችው . . . ያቺ ርጉም ሴት ናት . . . እሷ መሆን አለባት ይህን ሁሉ እንዲያደርግ የገፋፋችው ።

አየችው ። ትናንት ሌሊት ላይ አደጋው ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ ነፍሱን አያውቅም ። እንዲያም ቀና አላለም ።

ማሪየን ሂልያርድ ክፍሉን ቃኘችው ። ያን ክፍል በደንብ ታውቀዋለች ። ከዚህ በፊትም እዚህ ቦታ ተቀምጣ እንዲህ ሆና አይታዋለች ። ሐሳቧ ጠለፋት ። . . . የለም እሱ አይደለም ። ያኔ የታመመው ማይክል አልነበረም ። ሪቻርድ ነበር ። ሪቻ ርድ ሂልያርድ ፤ ሟች ባለቤቷ የማይክል አባት ትዝ አላት ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ሆስፒታሉ ይህ አልነበረም ። ግን ያው ነው ፣ ተመሳሳይ ነው አለች በሐሳቧ ።

ሪቻርድ ሂልያርድ በደም ሥሩ ውስጥ የረጋ ደም አጣድሮ ሲገድለው . . . ዕንባ አነቃት ። እንደምንም ታግላ መለሰችው ። ግን . . . ግን ማይክል አልሞተም ። አይሞትም ። እንዲሞት አል ፈቅድለትም ። እኔ እያለሁ አይሞትም ።

ለማይክል የተመደበችው ነርስ ስትመለከታት አየች ። በነ ርሷ ፊት ላይ ምንም ዓይነት የተለየ ስሜት አይታይባትም ነበር። ከተቀመጠችበት ተነስታ ማይክል ወደተኛበት ሄደች ። ዓይኑን ገልጣ ተመለከተች ። ይህን ስታይ ማሪዮን ሐሳቧን እቋ ርጣ ወደ አልጋው ቀረበች ። ነርሷ ቀና ብላ አየቻትና —

« ያው ነው ፣ ምንም ለውጥ አያሳይም » አለቻት ።

ቀኑን ሙሉ እንዲህ ስትላት ነው የዋለችው—ምንም የተለየ ሁኔታ የለም !

ነርሷ ይህን ብላ ማሪዮንን በሥጋት አየቻት ። ከማይክ ይልቅ ለማሪዮን ያዘነች ትመስላለች ።

« ዶክተር ዊክፊልድ አሥራ አንድ ሰዓት ሲሆን ዕረፍት እንድታደርግ ንገሪያት ብሎኝ ነበር » አለችና ሰዓቷን አየች ። «አሁን አሥራ አንድ ከሩብ ሆኗል » አለች በጊዜው መልዕክ ቷን ባለማድረሷ እያፈረች ።

« ስላሰባችሁልኝ አመሰግናለሁ ። ትንሽ ዘወር ዘወር ብዬ እመጣለሁ ። እስከማረፊያ ክፍል ድረስ ብሄድ ይበቃል ? » አለች ማሪዮን ።

ከመጣች ጊዜ ጀምሮ ካጠገቡ አልተለየችም ። ሙሉ አሥራ ሁለት ሰዓት አልተለየችውም ። ይህን ያህል ጊዜ ስትቆይ ነፍሷ ከሥጋዋ ጋር እንድትቆይ ለማድረግ ብቻ ሁለት ሲኒ ሻይ ጠጣች እንጂ ሌላ አልቀመሰችም ። አሁንም ልትለየው አትፈል ግም ። አጠገቡ ሆና ትጠብቀዋለች ። እሷ አጠገቡ ካለች አይ



t.me/OLDBOOKSPDF

ልጅቱ ምንም ቢደርስባት በጥፋቷ ነው ። ያለምንም ምክንያት እንደዚያ ዓይነት ነገር . . ማሪዮን ይህን ሐሳብ አን ጠልጥላ ሲጋራዋን ጣለችና በእግሯ በኃይል ረገጠችው ። ምንም ቢሆን አትሞትም ። ያው መናሯ አይቀርም ። ምን ሆነች ? ፌቷ ብቻ ነው ከጥቅም ውጭ የሆነው ። እንዲያ መሆኑ ደግሞ ማለ ፊያ ነው ። ይህን ስታስብ ትንሽ ተሰማት ። ለትንሽ ጊዜ ደግሞ ከስሜቷ ጋር ተጣላች ። በናንሲ ላይ ያላትን ቅሬታ ለውጣ ትንሽ ልታዝንላት ፈለገች ።

ሰውን ውደድ ፣ የተቸገሩትን መዕውት የሚለውን በማሰብ ርህራሄና ሐዘኔታ ስለተሰማት ልትመጸውታት ፈለገች ። ልጅዋን ይገድልና ይበቀላት ይሆን ? ይህን በማለት ለናንሲ ሐዘኔታ ልትመጸውት ከጀለች ። ግን አልቻለችም ። ማሪዮን ለናንሲ ያላት ጥላቻ እንፍ፴ ውስጥ ዘልቆ የገባና ሥር የሰደደ ነበር ።

ልጅዋን ፣ አንድ ያላትን ልትቀማት ልታሳጣት !

« ዕረፍት እንድታደርጊ እንዲነግሩሽ ትዕዛዝ አስተላልፌ የሄድኩ መሰሎኝ ነበር »

ይህን ድምፅ ስትሰማ ድንገጥ አለች ። ድምፁ ወደ መጣ በት አካባቢ ብትት ብላ ዞር አለች ። ዶክተር ዊክፊልድ ነበር ። በሚገባ ይተዋወቃሉ ። እንዲያውም በማቆላመጥ ዊስ ብላ ነው እምትጠራው ።

« ማሪዮን እንዲያው አንድ ቀን እንኳ ሳት ብሎሽ ሰው ያለሽን አትሰሚም ማለት ነው ? » አለ ዶክተሩ ።

« ችግሩ ለኔ ካልተሰማኝ ሰው መስማት የለብኝም ። እን ዴት ነው የማይከል ሁኔታ ? »

«ደህና ነው ። ወዳንቺ የመጣሁት የሱን ሁኔታ ገብቼ ካየሁ በኋላ ነው ። ምንም መጨነቅ አያስፈልግም ። አሁን ይሻለ ዋል ፣ አደጋው ሲደርስ ድንጋጤ አንጎሉን ከፋኛ ነክቶታል »



t.me/OLDBOOKSPDF

« እኔንም እንደዚያው » አለች ።

ምን ይደረግ በሚል የማስተዛዘን ሁኔታ አንገቱን ነቀነቀ ።

«ለወደፊቱ በጤናው ላይ ጠንቅ ጥሎ የሚያልፍ ነገር ይኖር ይሆን ? » አለችና በፊቷ ላይ ጭንቀት ውልብ ሲል ታዬ ። ቀጥሎም « የአንጎል መጎዳት ጠንቅ ? » ስትል እየፈራች ተናገረች ።

ዊከፊልድ ትከሻዋን መታ መታ አድርጎ በማረጋጋት ሁኔታ አጠገቧ እየተቀመጠ ፤

« ነገርኩሽ እኮ ማሪዮን ፣ በሚቻለኝ መጠን የማውቀውን ነገርኩሽ ። አሁን ባለበት ሁኔታ በጣም ረጅም ጊዜ ካልቆየ በስተቀር ምንም አይሆንም ። ይህ ደግሞ ይቆይበት አይመስለኝም ። ግለቱ ይቆይበታል ብሎ ልቤ አልፈራም » አለ ።

« የኔ ልብ ግን ፈርቷል » አለች ። ይህን ስትል ቀና ብሎ አያት ። ገረመው ። ለካ እሷም ትፈራለች ! አለ ። አንዳንድ ማንም ሰው የማያውቃቸው የማሪዮን የሆኑ የግል ባህርዮች አሉ ። እንዲህ ድንገት ካልሆነ በስተቀር ማንም አያውቃቸውም ።

« እሷስ እንዴት ናት ? » አለች ማሪዮን ።

ይቺ ሁሉ እማውቃት ማሪዮን ናት ? አለ ዶክተር ዊከ ፊልድ ስለልጅቷ ስትጠይቀውና ስለናንሲ ሲያስብ ልቡ በሐዘን ሰብር ብሎ ።

« እሷ ያው ናት ፣ እንዳገኘናት ናት ። ምንም ያህል ዕርዳታ ልናደርግላት አልቻልንም ። በርግጥ ነፍሷን ታውቃለች ። ከትናንት ጀምሮ ስትናገርም ፣ ምን ስትልም ደህና ናት ። ሚዛኗን የመሳት አዝማሚያ አይታይባትም ። በሕክምናው ረገድ ከሄድን ግን ምንም ዓይነት ነገር ልናደርግላት አልቻልንም ። አንደኛ ፣ ባሁኑ ደረጃ ላይ ዕርዳታ ሊደረግላት የሚያስችል አይደለም የደረሰባት አደጋ ። ሁለተኛ ፣ ጊዜው ሲመጣም ያንን ዓይነት ርዳታ ሊያደርግላት የሚችል ባለሙያ ከመ



t.me/OLDBOOKSPDF

ሕክላችን የለም ። የዚያ ዓይነቱን ሙሉ በሙሉ የፈረሰ አካል እንዳለ ለመመለስ የሚችሉ በመላው የዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ሁለት ሰዎች ብቻ ናቸው ። ፊቷ ' ኮ ፈዕም የለም ። አጥንቷ ተሰብሯል ። የ. ቷ ነርቮች ተበጣጥሰዋል ። ቆዳዋ ፈዕም የለም ። ባጠቃላይ በፊቷ ላይ ከሚገኙ አካላት በሚገርም ሁኔታ ምንም ጉዳት ያልደረሰባቸው ሁለቱ ዓይኖቿ ናቸው» አለ ዶክተር ዊክፊልድ ሐዘን በተመላ ድምፅ ።

« የተበላሸ ፊቷን ለማየት ይጠቅማታል ዓይኗ » አለች ማሪዮን ።

ዊክፊልድ ይህን ሲሰማ በጣም ደነገጠ ። በተለይ ማሪዮን ይህን የተናገረችበት የድምፅ ቃና ነፍሱን አናወጣት ።

« ማሪዮን ምን ማለትሽ ነው ? መኪናውን ሲነዳ የነበረው ማይክል ነው ! እሷ ምናጠፋች . . . ? » አለ መናገር ሲችል ።

ማሪዮን ግን መልስ አልሰጠችውም ። እውነትህን ነው ለማለት በሚመስል ሁኔታ አንገቷን ነቀነቀች ። ልጅቷ ጥፋተኛ መሆኗን ታውቃለች ። ወስናለች ። ለዚህ ሰው ግን ያንን ጥፋቷን ማሳየት አትችልም ። ስለዚህ ክርክር ውስጥ ልትገባ አልፈለችም ።

« እንዲህ ዓይነት አደጋ የደረሰበት ሰው ምንም ሕክምና ባይደረግለት ምን ይሆናል ? በሕይወት ሊኖር ይችላል ? » አለች ማሪዮን ።

« አለመታደል ሆኖ ለሞት አያበቃም » አለ ሐኪሙ ። « ግን እንዲህ ሆኖ መኖር ምን ኑሮ ሊሆን ይችላል ? የሃያ ሁለት ዓመት ጉብል ገፅታዋን ተገፍፋ ፣ ማስፈራሪያ ሆና ፣ እስዋ ርዋ እንዴት ሊስተካከል ይችላል ? እንዴት ነው ፣ ለመሆኑ መልከመልካም ነበረች ? »

« ይመስለኛል ። አንተዋወቅም ። አይቻት አላውቅም » አለች—ድምጿ በጭካኔ የጠጠረ ነበረ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

« እንዲያ ነው ? ያም ሆነ ያ ለሷ እንግዲህ ሕይወት ፈተና መሆኗ ነው ። ትንሽ ቁስሉ መጠጥ ሲል የቻሉትን ያህል ርዳታ ያደርጉላታል ። ግን ዋጋ የለውም ። ከዚያ በኋላ . . . ለመሆኑ ገንዘብ አላት ? »

«ምንም የላትም ?» አለች ምርር ብላ ።

« እንግዲያስ ያለቀለት ጉዳይ ነው ። የዚህ ዓይነቱን የፕላ ስቲክ ቀዶ ጥገና ሥራ የሚችሉ ባለሙያዎች ለነፍስ ብለው ሰው የሚረዱ ዓይነት አይደሉም ። ዋጋ የሌለው ልፋት ነው »

« ይህን ማድረግ የሚችል የምታውቀው ሰው አለ ? »

« አዎ ። ስማቸውን የማውቃቸው ሁለት ሐኪሞች አሉ ። ከሁለቱ አንደኛው በሙያው እጅግ የተራቀቀ ነው ። ሳንፍ ራንሲስኮ ነው መኖሪያው » አለ ዶክተር ዊክፊልድ ። ትንሽ የተስፋ ጭላንጭል ዕልቡ ላይ ፍንጥቅ ስትል ታየው ። ማሪ ዮን ሂልያርድ የተረፋት ቱጃር ናት ። ልቧ ቢራራ ! « ስሙ ፒተር ግሬግሰን ይባላል ። ከብዙ ዓመታት በፊት ተገናኝተን ተዋውቀን ነበር ። መቼም የችሎታው ነገር የሚደንቅ ነው » አለ ተስፋው ስለገፋፋው ።

« እንዲህ እንደሷ ከጥቅም ውጭ የሆነውን አካል በሚገባ ሊጠግን ይችል ይመስልሃል ? »

ይህን ስትል ተስፋው እጅግ ገነነ ። ምን ዓይነት ደግ ሰው ናት ! ሲል በልቡ ማሪዮንን አደነቃት ። ቀጥሎም ፣ —

« የሚቻል ከሆነ የሚችለው እሱ ብቻ ነው ። እንዴት ነው ? ማለት ልሞክር ? ማለት እንዳነጋግረው ትፈልጊያለሽ ? » አለ እየፈራ ። ተናግሮ ሲጨርስ ቀና ብላ አየችው ። የምትመዝነው መስሎ ተሰማው ። ምን ይሆን እምታስበው አለ በሀሳቡ ።

« ሐሳቤን እነግርሃለሁ » አለች ።

« ደግ » አለ ። እና አከታትሎ « አሁን ይበቃል ። ትንሽ ግረፍ አለብሽ ። ትጉጃለሽ ። ይህን የምልሽ ደግሞ ከልቤ ነው ። »



t.me/OLDBOOKSPDF

« እውቃለሁ » አለችና ፈገግ አለች ፣ ለደግንቱ ፈገግታ እንደመመፅወት ። ቀጥላም « ሆኖም አላደርገውም ። ይህ ደግሞ በሚገባ ይገባሃል ። ማይክልን ትቼ የትም ልሄድ አልችልም ። ላርፍም ወይም ሌላ ነገር ልሠራ »

« ሞትም አለኮ ! . . ልትሞችም ትችያለሽ 'ኮ »

« የለም ፤ የለም አልሞትም ። በጣም ክፉ ሰው ስለሆንኩ አልሞትም ። በዚያም ላይ ከመሞቴ በፊት የማከናውነው ብዙ ፣ ብዙ ሥራ አለ — እና አትስጋ ዊክ »

« እሺ ፤ እንዳልሽው ይሁን ። ሆኖም አንድ ሰዓት ብቻ ነው እምሰጥሽ ። ከዚያ በኋላ አላርፍም ካልሽ መጥቼ በግድም ቢሆን የዕንቅልፍ መርፌ ወግቼ እየጎተትኩ ወስጄ አስተኛሻለሁ ። ቀልዴን አይደለም ። በዚህ ተስማማን ? »

« ተስማምተናል » አለት ። ደጋግማ ከለኮሰቻቸው ሲጋራዎች በዚያ ሰዓት በእጇዋ ላይ የነበረውን ረግጣ ጉንጩን ቆንጠጥ አደረገችው እና በተጨማሪ ዊክ አለችና ቀና ብላ አየችው ። ለዚያች ቅፅበት ውብና ርህሩህ ሆና ታየችው ። በጥያቄ ዓይን ሲያያት «ለዚህ ሁሉ ነገር አመሰግንሀለሁ» አለች ። ትንበስ ብሎ ጉንጯን በለሆሳስ ሳም አደረጋት ። ክንዷን ጨበጥ አድርጎ አይዞሽ በሚል መንፈስ ለቀቅ አደረጋትና ትንሽ ፈንጠር ብሎ ቆመ ።

« አይዞሽ ማሪዮን ። ምንም አትስጊ ። አሁን ይሻለዋል » አለ ። ከዚያ በኋላ ናንሲ በሀሳቡ ብትመጣም በፊቷ ሊያነሳት ድፍረት አላገኘም ። ሊቆይ ይችላል ። ሰዓቱ የዚያ ቢሆን ራሱ ይነሳ የለም ? ምን ያስጨንቃል ? በፈገግታ ብቻ ተሰና ብቷት ሄደ ። የለም ያሰጋታል ። ቅድም ደውሎ ጆርጅ ኮሎዬ ይን መጥራቱ ጥሩ ዘዴ ነው ። በዚህ ሁኔታ ብቻዋን አትችልም ። የልቧን በመጠኑም ቢሆን የምትነግረው ሰው ያስፈልጋታል ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ማሪዮን ዶክተሩ እስኪሰወር በአይኗ ከተከተለችው በኋላ ሁለቱ እየተጫወቱ ሳለ የመጣላትን ሀሳብ ትንሽ አሰብ አደረገ ችና የምታደርገውን ወሰነች ።

★ ★ ★

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ናንሲ እተኛችበት አካባቢ ደረሰች። በጠና የታመሙና በጥብቅ የሚጠበቁ በሽተኞች የሚተኙበት አካባቢ ስለሆነ ፀጥ ያለ ነበር ። የለቅሶ ማንተግ አይነት ድምፅ ተሰማት ። ድምጹ በመጣበት አቅጣጫ ስትመለከት የክፍሉን ቁጥር አየች ። የናንሲ ክፍል ነበር ።

ቀስ ብላ ተጠጋች ። ለቅሶው አሁን በደንብ ተሰማት ። እበሩ ላይ ቆማ ለረጅም ጊዜ ፍዝዝ ብላ ቆየች ። ልግባና . . . ባድ ርገው ? . . . ግራ ገባት ።

ለማይከል ነው ። ለማይከል ስል ነው ። ማይክልን ነፃ ማው ጣት አለብኝ አለች ራሷን ለማበረታታት ።

ቀስ እያለች እግሮቿን እየጐተተች ወደ ክፍሉ ውስጥ ገባች። ክፍሉ ጨለማ ነበር ። ምንም ብርሃን እንዳይገባ የተከለከለ ይመ ስላል ። መብራቱም አልበራም ። ሻተሮቹም ተዘግተዋል ።

አሁንም የለቅሶው የማንተግ ድምፅ ይሰማታል ። ቀስ ብላ ተጠጋች ። አልጋው እንደ ጥላ ሆኖ ይታያል ። የልቅሶው ድምፅ ጉላ እያለ ይሰማ ጀመር ።

«ሰው ነው . . . ማነው ? » አለች ናንሲ ። ማሪዮን ተጠ ጋች ። የናንሲ ራሷ ፣ ፊቷ በጠቅላላ በፋሻ ተጠቅልሏል ። ድም ጿም የታፈነና እንግዳ ነገር ሆኖ ተሰማት ፤ ለናንሲ ለራሷ ።

«ማነው... ሰው አለ!» አለች ናንሲ ። እና ታለቅስ ጀመር ። «አይኔ አያይም ... ሰው አለ ?... አይኔ ፈፅሞ አያይም» አለችና ሳግ አከታትሎ ይንትጋት ጀመረ ።

« አይንሽ ምንም አልሆነም ። ሁለቱም አይኖችሽ ደህና ናቸው ። እንዳታዩ የሚከላከልሽ የተሸፈንሽበት ፋሻ ነው » አለች ማሪዮን ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ናንሲ ይህን ብትሰማም ለቅሶዋ ጨመረ ።

«ለምንድን ነው እንቅልፍ ያልወሰደሽ ?» አለች ማሪዮን ፤ ድርቅ ባለና ስሜቱ በተሟጠጠ ድምፅ ። «የሚያስተኛ መድሀኒት አልሰጡሽም ?»

ማሪዮን ራሲ በሀልሟ የምትነጋገር መሰሎ ተሰማት ።

«መርፌ ወግተውኝ ነበር ። ግን መድሀኒቱ ሊሰራ አልቻለም ። እንቅልፍ ባይኔ አልዞር አለ» አለች ናንሲ ።

«ይጠዘጥዝሻል...ወይም ውጋት የመሳሰለ ህመም አለው?»

«ምንም አይሰማኝም ። አካሌ በጠቅላላ ደንዝዟል ። ግን ... አንቺ ማን ነሽ ? »

ስሟን ልትነግራት አልደፈረችም ። በዚያ ፋንታ አልጋው አጠገብ ወንበር ስላየች ሄዳ እዚያ ላይ ቁጭ አለች ። የልጅቷን እጅ አየች ። ሁለቱም እጆቿ እንዲሁ በፋሻ ተጠቅልለዋል ። አይንቀሳቀሱም ። ትዝ አላት ዶክተር ዊክፊልድ የነገራት ። ፊቷ እንዳይጐዳ በእጅዋ መከላከሏ ያለ ነው ። ስለዚህ ሁለቱም እጆቿ በጣም ተጐድተዋል ። ለወደፊቱ በሰዓሊነት ሀይወቷን ለመቀጠል ተስፋ የላትም ስትል አሰበች ።

«ናንሲ» አለች ማሪዮን ለመጀመሪያ ጊዜ ይህን ስም እየጠራች ። ግድ የለም ይሁን ለማይክል ስል...

«ናንሲ ... » ድምጿ ለስለስ ያለ ነበር ። «ፊትሽ ምን ያህል እንደተጐዳ ሀኪሞቹ ነገሩሽ ?»

በክፍሉ ፀጥታ ነገሰ ። ዘለአለም አለም ያህል ጊዜ ሁለቱም ፀጥ ብለው ቆዩ ። ድንገት የለቅሶ ሳግ ፀጥታውን አደፈረሰው ።

«በፊትሽ ላይ የደረሰው አደጋ መጠን ከምን እስከምን እንደ ሆነ ነገሩሽ ? አስቀያሚ እንደሆነ አውቀሽዋል ?» አለች ማሪዮን።

አስቀያሚ የሚለውን ቃል ስትናገር ልቧ ሊከዳት ምንም አልቀራትም ። ሁሉ ነገር አስጠላት ። ሆዷ ተገላበጠ ። እንጀቷ ተላወሰ ። ወዲያው የለም፣ መዳከም አያስፈልግም አለች ማይክልን እያሰበች።



t.me/OLDBOOKSPDF

ለሚወዱት ሰው ስቃይ መሆን ደስ አይልም ። እንቺም...እንቺም ቢሆን መሰቃየት የለብሽም ። እንቺም አዲስ ህይወት 'ሀ' ብለሽ ልትመሰርቺ የምትችይበት መንገድ አለ ናንሲ »

ማሪዮን ናንሲ ትናገር እንደሆነ ጠበቀች ። ናንሲን ግን ሳግ ሲንትጋት ይሰማ እንጂ ምንም ቃል አልተነፈሰችም ።

«ይህ ቢሆን አዲስ ህይወት ፣ አዲስ አለም ልታገኝ የምትች ይበት መንገድ ይኖራል » አለች ማሪዮን ።

አሁንም መልስ የለም ።

«አዲስ ፊት ፣ አዲስ ገፅታ ፣ አዲስ ኑሮ !» አለች ማሪዮን ። ሳጉ ቆመ ።

«ከየት ? እንዴት ?» አለች ናንሲ ።

«እኔ አማውቀው ሰው አለ ። ሳንፍራንሲስኮ ውስጥ የሚኖር ። ይህ ሰው እንደገና ቆንጆ ቤት ሊያደርግሽ ይችላል ። ይህ ሰው የስእል ስራሽን እንድትቀጥይ ሊያደርግ ይችላል ። ይህን ለማድረግ በርግጥ ረጂም ጊዜና በርካታ ገንዘብም ይወስዳል ። ሆኖም ገንዘብም ቢጠፋ ፣ ጊዜም ቢወስድ ከሚገኘው ጥቅም ጋር ሲነፃፀር ኢምንት ይሆናል ። አይመስልሽም ናንሲ?»

አሁን ማሪዮን በነገሩ ገባችበት ። ውል መዋዋል ነው ። የንግድ ውል ። በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ የሚተረፍበት ውል ። ያ ደግሞ ሥራዋ ነው ።

«ታዲያ ያን ያህል ገንዘብ እኛ ከየት እናመጣለን ?» አለች ናንሲ። «እኛ » የሚለውን ቃል ስትሰማ ማሪዮን ሂልያርድ ሽምቅቅ አለች ። « እኛ» ያለችው እሷን ከማይክል ጋር ደብላ መሆኑ ነው ስትል አሰበች ። ተናደደች ። ቢሆንም ለጊዜው መቻል አለባት ። ይህን የጀመረችውን ነገር በትእግስት ከዳር ማድረስ አለባት ።

«ልክ ነሽ ናንሲ ። በቀላሉ የሚቻል አይደለም ። ግን እኔ እችላለሁ ። ማን እንደሆንኩ እስካሁን ሳታውቂ አልቀረሽም ፣ አይደለም ?»



t.me/OLDBOOKSPDF

« አውቃለሁ »

«እንዳልኩሽ ማይክል ከእንግዲህ ያንች ሲሆን እንደማይችል ገብቶኛል ፤ አይደለም ? በተለይ እንዲህ ሆነሽ ቢያይሽ አሁንም ፀፀቱ ሊገለው እንደሚችል ይገባሻል ፤ አይደለም ?»

«ይገባኛል »

«ስለዚህ ታማኝነትህን አሳየኝ ማለት ያውም ቢተርፍ ማለቱ ነው ፤ መፈታተን ፣ በጣም ከፍተኛ የሆነ ክፋት እንደሆነ ትረጂ ለሽ ፤ አይደለም ናንሲ ? ይህን አትረጂም ?»

«እረዳለሁ » አለች ድክም ባለ ድምፅ ።

«ስለዚህ የቀረ ነገር ቀርቷል ። የጠፋ ነገር ጠፍቷል ፤ አይደ ለም ? »

« አዎ »

«ናንሲ ፣ አንድ ሃሳብ ላቀርብልሽ እፈልጋለሁ ። ድርድር ነው። እንደምንስማማ ተስፋ አለኝ »

አሁን የንግድና የድርጅት ባለቤት የሆነችው ማሪዮን ሂልያርድ ሙሉ በሙሉ ብቅ አለች ። ልጅዋ ይህን ሁሉ ስትል ቢሰማ ልግ ደልሽ ሳይላት አይቀርም ነበር ።

«ናንሲ ፣ እስኪ ስለአዲሱ ገፅታሽ አስቢ ። ስለአዲሱ ህይወ ትሽ አስቢ ። ስለ አዲሲቷ ናንሲ አስቢ ። ስለነዚህ ነገሮች አስቢ ። አሁን ካለሽበት ሁኔታ ወጥተሽ ስለምታገኚው አዲስ ህይወት አስቢና አመዛዝኚ ፣ ናንሲ ።

« በሌላ በኩል እንዲህ እንዳለሽ ብትኖሪ የሚመጣብሽን ደግሞ አስቢው ። እንዲህ ማስፈራሪያ መስለሽ ምን ሆነሽ ልት ኖሪ ትችያለሽ ? ሱቅ ብትገቢ ፣ ሰዎች ለማየት ይፀየፉሻል ። በመ ገድ ላይ ድንገት ያዩሽ ሰዎች ይበረግጋሉ ። ህፃናት እያተውሽ እሪ ብለው ያለቅሳሉ ። ይህን ደግሞ አስቢው ። እንዲህ ሆኖ መኖር የሚቻል ይመስልሻል ? ግን እንዲህ ያለመሆን አማራጭ አለሽ »



t.me/OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ አምስት

ናንሲን እምቡላንስ ላይ ሲያሳፍሯት ፣ ማሪዮን ሂልያርድ ጥቁር የሱፍ ቀሚስና መደረቢያውን ለብሳ ሆስፒታሉ ሕንፃ በር ላይ ቆማ ትመለከት ነበር ። ጊዜው ከጥዋቱ አሥራ ሁለት ሰዓት ሲሆን ፣ ቀኑ ከናንሲ ጋር ከላይ የተገለጸውን ስምምነት ባደረጉ ማግሥት ነው ። ከናንሲ ጋር እዚያ ስምምነት ከደረሱ በኋላ ማሪዮን ዳግም ወደ ናንሲ ክፍል ዞር አላለችም ። ዳግም አላነጋገረቻትም ። ብቻ እስምምነት ላይ ከደረሱ በኋላ ጉዳዩን ለዶክተር ሮበርት ዊክፊልድ አንሳችለትና በፍጥነት ከዶክተር ፒተር ግሬግሰን ጋር እንዲጥቀል ጠየቀችው ። ዶክተር ዊክፊልድ ይህን ሲሰማ በደስታ ሰከር ማሪዮንን ጉንጯን ሳማት ። ግሬግሰንን አነጋገረው ። ግሬግሰንም ተስማማ ። በቃ ። ፒተር ግሬግሰን ናንሲን ሳይውል ሳያድር ወደ ሳንፍራንሲስኮ እንድትልክለት ስለጠየቀ ማሪዮን ደስ ተሰኘች ። ሁለት ነርሶች ቀጥራ በአንደኛ ማዕረግ የጀት ጉዞ ነርሶቹ ይዘዋት ወደ ሳንፍራንሲስኮ እንዲጓዙ ሁሉን ነገር ባንድ ቀን አዘጋጀች ። ማሪዮን ስለወጪው ቅር አልተሰኘችም ።

« መቼም የታደለች ልጅ ናት ማሪዮን » አለ ዶክተር ዊክፊልድ ማሪዮንን በአድናቆት እየተመለከተ ።

«ይመስለኛል » አለች ማሪዮን ። «አንድ ነገር . . . ይህን ጉዳይ ማይክል እንዲሰማ አልፈልግም ። ሰምተኸኛል ዊክ !»

«አልገባኝም » አለ ዶክተር ዊክፊልድ ግራ እየተጋባ ። «ለምን አይሰማም ? ለሚወዳት ልጅ እናቱ ያደረገችላትን ችሮታ የመስማት መብቱን መነፈግ አለበት እንዴ ? »

«የለም የለም የለም ! መስማት የለበትም ። እንዲያውም ከሰማ ውሉን እሰርዛለሁ —የማሳክመውን ውል »



t.me/OLDBOOKSPDF

ይህም ብቻ ሳይሆን ወጭው ብዙ ነው ። ለምሳሌ አንድ የአእምሮ ሀኪምም ያስፈልጋታል ። በየጊዜው ሊያነጋግራትና በአዲሱ ሰብእናዋ እንድታምን ሊያደርጋት ይገባል ። ለዚያም መክፈል ያለ ነው ።

ግሬግሰን ይህን ሲያስረዳ —

«አዲስ ሰው መሆኗ አይቀርም ። ምክንያቱም ያጣችውን ነገር ሁሉ ! ማለት በመንፈስ ያጣችውን—ለመመለስ አዳጋች ነው። አዲስ ሰብእናዋን እንድትቀበል ማድረግ ይኖርብናል » ብሏል ።

ይህ ደሞ ማሪዮንን በጣም ነበር ያስደሰታት ። ምክንያቱም ይህ ከሆነ ናንሲ ከማይክል ጋር ያላትን ግንኙነት ልትቀጥል አትደፍርም ማለት ነው ብላ ስለገመተች ነበር ። ማን ያውቃል ? ድንገት ሊገናኙ ይችላሉ ። አውሮፕላን ማረፊያ ላይ ሰው ይገናኛል ። ወይም ሆቴል ውስጥ ወይም ድንገት እመንገድ ላይ . . . ድንገት ። ይህ ደግሞ ለማሪዮን ደግ ነገር ሆኖ ሊታያት አይችልም ።

ግሬግሰን በጣም ግልፅና ሥራውን አጠናቆ የሚያውቅ ባለ ሙያ ሲሆን እድሜውም በአርባና በሃምሳ ዓመት መካከል ነው ። ዝናው በመላው ዓለም ታውቋል ።

እንዲህ ያለ የፕላስቲክ ሰርጀሪ ( የአካል መልሶ መተካት ቀዶ ህክምና ) ሙያ ያለው ሰው ነበር ናንሲን ያጋጠማት ። የታደለች ልጅ ነች አለች ማሪዮን በሀሳቧ ።

በውሉ ላይ የናንሲ ምቾት የሚጠበቅበት ሁኔታ ሁሉ አብሮ ገብቷል ። የሚመች መኖሪያ መከራየት አለባት ። ከላይ ያል ናቸውን ወጪዎች ጨምሮ ጠቅላላ የተከፈለው አራት መቶ ሺ ዶላር ነበር ።

ውሉ ሲታተም ማሪዮን አላንገራገረችም ። ገንዘቧን ለምታስቀምጥበት ባንክ ደውላ የተባለውን ያህል ገንዘብ ወደሚፈል



t.me/OLDBOOKSPDF

ገው ባንክ በስሙ እንዲዛወርለት የምታደርግ መሆኑን ወዲያውኑ ገለፀች ።

«ነገ ጠዋት በሶስት ሰአት ሂደህ ብትጠይቅ ገንዘቡን በስምህ ገቢ ሆኖ ታገኘዋለህ» አለች ማሪዮን ።

ፒተር ግሬግሰን አልተጠራጠረም። ማሪዮን ሂልያርድ ግን እንደሆነች አሳምሮ ያውቃል ። ለመሆኑ ማሪዮንን የማያውቅ ማን አለ!

«ለምን አትመጪና ቁርስ አትቀምሺም ማሪዮን» አለ ዶክተር ዊክፊልድ ከሀሳቧ እየቀሰቀሳት ። ግራ ተጋብቷል ። ጆርጅ ኮሎዌይን ነበር የተማመነው ። እሱም እስከ ነገ ጠዋት ከኒውዮርክ መውጣት እንደማይችል ገልጾለታል ። ዶክተር ዊክፊልድ አላወቀም እንጂ እንዳይመጣ የከለከለችው ማሪዮን ነበረች ።

«የምፈጽመው ጉዳይ ስላለ ብቻየን መሆን እፈልጋለሁ ። ስለዚህ መምጣት አያስፈልግህም » ብላ ። ሁሉም ነገር እንዳሰበችው ተሳካላት ። አሁን ደስ ብሏታል ።

« ማሪዮን »

« እህ »

«ቁርስ እንዴት ነው ?»

«በኋላ ይሻለኛል ! ዊክ ። በኋላ ። አሁን ልግባና ማይክልን ልየው »

«እኔ አይቸው እመጣለሁ »

ዶክተር ዊክፊልድ ወደ ፎቅ ሲወጣ እስዋ ወደ መጸዳጃ ቤት ጎራ አለች ።

★ ★ ★

ከጥቂት ጊዜ በኋላ ማይክል ወደተኛበት ክፍል ስትገባ ሁሉ ነገር ጸጥ ብሎ ነበር ። ዶክተር ዊክፊልድም ፀጥ ብሎ አልጋ አልጋውን ይመለከታል ። ነርስዋም የለች ።



t.me/OLDBOOKSPDF

የጥዋት ጸሐይ በመስኮት ገብታ አልጋው ላይ እርፋለች ። ከየት እንደሆነ እንጃ የተበላሸ ቧንቧ ይመስላል ውሀ ያለማቋረጥ ጠብ ጠብ ሲል ይሰማል ። ጸጥታው ታይቶ ፣ ተሰምቶ የማይታወቀውን ያህል ነበር ። ድንገት ልቧ ዘለለ ። ልቧ ዘልሎ ባፏ ሊወጣ ደረሰ—ልክ እንደያኔው ፣ ልክ ፍሬዴሪክ ሲሞት እንደሆነው ። ምነው አምላኬ! ምነው! እጅዋን ወደ ደረቷ ላከችው! ልቧን ለመያዝ። ልቧን ይዛ እበሩ ላይ እንደቆመች የጨው አምድ መስላ ቀረች ። አይኗን ከዶክተር ዊከፊልድ ወደ አልጋው ፣ ካልጋው ወደ ዶክተር ዊከፊልድ እያንከራተተች ባለችበት ድርቅ ብላ ቀረች ። እና እየ ችው፣ ልጅዋን ማይክን። የለም እንደያኔው አይደለም። እንደ ፍሬዴ ሪክ አደለም ። እንባ ተናነቃት ።

እግሯ እየተብረከረከ ቀስ ብላ ወደ አልጋው ሄደች ። ጎንበስ ብላ ፊቱን ዳበሰ ፣ ዳበስ አደረገችው ።

«ሄይ ሞም» አለ አይኑን ገለጥ አድርጎ ማይክ

በዚች ዓለም ላይ ለማሪዮን የእነዚያን ቃላት ያህል ውብ ነገር አልነበረም ።

የደስታ እንባ አፈሰሰች ፣ እየሳቀች ።

«ማይክ በጣም እወድሀለሁ » አለች ።

«እኔም እወድሻለሁ እናት አለም» አላት ።

ይህን ሲያይ በሕክምና ዓለም የኖረውና ብዙ ክፉና ደግ ፣ ብዙ ሞት ሽረት ያየው ዶክተር ዊከፊልድ ሳይቀር አይኑን እንባ ቋጠ ጠው ። ይህን ለጋ ለግላጋ ወጣትና ይህችን ይህን ያህል ጊዜ አንቆ ልፍ ባያሸንፋት ፣ እህል ባያምራት የልጅዋን መታመም ስታብሰለ ስል ከጎኑ ሳትለየው ለመቆየት የቻለች እናት ሲያይ ሐኪሙ እንዴ



t.me/OLDBOOKSPDF

አላስቻል ብሎት እንባው መጣበት ። ስለዚህም ቀስ ብሎ ትቷ ቸው ወጣ ። መውጣቱን ሁለቱም አላዩም ።

እቅፍ አድርጋ ይዛው ብዙ ሰዓት ቆየች ። እሱም ጸጉሯን በእጁ እያረሰ ፥

«በጣም አትሸበሪ ፤ ማሚ ። አሁን ሁሉም ነገር ተስተካከ ሏል።የክርስቶስ ያለህ ! እንዴት አድርጎ ነው የራበኝ እባካችሁ» አለ—ድምፁን ስትሰማ ነፍሱ ተመልሳ «ራበኝ» ሲል ዳነልኝ፤ በቃ የኔ ነው ! ማንም አይወስድብኝም ፤ ማንም አይቀማኝም ስትል አሰበች ። ደስ አላት ! ሳቀች ።

«ዊክን እንጠይቀውና ይሁን ካለ በዓለም ላይ ካሉት ቁር ሶች ሁሉ የላቀውንና የጣፈጠውን ቁርስ እናቀርብልሃለን » አለች ።

«ዊክ ቢፈልግ ገደል ይግባ ። እኔ በራብ መሞቴ ነው» አለ ማይክል ።

«ማይክል ምናልክ ! » አለች ።

ግን ቁጣ ሊሆንላት አልቻለም ። አትችልምም ። ልትወ ደው ብቻ ነው እምትችለው ። ቁጣዋ ያሳደረበትን ስሜት ለማ የት ፊቱን ስታጤን ልውጥ ሲል ታያት ። ቅር ተሰኝቶ አይ ደለም ። አልነበረም ። ድንገት አንድ ነገር ያስታወሰ መሆኑ በግ ልፅ ታይቷታል ። ለምን ሆስፒታል ውስጥ እንዳለ የገባው መሆኑ ገብቷታል። የመጀመሪያው አነሳሱ ሌላ ነበር ። በልጅ ነቱ ቶንሲል አሞት ሰንብቶ ከእንቅልፉ ሲነቃ እንደተሻለው ሲገነዘብ የሚሰማው አይነት ስሜት ነበር ። አይስ ክሬምና እናቱን ብቻ የፈለገው ለዚያ ነበር ። አሁን ግን ፊቱ ላይ ብዙ ነገር አነበበች ። ተነስቶ ሊቀመጥ ሞከረ ። ምን እንደ



t.me/OLDBOOKSPDF

ሚፈልግ ግራ ገባው እንጂ የሆነ ነገር ሊጠይቅ ፈልጎ ነበር ። ከፊቱ አንድ ነገር ለመረዳት የፈለገ ይመስላል ። ትኩር ብሎ አያት ። እሷ ቀም አየችው። እጁን ጭብጥ አድርጋ ይዛ ፤

«የኔ ውድ በቃ ፤ ቻለው » አለችው ።

«እማዬ . . . ያንለት ሌሊት . . . ሌሎቹስ ! . . . አውን ቀሣ አለኝ» አለ ።

«ቤን ወደ ቦስተን ተወስዷል ። ተገጫጭቷል ። ቢሆንም ደህና ነው ። ካንተ ይሻላል» አለችው ። ይህን ብላ በረጅሙ ተነፈሰች ፤ በጣም ማዘኗን ለመግለፅ ። እና እጁን ጥብቅ አድርጋ ያዘችው ። ቀጥሎ የሚመጣውን ጥያቄ አስቀድማ አውቃ ቀለች ። መልሱን አስተድማ ስላዘጋጀች አልተጨነቀችም ።

«ናንሲስ ? » አለ ። «ናንሲ የት አለች ማሚ ? »

ፊቷ መልሱን ነገረው ። እንባው ዱብ ዱብ አለ ። አጠገቡ ተቀምጣ እጁን ቀስ ብላ እያሻሸች ፤

«በጣም ተጎድታ ነበር . . . ስለዚህ አልተቻለም ። ሕይወቷን ማትረፍ አልተቻለም» አለች ።

ቀጥላም፤—

«ሀኪሞች ያልሞከሩት አልነበረም ። አልቻሉም » አለችና ንግግሯን አቋረጠች ።

«ዛሬ ጠዋት አረፈች » አለችው ቀጥላ ።

«አየሻት ? ሄደሽ አየሻት ?» አለ — ፊቷን ትኩር ብሎ ስትዋሽ ውሸቷን ለማንበብ የሚሞክር መስሎ ።

«ትናንት ሌሊት . . . ለጥቂት ጊዜ . . . አጠገቧ ሄጄ ቁጭ ብዬ ነበር ። »

«ምነው አምላኬ ! ምነው . . . ናንሲ ! ውዷ ! የኔ ናንሲ» አለ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

አትራሱ ላይ ተደፍቶ እንደልጅ አለቀሰ ። ማሪዮን እጀርባው ላይ እጅዋን ጣል አድርጋ ተወችው ። ስሟን እየደጋገመ እያነሳ አለቀሰ ። እስኪደክመውና ድምጹ ተዘግቶ ማልቀስ እስኪሳነው ።

ቀና ብሎ እናቱን አያት ። በዚህ ጊዜም ከዚህ በፊት አይታው የማታውቀው አዲስ ስሜት እፊቱ ላይ አየች ። የናንሲን ስም እየደጋገመ ሲጠራና ሲያለቅስላት ልክ ከውስጡ አንድ ነገር የጠፋ ያህል ነበር ። ያን ነገር አየችው ። ከውስጡ አንድ ነገር ጉድሎ ፣ የእሱ የአካል ክፍል ተነጥሎ እንደሞተ ታያት ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ ስድስት

የአውሮፕላኑ መስገሪያ ጎማ ከሆዱ ውስጥ ጉጉ ግርር ብሎ ሲወጣ ለናንሲ በደንብ ተሰማት ። እጅዋን ስትዘረጋ ከቦስተን ወደ ሳንፍራንሲስኮ ባደረገችው በዚህ ጉዞ ላይ ያዝ እያደረጉ መቶ ጊዜ ያህል ካፅናኗት ሁለት የተለያዩ እጆች አንዱ ያዝ አደረጋት ። ከሁለቱ ነርሶች አንደኛዋ ነበረች ፣ እጅዋን ያዝ አድርጋ ያጽናናቻት ። የነርሷ እጅ እጅዋን ሲቀበል መንፈሷ ተረጋጋ ። የትኛዋ ነርስ እንደሆነች ስታውቅ ደስ አላት ። በአያያዛቸው መለየት ጀምራ ነበር ። የአንደኛዋ ነርስ እጅ ቀጭን ሲሆን ልስልስ ያለ ነበር ። የዚች ነርስ እጅ ቀዝቃዛ ቢሆንም አጨባበጧ ግን ጠንካራ በመሆኑ ይህችኛዋ ሴት ስትጨብጣት ፍርሃት ፣ ፍርሃት የሚላት ይተዋትና ልቧ መድፈር ይጀምራል። የሁለተኛዋ ነርስ እጅ ወፍራምና ቡትቡት ያለ ሲሆን ገና ያዝ ስታደርጋት ከብካቤና ፍቅር ያልተለያት እንደሆነ ይሰማታል ። የዚች ነርስ ሞቃት እጅ ፍቅርን ይገልጽላታል ። ያዝ አድርጋ አትከሻዋ አካባቢ እጅዋ መባቀያ ላይ መታ ፣ መታ ስታደርጋት የፍቅሯን ጥልቀት ይገልጽላታል ፤ ለናንሲ ። ሀመሙ ጠንከር ሲልባት ሁለት ጊዜ መርፌ የወጋቻት ይህችው ነርስ ነበረች ። ድምጿም የሚያረጋጋ ሀይል አለው ። ልስልስ ያለ ነው ። ቀጭን እጅ ያላት ሴትዮ ስትናገር ትንሽ ያዝ ያደርጋታል ።

ናንሲ ሁለቱንም ሴቶች እየወደደቻቸው ስትሄድ ተሰማት ።

«አሁን ደርሰናል የኔ' መቤት ። ማረፊያው እየታየኝ ነው » አለች ጠንከር ያለ አያያዝ ያላት ነርስ እጅዋን እንደያዘች ።

★ ★ ★

ነገሩ እንደተባለው ነበር ። የቀራችው ሃያ ደቂቃ ያህል ሲሆን ፣ ይህንንም ፒተር ግሬግሰን ሰዓቱን በማየት አረጋገጠ ። ፒተር ግሬ



t.me/OLDBOOKSPDF

ግሰን በቀጠሮው መሠረት በጥቁሩ አውቶሞቢል ወደ አውሮፕላን ማረፊያው ሲነጉድ ይህን ተገንዝቧል። አምቡላንሱ እዚያው ይጠብቀዋል ። ፒተር ሕክምናውን ከሚያደርግላት ልጅና ከነርሶቹ ጋር በአምቡላንሱ ሊመለስ ወስኗል።ምክንያቱም የልጅቷ ሁኔታና የሚያደርግላት ሕክምና አንገብጋቢ ነውና ። አዲስ ፊት መስራት ! አዲስ ውብት መፍጠር ! ይህ ቀላል ነገር አይደለም ። በዚያ ላይ ምን አይነት ፊት እንደሚፈጥር ያውቃል ።

ፒተር በዚህ ሁኔታ ሀሳቡን ሊቀጥል አልፈለገም ። ስለዚህም ስለናንሲ ማንነት ማሰብ ቀጠለ ። አራት መቶ ሺህ ዶላር እጅግ በጣም ብዙ ገንዘብ ነው ። ልጅቷ ይህን የሚከፍልላት ሰው ማግኘቷ መታደል ነው ። ለማሪዮን ሂልያርድ ምኗ ትሆን ? ማሪዮን በጣም የምትወዳት ወይም የምታስብላት ሰው መሆን አለባት ። ያለዚያ ይህን ያህል ገንዘብ አታወጣም ነበር ። ይህን ያህል አትጨነቅላትም ነበር ። አራት መቶ ሺህ ዶላር ! ከዚህ ውስጥ ሦስት መቶ ሺህ ዶላር የሱ የአገልግሎት ዋጋ ነው ። ወጭውንና የመሳሰለውን ችሎ ። መቶው ሺህ ዶላር ግን የተከፈለው ለታካሚዋ ነው ። ሕክምናዋን እስከትጨርስ ለመኖር የሚያስፈልጋትን ነገር ለማሟላት የምትጠቀምበት ። በዚህ ገንዘብ የፈለገችውን ሁሉ ለማሟላት ወደ ኋላ አልልም አለ ፒተር ግሬግሰን በሀሳቡ ።

እንደገናም አመት ከመንፈቅ ሙሉ በአይኑ ላይ ውል ሲለው የኖረ ፊት ትዝ አለው ። ያ ፊት ናንሲን አዲስ ቤት ያደርጋታል ። ለአስራ ስምንት ወራት ያረገዘውን ፊት ናንሲ አድርጎ ይወልደዋል ። የናንሲና የእሱን የወደፊት ግንኙነት ሲያስበው ሲቃ ያዘው።ናንሲ የሙያውን ረቂቅነት የሚያይባት ብቻ አትሆንም ። የእሷና የእሱ ግንኙነት ከሐኪምና ታካሚ ግንኙነት ያልፋል ። ከመዋደድም ያልፋል ። ደፋርና በራሷ የምትተ



t.me/OLDBOOKSPDF

ታል ። ናንሲና እሱ ተረዳድተው ሕክምናው ባሰበው መንገድ ይፈጸማል ። ዛሬ የአርባ ሰባት አመት እድሜ ያለው ሰው ነው። በዚህ ባሳለፈው እድሜ ሁሉ ተሸንፎ አያውቅም ። ዛሬም አይሸነፍም ።

★ ★ ★

«ሄሎ ናንሲ ! እንኳን ደህና መጣሽ ። ጉዞው እንዴት ነበር ? » አለ ፒተር ግሬግሰን ካውርፕላኑ እንደወረደች ። ሁለቱን ነርሶች እንዳያቸው ተስማሚ እንደሆኑ ገምቷል ። ለነሱ በጥቅሻ ሰላምታ ሰጠ ።

ድምጹን ስትሰማ ደስ አላት ።

«ጥሩ ነበር ፣ ዶክተር ግሬግሰን » አለች ናንሲ ። ድምጿ እንደ ደከማት ቢያመለክትም ስልቸታ ግን አልነበረበትም ።

«ዶክተሬ ነህ ? »

«ነኝ ። ግን ካሁን ጀምሮ አብረን መሥራታችን አይደለም፣ ስለዚህ ሚስ ማክአሊስተር ፣ ዶክተር ግሬግሰን ከመባባል ፣ እኔም ናንሲ ብል አንችም ፒተር ብትይ ይበልጥ የሚያቀራርበን ይመስለኛል» አለ ፒተር ።

አቀራረቡ ደስ አላት ።

«ልትቀበለኝ ነው እዚህ ድረስ የመጣኸው ?» አለች ።

«አንቺ ብትሆኚ እዚህ ድረስ መጥተሽ አትቀበይኝም ነበር ማለት ነው?» ሲል ጠየቃት ።

«እቀበልህ ነበር እንጂ» አለች ።

ይህን ስትል በሚገርም ሁኔታ ነገሩ እውነት መሰላት ። ይህን ያህል ከሰው ጋር ባጭር ጊዜ መግባባት መቻሏ ገረማት ።

«እመሰግናለሁ» አለች ።

«እኔ የመጣሁት ስራሴ ደስ ስለሚለኝ ነበር ። ሆኖም አንችንም ደስ ሲልሽ አየሁ ። ይህ ደሞ ደስታዬን እጥፍ አድርገው። እንኳን መጣሁ አሰኘኝ» አለ ። በማከታተልም «ናንሲ» አለ ፣



t.me/OLDBOOKSPDF

«እቤት »

«ናንሲ ከዚህ በፊት ሳንፍራንሲስኮ መጥተሽ ታውቂያለሽ?»

«አላውቅም»

ደስ እምትል ከተማ ናት ። ፍሪስኮን እንደምትወጃት እተማመናለሁ ። ምርጥ የሆነ አፓርታማ እንፈልግልሻለን ። አለቀ ። ብዙ ሰዎች ሳንፍራሲስኮን ከረገጡ በኋላ የተወለዱበትን ፣ የኖሩበትን ቦታ ይረሳሉ ። እዚሁ ቅልጥ ብለው ነው የሚቀሩት ። ለም ሳሌ የእኔን ነገር ማንሳት እንችላለን ። የዛሬ አሥራ አምስት አመት አካባቢ ከሺካጎ መጣሁ ። መጣሁ ቀረሁ ። ዛሬ የፈለገው ነገር ቢመጣ ከዚች ከተማ ንቅንቅ አልልም ። አንቺ የት ነው የነበር ሽው? ቦስተን ?»

እንዲህ እያለ በቀላሉ የረጅም ጊዜ ትውውቅ ያላቸው እስኪ መስላት ራሱን አላመዳት ። ባንደ ። ይህን ሁሉ የሚላት ለመ ቀራረብ ብቻም አልነበረም ። በረጂም ጉዞ ላይ ስለነበረች ለጥቂት ጊዜ ያላንዳች እንቅስቃሴና ሀሳብ ስታርፍ ሰውነቷ በቀላሉ ዘና እንደሚል ስላወቀም ነበር ።

ነርሶቹም ደስ አላቸው ። እነሱም ከጉዞ ጣመናቸው ማረፍ ያስፈልጋቸው ነበርና ካንቡላንስ ነጂው ጋር እያወጉ ይዝናኑ ነበር ። ካለፍ አገደም ፊደናንሲ አይናቸውን ጣል ሲያደርጉ ዶክተር ግሬግሰን ናንሲን ሲያጫውታት ስላዩ ስውየው ደስ ብሏቸዋል ።

«እኔ ? እኔ እንኳ ያደኩት ኒው ሃምፕሻየር ነው ። እናትም አባትም አልነበረኝምና ኦዚያው ባለ የእጓለማውታን ማሳደጊያ ውስጥ አደኩ ። ወደ ቦተስን የመጣሁት አስራ ስምንት አመት ከሞላኝ በኋላ ነው»

«ይኸማ ልብ የሚሰቅል ታሪክ ነው ። ፎይስ ማሳደጊያ ቤቱ በቻርልስ ዲከንስ ልቦለዶች ውስጥ እንዳሉት ያለ በጭካኔ የተ



t.me/OLDBOOKSPDF

ምላ ነበር ?» አለ ፒተር ። ናንሲ በፒተር አጠያየቅ ፣ በተለይም ሁሉን ነገር ቀላል አድርጎ በመቀበል ችሎታው ተገረመች። የዲክንስ የእንግሊዝ ማሳደጊያዎችን ማሰቡ አሳቃት ።

«ዲክንስ ውስጥ ? በፍጹም ! ያሳደጉኝ መነኩሲቶች በጣም ደጋጎች ነበሩ ። ደስ የሚሉ ። በዚህ የተነሳ እንዲያውም እኔም እራሴ ለመመንኮስ ሀሳብ አድሮብኝ ነበር ። እንደነሱ ለመሆን » አለች ናንሲ ።

«ኧረ የስላሴ ያለህ ! ጆሮ አይሰማው የለ ! ሰሚ የኔ'ህት» አለ ፒተር ፤ ናንሲ ሳቀች ።

«የኔ' ህት ልክ ህክምናውን እንደጨረስሽ በቀጥታ ወደ ፊልሙ ከተማ ወደ ሆሊውድ ! . . . ገባሽ ? . . . ነገር ግን . . . ይህን አይሆንም ብለሽ ቁንጅናሽን ይዘሽ ገዳም ብትገቢ . . . አያድርገውና !... ገዳም ብትገቢ ... እኔ ምን የማደርግ . . . እኔ ሌላ ምንም አላደርግም ። ወደወደብ ሄጄ ፣ አንዱ ቋጥኝ ላይ ወጥቼ ፤ ከዚያ ላይ ተወርውሬ ስምጥ ። በቃ ። የለም የለም ፣ እንዲህ በቀላሉ አንላቀቅም ። እንዲያውም ህክምናዬን ከጨረስኩ በኋላ ቁንጅናዬን አንድ ገዳም ወስጄ ላልደብቅ ለፒተር ግሬግሰን ቃል እገባለሁ ስትይ ማይልኝ »

ይህ ቀልድ ነው ። ሆኖም እንደዘበትም ቢሆን ቃል መግባት ደግ አይደለም ። ይህን ታውቃለች ። ትወት እንጂ ቃል ለመግባት ደግሞ አይከብዳትም ። ምክንያቱም አካሏ ይመለስን'ጂ ወደየት እንደምትሔድ ታውቃለች ። ማይክል አለሳት ። በዚያ ላይ ምግዚቷና እናቷ እንደነበሩት እማሆይ ሜሪ የመሆን ፍላጎቷም አስቀድሞ ጠፍቶ ነበር ። ይህ ሁሉም ሆና ትንሽ ማወታ አይጎዳም በማለት ፣

«እንዲያ ከሆነ እሺ » አለች ።



t.me/OLDBOOKSPDF

«ምንድነው እሺ ? ቃል ገባሁ ማለትሽ ነው ? ቃል በቃል ልትናገሪ ይገባል። ቃል ገብቻለሁ በይ »

«እሺም ቃል ኪዳን ነው ። ስለዚህም ቃል ገብቻለሁ »

«ቃል ገብቻለሁ ! ብሎ ነገር ምን ለመሆን ነው ቃል የገባሽው ?»

«መነኩሴ ላለመሆን »

«እፉፉዎዬ ! አሁን ቀለል አለኝ » አለ ፒተር ።

እስካሁን ሰውነቷ ዘና እንደሚል ገባው ። ስለዚህም ነርሶቹ እንዲወጡ በጥቅሻ ጠራቸው ። በወሬ ብዙ ማድከሙም ደግ አይደለም ። ይበቃታል ፣ ሲል እያሰበ ። ሁለቱ ነርሶች ሲመጡ —

«ከጓደኞችሽ ጋር ለምን አላስተዋወቅሽኝም ? » አላት ።

«ደግ » አለችና ናንሲ ፣ «ባለቀዝቃዛ እጅዋ ሊሲ ትባላለች ። ባለሞቃት እጅዋ ደግሞ ግሬችን ትባላለች »

አራቱም በዚህ ንግግር ሳቁ ።

«አመሰግናለሁ ናንሲ »

ሊሲ የናንሲን እጅ በማበረታታት መንገድ ጨበጥ አደረገች ። ናንሲ በድንገት ደስ አላት ። እኒህ ሶስት ጓደኞቿ ምንም እንኳ እንግዳ ቢሆኑ የልብን የሚነግሯቸው ፣ የሚተማመኑባቸው ጓደኞቿ እንደሆኑ ተገነዘበች ። እነሱ እያሉ ምንም ችግር ይኖራል የሚል ሥጋት አልነበረባትምና ስለአስታማሚና ስለመሳሰሉት ያላትን ሀሳብ አራገፈች ። ይህን አራግፋ ፣ ድና ስትወጣ ለማይከል ምን መስላ እንደምትታየው ታሰላስል ጀመር ። ፒተር ግሬግሰንን አሰበችው ። የሚቀበሉት ፣ የሚወዱት ሰው ሆና አገኘታው ነበርና በሆስፒታሉ ተማመነችበት ። ውብ መልክ እንደሚሰጣት ገባት ። ምክንያቱም ለሰው ፍቅር አለው ። ስለዚህም ይጠነቅቃል ፣ ይጨነቃል ።



t.me/OLDBOOKSPDF

« ወደ ሳንፍራንሲስኮ እንኳን ደህና መጣሽ ብሮሊ ! » አለ ፒተር ግሬግሰን ። የሊሊ ሚጢጢ እጅ ናንሲን ለቅቋት የፒተር ሰፊ እጅ ያዛት ። ማረፊያቸው እስኪደርሱ ድረስ ፡ ማለትም በመንገድ ላይ አምቡላንስ ውስጥ እጅዋ በእጁ ውስጥ ነበር ። በሚያስገርም አኳኋን ስሜቷን ሁሉ ቀየረው ። እናም የመጣችው ወደ ማታውቀው ስፍራ ሳይሆን ወደ ቤቷ ፣ ወደተወለደችበት አገር እንደሆነ አድርጋ ገመተች ።



t.me/OLDBOOKSPDF

## ምዕራፍ ሰባት

የአንቡላንሱን በር በግ አድርገው ከፈቱና ወሳንሳውን በጥንቃቄ ተሸክመው ወደ ሆቴሉ ገቡ ። የሆቴሉ ማኔጀር እውጭ ደረጃውን ወርዶ ነበር የተቀበላቸው ። ወደተዘጋጀላቸው ክፍል እየመራ ወሰዳቸው ። በሆቴሉ ውስጥ የሚገኝ የአንድ ቪላ ያህል ምቾትና ስፋት ያለው ክፍልና ዙሪያ ገባው በጠቅላላ ለእነሱ ሲባል ተለቆ ነበር ። ሁለት ወይም ሶስት ቀን ያህል እዚህ ሊቆዩ አስበዋል ። ይህ የሆነው ደግሞ በሁለት ምክንያት ነው ። አንደኛ ማሪዮን ሂልያርድ በሰተን ከተማ ውስጥ አንድ ስብሰባ ላይ መገኘት ነበረባትና ወደኒውዮርክ ለመመለስ አትችልም ነበር። ሁለተኛ ማይክል ወደ እናቱ መኖሪያ ቤት ከመሔዱ በፊት ከሆስፒታል ወጥቶ ለተወሰነ ጊዜ ሆቴል ውስጥ ለመቆየት እንደሚፈልግ ተናግሮ ነበር ። እርግጥ ነው የማሪዮን ስብሰባ ቢኖርም ማይክል ግን ወደ ቤት ሄዶ እዚያው ኒውዮርክ ሊጠብቃት እንደሚችል ታውቃለች ። ግን ደግሞ ሆቴል መቆየት እፈልጋለሁ ካለ ይህን ፍላጎቱን ማሟላት አለባት ። ምንም እንኳ ፍላጐቱ የልጅ ቢመስልም ማሪዮን የጠየቀውን ሁሉ ልታሟላለት በልቧ ዝግጁ ነበረችና ይሁን ብላ ተቀበለችው ።

የአንቡላንስ ሠራተኞች ክ[illegible]ንሳው አውርደው እንደሚሰበር ዕቃ ተጠንቅቀው አልጋው ... ሲያስተኙት ፣

«ማሚ ፣ በክርስቶስ ይገርሻለሁ ፣ ይህን ያህል ጥንቃቄ አያስፈልገኝም ። ሀኪሞቹን ሰምተሻቸው የለም ? ደህና ነው ፣ ምንም አልሆነም ፣ ነበር'ኮ ያሉሽ » አለ ማይክል ።

« ቢሆንም ፣ ቢሆንም ችላ ማለት ደግ አይደለም » አለች ማሪዮን ።



t.me/OLDBOOKSPDF

«ችላ ማለት ! » አለ ማይክል ፡፡

ይህን ብሎ ክፍሉን ጸየቃኘ ትንሽ አጉረመረመ ፡፡ ማሪዮን ዝም ብላ ለአምቡላንሱ ሠራተኞች ጉርሻ ትሰጥ ነበር ፡፡

ክፍሉ በተለያዩ የአበባ ዓይነቶች ተሞልቷል ፡፡ አልጋው አጠገብ በሚገኝ ጠረጴዛ ላይም አንድ ትልቅ ቅርጫት በፍራ ፍሬ ተሞልቶ ተቀምጧል ፡፡

ዝግጅቱ ማይክልን እምብዛም አላስደነቀውም ፡፡ ምክንያቱም ሆቴሉ የማሪዮን ሂልያርድ ንብረት ነው ፡፡ ባለፈው ዓመት እንደ ገዛችው ያስታውሳል ፡፡

« አሁን ዘና ብላ የኔ መኳንንት ፣ ስለምንም ነገር ማሰብ ፣ መጨነቅ አያሻህም ፡፡ በነገራችን ላይ የሚበላ ነገር . . . ምን ይምጣልህ ? » አለች ፡፡

ነገራት ፡፡

«ምን ዓይነት የምግብ አመራረጥ ነው የኔ ሸጋ ? » አለች፡፡

እውነቱን ለመናገር ግን ምርጫው ተስማሚ ይሁን አይሁን አላወቀችም ፡፡ ምክንያቱም አልሰማችውም ፡፡ እሱ ምግብ ሲዘረዝር የሷ ሀሳብ እቀጠሮዋ ላይ ስለነበር ሰዓቷን በማየት ላይ ነበረች ፡፡ ስለዚህም—

«እንግዲህ እንደፍላጎትህ አድርግ ፡፡ ማለት የሚያስፈልግህን ነገር ራስህ ማዘዝ ትችላለህ ፡፡ በበኩሌ ፣ ጆርጅ እንደመጣ መሄድ አለብኝ— ወደ ስብሰባው » አለች ፡፡

ይህን እንዳለች ደመሉ ተንጫረረ ፡፡ በሩ ሲከፈት ጆርጅ ኮሉሜ ነበር ፡፡

« እጂ ፣ አሁንስ እንዴት ነው ? ተሻለህ ፣ ማይክል ?»



t.me/OLDBOOKSPDF

አንድ የሚያስደነግጥ ድምፅ ከትንፋሹ ጋር አስወጣ ። አስደን ጋጭ የድንጋጤ ድምፅ ።

«አ! አምላኬ ! የታለ ? ወዴት ?»

ሁሉም ነገር ባዶ ነበር። ሁሉም ነገር ። ጠረጴዛ የለ ! ወን በር ፤ ቀለም የለ ፤ ብሩሽ ፤ የሽራ መወጠሪያ አትሮኑስ የለ ፤ ቀለም ማደባለቂያ ፣ ቤት ውስጥ የበቀሉ አበቦች የሉ ! ምንጣፍ...አንድም ነገር አልቀረም ። ቤቱ ባዶ ...ወና ሆኗል ።

«የክርስቶስ ያለህ ! ናንሲ !» አለ አጠገቡ ያለች ይመስል፣ የት አደረስሽው ? ሊላት የፈለገ ይመስል ።

የሴሎቹን ክፍሎች በር እየከፈተ ተራወጠ ፤ እንባው በፊቱ ላይ እንደ ጐርፍ እየወረደ ። ጨዉ ፊቱን ሲያቃጥለው ተሰማው። አይኑን ሲቆጠቁጠው ተሰማው ። እንዲህ ሆኖ ነው ማልቀሱን እንኳ የተገነዘበው እንጂ እንባው'ስ ዝም ብሎ ነበር የወረደው፤ ፊቱን ያጠበው ።

የትም የት ምንም እቃ አልነበረም ። ባለበት ደንዝዞ ቀረ ። ሃሳቡ ሁሉ ሙልጭ ብሎ ከአእምሮው ወጣ ።

ድንገት በሩን በርግዶ ወጣና ወደታች መውረድ ጀመረ። ሁለቱን ደረጃ ባንዴ እየተራመደ ምድር ቤት የሚገኘውን የሕንፃውን ዋና አስተዳዳሪ ቢሮ ሲያይ ወደዚያው ሄደ ። በቡጢ ይነርተው ጀመር ። ደቃቃው አስተዳዳሪ ደንግጦ በሩን ቀስ ብሎ ከፈተው ፤ በሩን የሚመታው ሰው አደገኛ መስሎ ከታየው መልሶ ለመዝጋት በመጠንቀቅ ። ግን ወዲያው አወቀው ። ማይክልን አወቀው ። ስለዚህም በሩን በደንብ ከፈተው ።ሆኖም የገመተው ማይክል ሳይሆን ቀረ ። አንገቱን በሸሚዙ ሲያንቀው ደነገጠ ። ማይክል ሰውየውን አንቆ ይዞ እያርገፈገፈ ፣

«የታለ ! . . እቃዋ ሁሉ የታለ !? እቃዋ ሁሉ የታለ ካው ስኪ ? የት ወሰድከው ? የት ከተትከው ? » አለ ።

«የምን . . የምን እቃ ? . .አ ! አምላኬ ! ገባኝ ። የለም ! የለም እኔ አይደለሁም ። እንዲት ሰንጥር ነገር አልነካሁም ። ከአስራ



t.me/OLDBOOKSPDF

አምስት ቀን በፊት . . አካባቢ . . መጥተው ወሰዱት ። እና ደግሞ እንዲህ ብለው . . »ሰውየው መንቀጥቀጥ ጀምሮ ነበር ።

«ማናቸው ? እነማን ናቸው እነሱ ?»

«አላወኩም ። . . ብቻ ጠሩኝና ነገሩኝ ። ሚስ ማከአሊ ስተር . . »

ይህን እያለ ማይክልን ቀና ብሎ አየው ። ፊቱ በሐዘን ተውጦአል። አይኖቹ በእንባ ዳምነዋል ። ስለዚህም ሊናገረው የነበረውን ቃል ዋጠው ።

«ያው ታውቃለህ አይደል ! በኋላ ነገሩኝ ። ከጥቂት ቀናት በኋላ እቃውን እናወጣለን አሉኝ ። እንዳሉትም ሁለት ነርሶች መጥተው አንዳንድ እቃዎችን ወሰዱ ። በማግስቱ የጉድዊል ጭነት መኪና መጣ ። ሌላውን እቃ ሙልጭ አድርጎ ወሰደው። እኔ ... እኔ ምንም እቃ አልነካሁም ። አላደርገውም ። ያችን የመሰ ለች ልጅ . . »

«ሰዎች ያልካቸው እነማን እንደሆኑ አታውቅም ? ማለት ከየት እንደመጡ ። »

«ምንም አላወቅኩም ። ነጭ ልብስ ለብሰዋል ። ለዚህ ነው ነርስ የመሰሉኝ ። እነሱ የልብስ ሻንጣዋንና ስእሎቿን ብቻ ነው የወ ሰዱት ። ሌላው እቃ ወደ ጉድዊል ነው የተጫነው ። እኔ ... እኔ አንድም ነገር አልነካሁም ። በፍጹም እኔስ ነገ ... »

ግን ማይክል አይሰማውም ነበር ። አስተዳዳሪውን ትቶ ወደ ውጭ መውጣት ቀጠለ ። ሰውየውም ኢየውና በሀዘኔታ አንገ ቱን ነቀነቀ ። እና ድንገት ፡—

«ስማኝ . . . ልጄ . . . . » ሲል ተጣራ ።

ማይክል መለስ ብሎ አየው ።

« ስለሆነው ሁሉ አዝናለሁ ! በርታ » አለው ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ማይክል ማስተዛዘኛ ቃሉን ተቀብሎ መንገዱን ቀጠለ ። ወደ አውራው መንገድ እየተጓዘ አሰበ ። እነማን ናቸው ? ነርሶቹ ከሆ ስፒታል የተላኩ ይሆኑ ? . . . ጥንብ አንሳዎች ! ጥሪት ለመ ለቃቀምማ ማን ብሏቸው ! ምናልባት . . . ግን ምን ያገኛሉ ? ሥዕሎቿን ? እና ጥቂት ጌጣ ጌጦች እና . . . ጥንብ አንሳዎች ! ምነው . . . ምነው ሲለቃቅሙ በያዝኳቸው ኖሮ ! ወይኔ ! ቀኝ እጁን ጨብጦ የግራውን መዳፍ በቦቅስ ነጠረቀውና በቡጢ በተ መታው እጁ ጥብቅ አድርጎ ይዞ አሸው ። ድንገት ለቀቀውና ቡጢ የነበረውን እጁን ታክሲ ሊያስቆም ዘረጋው . . . መጠንከሩ አይከፋም ። ምናልባት የሆነ ፍንጭ . . . ሊሞክር . . . ፊቱ ላይ መጥቶ ቆመ ታክሲው . . . በሩን ከፍቶ ገባ ።

«በዚህ አካባቢ ያለው የጉድዊል ቅርንጫፍ የት ነው ? » አለ ማይክል ።

« ጉድ ዊል ምን ? . . . »

«ጉድ ዊል ዕቃ ማከማቻና መሸጫ . . . አሮጌ ልብስ — አሮጌ የቤት ዕቃ ምናምን . . . »

« ገባኝ ፡ ገባኝ »

★ ★ ★

ጉድዊል ያገለገሉ ዕቃዎች ማከማቻና መሸጫ መደብር ሊገባ ሲል እውነት ምን ለማድረግ ነው የመጣሁት ? ዕቃዎቹ በጠ ቅላላ ቢኖሩስ ምን ለማድረግ ? አጠቃላዩን ልገዛ ? ከዚያስ ? ግራ ገባው ። ሊመለስ ከጀለ ። ግን አላደረገውም ። ወደ መደብሩ ውስጥ ሰተት ብሎ ገባ ። ወጣ ወረደ ። አንድም ዕቃ ፤ የሷ የነበረ ነገር አላየም ። ግራ ገባው ። እንደገና አሰሳውን ጀመረ ወዲያው አንድ ነገር ብልጭ አለለት ። ለካ ለዕቃዎቹ ደንታ የለ ውም ! ለካ የሚፈልገው ዕቃ ሳይሆን ሰው ኖሯል ። እሷን ? ናንሲን ! አፓርትማውን እንዳለ ፡ እንደነበረ ቢያገኘውም ለካ ጥቅም አልነበረውም ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ለካ ይኽ ሁሉ ልፋት ከንቱ ሽሽት ነበር ።

ከመደብሩ ወጣ ፤ ባዶ ሆኖ ሙት ሆኖ ። እንደህያው የሚን ቀሳቀስ ሙት ሆኖ ወጣ ።

ቃክሲ አልያዘም ። እንዲያ እሚባል ነገር ከነመኖሩም ለማስታወስ የሚችልበት አእምሮ አልነበረውም ። በዘፈቀደ መን ገዱን ተያያዘው ። ግን ይህም ይባል ዘንድ ልክ አይመስልም ። ምክንያቱም በእግር ለመጓዝ ኃይል ያስፈልጋል ። አካል ፥ ሥጋ ፥ ኃይል ይፈልጋል ። አካሉ አጥንት አልባ የሆነ ለስላሳ ሆኖ ተሰማው ። ነፍሱ ግን ጠንካራ ነበረች ። ቆመ ግን ድንገት አልነበረም ። መንገድ ማቋረጥ ነበረበትና አረንጓዴው መብራት ጠፍቶ ቀዩ መብራት እስኪበራ ለመጠበቅ ቆመ ፤ ግን እስኪበራ አል ጠበቀም ። የመጣው ይምጣ ብሎ ለመራመድ ሲሞክር ሰማይ ምድሩ ጨለመበት ። ባዶ ።

ሲነቃ ሰዎች ከበውታል ። ከመንገድ አለፍ ብሎ በሚገኘው ሰው ሠራሽ መስክ ላይ ነበር የተንጋለለው ። ሰዎች ከበውታል ። ዓይኑን እንደገለጠ ፤

«ተሻለህ ፥ የኔ ልጅ» አለ አንዱ ፖሊስ

ፖሊሱ ልጁን በደንብ ሲያጤነው ቆይቷል ። ጠጥቶ እንዳ ልሰከረ ወይም አደንዛዥ እፅ እንዳልወሰደ ፥ ወይም ተደባድቦ አደጋ እንዳልደረሰበት ተረድቷል ። ህመም መሆኑን አውቆታል ።

«ደህና ነኝ» አለ ማይክል ።

ረሀብ ይሆንን አለ ፖሊሱ በሀሳቡ ። ደግሞ ይህን ሀሳብ ለመቀበል አስቸጋሪ ሆነበት ። ልጁ በደህና እንክብካቤ ያደገ ይመስላል ። የተጎሳቆለ ነገር አይታይበትም ።

«ያውቅሀል ፥ ከዚህ በፊት?»



t.me/OLDBOOKSPDF

«አይ ፣ ትንሽ ስላመመኝ... ዛሬ ነው ከሆስፒታል የወጣሁት ። እኔም ትንሽ አበዛሁት መሰለኝ »

ማይክል እዚያው እንደተጋደመ የከበቡትን ሰዎች አየ ። ሙሉ ከብ ሰው ። ቀና ሊል ሲሞክር ከሰዎች የተሰራው ከብ እንደመንኮራኩር መሽከርከር ጀመረ ። ተመልሶ ተዘረጋ ። ይህን የተመለከተው ፖሊስ ሰዉን በተነና ተመልሶ ፦

«መኪና ይመጣልሀል ። ለጥበቃ የተሰማሩ መኪናዎች አሉ ፣ እናደርስሀለን» አለ ።

«አይ ይህን ያህልም...»

«ግዴለም»

ፖሊሱ ይህን ብሎ ባጭር ርቀት መነጋገሪያ ሬድዮው መል እክቱን አስተላለፈ ።

መኪናው ካካባቢው አልራቀ ኖሮ ወዲያውኑ ከች አለ ። ማይክል ተሳፈረ ። ከሆቴሉ አንድ ምዕራፍ ያህል መለስ ያለ አድራሻ ሰጣቸው ።

እተባለው ቦታ እንደደረሱ አወረዱት ።

«አይዞህ» አለው ፖሊሱ ።

«እግዜር ይስጥልኝ »

እሆቴሉ ሲደርስ ማንም አልነበረም ። ቀድመውት አልደረሱም ማለት ነው ። ልብሱን አወላልቆ አልጋው ላይ ወጥቶ ሊተኛና ሊጠብቃቸው አሰበ ። ግን ወዲያው ሐሳቡን ሰረዘው። ምን ዋጋ አለው? ምን ድብብቆሽ መጫወት ያስፈልጋል ? ሲያደርገው ያሰበውን እንደሆነ አድርጓል ። ምንም እንኳ ከእውነቱ ፈቀቅ ሊያደርገው ባይችል ቁርጥ ማወቅም ደግ ነው ። ናንሲን ነበር የሚፈልገው ። ናንሲን አላገኛትም ። ሊያገኛት እንደማይችል ቀድሞውኑ መገንዘብ ነበረበት ። ዛሬም ፣ ወደፊትም ፣ የትም የት ሄዶ መፈለግ የለበትም ። ፍለጋው ፋይዳ ቢስ ነው ። ግን



t.me/OLDBOOKSPDF

ኖንሲ ሁልጊዜም አለች ። ያለችውም እንዲት ቦታ ነው ። እልቡ ውስጥ ፣ እራሱ እማይክል ውስጥ—በቃ!

የክፍሉ በር ሲከፈት ይህን እያሰበ እመስኮቱ አጠገብ ቆሞ ወዲያን ይመለከት ነበር ። ወደ ውጭ ። ወዲያ በጣም ወዲያ ።

«ምን ትሰራለህ እዚያ ጋ ማይክል?» አለች ማሪዮን ሂልያርድ ።

ሁልጊዜ እንደ ሕጻን! ሃያ አምስት አመቴን ልደፍን እንደ ሆነ አንድም ቀን አትገነዘብም አለ በሐሳቡ ።

«ከእንግዲህማ ይብቃኝ ፣ ማማ» አለ ማይክል ። «ቀና ፣ ቀና እያልኩ ካልተለማመድኩኮ ተኝቼ መባጀቴ ነው ። እንዲያውም ዛሬውኑ ኒውዮርክ ሄጄ ለማደር አስቤአለሁ »

«ምን አልክ?»

«ኒውዮርክ ለመሄድ አስቤአለሁ»

«ግን-- እዚህ ትንሽ ቀን ለማሳለፍ እፈልጋለሁ ብለህ ነበረ ኮ!»

ግራ የመጋባት ሁኔታ ይታይባት ነበር ።

«ምን አደርጋለሁ? በዚያም ላይ አንችም ስብሰባሽን ጨርሰሻል» አለና በልቡ ደግሞ እኔም ጉዳዩን ፈጽሜአለሁ ሲል ጨመረ ። ቀጥሎም «ስለዚህም መሄዱ ይሻላል ። እንዲያውም ነገውኑ በጧት ሥራ መጀመር አለብኝ ። አይመስልህም ጆርጅ?» ብሉ ጆርጅን አየው ።

ጆርጅ ማይክልን በደንብ ካጠናው በኋላ ፣ ልጁ በሀዘን ተሰብሯል ። ምናልባት ሥራው ያፅናናው ፣ ያረሳሳው ይሆናል ሲል አሰበና ፡-

«ወርቅ ሀሳብ ነው» ሲል መለሰ ። « ግን እስከትጠና ድረስ ግማሽ ቀን ብትሰራ በቂ ነው»

«አልገባኝም ። አበዳችሁ ልበል ወይስ...? ትናንት ከሆስፒታል ወጥቶ ሥራ...!» አለች ማሪዮን ።



t.me/OLDBOOKSPDF

«አቤት! አቤት!» አለ ማይክል ነገሩን ወዶቀልድ እየለ ወጠ «አሁን እንዲህ ሲሉ እሳቸው ይረቱ ቢሏቸው በጂ እሚሉ አይመስሉም!»

ይህን ብሎ «በያ መልስ ስጪ!» በሚል አስተያየት አያት። ቀስ ብላ እሰፋው ላይ አረፈችና ተደግፋ ተቀመጠች።

«እሺ በቃ ይሁን ፣ አታፍጥብኝ» አለች ቀልዱ ደስ ብሏት ፈገግ እያለች ።

ይኸኔ የንግግሩን ፈር እየቀየረ ፣

«ስብሰባው እንዴት ነበር?» ሲል ጠየቀ ።

ፈር መቀየሩ ብቻ ሳይሆን ካቀዳቸው ነገሮች መካከል ዋና ውን መጀመሩ መሆኑን ወዲያው ተገንዘበ ። ዛሬ ለማይክል በአ ለም ላይ የቀረው ነገር ቢኖር ይኸው ነው ። ለመኖር ከፈለገ አሁን ሊሄድበት በጀመረው መንገድ ጭልጥ ብሎ መሄድ አለ በት ። ወሬው ፣ ሐሳቡ ሁሉ አድርጅቱና እሥራው ላይ መሆን አለ በት ። ጉልበቱ ፣ ፍቅሩ ለድርጅቱና ለሥራው መሆን አለበት ። ሕይወቱ እሱ ብቻ ነው ። ምን ቀረው? ከሥራው ውጭ ያለ ሕይ ወቱማ አበቃ ። አለቀ ። ከናንሲ ጋር ተቀበረ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ ስምንት

«ተዘጋጅተሻል ?»

« ይመስለኛል »

ናንሲ ማክአሊስተር የመጀመሪያው አፕራሲዮን ሲደረግ ላት ነው ። ካንገቷ በላይ ምንም ስሜት አይሰማትም ። በዓይ ኖቿ ያለችበትን ባታይ ኖሮ ፊቷ ለመኖሩ ርግጠኛ ባልሆነች ነበር ።

የአፕራሲዮን ማድረጊያው ክፍል መብራት ስለሚያብረቀ ርቅ አይኗን በደንብ መግለጥ እያስቸገራት ነው ። ዓይኗን ማጨ ንቆር ይኖርባት ነበር ። ይህን እንኳን ማድረግ አልተቻላትም ።

የሚታያት የፒተር ፊት ብቻ ነው ። አፕራሲዮን የሚያደርግ ሀኪም የሚለብሰውን ልብስ ለብሷል ። አፉንም ተሸፍኗል ። ዓይኖቹ ፤ ፍቅርን የሚረጩ ዓይኖቹ ያበራሉ ።

ፒተር ግሬግሰን ናንሲ ከመጣችበት ጊዜ ጀምሮ አላረፈም። አፕራሲዮን ከመጀመሩ በፊት ቀዶ ህክምናውን የሚያካሒድ በትን ዘዴ ሲቀይስ ፤ ሲነድፍ ፤ አጠናክሮ ንድፉን ሲያወጣ ፤ ሲለካ ሲዘጋጅና ሲያሜውታት ሰባት ሳምንት አለፈ ። ይህን ሁሉ የሚያደርገው ደግሞ ፊቷን በተለያየ ጊዜ ራጅ አንስቶ ነበርና ከራጁ ያገኘውን ምስል እንደመነሻ በማድረግ የጉደለ ውን በማየት ፤ የሚሟላውን በማጥናት ነበር ። የናንሲን ፊት እንደገና ለማነጽ ፎቶ ግራፉን ማግኘት ይፈልግ ይሆናል። ሆኖም የተገኘው አንድ ፎቶ ግራፍ ብቻ ነበር ። ይኸውም እሷና ማይ ክል ርሄት በትለርና ስካርለት አሀራን ሆነው በባዛር ላይ የተነ ሱት ፎቶግራፍ ብቻ ። እሱም በደንብ አልወጣም ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ያም ሆነ ያ እሱም አያስፈልገውም ። ለመነሻ ያህልም ቢሆን ያቀደው ፊት አለ ።

«ነቃ ፥ ነቃ ማለት አለብሽ ። ትንሽ ሰመመን . . . ኖ . . . መተኛት የለብሽም ። ያ እንዳይሆን ደግሞ አነጋግሪኝ » አለ እንቅልፍ ሲሜናት ሽፋኗ ሲሰበር ስላየ፦በልቡ ደግሞ ያለዚያ ደምሽ ያንቅሻል ሲል ጨመረ ። ይህን ግን አልነገራትም ። ሊነግራትም አልፈለገም ።

«እማሆይ አግኒስ ሜሪን መሆን እንደምትፈልጊ አሁንም ርግጠኛ ነሽ ? » አላት ፤ እንዳትተኛ ለማድረግ ።

«እንዴ . . . ሃ ! ሃ ! ሃ ! . . . ቃል ፥ ቃል አይደለምንዴ » አለች ።

ሶስት ሰዓት የፈጀው ኦፕራሲዮን ሲከናወን በዚህ ሁኔታ እየተቀባበሉ አሳለፉት ። ይህ ሁሉ ሲሆን ታዲያ እጁ አንዴም አላረፈም ። ናንሲ የእጁን እንቅስቃሴ ስታይ ልክ የባሌ ተውኔት ዳንስ እንደማየት ሆኖ ነበር የተሰማት ።

«በዚህ ሁኔታ ከጥቂት ሣምንታት በኋላ አዲሱን አፓርትማ እንከራይና ትገቢያለሽ . . . እስኪ አስቢው ፥ ደስ የሚል ነገር አይመስልሽም ? . . . እንዴ እንቅልፍ ! መተኛትሽ ነውን' ዴ . . . . የአዲሱ አፓርትማ አቀማመጥ እንዴት ቢሆን ይሻል ይመስልሻል ? እመኝታ ቤትሽ ሆኖ በመስኮት የሳንፍራንሲስኮን ወደብ የሚያሳይ ቢሆን ይስማማሻል ? »

« አዎና ፥ ለምን አይስማማኝም »

«አዎና ብቻ ነው እምትይው ? በጣም ፥ በጣም . . . ምና ምን አይባልም ! የለም ፥ የለም ይህ ከሆስፒታሉ ላይ ሆነሽ የሚታይሽ ነገር አእምሮሽን እያሻገተው ሳይሆን አይቀርም »

«ውሸት ነው ። በጣም ነው የሚያስደስተኝ እንዲያውም»

«ደግ' ንግዲያ ። አንድ ቀን አብረን ወጣ እንልና ከዚህ በጣም የተሻለ ቤት እንመርጣለን »



t.me/OLDBOOKSPDF

«ጥሩ» አለች እንቅልፍ በተጫነው ድምፅ። እንቅልፍ በተጫጫነው ድምፅ ብትናገርም ደስ መሰኘቷ ይታወቅ ነበር።

«እንዴት ነው አሁን መተኛት አልችልም ማለት ነው ?» አለች ።

«ልዕልት ሆይ እንሆ የመኝታ ጊዜ ተቃርቧል ። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ወደ መኝታ ቤትዎ እናደርስዎታለን ። ከዚ ያም ልዕልትነትዎ የፈቀደውን ያህል ሊተኛ ይችላል»

«መልካም»

«አሃ ! ሳሰለችሽ ነበር ማለት ነው የቆየሁት !»

ይህን ያለበት የቀልድ ኩርፊያ ድምፅ አሳቃት ።

«እሺ ፍቅሬ... አሁን ሁሉም ዝግጁ ነው» አለና ረዳ ቱን ተመለከተ ። በጥቅሻ አመለካከት ። ይህን ያየችው ነርስ ናንሲን መርፌ ወጋቻት ። ይህ ሲደረግ ፒተር አላየም ። ወደና ንሲ ጠጋ ብሎ ዓይን ዓይኗን ያይ ነበር ። እሱ ፣ የሷን ! እሷም የሱን ዓይን በሚገባ ያውቃሉ ። መግባባታቸውን የሚያዩት በዓይኖቻቸው ውስጥ ነበር ።

«ዛሬ ለየት ያለቀን መሆኑን ታውቂያለሽ ?» አላት

«አዎ» አለችው ።

«ኧረ ?... እንዴት ልታውቂ ቻልሽ ?» ምክንያቱም አለች በልቧ ፣ ምክንያቱም ዛሬ የማይከል ልደት ነው ። ማይ ከል ዛሬ ልክ ሃያ አምስት ዓመት ይሆነዋል ። አሁን በዚህ ሰዓት ምን እያደረገ ይሆን ?

ይህን በልቧ ብላ በአፏ ግን —

«እንዲሁ አውቀዋለሁ» አለችው ።

«ደግ ። ሆኖም መልሱ አላጠገበኝም ። ስለዚህ እኔ ልንገ ርሽ ። ይህ ቀን የተለየ ቀን የሚሆንበት ዋና ምክንያት የመጀ



t.me/OLDBOOKSPDF

መሪያ ቀን በመሆኑ ነው ። የቀዶ ህክምና ሥራችን መጀመሪያ፣ እንችን ለመፍጠር በምናደርገው አስደናቂ ጉዞ የመጀመሪያው ርምጃችን በመሆኑ ነው ። ምን ይመስልሻል ?»

ይህን ብሎ ፈገግ አለ ። ዓይኖቿ በእንቅልፍ ተሸበቡ ። የተወጋችው የእንቅልፍ መርፌ ሥራ ማለት ነው ።

★ ★ ★

«መልካም ልደት አለቃዬ»

«እንደሱ ብለህ አትጥራኝ አላልኩም ! አንተ ወፈፌ ። የከር ስቶስ ያለህ ። ምን መሰልክ ቤን ? ለማኝ »

«አመሰግናለሁ ስለመልካም አስተያየትህ» አለ ቤን አብሪ ። ይህን ብሎ እንዲት ፀሐፊ ደግፋው በክራንች እየተረዳ ወደ ማይክል ቢሮ ገባ ። ፀሐፊዋ ደጋግፋ አስቀምጣው ወጣች ።

«እንዴት ያለ ቆንጆ ቢሮ ሰጡህ እባክህ ። የኔም እንደዚህ ያማረ ይሆን ይሆን?» አለ ቤን ።

«ከፈለክ ይህን ራሱን መውሰድ ትችላለህ ። እኔን እንደሆነ ገና ሳይጀመር ስልችት ብሎኛል» አለ ማይክል ።

«እሱም የሚከፋ ሃሳብ አይደለም ። አዲስ ነገር ቢኖር ...» አለ ቤን። ቤንና ማይክል ሁለት ጊዜ ያህል መገናኘታቸው ነው። ቤን ከቦስተን ወደ ኒውዮርክ ከመጣ ጀምሮ ገና ያላነሱት ነገር አለ ። የሚሸሹት ነገር አለ ። ሁለቱም ሊያነሱት ይፈልጋሉ ። ግን ይሸሻሉ ። ስለናንሲ ማውራት ሁለቱም ይፈልጋሉ ። ሀዘናቸውን ሊወጡ ይሻሉ ። ግን አልቻሉም ። ዳርዳር ማለት ብቻ ።

«ሐኪሙ ከሣምንት በኋላ ፡ ማለት በሚቀጥለው ሳምንት ስራ ህን መጀመር ትችላለህ ብሎኛል » አለ ቤን አብሪ

ማይክል ይህን ሲሰማ ስቆ—

«ቤን በቃ'ኮ አለቀልህ—የወጣለት ጅል ሆንክ'ኮ » አለ ።

« አንተሳ ! ጤነኛ ! »



t.me/OLDBOOKSPDF

«ነኝና!» አለና ፊቱ ድንገት ቅጭም ብሎ ወዲያው ፈካ አለ። ቢያንስ የሚታይ የተሰበረ ነገር የለም ብሎ። ከዚያም «ስንት ጊዜ ልንገርህ? ቢያንስ ሶስት ሳምንት ማረፍ ትችላለህ—ካሁን በኋላ ነውኮ የምልህ! አስፈላጊ ከሆነ ደግሞ ከዚያ በላይ ...» በደንብ ካየው በኋላ፦

«እንዲያውስ ለምን ወደ አውሮፓ አትሄዱም! አንተና እህትህ?» አለው።

«ምን ልሠራ? በአካለ ስንኩል ተሽከርካሪ ወንበር ላይ ተቀምጬ የሴቶችን ኋላና የዋና ልብስ እያየሁ ልጎመዥ? ይልቅስ አሁን እውነቱን ነው ስራ መጀመር እፈልጋለሁ»

«ደግ! እንደሁኔታው እናደርጋለን»

ሁለቱም ዝም አሉ! ድንገት። ከዚያም ማይክል ቀና ብሎ ምርር ባለ አተያይ ቤንን ከተመለከተው በኋላ፣

«ከዚያስ?» አለው።

«ከዚያ ስትል ምን ማለትህ ነው ማይክል?» አለ ቤን።

«ከዚያስ ማለቴ ነዋ! ስራ ጀመርን። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ወደ ፊት ለሚመጣው ሃምሣ ዓመት ያህል ስንለፋ፣ ስንባዝን እንኖራለን። ኖረንስ ምን እናደርጋለን? ማለት የመልፋት፣ የመባዘን ጥቅሙ ምንድነው? ስራህ! ለፋህ! ተከበርክ—እና ምን ይጠበስ?»

«ደህና ደህናውን እያሳሰበህ ነውና ጂል! ምን ነካህና እንዲህ ምርር አልህ? በጧቱ ጣትህን በር ቀረጠፈህ?»

«የለም ቤን፣ ቀልድ ይቅም። በስላሴ፣ ላፍታ ያህል ቁም ነገር እንነጋገር። እና ምን ይጠበስ?»

«ምንም የማውቀው ነገር የለም። እኔም አደጋው ከደረሰብኝ ጊዜ ጀምሮ የዚህ አይነቱ ሀሳብ፣ የዚህ አይነቱ ጥያቄ አእምሮዬን እየኮረኮረ ሲያስቸግረኝ ነው የሰነበተው።»

«ምን— ምን መልስ አገኘህለት?»



t.me/OLDBOOKSPDF

«ኢንጃ፤ ማይክ ። እንጃ ። ርግጠኛ አይደለሁም ። እንዲያውም መምጣቴ ደግ ሆነ መሰለኝ ። ምናልባት ሞትን ተምሽ በመዳኔ ህይወትን ይበልጥ እንድወዳት እያደረገኝ ይሆናል» አለና ሀዘን ፊቱን ሲሰብረው ታዩ ።

ፀጥታ ሆነ። ሁለቱም ተዋጡ። ማይክል አይኑን ጨፈነ። ከዚያም ተነስቶ ወደ ቤን ሄደ ። እፊቱ ተንበረከከ ። ፊት ለፊት እየተያዩ አለቀሱ ። እንባቸው በፊታቸው ላይ ተረጨ። እጅ ለእጅ ተጨባብጥው እርስ በርስ ተፅናኑ ። የአስር ዓመት ጓደኝነት፣ የአስር ዓመት ፅኑ መግባባት፣ ፅኑ ፍቅር ።

«አመሰግናለሁ ቤን ፣ እግዜር ይስጥልኝ » አለ ማይክል ።

«ማይክ ስማ!» አለ ቤን እንባውን እየጠረገና ተንኮል እፊቱ ላይ እየነጋ ። «ስማ፣ ዛሬ የልደት ቀንህ አይደለም ? ለምን አንወጣምና አንቀማምስም ? »

ማይክም ፈገግ አለና ቤንን አየው። ተስማማ፤ በአንገት እንቅስቃሴ ። ከዚያም ሰአቱን አዩ ።

«አስራ አንድ ሰዓት መሆኑ ነው ። ስብሰባም የለብኝም ። እንሂድ» አለና ቤንን ደግፎ አነሳው ። ተደጋግፈው ወጡ ። ደግፎ እመኪና ውስጥ አስገባው ። ከግማሽ ሰአት በኋላ ወደ ሞቅታ አለም በመጋለብ ላይ ነበሩ።

★ ★ ★

ጢት እንደምንም ብሎ ተነሳ ። ከእኩለ ሌሊት በኋላ ነበር እቤቱ የደረሰው። ወደ መኝታ ክፍሉ ያስገባው ዘበኛ ነበር ። ሰራተኛዋ ለቁርስ ስትቀሰቅሰው አልጋው ላይ አልነበረም ። እወለሉ ላይ ተኝቶ ነበር ያገኘችው ።

እንደምንም ብሎ ወደ ምግብ ቤት ሄደ ። ግሪኮን ተድግፃ ለባብሳ ጋዜጣ ስታነብ አገኛት ። ለቁርስ የቀረበውን ነገር ሲያይ አቅለሸለሸው ። ራሱን ይወቅረዋል ።



t.me/OLDBOOKSPDF

«ትናንት እንዴት ነበር ? » አለች ማሪዮን ።

«ከቤን ጋር ነበር ያመሸሁት »

«ኢብራችሁ እንደወጣችሁማ ጸሐፊህ ነገረችኝ ። የዚህ ዓይነት ነገር ባይለምድብህ መልካም ነው ። »

እኮ ለምን ? አለ በሀሳቡ ።

«ምኑ ! መጠጣቱ ? »

« ሰዓት ከመድረሱ በፊት ቢሮ ጥሎ መውጣት ማለቴ ነበር ። መጠጣቱም ቢሆን በርታ የሚያስኝ አይደለም ። ወደ ቤት ስትገባ አምሮብህ እንደገባህ ነው »

«እንጃ ትዝ አይለኝም » አለ ! ፉት ያለው ቡና ሽቅብ እየ ተናነቀው ።

«ሌላ የዘነጋኸው ነገር ትናንት ለራት ጋብዤህ ነበር ። ግን አልመጣህም ። እኔና ሌሎች እንግዶች አሥር ሆነን ስንጠብ ቅህ ነው ያመሸነው »

«አላወቅኩም ። ራት ጋብዤሀለሁ ስትይኝ ሁለታችን ብቻ የምንገኝ መስሎኝ ነበር »

« እና. . . እኔስ ብሆን ፣ እኔ መጠበቅ ነበረብኝ ? »

« እንደሱ ማለቴ ሳይሆን . . . ዘነጋሁት ። ተረጂልኝ እንጂ ችግሬን ግሚ ። የትናንቱ የልደት በዓል ለኔ በእል አልነበረም እኮ ! ደስ ብሎኝ ላከብረው እችላለሁ ? » ።

« በቃ ተወው ። ይቅርታ » አለች ።

ትበል እንጂ ያ ቀን ለእሱ ለምን መልካም ቀን እንዳል ሆነ የተገነዘበች አትመስልም ነበር ።

« ነገርን ነገር ያመጣዋል ። ቤት ተከራይቼ ለብቻዬ መኖር እፈልጋለሁ »

በመገረም ቀና ብላ አየችውና ! « ለምን ? » አለች ።



t.me/OLDBOOKSPDF

«ምክንያቱም ሃያ አምስት ዓመት ሞላኝ ። ሠራተኛ ነኝ። ዘላለም አብሬሽ መኖር የለብኝም »

« ምንም ነገር በግዴታ ማድረግ የለብህም » አለች ። በልቧ ስለ ቤን አብሮ ጓደኝነት ማስላሰል እየጀመረች ።

«የለም ነገሩን በከፋ እንድትተረጉሚው አይደለም ። ሆኖም እንተወው ። ራስ ምታት እንደወፍጮ እየወቀረኝ ነው »

«የዞረ ድምር መሆኑ ነዋ » አለችና ተነሳች ፤ ሰዓቷን እያየች «ቢሮ እንገናኝ ። በሰዓቱ ግባ ። ደሞ ስብሰባ አለ እንዳትረሳ። የሀውስተንን ጉዳይ በሚመለከት ስብሰባ መኖሩ ተነግሮህ የለ ? እንዴት ነው ልትገኝ ትችላለህ ? »

« እችላለሁ . . . . እና ስለቤቱ ጉዳይ . . . እሚከፋሽ ከሆነ ይቅርታ ። ግን ወስኜ ጨርሻለሁ ። ጊዜው የደረሰ ይመስለኛል። »

ኮስተር ብላ ካጤነችው በኋላ ፤

« ይሆናል ማይክል ። ምናልባት ጊዜው ይሆናል ። በነገራችን ላይ መልካም የልደት በዓል ይሁንልህ » ብላ ግንባሩን ሳመችው። መልካም ምኞቷን በፈገግታ ተቀብሎ ራስ ምታቱ እየወቀረው «እቢሮ ጠረጴዛህ ላይ ስጦታ ቢጤ አስቀምጬልሀለሁ» ስትለው፣

« አስፈላጊ አልነበረም » አለ ።

ከልቡ ነበር ። ካሁን በኋላ ለሱ ምንም ምን ነገር አያስፈልገውም ። ልቡን ሊያፈካ የሚችል ምንም ዓይነት ስጦታ አይኖርም ። ቤን ይህን ተረድቶለታል ። ስለዚህም የልደት ስጦታ አልገዛለትም ።

« ለኔ የልደት ቀንህ ነው ማይክል ። የሆነውም ቢሆን ላንተ የተወለድክበት ቀን ልዩ መሆኑን አትዘንጋ ። በል መሥሪያ ቤት እንገናኝ » ብላ ወጣች ።

እናቱ ወደ ሥራ ከሔደች በኋላ እዚያው ምግብ ቤት ተቀምጦ ለረጅም ጊዜ ቆየ ። የውጭውን ትዕይንት እየተመለከተ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

የሱ መኖሪያ ሌላ ነው ። መኖሪያውን በሚገባ ያውቀዋል ። ግን ያ አፓርትማ የሚገኘው በስተን ውስጥ ነው ። ቢሆንም የተቻለውን ያህል ይፈልጋል ፣ ተመሳሳዩን እስኪያገኝ ። ዛሬም ልቡ አላመነም ። ዛሬም ተስፋ ያደርጋል ። ምንም እንኳ ከንቱ ተስፋ ፣ የሞኝ ተስፋ ቢሆንም ውስጡ ግን አልቆረጠም ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ ዘጠኝ

«ሃይ ! ሱ ! ሚስተር ሂልያርድ አለ ?»

ቤን አብሮ እማይክል ቢሮ ሲገባ ደስ ብሎት ነበር። አሰ ልቺው የስራ ሰዓት ወደ መገባደዱ ተቃርቦ ስለነበር ደስ ብሎ ታል ። ቀኑን በሙሉ ወዲያ ወዲህ ሲዋከብ ነው የሚውለው ። ማረፍ ቀርቶ ቁጢ መሬት ሊነካ የሚችልበት ጊዜ የለውም ።

«አዎ ፣ ልታነጋግረው እንደምትፈልግ ልንገረው ? » አለች ሱ ፈገግ እያለች ።

በአለባበስ የተሸፈነው መልካም ቅርጽ አይኑን ሳበው ። ማሪ ዮን ሂልያርድ ሽቅርቅር ነኝ ባይ ፀሐፊዎችን አትቀበልም ፤ ለሌላ ሠራተኛ ቀርቶ ለልጅዋ እንኳን አለ በሃሳቡ ። ቀጥሎም ወይስ በተለይ ለልጅዋ ይሆን ? ቤን ይህን እያሰበ «ልንገረው ?» ላለችው እንገቱን በአሉታ እየነቀነቀ ፤—

«የለም ። እንችን ማድከምም አያስፈልግም ። እኔው ዝም ብዬ እገባለሁ» አላት ። የማይክልን ቢሮ በር አንኳኳ ።

«እዚህ ቤት ! ሰው የለም ?» አለ እንደቀልድ ።

ምንም መልስ አልነበረም ። እንደገና አንኳኳ ። አሁንም መልስ አልነበረም ።

«ርግጠኛ ነሽ—እውስጥ አለ » አለ ቤን ፀሐፊዋን ዞር ብሎ እየተመለከተ ።

«እርግጠኛ ነኝ»

«ነው ?» አለና እንደገና አንኳኳ ።

በዚህ ጊዜ የሻከረ ድምፅ «ይግቡ » አለ ከውስጥ ። ቤን በሩን ቀስ ብሎ ገፋ አድርጎ ገባ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

«ምን ሆንክ? ተኝተህ ነበር ወይስ ምን?»

ማይክል ቀና ብሎ እየውና፣

«ያማ መታደል ነበር ። መተኛት ዕድቅ አይደለም እንዴ፣ እስቲ ይኸን ጉድ ተመልከትልኝ» አለ ።

በጠረቤዛው ላይ የተከመረው ፋይል ብዛት መጠን አልነበረውም ። ያን ሁሉ ስራ የተመለከተው ቤን በልቡ ይህን ስራ ለማጠናቀቅ እስር ሰዎች ዓመት ይፈጅባቸዋል ሲል አሰበ ።

«ተቀመጣ፤ ቤን» አለ ማይክል ።

«እሺ አመሰግናለሁ፤ አለቃዬ» አለ ቤን ። ሁሌም እንደዚህ እያለ ያሾፍበታል ።

«ዝጋ እንግዲህ ! ደሞ ምንድነው የተሸከምከው ? አንተም ሌላ ተጨማሪ ስራ ይዘህብኝ መጣህ ልበል ?» አለ ማይክል ። «ይሞ ሌላ ተጨማሪ ስራ በተለይ ስለዚያ ጣጠኛ የገበያ ማዕከልና ስለ ካንሳስ ሰቲው ገበያ ይዘህብኝ መጥተህ እንዳይሆን ፤ ራሴን ሲያ ዞረኝ ምንም አልቀረውም ለራሱ »

« ግን ያን ያህል አልጠላኸውም ። እንዲያውም ትወደዋለህ ። ማይክ፤ እስኪ ንገረኝ በመጨረሻ ያየኸው ፊልም ምንድነው? ዘ ብሪጅ ኦን ዘ ሪቨር ክዌይ ወይስ ፋንታሲያ? ለምንድነው ከዚህ ጉረኖህ አንዳንዴ ወጣ የማትለው?» አለ ቤን ።

« እንግዲህ ፋታ ሳገኝ መሞከሬ አይቀርም » አለ ማይክ «በነገራችን ላይ የምን ፋይል ነው የያዝከው ?»

«አትጨነቅ ። ማስመሰያ ነው ። ላሜውትህ ፈለኩና ይህን ተሸከሜ መጣሁ »

« ዝም ብለህ ብትመጣ የሚከለክልህ ነገር አለ?»

«አይ እንዲያው ነው ። አንዳንዴ እናትህ ስንስርዓት አጥባቂውን የት/ቤት ሞግዚት እንዳልሆነች እየተረሳኝ...»



t.me/OLDBOOKSPDF

«እሱን ባለመሆኗ እግዜር ምስጋና ይግባው . . . »

ይቦሉ እንጂ ሁለቱም ያውቃሉ ፤ ማሪዮን ከዚያ ከሚያመጡት ምግዚት ብትብስ እንጂ እንደማትሻል ።

ከዚህ በኋላ ባለፈው የዓመት ፈቃዱን ስላሳለፈበት ሁኔታ ጠየቀው ማይክል ፤ ቤንን ።

«ታስብልኛለህ አደለም ? » አለ ቤን ።

« ለምን አላስብልህም ? »

«ልክ ነህ» አለ ቤን ትንሽ ካሰበ በኋላ ትክዝ ብሎ «እምን ሃለሁ ፤ ለኔ ታስብልኛለህ ። ለራስህ ግን ግድ የለህም »

ሁለቱም ዝም አሉ ።

« ማይክ ፤ ለመሆኑ በቅርብ ጊዜ ፊትህን በመስታወት አይተ ኸው ታውቃለህ ? ማስፈራሪያ መስለሃልኮ ! ማይክ እባክህ እምቢ አትበል ። አንድ ነገር ልለምንህ »

« ምን ? »

« እምቢ አትበል »

« እኮ ጠይቀኝ »

« በዚህ በመጭው እሁድ ቅዳሜ አንድ ቦታ ሄደን እናሳ ልፍ ። ሁሉም ፤ ጓደኞቻችን ሁሉ ይምጣ ብለዋል ። »

ቤን ይህንን ያለው ከልቡ ነበር ። ይህ ደግሞ ለማይክል በደ ንብ ገብቶታል ። ሆኖም አራሱን በአሉታ ነቀነቀ ።

«ቤን ደስ ይለኝ ነበር ። እውነት ። ግን ይኸው እንደምታ የው ነው ስራው ፤ በተለይ የካንሳስ ሲቲ የገበያ ማዕከል ጉዳይ። ሌላም አለ ። ምን ዋጋ አለው ብለህ ነው ። ምንም መልስ የማይገኝ ለት አርባ ሰባት ጥያቄ ሆነኮ ። ትናንት ስብሰባው ላይ አንተስ ነበርክ አይደለምንዴ ?

«እኔም ብቻ ሳልሆን ሌሎች ሃያ ሶስት ሰዎችም ነበሩ ። ታዲያ ያ ሁሉ ሰው እያለ አንተ ብቻህን ምን በወጣህ ነው



t.me/OLDBOOKSPDF

ህ ያው ይምሰል እንጂ እማውቅህ እምወድህ ሰው አይደለህም ። የማውቀውን ፣ የምወደውን ሰው ሌላ የማላውቀው ሰው ድቡሽት ሲጭንበት እያየሁ ነው ። ይህን ደግሞ አልቀበለውም ። ወጣ ብል። ለመኖር ሞክር ። ከዚህ ከቅርብ እንጀምር ። ከቆንጆ ፀሐፊህ ጋር ውጣ ። ወይም በየፓርቲው በቀን መአት ቆንጃጅት ማግኘት ይቻላል ። ወይም . . . »

« ውጣ ! » አለ ማይክ ከጣራ በላይ ጮሆ አቋርጦት «ውጣ ልኝ ቤን ! . . . ከቢሮዬ ውጣልኝ ። ሳላንቅህ ፣ ሳልገልህ ውጣልኝ ! »

ከመቀመጫው ተነስቶ ፣ ጣቶቹን ለማነቅ እንጨፍርሮ በጠ ጴዛው ላይ ሰውነቱን አስግጎ ነበር እንዲህ ያለው ።

ጩኸቱ የቆሰለ አንበሳ ጩኸት ነበር ። ለቅጽበት ያህል ሁለቱም ጓደኞች ተፋጠው እያሉ በያሉበት ቆመው ቀሩ ። ሁለ ቱም ስለተናገሩት ነገር ፣ በመካከላቸው ስለተፈጠረው ሁኔታ ሲያሰቡ ደንግጠው ፈርተው ነበር ።

« አ ይቅርታ አድርግልኝ ቤን » አለና ተቀመጠ ። እና ራሱን በእጆቹ ደግፎ አቀረቀረ ። እዚያው እንዳቀረቀረ ቆይቶ ቀና ሳይል ፣

«ለምን አንተወውም ። ይለፍ ሌላ ቀን » አለ ማይክ ።

ቤን አብሪ ቃል አልተነፈሰም ። ቀስ ብሎ የቢሮውን በር ከፍቶ ወጣ ። ሲወጣ እንኳ ማይክ ቀና ብሎ ሊያየው አልቻለም ። በሩን ዘግቶ ሔደ ፣ ቤን ። ሌላ የሚባል የሚጨመር ነገር አልነ በረምና ምን ምን ሊል አልቻለም ።

★ ★ ★

ያን ለት ቤን አብሪ ከቢሮው የወጣው በሥራ ሰዓት ላይ አንድ ሰዓት ተኩል ጨምሮ ነበር ። ከምሽቱ አሥራ ሁለት ተኩል ላይ ከቢሮው ሲወጣ የማይክል ቢሮ መብራት እንደበራ



t.me/OLDBOOKSPDF

ነበር ። ገና እስከምሽቱ አምስት ሰዓት ድረስ ያ መብራት እንደ ማይጠፋ ቤን ተገነዘበ ። እውነት አለው ። የት ይሂድ ? ወደ ቤቱ እሚሔድበት ምን ምክንያትስ አለው ? ከሶስት ወር በፊት ማይክል የተከራየው አፓርትማ ባዶ ነው። ሁለት ታጣፊ ወንበሮች ፡ አንድ አልጋ . . . ሌላ ምንም ዕቃ የለበትም ። ቤን ያ አፓርትማ በሆነ መንገድ የናንሲን የቦስተን አፓርትማ እንደ ሚመስል ተገንዝቧል ። ማይክም ይህን ሳያይ አይቀርም ። ምናልባትም የተከራየው ያን ስላየ ይሆናል ። ግን ዋጋ የለውም ። ቤቱ ቤት ሊመስለው አልቻለም ። ኑሮው ኑሮ ሊሆንለት አልቻለም ። ስለዚህም እሥራው ላይ ተደፍቶ መዋል ! ማምሸት አመጣ ። እንደ እብደት ሥራ ሥራ ሥራ አለ ። ካልደከመው እንቅልፍ ሊወስደው ስለማይችል ይሆናል ።

ይህ ነገር ቤንን ደስ ሊያሰኘው አይችልም ። ሆኖም እሱም ሆነ ሌላ ሰው ምንም ማድረግ አይችልም ። ማንም ሰው ማይ ክልን ሊያድነው ፣ ከገባበት ማጥ ጎትቶ ሊያወጣው አይችልም ። ያለ አንድ ሰው በስተቀር ። ያለ ናንሲ በስተቀር። ናንሲ ደግሞ የለችም ። ናንሲ ደግሞ ቀርታለች ። ሞታለች ።

ቤን ስለናንሲ ሲያስብ መላ አካሉን ስቅቅ አለው ። ሆዱን አመመው ። ቢሆንም የሱ የአካልም ሆነ የመንፈስ ቁስል እየሻ ረለት ነበር ። ወጣት ነውና እየሻረለት ነበር ። ምነው የማይክ ልም ቁስል እንደሱ ቁስል ቢሽር ? ነገር ግን የማይክል ስብራት ድርብ ነው ፣ የነፍስና የሥጋ ሥብራት . . . .



t.me/OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ አሥር

«ኢሺ ወጣቷ እመቤት ? እንዴት ነው ፣ ቃሌን የምጠብቅ ሰው ነኝ ወይስ አይደለሁም ? ቤቱ እንዴት ነው ? ውበትን ለማሳየት ታቅዶ የተሠራ አይመስልሽም ?» አለ ፒተር ግሬግሰን ።

ግሬግሰን ይህን የሚለው ለናንሲ በተከራየላት አፓርታማ መናፈሻ ሰገነት ላይ ተቀምጠው የአካባቢውን ትዕይንት በማየት ላይ እንዳሉ ነበር ። ይህን ሲል መለስ ብላ አየችው። እሱም አያት ። በመተያየት ሐሳባቸውን ተለዋወጡ ።

የናንሲ ፊት አሁንም በፋሻ እንደተጠቀለለ ሲሆን ዓይኖቿ አፋሻው መሐል በደስታ ሲጨፋፍሩ ይታያሉ። የእጅዋ ላይ ፋሻ ተፈትቷል ። ምንም እንኳ የከዚህ በፊቱ እጆቿን ባይመስሉም ውብ ነበሩ ።

አፓርትሜንቱ ፣ አመናፈሻ ሰገነቱ ላይ ሆኖ ማታ የፀሐይን መጥለቅ ፣ ጥዋት የፀሐይን መውጣት ለማየት እንዲያመች ሆኖ የተሠራ ሲሆን ይህ ደግሞ ለናንሲ ወሰን የሌለው ደስታን ሰጥቷት ነበር ። ፒተር እንደፎከረው ከሁሉም የተሻለውን አፓርትማ አገኘላት ።

ይህን ስታስብ

«ታውቃለህ ፒተር ፣ አንዳንዴ እንደኛየን ሙልቅቅ አልኩኮ እያልኩ እስባለሁ» አለች ።

«ሲያንስሽ ነው ። ይልቅስ አንድ ነገር አስታወስከኝ ። አንድ ዕቃ እምጥቼልሻለሁ» አለ ፒተር ።

ገና ዕቃ እንዳመጣላት ሲናገር እንደሕፃን ልጅ መፈንጠዝ ጀመረች ። ፒተር አየት አድርጓት ፊቱ በደስታ እንደበራ ወደ ቤት ገባ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ናንሲ ስለፒተር አሰበች ። ደግ ሰው ነው ። ትወደዋለች። ምን ጊዜም ቢሆን የሚያስደስታትን ነገር ሲያድን የሚውል ይመስላታል ። የማይሰጣት ስጦታ የለም ። እንደልጅ ያጫውታታል ፤ የመጽሔት ክምር ፣ የመጻሕፍት ቁልል ፣ አስቂኝ አሠራር ያለው ባርኔጣ ፣ ወደር የሌለው ያንገት ልብስ ያበረክትላታል ።

እጆቿን ጠግና ፋሻውን ሲፈታ ላዲሱ እጅዋ መመረቂያ የሚያማምሩ አምባሮች ሰጣት ።

አንድ ከበድ ያለና የተጠቀለለ አራት ማዕዘን ነገር ይዞ መጣ ። ገና ስታየው መፈንደቋ ጨመረ ። ምን ይሆን ? ትልቅ ነገር መሆን አለበት ። ጭኗ ላይ አስቀመጠላት ። ልክ ነው የገመትኩት ፡ ልክ ነው ! ስትል አሰበች ።

«ምንድነው ፒተር ? የሆነ እንደ ድንጋይ የሚከብድ ነገር» አለች ።

«እንደ ድንጋይ አልሺኝ ? አልተሳሳትሽም ። በየሱቁ ዞሬ በገበያ ላይ ያገኘሁትን የመጨረሻውን ትልቅ የከበረ ድንጋይ ነው ገዝቼ ያመጣሁልሽ» አላት ።

ይህን ነበር የገመተችው ። ፈታችው ። ከገመተችው ፣ ካሰበችው ውጭ ነበር የዛሬው ስጦታ ። ሆኖም ልክ ነው ። ካሰበችውም የሚበልጥ ታላቅ ስጦታ ሆኖ አገኘችው ።

«ፒተር ! አምላኬ ፣ ምን ዓይነት ስጦታ ነው ይሄ ? በፍጹም ልቀበልህ አል... »

« ትችያለሽ እንጂ ! መቀበል አለብሽ ። ሆኖም ይህን ስጦታ በነፃ ልሰጥሽ አልፈልግም ። ብዙ ሥራ ፣ ቆንጆ ሥራ ሠርተሽ እንድታሳይኝ እፈልጋለሁ »

ካሜራ ነበር ስጦታው ።

ይህ ደግሞ ቀላል ነገር አልነበረም ። ፒተር ይህን ስጦታ ብዙ አስቦበት ፣ አውጥቶ አውርዶ ነበር የገዛው ። ምክንያቱ ለፒተርም ለናንሲም ግልጽ ነው ።

እንግዲህ ናንሲ የስዕል ሥራዋን እንደገና ለመጀመር ሐሳቧ እምቢ እንዳላት ሁለቱም ያውቃሉ ። ሥዕል ሞክራ ስትባል



t.me/OLDBOOKSPDF

በመጀመሪያ በእጅዋ ስታመካኝ ቆየች ። አሁን የእጅዋ ሕክምና ሲያልቅና ሲፈታ ምን ምክንያት ልትፈጥር ትችላለች ? ለናንሲ ይህ ጭንቅ ነበር ። ለፒተር ደግሞ መፍትሔ የሚፈለግለት ጉዳይ ነበር ። መፍትሔ ይኸው ካሜራ ። ሥዕል ለመሳል ስላልፈለገች ፣ ነርሶች ያመጡአቸው የዱሮ ሥዕሎቿ እንኳ ለጉዞ እንደተቀረቀቡ ናቸው ። ልታያቸው አልፈለገችም ። አሁን በቃ ። ፎቶ ግራፍ ታነሳለች ።

«በነገራችን ላይ ካሜራው መመሪያ አለው ። እኔ ላነበው ብሞክር ምኑም አልገባህ አለኝ ። ከዚህ ካሜራ አሠራር ይልቅ የሕክምና ሙያ ትምህርት ቀለል ሳይል አይቀርም ። ላንቺ ግን ይገባሻል ብዬ ነው » አለና ሰጣት ።

ተቀበለችውና ገልበጥ ገልበጥ አደረገችው ። ላንድ ካሜራ ይህን ያህል መመሪያ ! ካሜራው በጣም የተራቀቀ መሆን አለበት። ገልበጥ ፤ ገልበጥ ።

ትንሽ አነበበች ። ተመሰጠች ።

በኋላ ማስረዳት ቀጠለች—ካሜራውን ይዛ ።

«እየህ—እየው ፤ እዚህ ላይ ጠቅ ስታደርገው . . . ይታይሃል ? » እያለች ፤

«ይህን ስተነካው ደሞ . . . » እያለች ።

«ታዲያ ይህ ስጦታ በሕይወቴ ከተሰጡኝ ስጦታዎች ሁሉ የላቀና ያማረ ነው» አለች ። ሆኖም ማይክል እባዛሩ ላይ አሸንፎ ከሰጠኝ ያንገት ጌጥ ሌላ ብላ በልቧ ጨመረች ። ይህን ሐሳብ ግን ልትገፋበት አልደፈረችም ።

ይህ ሐሳብ በፊቷ ላይ ሲዳምን ፒተር አይቷል ። ብዙ ጊዜ ይጠብቀዋል ። አንድ የተጐዳችበት ነገር . . . ያለፈ ሕይወቷ ቁስል . . .

ቢሆንም በጊዜ ብዛት ልትረሳው ትችላለች—ተስፋ ያደርጋል።

«ፊልምስ ? ፊልም አላመጣህልኝም ? »



t.me/OLDBOOKSPDF

«እምጥቻለሁ እንጂ !» አለና አነስ ያለች አራት ማዕዘን ጥቅል እየወረወረላት ፣ «ካሜራ እምጥቼ ፊልም ልርሳ ?» ሲል ጠየቃት ።

«አንተ !! አንተ ምንም አትረሳ !» አለችና መጣደፍ ጀመረች ፣ ካሜራውን ፊልም ለመሙላት ። ወዲያው በተለያዩ አቅጣጫዎች ፣ በተለያየ መንገድ ጠቅ ! ጠቅ ! ጠቅ . . . ፎቶ ታነሳው ጀመር ።

ይህን እያደረገች እያለ አነስ ያለ ቁጥር ያላቸው ወፎች ባጠገባቸው ሲበሩ ቶሎ ብላ አነሳቻቸው ።

«ምናልባት ደህና ፎቶ ላይወጣ ይችላል ። ግን ለመነሻ ምንም አይልም» አለች ።

እሱ ግን በጽሞና ይመለከታት ነበር ። ለረጅም ጊዜ በዚህ ሁኔታ ሲያጤናት ከቆየ በኋላ ብድግ ብሎ አጠገቧ ቆመና እጁን ጣል አደረገው እትከሻዋ ላይ ። ከዚያም ፣

«ናንሲ ዛሬ ላበረክትልሽ ያቀድኩት ሌላም ስጦታ አለኝ» አላት ።

«ገባኝ ፣ አወቅኩት ! መርሰድስ ነው አይደል ?»

«የለም ናንሲ ፣ አሁን እውነቴን ነው» አለና በለስላሳ የጽሞና ፈገግታ ተመለከታት ! «ካንዲት ጓደኛዬ ጋር ላስተዋውቅሽ እፈልጋለሁ ፣ የሁለታችንም ጓደኛ እንድትሆን ። ለየት ያለች እመቤት ነች»

አንዳንድ ቅጽበት አለች ። የምናስበውን በቅጡ መረዳት የማንችልባት ። በዚያች ዓይነቲቱ ቅጽበት ናንሲን የሆነ ቅናት መላ አካሏን ሲወርራት ተሰማት ። ቢሆንም ከፒተር ሁኔታ ያ ስሜት ሊሰማት እንደማይገባ ተረዳች ።

«ፌ ትባላለች» አለ ፒተር ። «ሕክምና ያጠናነው ባንድ ላይ ነው ። ባሁኑ ጊዜ ፌ አሊሰን በምዕራብ ዩናይትድ ስቴትስ ከሚገኙት ሳይኪያትሪስቶች አንዷ ናት ። ምናልባትም በሀገሪቱ አሉ



t.me/OLDBOOKSPDF

ከሚባሉት ታላላቅ የአዕምሮ ሐኪሞች አንዷ ልትሆንም ትች ላለች ። በጓደኝነት መልክ ከሆነ ደግሞ ጓደኛ ሳይሆን ሁሉን ነገር የማለት ያህል ናት ። እንደምትወጂያት ተስፋ አለኝ ።»

«እና ?» አለች ናንሲ—በመንፈሷ ውጥረትና የማወቅ ጉጉት ይታይባታል ።

«እናማ ብትተዋወቁ… ብታነጋግሪያት ደህና ይመስለኛል ። ማለት ነገሩን ከዚህ በፊት በመጠኑ ይሁን እንጂ ተነጋግረንበታል»

«ትንሽ የተዛባ ፣ ማለቴ መንፈሴ በቅጡ የተረጋጋ መስሎ አልታየህም ማለት ነው ?» —የመከፋት ድምጽ ነበር ።

ይህን ስትጠይቀው ካሜራውን ወደ ጐን ቁጭ አደረገች ።

«አላልኩም ናንሲ ፣ በሁሉም በኩል ምንም እንከን የለብ ሽም ። ከቀን ወደ ቀን እየተረጋጋሽ ፣ ከቀን ወደ ቀን አዲስ እየሆ ንሽ እንደምትሄጂ አትጠራጠሪ ። ግን ደግሞ አስቢው ። ሌላው ቢቀር የሚያዋራሽ ፣ ከኔ ሌላ ሰው ያስፈልግሻል ። እኔ ፣ ሊሊና ግሬችን ብቻ በቂ አይደለንም ። ሌላ ሰው ያስፈልግሻል—ወይስ አያስፈልግሽም ?» አለ ።

መልሱን በልቧ ሰጠች ።

አዎ አለች በልቧ ! ያስፈልገኛል ። ያም ሌላ ሰው ማይክል ፣ እሱ ብቻ ነው ።

«እንጃ ርግጠኛ አይደለሁም ። አስቤው አላውቅም» አለችው።

«ከሌ ጋር ከተዋወቃችሁ በኋላ ለካ ታስፈልገኝ ኖሯል እንደምትይ ርግጠኛ ነኝ ። በጣም ደግና ሰው ወዳድ ፍጡር ናት። በዚያም ላይ ስላንቺ ሁልጊዜ ትጠይቀኛለች»

«ታውቃለች ማለት ነው ?»

«ገና ነገሩ ሲወጠን ጀምሮ !» አለ ።

ይህን ያለውም ናንሲን ለማግባባት አልነበረም ። እውነቱን ነበር ። ዶክተር ዊክፊልድና ማሪዮን ሂልያርድ ደውለው ያነጋ



t.me/OLDBOOKSPDF

ወደያው ፌ ስላሳለፈቻቸው ነገሮች ቀስ እያለች ታጫውታት ጀመር ። ቁርጥራጭ አጋጣሚዎችን ከሕይወቷ ውጥንቅጥ እየመዘዘች ነገረቻት ።

ናንሲም ሳታስበው ከሕይወቷ አካል ትንሽ ገለጥ እያደረገች በጨረፍታ አሳየቻት ። እየቆየች ከዚያ በፊት በተለይም ከማይክል ጋር ከመገናኘቷ በፊት ለማንም ሰው ነግራ የማታውቃቸውን ነገሮች ሁሉ ነገረቻት ። ስለ እጓለማውታን ማሳደጊያው አወጋቻት ። ይህም ለፒተር በነገረችው መንገድ ሳይሆን ፣ ማለት በቀልድ ሳይሆን የምር ይሰማት የነበረውን ትዘከዝከላት ጀመር ። ብቸኝነቱን ፤ ማን ነኝ ? ከየት መጣሁ ? ብላ ትጠይቀው የነበረውን ፣ ማን ለምን እዚያ ወስዶ ከተተኝ ? ትል የነበረውን ሁሉ ።

ከዚህ ሁሉ በኋላ እንዴት እንደተነሳ ሳታውቅ ስለ ማሪዮን ሂልያርድ ታጫውታት ጀመር ።

ፌ አሊስን ይህን ሁሉ የምታዳምጣት በጽሞና ነበር ፤ መገረም የለ ፣ መጨነቅ የለ ። በጽሞና ፣

«እኔ ‘ንጃ ፣ ብቻ ስናገረው እንኳ ለራሴም እንግዳ መሆኑ ይታወቀኛል ። ግን—» አለችና ንግግሯን መቀጠል ተሳናት ። ለምን ? ቂል የሆነች ፣ ልጅ የሆነች መስሎ ተሰማት ። እና በጽሞና እምታዳምጠውን አዲስ ጓደኛዋን ቀና ብላ አይታ ለመቀጠል ሞከረች ።

«ግን አየሽ እኔ . . . እንዳልኩሽ ያላባትና ያለናት ስላደግኩ» አሁን አፏ ፈታ እያለ ሄደ ። «ምንም ዘመድ አዝማድ የሚባል ነገር ኖሮኝ አያውቅም ነበር ። እናት ወደሚባለው ነገር ቀረብ ልትል የምትችለው ያው የሕፃናት ማሳደጊያው ዋና ነበረች ። አበምኔቷ ። እሷም ያው እንደ እናት ሳይሆን ምናልባት እንደ ጋለሞታ አክስት ብትቆጠር ነው ። ስለማሪዮን ግን ያው መቼም ማይክልም ፣ ቤን የሚባለው የሱ ጓደኛም ሆነ ብለው ከነገሩኝ ወይም ድንገት ከምሰማው ብዙ ነገር እየሰማሁም ይህ


t.me/OLDBOOKSPDF

ሁሉ እያለ፣ ብንገናኝ ትወደኝ ነበር፤ በተገናኘን ብቻ ! የሚለው ጅል ሐሳብ ልበልሽ ቅዠት ወይስ ሕልም—ሁልጊዜ ይታየኝ ነበር ። መቼም ቢሆን ፣ ማሪዮንና እኔ ስምም ሆነን እንኖራለን የሚለውን ሐሳብ አምንበት ነበር»

ድንገት ዓይኗ ላይ እንባ ግጥም አለ ። ሳለማልቀስ እየታገለች ፊቷን ወደ ሌላ አዞረች ።

«ምናልባትም እናቴ ትሆናለች፣ ማለት እንደ እናት ትሆነኛለች ብለሽ ታስቢ ነበር ?»

ናንሲ በአዎንታ ራሷን ነቀነቀች ።

«እብደት አይደለም ይኸ ታዲያ ?»

«በፍጹም ። በፍጹም እብደት አይደለም ። ያለ ነገር ነው። ያለ እናት አደግሽ ። ማይክልን ወደድሽ ። የማይክልን እናት እንደ እናትሽ ለማየት፣ እናትሽ ለማድረግ ተመኘሽ ። ያለ ነው ። ምናልባት በዚህ ምክንያት ይሆን፣ በመጨረሻ በውል መልክ ስትስማሙ በማሪዮን በጣም የተማረርሽባት ፣ እንችንም በጣም የከፋሽ ?»

«አዎ ። አየሽ እንዲያ ባለ ሁኔታ ቃል ስታስገባኝ ለመጀመሪያ ጊዜ ምን ያህል እንደምትጠላኝ አረጋገጠችልኝ»

«እኔ ደሞ እንዲያ አይመስለኝም ። የሆነ ነገር ያላት ይመስለኛል ። ያ ባይሆን ይህን ሁሉ ነገር አታደርግልሽም ነበር ። ያን ሁሉ ገንዘብ ከፍላ አካልሽ እንዲመለስ ማድረጓ በጣም ስለምትጠላሽ አይመስለኝም»

ይህን ሁሉ ምኞት ትተን አለች በልቧ ፌ አሊስን ።

«ግን ውሉን አስቢው ። ይህን ሁሉ ያደረገችልኝ እኮ ማይክልን እንድተውላት ነው ። ከማይክል ጋር ግንኙነት ብፈጥር —እኔ ፈልጌ—ውሉ ሙሉ በሙሉ ይፈርሳል ። ይህ እኮ ሂሳብሽን ተቀብለሽ ከሱም ፊት ከኔም ፊት ጥፊ እንደማለት ነው ። ያኔ ስታነጋግረኝ ገባኝ ። ማሪዮን መቼም ቢሆን ልትቀበለኝ አት



t.me/OLDBOOKSPDF

ፈልገም ፥ ብዬ አሰብኩ ። ይህ ሐሳብ እንዲተሰማኝ የሆንኩትን ልነግርሽ አልችልም ። በሕይወቴ ውስጥ ካጋጠሙኝ አስከፊ ነገሮች አንዱ ነበር»

ይህን ብላ በረጅሙ ተነፈሰች ። እንደገና መናገር ስትጀምር ድምጿ ለስለስ ብሎ ነበር ።

«ግን ችግርም ፥ ስቃይም ፥ መከፋትም ለኔ አዲስ አይደሉም ። ደጋግመው ደርሰውብኝ ደጋግሜ አሳልፌአቸዋለሁ»

«ወላጆችሽ ሲሞቱ ነፍስ ታውቂ ነበር ?»

«ይህን ያህል የጐላ ትዝታ የለኝም»

የምታስታውሰውን ያህል ነገረቻት ። ቀጥላም ፥

«ትዝ የሚለኝ የሚመስለኝ ምናልባት ብቻን መቅረት አለ አይደል—እንደዚያ ዓይነት ስሜት ተሰምቶኝ ነበር መሰለኝ» አለች ።

«ልክ አሁን እንደሚሰማሽ ዓይነት ስሜት ?»

ግምት ነበር ። ቢሆንም ባዶ ግምትም አልነበረም ።

«ምናልባት ሳይሆን አይቀርም ። የት እገባ ብሎ ማሰብ ። ልክ ሳይሆን አይቀርም ። ከዚህ በኋላ የት ነው እምገባ ? ማነው አይዞሽ የሚለኝ ? የሚል ስጋት ። አሁንም አልፎ አልፎ የዚህ ዓይነት ስሜት ይሰማኛል»

«ምናልባት ማይክል ? ማይክል ይፈልገኛል ፥ አይጥለኝም ብለሽ ትገምቻለሽ ? »

«እዎ ፥ እንዳንዴ እንደሱ አስባለሁ ። የለም እንዳንዴ ሳይሆን ብዙ ጊዜ ። »

«በሌላ ጊዜስ ? ማለት ሁሌም አላልሽም»

«አሁን አሁን መጠራጠር ጀምሬአለሁ ። በፊት በፊት አየሽ ሳይመጣ ሲቀር ጊዜ ፊቱን ማየት ፈርቶ ነው ፥ ተሳቆ ነው እል



t.me/OLDBOOKSPDF

ነበር ። አሁን አሁን ግን ስለሕክምናው ያውቃል ። ስለዚህ ምን ደረሰች ፣ እንዴት ነው ብሎ መጠየቅ ነበረበት ። ታዲያ እን ዴት እንዲህ አልም ሲል በቃ ? እላለሁ»

«የግምት መልስ ሰጥተሽዋል ለጥያቄሽ ? »

«አዎ ። ግን በቂ መልስ የምትይው አይደለም ። አንዳንዴ ማሪዮን ያሳመነችው ይመስለኛል ። የሱ ዓይነቱን መልካም ስም ከሌለው ቤተሰብ የወጣች ሴት ጋር ማጋባት ለሙያህ ደግ አይደለም ብላ አሳምናው ይሆን እላለሁ ። ማሪዮን ቀላል ሰው እንዳትመ ስልሽ ! »

«እሱ እንዲህ ዓይነቱን ሐሳብ ይቀበላል ትያለሽ ? »

«በፊት እንኳ ርግጠኛ ነኝ አይቀበልም ። አያምንበትም ፣ ነበር . . . አሁን ግን እንጃ ፣ ምን ይታወቃል ? »

«ሌላ ቢያገባ . . . ቢተውሽ ምን ያህል የምትጎጂ ይመስል ሻል ? »

ናንሲ ኩምትር ስትል ታየች ። መልስ አልሰጠችም ። ግን መላ አካሏ መልሱን ሰጥቷል ።

«የሆንሽውን ሲሰማ ደንግጦ ወይም እንዲያ ሆና ላያት አል ፈልግም ብሎ እንደሆነስ ያልመጣው ? አየሽ ናንሲ ፤ አንዳንድ ወንዶች እኛ የምንፈልገውን ያህል ጠንካሮች አይደሉም»

« ይሆን ይሆናል »

«ታዲያ . . . በኋላ ከዳንሽ ከተስተካከልሽ በኋላ ቢመጣ ቅር አትሰኝበትም ? »

«ምናልባት ቅር ይለኝ ይሆናል ። ምኑም ግልጽ ሆኖ አይ ታወቀኝም ። አስባለሁ ፣ አስባለሁ ። ግን መልስ የለም»

«መልሱን መፈለግም አያሻም ። መቆየት ይመልሰዋል ። ጊዜ ይመልሰዋል ። ዋናው ነገር ግን ስሜትሽን መሸሽ የለብ ሽም ። ስሜትሽን በትክክል ለመረዳት መሞከር አለብሽ ። ያ



t.me/OLDBOOKSPDF

በቂ ነው ። ለመሆኑ ስላንቺ የሚሰማሽ ምንድነው ? ማለት ፈትሽ እንግዳ ነው ። እንግዳ ነሽ ለራስሽም ። ይህን ስታስቢ ትቅበጠ በጫለሽ ? ትፈሪያለሽ ? ትደሰቻለሽ ? ትናደጃለሽ ? »

«ከላይ የተጠቀሱት በሙሉ» አለች ። ሁሉቱም ሳቁ «ግን አብዛኛውን ጊዜ በጣም እፈራለሁ ፣ እጨነቃለሁ ። አብሮ የኖረ ነገር ቀላል አይደለም ። ሀያ ሁለት ዓመት ሙሉ እኔ ያልኩት ሌላ ሲሆን አስቢው ፣ እያበሳጭም ብለሽ ነው ? »

«እንዲያ ዓይነት ስሜት ተሰምቶሽ ያውቃል ? »

«አንዳንዴ . . . ግን አብዛኛውን ጊዜ ደፍሬ አላስብም ስለ ዚህ ጉዳይ»

«ብዙ ጊዜ እምታስቢው ስለምንድነው ? »

«እውነት ንገሪኝ ነው እምትይኝ ? »

«አዎና»

«ማይክልን ። አንዳንድ ጊዜ ፒተር በሐሳቤ ይገባል ። እብ ዛኛውን ጊዜ ግን ስለማይክል ነው እማስበው»

«ፒተርን ማፍቀር እየጀመርሽ ይመስልሻል ? »

«አይ ! አይመስለኝም ። ፒተርን እንዳባቴ ነው እማየው ። አየሽ እንደማላውቀው አባቴ ። ስጦታ ሲሰጠኝ ሲያሞላቅቀኝ አባቴ ነው እሚመስለኝ ። ፍቅር ከማይክል ጋር ነው»

«እሱንም ስንቀይ እናያለን» አለችና ፈ አሲሰን ሰዓቷን አየች ። «ያምላክ ያለህ ! ስንት ሰዓት እንደሆነ ታውቂያለሽ ? » አለች ።

ናንሲ ሰዓቷን አየች ። በጊዜው ያን ያህል መክነፍ በጣም ተደነቀች ።

« ፒተር እንዳለው እውነትም የምትገርሚ ልዩ ዓይነት ሰው ነሽ ! ምን አድርገሽ ነው እንዲህ ጊዜውን ያስረሳሽኝ ፈ? እውነትም ልዩ ሰው ነሽ ! »



t.me/OLDBOOKSPDF

«በመስማማታችን ደስ ይለኛል ። እንዲያውም ፒተር በተወሰነ ጊዜ ዘወትር መገናኘት እንዳለብን ነው የሚያስበው ። ምን ይመስልሻል ናንሲ ? »

«በጣም ደስ ይለኛል»

«ግን በየጊዜው ይህን ያህል አብረን ልንቆይ እንችላለን ማለት አይቻልም ። ጊዜ ላይኖረን ይችላል ። ስለዚህ በሳምንት ሦስት ቀን ብንገናኝ ምን ይመስልሻል ? በተረፈ ግን እንደጓደኛ በትርፍ ጊዜ መገናኘት ይቻላል ። ይስማማሻል ? »

«በጣም በጣም ይስማማኛል»

ተጨባብጠው እንደተለያዩ ናንሲ ከሁለት ቀን በኋላ ሊገናኙ የወሰዱት ቀጠሮ ሩቅ መስሎ ታያት—የራሷ ስሜት ራሷን አስገረማት ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ አሥራ አንድ

ናንሲ በክፍል ማሞቂያው ምድጃ አጠገብ በሚገኝ ምቹ ወንበር ላይ ተዝናንታ ተቀመጠችና በረጅሙ እየተነፈሰች ራሷን ጕወንበሩ የራስ መከዳ ላይ አሳረፈች ። ከፊ ጋር ባደረጉት ቀጠሮ መሰረት ነበር የመጣችው ። የቀጠሮው ሰዓት ገና አምስት ደቂቃ ያህል ቢቀረውም እሷ ግን ከዚያች ሴት ጋር ለመጨዋወት ቸኩላ ነች ፤ ወዲያው እሌላኛው ክፍል ውስጥ ቀጭ ፤ ቋ የሚለው የፊ ኮቴ ተሰማት ። ናንሲ የተቀመጠችው ፊ የአዕምሮ ችግር ያለባቸውን ሰዎች በምታነጋግርበት ፥ በምትመረምርበትና ህክምና በምታደርግበት ክፍል ነበር ። የፊን ኮቴ እንደሰማች በደስታ ፈገግ ብላ ተስተካክላ ተቀመጠች ። ሁሉም ነገር ፊ እንደለመደችውና እንደምትፈልገው እንዲሆንላት ለማድረግ አስባበታለች ።

« እንደምን አደርሽ ፥ የንጋት ወፍ ። ይኸ ቀይ ልብስ እንዴት አድርጎ ተስማምቶሻል እባክሽ ! »

ፊ ይህን ብላ እበሩ ላይ እንደቆመች ፈገግ አለች ። ቀጥ ሳም፥—

« ቀዩን ውብ ልብስ እንትወውና እስኪ አዲሱን ፊትሽን አሳይኝ » አለች ።

ይህን ብላ ናንሲ ወዳለችበት ቀስ እያለች ተጠጋች ። ከፋሻ የተገለጠውን ፥ ከፊት አጥንቷ በታች የሚገኘውን ጉንጯን ካየች በኋላ እንኳን ደስ አለን የሚል ፈገግታ እፊቷ ላይ ነጋ ። አይኖቻቸው ግጥምጥም አሉ ።

« እንዴት ነው ? ጥሩ ነው ? » አለች ናንሲ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

«ናንሲ ፣ በጣም ቆንጆዬ ልጅ ሆንሽኮ ። ቆንጆዬ—ቢቃ!»
አለች ፌ ። ናንሲ አመነቻት ። ምክንያቱም የፌ ፊት በናንሲ
መዳን ደስ መሰኘቷን ፣ በፒተር ስራ መደነቋን ቁልጭ አድርጉ
ይናገር ነበር ።

ፌ ደግሞ እንዲያ ስትል ከልቧ ነበር ። ለግላጋ አንገቷ ከተ
ርጸ መልካም ትከሻዋ ላይ እንደ ባህር ሽንበቆ ተመዞ ፣ ልስልስ
ጉንጯ ፣ ገርና ሳሙኝ የሚል አፏ ተገልጦ ያየ ሰው ቢደነቅ የማ
ያስገርም ነገር ሊሆን አይችልም ። ሁሉም ከናንሲ የተፈጥሮ ጠባይ
ጋር የሰመረ አካል ሆኖ ታያት ፣ ለፌ ።

የፒተር ሁልቆ መስፈርት የሌለው የንድፍና የጥገና ፣ የሞ
ዴል መቅረፅ ሥራ ፣ በከንቱ እንዳልነበረ ግልፅ ሆኖ የታያት ፌ፣

«አስቀናሽን ! ዕውነት ቀናሁ ። እኔም እንዳንቺ ብሆን እን
ዴት ደስ ይለኝ ነበር መሰለሽ ! » አለች ።

ይህን የሰማችው ናንሲ በሳቅ እየተፍለቀለቀች ወደ ኋላዋ
ተለጠጠች ። ከጉንጯ በላይ ያለው ፊቷ ገና በፋሻ እንደታሰረ
ሲሆን ፣ ባደረገችው ጥቁር ቡናማ ዘናጭ ባርኔጣ ጥላ ደብዘዝ
ብሏል ። ይህን ባርኔጣ የገዛችው ከአሥራ አምስት ቀን በፊት
ሲሆን በቀይ ቀሚስ ላይ ከለበሰችው ቡና ዓይነት ሱፍ ኮትና
ካደረገችው ቡናማ ቡት ጫማ ጋር ይሄዳል ። ናንሲ ዱሮም
ትርጸ መልካም ልጅ ነች ። አዲሱ ፊቷ ሲጨመር ወንድን ሁሉ
በያለበት የምትጥል ሴት ትሆናለች ስትል አሰበች ፣ ፌ ።

ናንሲም ቢሆን ይህ ሊሰማት ጀምሯል ። ፒተር ቃሉን ለመ
ጠበቅ የሚችል ሰው እንደሆነ አምናለችና ።

« ፌ በጣም ደስ ይለኛል ። አንዳንድ ጊዜማ ደስታ የሰራ
አካላቴን ውጥር አስኪል ስለሚሞላው ጩሂ ! ጩሂና አሮይ
ባይ ይለኛል » አለች ናንሲ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

«እንደሱ ዓይነት ስሜት ይሰማኛል ስላልሺኝ ደስ አለኝ ናንሲ ። ግን ይኸ ሌላ መሆኑስ ? ያልለመድሽው ገፅታ መሆኑስ ?—ትንገሽ አያስጨንቅሽም ?»

«የለም የፈራሁትን ያህል አይደለም ። ግን ሙሉ ፊቴን በላላየሁት ሙሉውን ሳይ ምን እንደሚሰማኝ እንጃ— ብቻ አየሽ ዱሮውንም ያን የአፊን ቅርፅ አልወደውም ነበር — ብቻ ሲሆን ይታያል »

«ናንሲ—አንድ ነገር አለ »

« ምን ? ምን ነገር ? »

« አየሽ ፣ ናንሲነትሽን ቀስ በቀስ እንድትረሺ ያስፈልጋል ። ግድ የለበትም ። አንቺ እንደትቻለሽ ። ስለዚህ ናንሲን ለመር ሳት ናንሲን በደንብ ማስታወስ ያሻ ይሆናል ። ለምሳሌ እንበል የዱሮ አካሄድሽን ትወጂው ነበር ? »

ይህ ነገር ለናንሲ ፈፅሞ አዲስ ነበር ፣ ተነስቶ ተወስቶ የማያውቅ ።

« እኔ እንጃ ፣ በሳረግመዱ አስቤ እማውቅ አይመስለኝም » አለች ።

« ለወያፊቱ በደንብ ታስቢበታለሽ ። ድምፅሽን መስማት ትወጂ ነበር ? ለምሳሌ ድምፅሽን ለመገራት የዜማ አለማማጅ ቢቀጠርልሽ ምን ትያለሽ ? አየሽ በጣም ቀንጆ ድምፅ አለሽኮ ። ለምን መሰለሽ እንዲህ እምልሽ ? ከዚህ በፊት ያልሆንሽው ግን ልትሆኚው የምትችይውን ነገር እንድትለማመጅ ብናደርግስ ለማለት ነው ። ያን ስትሆኚ ያው አዲስ ሰው ሆንሽ ማለት ነው’ኮ ። ፒተር የተቻለውን እያደረገ ነው ። እኛስ ለምን አን ሞከርም ? »

ሃሳቡ በግ ብሎ የታያትን ያህል በደስታ ብፊቻ ፣ ናንሲ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

«ማለት ፒያኖ ብለማመድ ፣ አካሄዴን ብቀይር ፣ አዲስ ሰው ፣ ሌላ ሰው ሆንኩ ማለት ነው ፤ አደል ? ከዚያ በኋላ እኮ ብፈልግ ስሜንም መቀየር እችላለሁ ! » አለች ናንሲ ።

« ያን ያህልም መቻኮል የለብንም ፣ ስም እስከመለወጥ ማለቱ ነው ። እንደኛሽን ራስሽን ያጣሽ መስሎ እንዲሰማሽ አያስፈልግም ።

ራስሽን ማጣትሽ ሳይሆን መጨመርሽ ፣ ማደግሽ መሆኑን ማወቅ አለብሽ ። እስኪ እናስብበትና እንሞክረው ። ድንቅ ነገር ሳይገጥመን አይቀርም » አለች የአዕምሮ ሀኪምና ሊቋ ፌ ።

« በመጀመሪያ ድምፄን—ሌላ ድምፅ እፈልጋለሁ » አለች ናንሲ እየሳቀች ። « እንደዚህ ዓይነት ድምፅ » አለች ፣ ድምጿን ቀነስ ወፈር አድርጋ ።

ፌ ሳቀች ። እና ፦

« እሱን ድምፅ በደንብ ከተለማመድሽው ፒተር ሥራ ሊበዛበት ነው ማለት ነው » አለች ።

« እንዴት ? » አለች ናንሲ በዚያው ጉርነን ባለው ድምፅ ።

« ቧም መሥራት ግድ ይሆንበታላ ! »

« እንዲህ ነው ። እንኳን ነገርሺኝ ! »

ሁለቱም እንደ በሳቅ መንከትከት ጀመሩ ።

ተነስታ እንደትንሽ ልጅ መቅበጥበጥ ጀመረች ። ናንሲን እንዲያ ስትሆን ስታያት ፌ ሁልጊዜም ይገርማታል ። ሃያ ሶስት አመቷ ነው ። ናንሲ ግን ሃያ ሶስት ዘመን ቀርቶ ረጅም ዘመን የኖረም ሰው ቢሆን ያላየውን ብዙ ነገር አያየች ነው ፣ እየሆነች ነው ። ውስጧ ግን ትንሽ ልጅ ናት ። ይኸው ስትቀብጥ ፣ ስትቅበጠበጥ !

« ግን አንድ ነገር አለ ፣ ናንሲ »

« ምን ነገር ? »



t.me/OLDBOOKSPDF

« ለምን አዲስ አንችን መፍጠር እንዳለብን ማወቅ አለብሽ ። ምክንያቱን ካወቅሽው ፣ ችግሩን ከተረዳሽው ነገሩ ቀላል ይሆናል ። እናትና አባትሽን አታውቂያቸውም ፣ አይደለም ? ይኸ ደግሞ ምን እንደሚያስከትል ማወቅ አለብሽ ። እናትና አባት እኛ ራሳችንን ለመሆናችን ምስክር ናቸው ። ከየት መጣሁ ? እናትና አባቴ ወለዱኝ ። እውን ይሆናል ነገሩ ። ያ ጥያቄ ሳንች ክፍት ቦታ ቢጤ ነው ። እሱን የምትሸሺ መምሰል የለበትም ። ሌላ ሰው ልትሆኝ እንደምትፈልጊ መሆን ነው ያለበት ። ያኔ መንገዱ ቀላል ይሆናል » አለች ሬ ።

ናንሲ ምንም ምን ሳትል ጸጥ ብላ ተቀመጠች ። ይህን ያየ ችው ሬ በፍቅር ፈገግ ብላ ኢትመለከተቻት በኋላ ወደኋላዋ ተለጥጣ ትዝናንታ ተቀመጠች ። ክፍሉ ምቾት የሚሰጥና መከፋ ትን ባንድ ጊዜ ከአዕምሮ ውስጥ እንደሚደመስስ ሆኖ የተዘጋጀ ይመስላል ። የግድግዳው ቀለም ፣ የዕቃዎቹ ዓይነት ፣ የዕቃዎቹ አቀማመጥ ፣ ሁሉ ነገር የመንፈስ ሰላም የሚለግስ ነው ።

« እሺ እንግዲህ አሁን ያልኩሽን ቀስ እያልሽ አስቢበት ። ለጊዜው ሌላ ነገር አለ ፣ ልንነጋገርበት የሚገባ ። የእረፍት ጉዳይ፤ ያመትባል ጉዳይ »

« የመጪው አመትባል ምን እንዲሆን ? »

«ዘመን መለወጫ መምጣቱን ስታስቢ ምን ይሰማሻል ? ይጨንቅሻል ? ፍርሃት ፍርሃት ይልሻል ? »

«አይለኝም»

«ይከፋሻል ? »

«በፍጹም »

«ደግ ፣ ናንሲ ። እኔ ከምገምትና ብዙ ከምሳሳት የሚሰማ ሽን አንች ብትነግሪኝስ ? »

«ምን እንደሚሰማኝ ለማወቅ ነው እምትፈልጊው ?»አለች ናንሲ « በእርግጥ ማወቅ ትፈልጊያለሽ ? »



t.me/OLDBOOKSPDF

ከተቀመጠችበት ተነሥታ እንዴ በክፍሉ ውስጥ በፍጥነት ወዲያ ደርሳ ወዲህ ከተመለሰች በኋላ ፡—

«ምን እንደተሰማኝ ልንገርሽ ? » አለች «የተጣልኩ ፣ እንደሽንት ተከፍዬ የተደፋሁ ይመስለኛል ፤ ስለዚህ ብሽቅ እላለሁ »

«እንደሽንት ? »

«አዎ ! ሽንቴ የደፋኝ መስሎ ይሰማኛል ፤ አናዶኛል ፣ አበሳጭቶኛል ፡ አብግኖኛል »

« ማ ? »

«ማይክል ። አየሽ እስካሁን—ቢፈልግ እስካሁን ድረስ የት እንዳለሁ ማወቅ የሚቸግር አይመስለኝም ። ግን አልፈለገኝም። ወርውሮ ጥሎኛል »

«ሌላስ—ሌላስ ያናደደሽ ሰው አለ ? የበሸቅሽበት ? »

« አዎ »

« ማ »

« እኔ ራሴ »

« ለምንድነው በራስሽ የበሸቅሽው ? »

« ከማሪዮን ሂልያርድ ጋር ያደረግሁት ውል ልክ አልነበረም ። እሷ መቼም ደፋር ናት ። ድፍረቷ ይዘገንነኛል ። ከሷ ደግሞ የኔ ይብሳል ። ሸጥኩት አየሽ ?—ፍቅሬን ለሥጋዩ ሸጥኩት »

«በእውነት ፍቅሬን ሸጥኩት ብለሽ ታስቢያለሽ ? »

«ይመስለኛል ። ያውም በአዲስ ጉንጭ ! ፍቅርን ያህል ነገር በጉንጭ ! በመልክ »

«አይመስለኝም ፣ ናንሲ ። እኔ እንደምትይው አይመስለኝም ። ለመልክ ሳይሆን ለመኖር ነው ። ነፍስሽን ለማቆየት ፣



t.me/OLDBOOKSPDF

ባንቺ ዕድሜ ምን አማራጭ አለሽ ? ሌላ ሴት ልጅ ባንቺ ዕድሜ ያለች ይህን አንቺ ያደረግሽውን ብታደርግ ምን ትያት ነበር ? »

«እንጃ ! አላውቅም ። ምናልባት ችግሯን እረዳላት ይሆናል ። ወይም ንቄ እፈርድባት ይሆናል »

«ናንሲ—ከጥቂት ደቂቃ በፊት አዲስ ሕይወት መጀመር እንዳለብሽ ስንነጋገር ነበር ። አዲስ ድምጽ ፣ አዲስ አረማመድ፣ አዲስ ገጽታ—አዲስ ሁሉ ነገር ። ነገር ግን . . . ካንድ ነገር በስተቀር » አለች ፊ—እና ዝም አለች ።

ናንሲ ጠበቀቻት ።

«ሁሉን ነገር እንድትቀይሪ ፣ የቀድሞውን እንድትረሺ ተነጋግረናል ። አንድ ነገር አላነሳንም »

ዝም አሉ ሁለቱም ።

«ማይክል—ስለማይክል አላነሳንም ። ናንሲ ፣ ማይክልን ከሆድሽ አውጥተሽ ጥለሽ ፣ ማይክል የለም ብለሽ አዲስ ሕይወት መመሥረት የምትችይ ይመስልሻል ? »

«አልችልም — አልችልም »

እንባዋ ቅርዝዝ አለ ። ሆኖም ሁለቱም ይህ አባባል ውሸትም እንዳለበት ገብቷቸዋል ።

«በፍጹም አትችይም ? »

«ፊ ፣ ሌላ ወንድ አስቤ አላውቅም ፣ ከማይክል ሌላ ። ግን ደግሞ አንዳንዴ ያለ ማይክል መኖር ይቻል ይሆንን እብሰ ለስላለሁ »

«እንዲያ ብለሽ ስታስቢ ምን ዓይነት ስሜት ይሰማሻል ?»

«ሞቴን እመኛለሁ »

«ለምን ናንሲ ? — ለምሳሌ አሁን ከማይክል ጋር እየደለም እምትኖሪው ። ግን መከፋት የለብሽም ይመስለኛል ፣ እይደለም ንዴ ! »



t.me/OLDBOOKSPDF

ናንሲ እዎንታዋን በአካል እንቅስቃሴ ገለጸች ።

«ናንሲ» አለች ፊ « ምናልባትም መድኃኒቱ የሚሠራው ይህንንም በደንብ ብታስቢበት ይመስለኛል »

«በቃ ! ማይክል ከአሁን በኋላ መምጣት አይፈልጋትም ፤ ብለሽ አስበሻል ማለት ነው ?»

«ስለሱ ምንም እማውቀው ነገር የለም ፣ ናንሲ ። ይምጣ ይቅርን ማንም ሊያውቀው አይችልም—ከማይክል በስተቀር ማለቴ ነው »

«ልክ ነሽ ፡ ያ የውሻ ልጅ መልሱን እሱ ብቻ ነው እሚያውቀው ! »

ናንሲ ይህን እያለች ከተቀመጠችበት ፊንጠር ብላ ተነሳች። አንዴ ካንዱ ዳር እስከ አንዱ ዳር ቤቱን በፍጥነት አካሔደ አዳረሰችው ። ከዚያም አካሔዱዋ ድንገት ቀነሰ ፣ ፍጥነቷ ኃይሏን የጨረሰው ይመስል ። ቆመች ። ባለችበት ላይ ። ስትቆመጥ ዕንባዋ በጉንጩዋ ላይ ፈስሶ ነበር ።

«ፊ ! በጣም ፈራሁ ። በጣም በጣም ፈራሁ » አለች።

«ምኑን ነው የፈራሽው ፣ ናንሲ ? » ስትል ጠየቀች ፊ ።

«ሁሉን ነገር» አለች ናንሲ «ሁሉን ነገር ። ብቸኛ መሆኔን ፣ ብቻዬን መሆኔን ፣ እራሴን ማጣቴን ፣ እኔን አለመሆኔን ። እኔንጃ — ምናልባት ያጠፋሁት ጥፋት ትልቅ በመሆኑ ቅጣቴ ሳይከብድ አይቀርም ይሆናል ። ፍቅርን ያህል ክቡር ነገር ለመልከ መለወጥ ! »

«ግን ' ኮ ናንሲ ምርጫሽ ልክ ይመስለኛል ። ሙሉ አካል ከሌለ ፍቅርም እንደሌለ ተረዳሽ ። ቢያንስ የገጽታሽ መስተካከል የሚቻል ነው አሉሽ ። ተስማማሽ ። የለም ናንሲ ፣ ወይፈትም ቢሆን በምርጫሽ የምትፀፀችበት ምክንያት ያለ አይመስለኝም »

«ምናልባት ... ምናልባት »

ናንሲን የለቅሶ ሳግ ይነትጋት ጀመር ።



t.me/OLDBOOKSPDF

«ገና ፣ ዘመን መለወጫ ፣ አመትባል ። አመትባሉንም እንዴት እንደማሳልፈው ጨንቆኛል ። የዘንድሮውን አመትባል ላስበው እጓለ ማውታን ማሳደጊያው ውስጥ ከነበረው ይበልጥ ጭንቅ ጭንቅ ይለኛል ። ያኔ አየሽ ቢያንስ ሰው ነበረ ። ዘን ድሮ ግን ብቻዬን ! አስቢው ‘ስኪ ። ሊሊና ግሬቸን ካለፈው ወር ጀምሮ መሰናበታቸውን ታስታውሻለሽ ። እንች በበረዶ ሸርተቴ ለመዝናናት መሔድሽ ነው ። ፒተር ለሳምንት ያህልም ቢሆን ወደ አውሮፓ ይሔዳል ። እና . . . .» ይህንን ሁሉ በእ ንባና በሳግ መካከል ነበር የተናገረችው ። ድንገት ንግግሯን አቋ ረጠች ። ምክንያቱም ፌንና ፒተርን አትሂዱ እንደማለት መሰ ላት ።

«ምናልባት ከሌሎች ሰዎች ጋር መተዋወቅ ያስፈልግሽ ይሆን ? ቢያንስ ለእንደዚህ ዓይነቱ ጊዜ» አለች ፌ ።

«እስኪ እይኝ ፣ ፌ » አለች ናንሲ ባርኔጣውን ከፍ እያደ ረገች ፊቷ በሙሉ እንዲታይ ፤ «እንዲህ ሆኜ ከማን ጋር ልተዋ ወቅ ፣ ፌ ?»

«እንደሱ ብትሆኚ ምንድነው ። ባርኔጣውን ሳታነሽው የሚ ታየው ፋሻ ነው ። ፋሻ የአንድ ሰው ቆዳ እንዳልሆነ ፣ አደጋ ደርሶብሽ እንደነበረ ማንም ሰው ይገባዋል »

«ምናልባት . . . ምናልባትም ይሆናል » አለች ።

ሁለቱም ዝም አሉ ። ናንሲ በነገሩ ሙሉ በሙሉ እንዳላ መነችበት ፌ ገብቷታል ። ያ ዓይነት ሐሳብ መኖሩን እንድታ ውቅ እንጂ ወዲያውኑ ልትቀበላት እንደማትችል ዱሮውንም ታውቃለች ።

«ተቀበሉኝም ሸሹኝ ፣ አሁን እኔ ሰዎችን መተዋወቅ አል ፈልግም ። እግዜር ይስጠው ፣ ፒተር የገዛልኝ ጓደኛ አለኝ ። ካሜራዬ ። ከሱ ጋር እጫወታለሁ ። በሱ ጊዜዬን አሳልፋለሁ» አለች ።



t.me/OLDBOOKSPDF

በጣም ለየት ይላል ። በዚህ ሁሉ መከራዋ ላይ አመትባሉን ያላ ንድ ሰው ብቻዋን ስትውል ናንሲ በጣም እንደምትደበር የተረ ጋገጠ ነው ። ዓመትባል ሲባል ደግሞ እንደለመዱት ካልዋሉት መከፋትን በልብ ውስጥ አጉልቶ የማስረጽ ባሕሪ አለው ፣ሆኖ ም ይህን ለናንሲ መንገር አያስፈልግም ። እንደተሰማትም ማሳ ፋት የለባትም ። ስለዚህ ነገሩን ቀላል አድርጋ ፦

«ለምን የዛሬ ሁለት ሳምንት ልንገናኝ አንቃጠርም ? እኔ ም ስለጉዞዬ ልንግርሽ ፣ አንችም ያነሳሻቸውን ፎቶግራፎች አትመሽ እንድትጠብቂኝ» አለች ።

«ያ ! የረሳሁትን ነገር አስታውስሽኝ » አለችና ናንሲ ከመቀመጫዋ ላይ እመር ብላ ተነሣች ። እና ከነበሩበት ክፍል ወጣች ። እንደተመለሰች በስጦታ መጠቅለያ ወረቀት የታሸገ ነገር እየሰጠቻት ፦

«መልካም የገና በዓል ይሁንልሽ ! » አለች ።

ፊ ከልብ በመነጨ ደስታ ፊቷ ፈገግ አለ ። እሽጉን ስት ፈታውና ከውስጡ የወጣውን ነገር ስታይ ዓይኗን ማመን አቃ ታት ። የራሷ የፊ ፎቶግራፍ ነበር ። ናንሲ ያን ፎቶ መቼ እንዳነሣቻት ትዝ ባይላትም ፎቶውን ያዩ ማንም ሰው ግን «ፈገግ በይ ፣ እንደዚህ ሁኚ» እያለች ያነሣቻት ይመስለዋል፣ በዝግጅት ። በፎቶው ላይ የምትታየዋ ፊ እናንሲ መኖሪያ ቤት ስገንት ላይ ቆማለች ። ንፋሱ ፀጉሯን ያውለበልበዋል ። የለበሰ ችው ሐምራዊ ቀለም ሽሚዝ ከምትጠልቀዋ ፀሐይ ቀለም ጋር ተቀላቅሎ ሕብር ፈጥሯል ።

«መቼ ነው ያነሣሽኝ ? » አለች ፊ፣ በአድናቆት እንደተሞ ላች ።

«ቀኑም ትዝ አይልሽ ?»

«ቀኑን አስታወስኩት — ግን — »

«ሳታይኝ ነው ያነሣሁሽ »



t.me/OLDBOOKSPDF

ሬ ያን ያህል ደስ ሲላት ስታይ ፣ ናንሲ በጣም ተደሰተች። ይህንኑ ነበር የፈለገችው ። ፎቶግራፉን ያጠቆረችውም ያተመችውም ራሷ ነበረች ። በጥንቃቄ ። ከዚያ ፍሬም አስገባችለት ። ሲያዩት የሥነጥበብ ሥራ መሆኑ ባያጠራጥርም ከፎቶ ይልቅ የእጅ ሥዕል ይመስል ነበር ። ወደዚያ የሚጠጋ ውበት ነበረው ።

«የማትታመኝ ጉድ ነሽ ' ኮ ናንሲ ። በጣም በጣም ውብ ነው ። በጣም ትልቅ ስጦታ ነው » አለች ሬ ።

«ውብ ነገርን ተመርኩዘው የሠሩት ሥራ ሁሉ ውብ ነው» አለች ናንሲ በደስታ እየተፍለቀለቀች ።

ሁለቱ ሴቶች ተቃቅፈው ተሳሳሙ ። የሬን መሔድ ፣ ለትንሽ ጊዜም ቢሆን ሊገናኙ እንደማይችሉ ስታስብ ናንሲ ኀዘን ተሰማት ።

«በይ እንግዲህ መልካም መዝናናት ይሁንልሽ» አለች ።

«በይ በደህና ቆይኝ ። ስመለስ ጥገር በረዶ ይዤልሽ እመጣለሁ » አለች ሬ ።

«አትጃጃይ ፣ እሺ ? ! » አለችና እንደገና እቅፍ አደረገቻት ናንሲ ።

ናንሲና ሬ ተሰነባብተው ፣ መልካም አዲስ ዓመት ፣ መልካም የገና በዓል ተባብለው ተለያዩ ።

ናንሲ ከሔደች በኋላ ሁሉ ሬ የምታስበው ስለናንሲ ነበር ። ናንሲ ጥሩ ልጅ ናት ። ባሕርይዋ ንጹሕ ነው ። ሰው የሚባለው ደግም ያ ነው ስትል አሰበች ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ አሥራ ሁለት

የውስጥ ስልክ ተደውሎ ጆርጅ ኮሉዌ የውጭ ስልክ እን ደሚፈልገው ነገረው ። የቴሌፎን ጭርርታ እስኪቀሰቅሰው ድረስ በስራው ላይ ስለተመሰጠ ምንም ነገር አይሰማውም ነበር ፣ ማይ ክል ሂልያርድ ። ለአምስት ወይም ለስድስት ሰዓት ያህል ያለማ ቋረጥ የወረደው በረዶ በቀለጠ በረዶ ድጥ የተጥለቀለቁትን መን ገዶች ይበልጥ እያጥለቀለቀ ሲወርድ እንኳ ማይክል ሂልያርድ ወላ ሀንቲ ነገር አልሰማም ። ስራ የገባው ከንጋቱ አስራ ሁለት ሰዓት ላይ ቢሆንም ፣ ስልኩ የተደወለለት ከሰዓት በኋላ አስራ አንድ ሰዓት ላይ ቢሆንም ፣ ማይክል ግን ከቢሮውም አልወጣ ፤ ከስራውም ላይ ንቅንቅ አላለም ነበር ። የውጭ ጥሪ መቀበያውን ስልክ በግራ እጁ ሲያነሳ እንኳ ቀኝ እጁ ስራ አልፈታም ። በፖስታ የሚ ላኩ ደብዳቤዎች ተቆልለው ነበረና እየፈረመ ነበር ስልኩን ያነ ሳው። የስራ ብዛት። የስራ ብዛት ። የስራ ብዛት— ማይክል ሂልያ ርድ ትንፋሹን አስተካክሎ የሚተነፍስበት ጊዜ አልነበረውም። ያ አንድ ሰሞን ቁም ስቅሉን አሳጥቶት የነበረው የካንባስ ሲቲ ፕሮ ጀክት አሁን እያስቸገረውም ። ከሱ ትከሻ ላይ ወርዷል ። አሁን ደግሞ የሀውስተኑ ፕሮጀክት ነው የሚያባዝነው ። ይኸ ሲያልቅ ደግሞ ያ የሳንፍራንሲስኮ የሕክምና ማእከል ይተካና ራስ ምታት ይሆንበታል ። ግን ስራ ጥሩ ነው። አለመቦዘኑ ነው እስከ ዛሬ ቆሞ እንዲሄድ የረዳው ። እምላክ ምስጋና ይግባው ።

«ጆርጅ ነህ ? ማይክል ነኝ ። ምን ነገር ተፈጠረ ? »

« እናትህ ይደውልልኝ ስላለችኝ ነው » አለ የጆርጅ ኮሉዌ ድምፅ ከወዲያ ።

«ስብሰባው ተፈፀመ ? »



t.me/OLDBOOKSPDF

«ኢላለቀም። እቷ አሁንም እስብሰባው ላይ ነች »

« እሺ »

«በረዶው ጋብ ካለ ዛሬውኑ ከቦስተን እንመለሳለን፤ ጋብ ካላለ ግን ነገ እንመጣለን ብለህ ንገረው ስላለችኝ ነው የደወልኩልህ»

«በረዶ እየጣለ ነው’ ንዴ ቦስተን?»

«ቦስተን ምንም በረዶ የለም። ግን ኒውዮርክ ዶፉን እያወረደው ነው ብለው ነገሩን— ውሸት ነው’ ንዴ?»

ማይክል ገርገብ ብሎ ወደውጭ ተመለከተ፤ በመስኮት በኩል። ያወርደዋል ፤ ዶፉን ፡ የመገረም ፈገግታ ለመናገሪያው እያሳዩ—

«እውነትም ዶፉን እያወረደው ነው። አልተሰማኝም ነበር። ቀና አላልኩም— ይቅርታ»»

ጆርጅ ኮሎኔ ይህን ሲሰማ ይህ ልጅ በዚህ ሁኔታ እየሰራ ምትን ሰው ሆነው፤ ያው እንደ እናቱ በስራ ብዛት ስውነቷንም ጤናውንም ሊጨርስ ነው’ ንጂ ፣ ሲል አሰበ ። ከዚያም በመገረም ባጭሩ ስቆ ፡—

«እንግዲህ እንዲያ ከሆነ ፣ ነገ ያው ገና አይደለም ? ራት አብ ረን ስለምንበላ እንድትገኝ ብላሃለች ። ሌሎች እንግዶችም እን ዳሉ ነግሬኛለች። እንዳትቀር አደራ በለው ብላ አጥብቃ ነው የነ ገረችኝ» ። ሌሎች ጥቂት ሰዎች አለ ማይክል ትንፋሹን ውጦ በረ ጅሙ እያስመጣ ፣ ይኸኔ ሰላሳ ወይም አርባ ሰዎች ይሆናሉ ።

«ጆርጅ ይቅርታ ትጠይቅልኛለህ።ቀደም ያለ ቀጠሮ አለኝ» አለ ማይክል፤ ለስልኩ መናገሪያ ።

«አለህ?» አለ ጆርጅ በአድናቆት በተሞጠ ድምፅ።

«ይገርምሀል ከጣምንት በፊት የተያዘ ቀጠሮ ነው ። ባለፈው ሳምንት ልነግራት አስቤ ረሳሁት ። ይኼ የሆውስተን ማዕከል ጉዳይ እያፈናፍነንም [እንደምታየው ። አሁንም ግዴለም አንተ ንገራት— ይገባታል»።



t.me/OLDBOOKSPDF

የሀውስተንን ማዕከል ጉዳይ እንዴት ቀጥ አድርጎ እንደያዘ ላት ታውቃለች ። ቢያንስ በስራው ላይ ከነመቶችው በላይ የሆኑ ነገሮችን በመፈፀምና በማድረግ ደስ እንዳሰኛት ርግጠኛ ነው ። ሌላው እንግዲህ ሌላ ነው።ሌላውም ሊገባት ይገባል፡ አለ በሀሳቡ።

«መቼም ቅር እንደሚላት የታወቀ ነው» አለ ጆርጅ «ሆኖም ቀጠሮ እንዳለህ ማወቁ ራሱ የሚያስደስታትም ይመስለኛል ። ቀጠሮውስ እንዴት ነው? መቼም ደስ የሚል መሆን አለበት— ይመስለኛል»

«በጣም በጣም ሀሪፍ ነው»

«እንዴት ነው—ከልብ የሆነ ነገር ነው?»

በጆርጅ ድምፅ ውስጥ መጨነቁን ሰማበት ። በቃ እኮ ምንም ነገር ቢመጣ ማፍተልተላቸው አይቀርም አለ በሀሳቡ ።

«አይ! አይ! ይህን ያህል የሚያሳስበን ነገር አይደለም ። አለ አይደል ጊዜያዊ ሆይ ሆይ— የዚያ አይነት ነገር ነው» አለ ማይክል ።

«እንዲያ ከሆነ ማለፊያ—በል እንግዲህ በእሉን የደስታና የፈንጠዝያ ያድርግልህ ማይክ»

« ላንተም እንደዚያው ። እማዬን ሳምልኝ ። ነገ እደውልል ሻለሁ በላት »

« ይሁን ። እንግራታለሁ »

ስልኩን እንደዘጋ የጆርጅ ኮልዌ ገፅታ በፈገግታ እበባ አጊጠ።በቃ አሁን ሊመለስ ነው ማለት ነው፣የሚል ሀሳብ መጣበት ። ከናንሲ ጋር ባለፈው የመፀው ወራት የደረሰበት አደጋ፣ የሚወዳ ትን ልጅ ማጣቱን ሲሰማ ያደረበት የመንፈስ መናወዕና መዳከም፣ እንዲህ በቀላሉ የሚሽር አይመስልም ነበረና ሁኔታውን ባዩ ቁጥር ጆርጅ ይከፋውነበር። እንዲህ ወጣ ወጣ ካለ የመንፈስ ስብራቱ ቀስ በቀስ ሊሽርለት ይችላል ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ምንድነው እምትፈልገው? ይህን ያህል እውቂያ የላቸውም ። በስራም ቢሆን በቀጥታ እሚያገናኛቸው ነገር የለም ።

«ምን ልታዘዝ ሚስ» አለና አቋረጠ ።

ይኸ የተረገመ አንጎል እሚሉት ነገር ! ስሟ ጠፋበት ። ይህ የገባት ቆንጆ ፣

«ዌንዲ— ዌንዲ ታውንሴንድ» ብላ ስሟን ነገረችው ። «ለማ ዘዝ መታዘዝ ሳይሆን ፤ ለብርሃኑ ልደቱ እንኳን አደረሰህ ልልህ ነው የመጣሁት »

« ነው ? እሃ ተጠምቆ እማይነጻ የተዋጣለት ገብጋባ ነው አላሉሽም? ደቡር ነው ብለው አልነገሩሽም ? »

«ባይነግሩኝም ሳይገባኝ አልቀረም ። ለምሳሌ ባለፈው ጊዜ ሠራተኞች ባዘጋጁት ፓርቲ ላይ አልተገኘህም። የገናን በአል ምክ ንያት በማድረግ በተዘጋጀው የራት ምሽት ላይም አልነበርክም ። ከሰው የምስማው ሌላ ነው ፤ ይሰራል፣ ይሰራል፣ ይሰራል ነው »

«ሥራ ሁሉንም ነገር ያስተካክላል ቢሉኝ ነዋ»

«ይሆናል ፣ ግን ሌሎች ነገሮችም ያው ናቸው »

በዚህ ጊዜ እቢሮው ገብታ እፊት ለፊቱ ባለው ወንበር ላይ ተቀምጣ ነበር ። ቀና ሲል አንደኛውን እግሯን እንስታ እሌላኛው ላይ አነባበረችው ። እግሮቿ በጣም ያምራሉ ። ማይክል ሂልያርድ ግን ይህን አላጤነም ።

«በዚያም ላይ» አለች ። «ባለፈው ጊዜ ለተደረገልኝ እድገት ምስጋናዬን ለማቅረብም ነው »

« በእሱ እንኳ እኔ አልመሰገንም ። እድገቱን እንድታገኚ ያደ ረገው ቤን አቨሪ ነው ። እሱኑ ነው ማመስገን ያለብሽ»

« ገባኝ »

በደንብ ነበር የገባት ። የትም እማያደርስ ወሬ ነበር የጀመ ሩት ። ባደረገችው ነገር እየተፀፀተች ከመቀመጫዋ ተነሳችና በመ ስኮት ወደ ውጭ እያዬች—



t.me/OLDBOOKSPDF

መለከት ነገሩ ሁሉ የገና በአል አልመሰልሽ አላት ። ምንም እንኳ የገና ዛፉ ፣ ተርኪናውና ሌላው ሌላው ሁሉ ሲሸጥ ፡ ሲጓጓዝ ያየች ቢሆንም ምስራቅ ዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ስትኖር የምታከብ ረውን አይነት ገና አልመስል አላት ። የሳንፍራንሲስኮ የአየር ጠባይ ካደገችበት ምስራቃዊ ግዛት የተለየ ነው ። የገናን በአል ያለ በረዶ ፤ ይህን በአል ያለዚያ አየር ጠባይ ላስብህ ብትለው የማይሆን ሆነ ። በዚያ አካባቢ ያሉ ሰዎች ገናን አከበርን ለማለት የሚሞክሩ ፤ የሚያስመስሉ መሰላት እንጂ ገናን እያከበሩ መሆኑ ከቶም እውን ሊሆንላት አልቻለም ። ይህ ግን ሀዘኗንና ጭንቀቷን ቀላል አደረገላት ።

የሰራችውን ዶሮና ሌላም ሌላም ነገር ቀማምሳ ስታበቃ ፊ ለገና በአል የሰጠቻትን የቀልዶች መጽሐፍ ማንበብ ጀመረች ። በዘንድሮው በአል ያገኘችው ሁለት ስጦታ ብቻ ነበረ ። አንደ ኛው ፒተር ግሬግሰን (የቀዶ ሕክምና ሊቁ እና ሀኪሟ) የሰጣት ውድም ውብም የሆነ የእጅ ቦርሳና ይህ ከላይ የተባለው ፊ የሰጠ ቻት የቀልዶች መጽሐፍ ።

እስከ አስራ ሁለት ሰዓት ድረስ ስታነብ ዋለች ። ከዚያ በኋላ ተነስታ ካሜራዋን አዘጋጀች ። ጉምም ሆነ ጭጋግ የማይታይበት ብሩህ ምሽት ፎቶግራፎች ለማንሳት አመቺ ነው ።

ከቤቷ ስትወጣ መንገዱን ሁሉ ጭር ብሉ አገኘችው ። ሰዉ ለአመት ባሉ የበላው ምግብ ከብዶት በየቤቱና በየጓሮው ያና ውዛል ማለት ነው ። አንዳንዱ ይኸኔ ቲቪ ከፍቶ ደፋ ቀና እያለ ይመለከት ይሆናል ። ይህን ስታስብ የራሷ አስተሳሰብ ገረማትና ለብቻዋም ቢሆን ፈገግ አለች ። በዚህ ጊዜ አንድ ነገር አደናቀ ፋት ። ልትወድቅ ስትንደረደር ፒተር ያስጠነቀቃት ትዝ አላት። መውደቅ የለባትም ። በዚህ የሕክምና ወቅት ውስጥ ። በዚህም የተነሳ ነው ከፊ ጋር ወደ በረዶ ሸርተቴ መጫወቻ ቀበሌዎች እንዳትሄድ የተከለከለችው ። እጇዋ ቀድሞ መሬት ይዞ ባይደግፋት አወዳደቋ አደገኛና አስቃቂ ይሆን ነበር ። ያ ነገር ሲያደናቅፋት



t.me/OLDBOOKSPDF

ገልፅ ዘለበት እንገቱ ላይ ፈለገች ። ግን አልነበረውም ። ምንም ምን የሌለው ውሻ ስትል አሰበች ። ምን ይሻላል ? ካሜራዋን አስ ታወሰች ። ፎቶግራፍ ልታነሳው አሰበች ። ገና እንዴ እንዳነሳ ችው ፎቶ መነሳቱን ያወቀ ይመስል በተለያየ ሁኔታ ይስተካከል ላት ጀመር ። መቼም በሷ አስተያየት እነዚያን ሁኔታዎች ስለወ ደደቻቸው ሊሆን ይችላል እንጂ ውሻው ይህን አውቆ አደረገው ለማለት ያስቸግር ይሆናል ። ለሷ ግን የሚገርም አጋጣሚ ሆና ታያት ።

በመጀመሪያ ሲሄዱ ሲቆሙ ፣ ቀጥሎ ፎቶ ስታነሳው ቁጢጥ ሲል ፣ ሲፈነጥዝ ፣ የቀልድ ሊናከስ ሲፈልግ ፣ ከዚያም ሄድ ስትል ከኋላዋ ቱስ ቱስ እያለ ሲከተላት— በዚህ ሁኔታ ግማሽ ሰዓት አለፈ ። በዚህ ጊዜ ፦—

«እሺ እንግዲህ አብረን እንሂድ» አለች ።

አብረው ሄዱ ። መርከቦች እቃ ወደሚጭኑበትና እሚያራግፉ በት ወደብ ። እዚያም የትያትር መድረክ በመሰለው ዋቅራ ላይ ወጥታ የተለያዩ ፎቶግራፎችን አነሳች ። የጉርምጥ ማጠራቀሚ ያዎችን ፣ የሸርጣን ማጥመጃዎችን ፣ ቱሪስቶችን ፣ የሰከሩ የገና አባቶችን ፣ ጀልባዎችን ፣ የባህር ላይ ወፎችን አነሳች ። በዚህ መሀ ል ውሻውንም እንስታው ነበር— ሳይበዛ ።

ያገለት ያሰበችውን ያፀል ፣ የፈራችውን ያህል የገናን በአል ሳይከፋት ዋለች ። በተለይ ከቤቷ ከወጣች በኋላ ሁሉም ነገር ደስ የሚል ነበር ። ውሻውም ይበልጥ እየለመዳት እየተጠጋት ሄደ እንጂ ከቶም ካጠገቧ አልተለያትም ።

ትንሽ እንደመድከም አላት ። በዚህ ጊዜም ካሜራዋን ወደ ማህደሩ መልሳ ቡና ለመጠጣት ወደ አንዲት ትንሽ ቁርስ ቤት ጎራ አለች ። ወደ ቡናቤትና ትናንሽ ቁርስ ቤቶች መግባት ቀደም ብላ የተለማመደችው ነገር ሆኗል ። ይህን ያህልም



t.me/OLDBOOKSPDF

ፊቷ አያሳፍራትም ። ማለትም ከባርኔጣዋ ተርፎ በዘለቀው ፀጉሯ ፊቷን ሸፈን ታደርግና የምትፈልገውን ነገር ታዛለች። ለምዳዋለች። ዛሬግ የታችኛው የፊቷ ክፍል ስለተገለጠ «አመሰግናለሁ»ብላ ፈገግ ማለትም ትችላለች ። ፊቷን በመስታወት ያየችው ትዝ አላት።

እዲሱን ፈገግታዋን ወዳዋለች ። ፒተር ሕክምናውን ሲጨርስ ምን ትመስል ይሆን? ሁኔታውን ስታየው የሚያልማትን ሴት ፊት ሊያለብሳት የሚፈልግ ይመስላል ። እንዲያውም እንዴ በሀሳቤ ውስጥ የማልማትን ሴት ልሰራ እፈልጋለሁ ብሏት እንደነበር ታስታውሳለች። ሰው የሰራው ፊት ለራስ ስሜት ይጎረብጣል ። ሆኖም ይህን ሰው የሰራውን ፈገግታዋን ወዳዋለች ።

ቡና አዘዘች ፣ ጥቁር ቡና ለራሷ ። ለውሻው ደግሞ የአሳማ ስጋ ሳንድዊች ። እመተላለፊያው ላይ በወረቀት ሳህኑ የመጣለትን ሳንዱች አስቀመጠችለት ። ያው በውሻ አበላል ፣ ያውም የራበው ውሻ !ስልጥቅ አደረገና ቀና ብሎ ያችን ገር «ዉዉ»ውን አሰማት።

«አመሰግናለሁ ማለት ብቻ ነው ወይስ ሌላ ተጨማሪ ነገር አለበት ?»ስትል ጠየቀችው ።

«ዉዉ ! » አላት ደግሞ ። ሳቀች ። አንድ ሰው መጣና ጎንበስ ብሎ ደባበሰበው ። እና—

«ማንነው ስሙ» ሲል ጠየቃት ።

«እኔ እንጃ ! በመንገድ ላይ ተገናኝተን እምታለሁ እንጃ ካንች አልለይም ብሎ ጥብቅአለብኝ» ስትል መለሰችለት ።

«ለፖሊስ ወይም በእንስሳት ላይ የሚደረገውን ጭካኔ ማስወገጃ ማኅበር ለሚባለው ብታስታውቂ አይከፋም» አለ ሰውየው ።



t.me/OLDBOOKSPDF

«ጥሩ ። እስካሁን ትዝ አላለኝም ነበር »

እቤቷ ከደረሰች በኋላ ለተባሉት ድርጅቶች አመለከተች ። ያን የመሰለ ውሻ ጠፋብኝ ብሎ ያመለከተ ሰው እንደሌለና ከፈለገች ውሻውን ማቆየት እንደምትችል፣ ካልፈለገች ደግሞ ባካባቢው ወደሚገኘው የጠፉ ውሾች መጠለያ እንድትወስደው ነገሯት ። መጠለያ የሚለውን ነገር ስትሰማ ተናደደች ። ትንሹን፣ ውድ ጓደኛዋን ወደ መጠለያ! -ሆሆይ!

«እውን ይህ ነገር ደግ ነው ?» አለች ።

«ዉዉ!» ሲል መለሰላት ።

ስቃ ታሻሻው ጀመር ። ብዙ ቀን ሲንከራተት እንደቆየና ታጥቦ እንደማያውቅ ሲገባት «ገላዎትን ቢታጠቡ ምን ይመስልዎታል?» ስትል በፌዝ መልክ ጠየቀችው ።

ምላሱንና ጭራውን ባንዴ እያወዛወዘ ተቅበጠበጠ ። አቅፋ ወደ መታጠቢያ ቤት ይዛው ሄደች ። አጠበችው ። በእውነቱ ይህን ማድረግ አልነበረባትም ። ምክንያቱም ውሻው ደርሶ ሰውነቱን ቢያራግፍ ወይም ቢዘል ውሀው ተሞቦራጭቆ ፊቷ ላይ ያለውን ፋሻ ቢያረጥበው የስንት ጊዜ ልፋት ብላሽ ሊሆን ይችል ነበር ። በእርግጥ ተጠንቅቃ ነበር ይህን ያደረገችው ። ግን . . . አጥባ በፎጣ አድርቃ ስትመለከተው ሌላ ውሻ ሆኖ ታያት ። አቁስጣ ሳይሆን ነጭና ቡናማ መልክ ያለው ዝንጉርጉር ሆኖ አገኘችው። ለድርጅቶቹ በትክክል እንዳላስታወቀች ቢገባትም ውሻዋን መስጠት አልፈለገችም ። ከልጅነቷ ጀምሮ ትመኝለች ። ውሻ የማግኘት እድል ግን አልነበራትም ።

«ዋናው ነገር አሁን ስም ነው ። ስምዎን ማን ብንል ይፈቅዳሉ?» ጭራውን እያወዛወዘ ተመለከታት ። አንድ ስም አስታ



t.me/OLDBOOKSPDF

ወሰች ። ያን ስም ማይክል ነበረ የነገራት ። አንዱ በጣም የሚወደው ውሻ እንደነበረው ሲያጫውታት ።

«ፍሬድ የሚለው ስም ይስማማዎታል ፣ ትንሹ ወዳጃችን ? » ስትል ጠየቀችው ውሻውን ። «ዉ.ዉ!- ዉ.ዉ! አለ ።

በጣም በጣም ! ማለቱ ነው ስትል ተረጎመችው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ አሥራ ሦስት

ናንሲ የተዘጋውን በር በቀስታ ከፍታ አንገቷን ብቻ ወደ ክፍሉ ውስጥ አሰግጋ ስትመለከት ፌ አሊሰን (የአእምሮ ሐኪም የሆነችው ጓደኛዋ) አሳቱ አጠገብ ተመቻችታ ተቀምጣ አየች ። ፌ ናንሲን ስታይ በደስታ ፈገግታ በራች ።

« ምነው ያጮልቃሉ ? ምን ያስቡት ተንኮል አለ ፣ እመቤቲቱ ? » አለች ፌ አሊሰን ፣ ፈገግ ብላ ። ፈገግ ያደረጋት የናንሲ አመጣጥ ብቻ ሳይሆን ናንሲ ብቻዋን ያሳለፈቻቸውን ሁለት ሳምንቶች ስታስብና ሁኔታውን ስትመለከት ብዙ ለውጥ እንዳላየች ስለገባት ነበር ።

« አንድ ጓደኛዬ አብሮኝ መጥቷል » አለች ናንሲ—

« አትይኝም ! በሁለት ሳምንት ውስጥ ከዳሽኝና ሌላ ጓደኛ አበጀሽ ? ምናለ ብትጠብቂኝ ? ለመሆኑ እንዴት ቀናሽ ፣ በይ ? »

ፌ አሊሰን ይህን ስትል ናንሲ በሩን ከፈት አደረገችው ። በዚህ ጊዜ ፍሬድ እየፈነጠዘ ወደ ክፍሉ ውስጥ ገባ ። ፍሬድ አንገቱ ላይ በተደረገለት አዲስ ቀይ ዘለበት ኩራት የተሰማው መሆኑ በግልፅ ይታወቅበታል ።

ናንሲ ፍሬድን ስታጥበው ሌላ መልክ እንዳመጣ ባለፈው ምዕራፍ ተናግረን ነበር ። ይህንን መልኩን ጠቅሳ ለሚመለከተው አስታወቀች — ቆይታ ። አሁንም የዚያ ዓይነት ውሻ ጠፋብኝ የሚል ብቅ ሳይል ቀረ ። ስለዚህም ፍሬድ የናንሲ ንብረት ሆኗል ። በሷ ስም ተመዝግቧል ። ጤንነቱ ተመርምሮ « ነፃ » የሚል ምስክር ወረቀት ተሰጥቶታል ። ዛሬ ፍሬድ የግሉ መኝታ ፣ የግሉ መመገቢያ ገንዳ ፣ በርከት ያሉ መጫወቻ አሻንጉሊቶች ያሉት የኩራ ውሻ ነው ። ናንሲ ደግሞ ትወደዋለች ።

t.me/OLDBOOKSPDF

« ፌ ፣ ከፍሬድ ጋር ተዋወቁ » አለች ናንሲ ውሻውን በፍቅር ዓይን እየተመለከተች ።

« ድንቅ ውሻ ነው ። የት አገኘሽው ልጄ ? »

« የገና ለት ማታ እመንገድ ላይ በድንገት ተገናኘን ። የጉዲፈቻ ልጅሽ ነኝ ብሎ ተጣበቀብኝ »

« እንቺም ተቀበልሽው ፣ አደል ? »

« ምንም ማድረግ አይቻልም ። ስሙን ኖየል (ልደቱ) ብለው ነበር ልክ እሚመጣው ። ሆኖም . . . ፍሬድን መረጥኩለት »

ለምን ፍሬድ አልሽው ብትለኝ — ማይክል ፍሬድ የሚባል ቡችላ ስለነበረው ብላት ፣ እያለች ስትጨነቅ — ፌ አሊሰን ግን ያን ጥያቄ ሳታነሳው ዘግዩት አለች ። ስለዚህም ናንሲ ፣

« ደሞ ይህ ምን ይመስልሻል ? ይህ የፎቶ ግራፎች ቅርቅብ ነው ። እንድትመለከቻቸው ነው ያመጣሁልሽ »

« ኧረ በስላሴ ። ንብ ሆነሽ ነው የከረምሽው ማለት ኮ ነው ፣ እንዲህ ከሆነ — አሁንም ወደ ሌላ ቦታ ዘወር ብልልሽ ሳይሻል አይቀርም »

« ፌ ፣ አንድ ነገር ልለምንሽ — የትም የት አትሒጂ ፣ አብረን እንድንሆን እፈልጋለሁ »

ናንሲ ይህን ስትል ፌ አሊሰን በመጠኑ ቢሰማትም ፣ ሁኔታዋን ላየው ግን ናንሲ ልትገልጸው የፈለገችውን ያህል ብቸኝነቱ እንዳልተሰማትም ግልፅ ሆኖ ገብቷታል ።

« ደሞ ሌላ ነገር — » አለች ናንሲ በኩራት ።

« ምን ? »

« ደሞ ሌላ ነገር የድምፅ አወጣጥ ልምምድ ለማድረግ ይህ ሙያ ካለው ሰው ጋር ተዋውቄ ጨርሻለሁ »

ፌ አሊሰን በአድናቆት ተመለከተቻት ።



t.me/OLDBOOKSPDF

« ለፒተር ነግሬዋለሁ ። የሙሉ አካል አንድ ብልት ነው የድምፅ ጉዳይ ብሎ አስፈላጊ መሆኑን ነገረኝ ። ነገ ዘጠኝ ሰዓት ላይ ልምምዱን እጀምራለሁ ። ዳንስ ግን ትንሽ አስቸጋሪ ነገር ሆኗል ። አፕራሲዮን ስላልጨረስኩ መቆየት ይኖርበታል ። በሚቀጥለው ዓመት በጋ ላይ የዳንስ ልምምዴን ልጀምር እንደምችል ፒተር ነግሮኛል »

« በጣም ሊኮራብሽ የሚገባ ጓደኛ ነሽ'ኮ ናንሲ ! » አለች ፌ

« እኔም'ንኳ በራሴ ኩራት ይሰማኛል »

ያን'ለት ፌ አሊሰንና ናንሲ ማክአሊስተር ብዙ ተነጋገሩ ። ዶክተር ፌ አሊሰን የናንሲን የመንፈስ ጥንካሬ ለመገንባት የተቻላትን ያህል ስታደርግ ፣ ዶክተር ፒተር ግሬግስን ደሞ የናንሲን ፊት ለመጠገን ብቻ ሳይሆን እንደ አዲስ ለመስራት ያለውን ዕውቀት ፣ የተሰጠውን ጥበብ ሁሉ በሥራ ላይ ለማዋል ቆርጦ ተነስቶ ነበር ።

ከላይ በተባለው ቀን የፌ አሊሰንና የናንሲ ውድይት የተቃና ነበር ። የሚገርመው ደግሞ በዕለቱ የማይክል ሂልያርድ ስም አልተነሳም ። ይገርማል የተባለውም ሁለቱ ሴቶች — ፌ እና ናንሲ - ስምንት ወራት ያህል ሲወያዩ የማይክል ስም ያልተነሳው በዚህ ቀን ብቻ ነበርና ነው ።

ከዚያ ቀን በኋላ ግን ሙሉ የዝናሙ ወቅት እስኪያልፍ ናንሲ ስለማይክል ፈፅሞ አላነሳችም ። የምታወራው ለወደፊት ስላቀደችው የዳንስ ትምህርት ፣ የድምፅ አወጣጥና የዘፈን አሰልጣኟ ስለሰጣት አስተያየት ፣ ስለመሳሰሉትና — በተለይም በፎቶግራፍ ማንሳት ጥበብ እየረቀቀች ስትሄድ ፣ ስለ « ፎቶግራፍ አነሳስና ስለኪነጥበብነቱ ፣ ለወደፊት ይህን ሙያ በምን ሁኔታ ልትሞክረው እንደምትሻ ብቻ ነበር ። ክረምቱ አልፎ የጸደይ ወራት ሲገባ ፣ ናንሲና ፍሬድ ወደ ተለያዩ መናፈሻዎች ፣ የአበባ ቦታዎችና መዝናኛዎች እየሄዱ ሽርሽር ያደርጉ ጀመር ። አንዳንድ ቀን ደግሞ ፒተር ግሬግስን (ሐኪሙ) ናንሲን ጭር



t.me/OLDBOOKSPDF

ወዳሉ የወደብ መናፈሻዎች ይወስዳታል ። ይህም ናንሲ ስለ ፊቷና ፋሻው ብዙ እንዳይሰማት ለማድረግ ነው ።

ጊዜ እየገፋ ሲሄድ የናንሲ ፊትም ብቅ እያለ ሄደ ። ከና ፍሯን ፣ አፍንጫዋን ፣ ጉንጯን በሕክምና ጥበብ አስተካክሎ ሲሠራ ፣ እነዚህ ነገሮች አዲስ ሆነው ብቅ ሲሉ ፣ ሰብአዊ ባህ ሪዋም ፣ ውስጣዊ ነፍሷም ብቅ ማለት ጀመረች ። ያች ባለፈው ዓመት ብዙ ችሎታዎችን የማታውቀው ናንሲ ፣ ያች ያላትን ብርቅ ድንቅ የሆነች ንጹህ ነፍስ ያልተገነዘበች ናንሲ — በመ ጪው ወር — ማለት አደጋው በደረሰ ባመቱ የበሰለች በጣም በርካታ ነገሮችን ተገንዝባ ፣ ራሷን ችላ — በርካታ ነገሮችን መፈጸም የምትችል አዲስ ሰው ሆና ብቅ ስትል እየቻት ፣ ፊ ልሊስን ። ፊ የጊዜውን መንገድ ስታስበው ደነቃት ።

« አንድ ዓመት ሆነ ማለት ነው ? » አለች ፊ ።

« አዎ ልክ አንድ ዓመት ። እምና በግንቦት ወር ላይ አይ ደለም አደጋው የደረሰው ? »

« ይገርማል ። ጊዜ ‘ኮ . . . »

« ፊ ፣ ካንቺ ጋር ከተገናኘን ደግሞ ልክ ስምንተኛ ወራ ችን ሞላ ። እንዴት ነው ፣ በዚህ ጊዜ ውስጥ ብዙ ያሻሻልኩት ነገር ያለ ይመስልሻል ? »

ናንሲ ይህን ስትል ትንሽ የመሰላቸትና ተስፋ የመቁረጥ ቃና በድምጿ ውስጥ ይሰማ ነበር ። ምንም አይደለም ። ያለፈው ቀን ኦፐራሲዮን ስላደከማት ነው ። ድካሙ ለቀቅ ቢያደርጋት መንፈሷም ይነቃል ስትል አሰበች ፊ ።

ፒተር በዚያ ሰሞን ዓይኗንና የዓይኗን አካባቢ በመጠገን ፣ በማስተካከል ላይ ነበር ። አፊቷ ላይ ያለው ፋሻ ተነስቶ ሰፊ ጥቁር መነፅር አድርጋለች ። ዓይኗን አጉንጭ እጥንቷ ድረስ ይሸ ፍናል ፣ መነፅሩ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

« ትጠራጠሪያለሽ ናንሲ ? » አለች ፌ ፡ ያሻሻልኩት ነገር ያለ ይመስልሻል ? ስትል ለጠየቀቻት ጥያቄ ስትመልስ ።

« አንዳንዴ እጠራጠራለሁ ። ምክንያቱም ደርሼ ስለማይ ከል አስባለሁ ፡ እየሽ ! የሚመጣ ፡ የማሪዮንንም ውል ገደል ይገባ ብሎ የሚመጣ ፡ አብረን የምንሆን ይመስለኛል»

ዝም አለች ፌ አሊሰን ።

« እየሽ» ቀጠለች ናንሲ ማክአሊስተር « ስለማይክል ማሰብ ምንም እንደማይጠቅመኝ ፡ እንዲያውም እንደሚጎዳኝ ይገባኛል ። ግን አልችልም ። እኔ'ንጃ ብቻ . . . »

ናንሲ ንግግሯን አቋርጣ ፌን ትመለከታት ጀመር ።

« አይዞሽ» አለች ፌ አሊሰን « ትንሽ ጊዜ ታገሽማ — እና ታያለሽ ። እሁን ሁሉ ነገር ሲነሳ ፡ ከሰው ጋር መዋል ስትጀ ምሪ ፡ አድርገሽው የማታውቂውን ነገር ስታደርጊ ፡ ሌላ ሰው ልዩ ሰው ስትሆኚ ትረሽዋለሽ ። ሀሳቡ ራሱ አሁን የሚመጣውን ያህል ያኔ ራሱ ይቀራል ። አትስጊ ። ትንሽ ታገሽ ግን »

« መታገስ ፡ መታገስ — አሁንስ እንደመታገስ የሰለቸኝ ነገር የለም ! » አለች ናንሲ ።

ፌ አሊሰን በጸጥታ ታዳምጣት ነበር ።

« ታውቂያለሽ» አለች ናንሲ « አንዳንዴ ይኸ ፋሻ መቼ ነው የሚነሳ ? እላለሁ ። ይነሳል ትንሽ ታገሽ ይለኛል ፒተር ። ይህን ሲለኝ ፡ ይህን ሲደጋግም መታገስ እስጠላኝ ፡ ሰለቸኝ ። አን ዳንዴ ፊቴን ሲያፈርስ ሲሠራ ፡ ሲለጥፍ ሲለስን ፡ ሲቆልል ሲያ ድቦለቡል — ዘላለም የሚኖር መስሎ ይሰማኛል ። ፒተርን ምርዝ አድርጊ እጠላለሁ ። ሞኝ አትሁኚ ። ፒተር እንዳልበዘን ፡ ወይም እንዳልሰገመ እውቃለሁ ። ግን ዝም ብዬ እለ እይደል እጠላ ዋለሁ »



t.me/OLDBOOKSPDF

« ግንኙ ብታስቢው የፈጀው ጊዜና ያስገኘው ፍሬ የትና የት ነው ። ይህችን የመሰለች ቆንጆ ስትወጣ ! » አለች ፈ የናንሲን ፊት እየተመለከተች ። ሁለቱም በደስታ ፈገግታ በሩ።

የናንሲ ፊት ተስተካክሎ እየወጣ ሲሄድ ድምጿም ለሰለ ተኛና የሙዚቀኛ ቃና ያለው ሆኖ ነበር ። ናንሲ ስትናገር ስት ሰማ ፈ እጅግ ተገረመች ። የሰው ልጅ ምንም ያህል ጎበዝ አሰልጣኝ ቢያጋጥመው ይህን የመሰለ ጥዑም ድምፅ ይኖረዋል ብላ አስባ እንደማታውቅ በልቧ እያሰበች ።

« ለምን የተዋናይነት ሙያ አትሞክሪም ? ጥሩ ሙያ ነው ። ይህ ሁሉ ነገር ከደረሰብሽ በኋላ » አለች ፈ ።

« ተዋናይነትንማ እንጃ ። ግን ከካሜራዬ ጀርባ ቆሜ ፎቶግራፍ አንሺነትን አልጠላውም » አለች ናንሲ ።

« ደስ እንዳለሽ ። ድንገት ብልጭ ስላለብኝ ነው ። የዚህ ሳምንት ዕቅድሽ ምንድነው ? »

« ፒተርን ፎቶ ላነሳው አስቤአለሁ ። ነግሬዋለሁ ። እሱ ደግሞ ወደ ሳንታ ባርባራ ሰዎች ሊጠይቅ እንደሚሄድ ነግ ሮኝ አብረን ልንሄድ ተስማምተናል »

« እናንተ ዓለማችሁን ቅጩ። እኔ ምን ይዋጠኝ ? — ደግ እንግዲህ — ማክ ፣ የለም ረቡዕ ለት እንገናኝ »

« እሺ እመቤቴ »

ከፈ አሲሰን ቢሮ ወጥታ ምን ጊዜም የማይለያትን ፍሬ ድን አስከትላ አንድ ሁለት ሕንፃዎች አልፎ ወደሚገኝ የሕ ፃናት መጫወቻ ቦታ አመራች ። በቅርብ ልጆችን ፎቶ አን ስታ አታውቅም ነበረ ። ልጆች ነበሩ ። እንደደረሰች አንድ ማረፊያ ወንበር ላይ ቁጭ ብላ ሲጫወቱ ትመለከት ጀመር ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ከየት መጡ ? የማናቸው ? ለማን ነው የሚለፉት ? አለች በሀሳቧ። የማንም ሆኑ የማን ሲጫወቱ ደስ ይላሉ ።

ልጆች ደስ ይላሉ ።

ቀኑም ደስ የሚል ቀን ነበር ።

ስለዚህ እሷም ደስ አላት ።

★ ★ ★

«እዚህ ቦታ ሁልጊዜ ትመጣለህ ?»

ማይክል በድንጋጤ ባንኖ ቀና አለ ። እንዲህ የጸደይ ወር ሲመጣ በፊትም ነጭ ሆኖ የከረመው ፣ በኋላም ወደግራጫነት የተለወጠው ነገር ሁሉ ደርሶ ሲለመልምና አረንጓዴ ሲሆን መንፈስን የሚያድስ ኃይል አለው ። ማይክል ሂልያርድ የቢሮው መታፈን ሲበዛበት ጊዜ ትንሽ መንፈሴ ዘና ቢል ብሎ ባቅራቢያው ወደሚገኘው መናፈሻ ቦታ ሄዶ ቁጭ ብሎ ነበር ። እዚያ ቦታ ማንም እንደማይረብሸው ተስፋ ነበረው ። ተሳስቶ ኖሮ ከላይ የጠቀስናቸውን ቃላት ሰማ ። ቀና ሲል ፔንዲ ታውን ሴንድ አጠገቡ ቆማ ተመለከተ ።

« የ . . . የለም . . . ሁልጊዜስ አልመጣም ። እንዲያው የሆነ የጸደይን ፍስሀ የመቅመስ ድንገተኛ አባዜ ያዘኝና መጣሁ ፣ ነጂ . . . »

«እኔንም ልክ ያንተው ዓይነት ነገር ነው ያመጣኝ »

አይስክሬም ይዛ ነበረና እንደማፈር ያለች መሰለች ። ይባስ ብሎ ከላይ ቸኮላቱ ተፈርክሶ ሊወድቅ ሲል እንደምንም ብላ ባፏ ተቀበለችው ።

«ሲያዩት በጣም የሚጥም ይመስላል» አለ ማይክል ከፊ ላው የጸደይ አየር ጋር ፈካ ያለ ፈገግታ እያሳያት ።

«ላካፍልህ ?»



t.me/OLDBOOKSPDF

« ተይው ይቅርብኝ ። ስለልግስናሽ አመሰግናለሁ ። መቆ
መጥ ትፈልጊያለሽ ? »

እንደሥራ ፊት በሥራ ሰዓት እመናፈሻ ውስጥ ሲያውደለ
ድል በመያዙ እፍረት ተሰምቶታል ። የገና በዓል ዋዜማ ዕለት
እቢሮው ድረስ ሄዳ እንኳን አደረሰህ ካለችው በኋላ በየጊዜው
ሲተያዩ ፣ በአንዳንድ ምክንያትም ሲገናኙ ቆይተዋል ። ደስ የም
ትል ልጅ ናት የሚል ሃሳብ በልቡ ውስጥ እየፀነሰ ሲሄድ ቆይ
ቷል ።

እጠገቡ ቁጭ ብላ አይስክሬሟን ጨረሰች ።

« ሥራ እንዴት ነው ? ለመሆኑ አሁን ምን እየሠራሽ ነው?»
አላት ።

«የሀውስተንና የካንሳስ ሲቲ ፕሮጀክቶችን እየሠራሁ ነው።
አንድ ፕሮጀክት ላይ የኔ ሥራ ሁልጊዜም አንተ ከጨረስክ ከመ
ንፈቅ በኋላ ነው የሚጀምረው ። የአንተን ዱካ እየተከታተሉ
መሥራት በጣም ያስደስተኛል »

«ይኸን ንግግር ምን እንደምለው አላውቅም »

«ምስጋና በለው »

«እግዜር ይስጥልኝ ። በነገራችን ላይ ቤን ምን ዓይነት
አለቃ ነው ? ማለቴ ደግ ነው ወይስ መሆን አለብህ ብዬ ባስጠነ
ቀቅሁት መሰረት ጨካኝ ባሪያ ፈንጋይ ነው ? »

«ጭካኔ የሚባል ነገር ቢሞክርም አይሳካለት »

« ይገባኛል ። አውቃለሁ » አለ ማይክል በትዝታ ፈገግታ
ተውጦ ። « ታውቂያለሽ ፣ እኔና ቤን የረጅም ጊዜ ትውውቅ
አለን ። እንዲያውም ወንድማማች ማለት ነን »

«በጣም ግሩም ፣ ሊወደድ የሚገባ ሰው ነው »

ማይክል ራሱን በአወንታ ነቀነቀ ፣ በጸጥታ ። ወደ ሀሳቡ
ውስጥ ገባ ። ቤንን ካየው ምን ያህል ሩቅ ነው ። ይሆን



t.me/OLDBOOKSPDF

ሥራ ከጀመሩበት ጊዜ ጀምሮ እንደዱሮው አይገናኙም ። ጊዜም የለም ። ወይም አመቺ ጊዜ አይፈጠርም ። ቤን እንዴት እንደ ሚኖር እንኳ አያውቅም ። ሁልጊዜ ተገናኝተን የምንነጋገርበትን መንገድ እፈጥራለሁ ይላል ። ግን አይሳካለትም ። ማይክል፥ የዱሮው ማይክል አይደለም ። ተለውጧል ። በህይወቱ ብዙ ነገር ሲለወጥ—እሱም ተለውጧል ።

« በሐሳብህ እሩቅ አገር የሄድህ ትመስላለህ ሚስተር ሂልያርድ ። ደስ የሚል አገር ይሆን ? »

ትከሻውን ነቅንቆ ፤

« የጸደይ ወራት ሁሌም እንዲህ ያደርገኛል ። እንዲህ ባለሁበት ላይ እንድቆም ያደርገኝና ያለፈውን ኑሮዬን እንድቃኝ ይገፋፋኛል ። ያን እያደረግሁ ነው መሰለኝ ዛሬም »

« ነገሩ አይከፋም ። እኔም እንደሱ ዓይነት ነገር አለብኝ ። ግን እኔ እንዲህ እማደርገው ባመት ባመት በመስከረም ወር ላይ ነው ። ምናልባት ከትምህርት ቤት መከፈት ጋር ተያይዞ ፣ በዚያው ልማድ ሆኖብኝ ቀርቶ ይሆናል ። አብዛኛው ሰው የዚህ ዓይነት ስሜት ይሰማኛል የሚለው በጥር ወር ላይ ነው ። ግን አሁን ስትለኝ እንደገባኝ ይህ መሆን የሚገባው በጸደይ ወራት ነው ። ያኔ ነዋ ሁሉ ነገር ለምልሞ አዲስ ሆኖ የሚወጣው ። ያኔ አብሮ ኑሮን እንደ አዲስ መጀመሩ መልካም ሳይሆን አይቀርም ። »

ይህን ስትል አያትና ፈገግታ ተለዋወጡ ። ከዚያም ዓይኑን ፊት ለፊቱ እሚገኘው ኩሬ ላይ ተከለ ። ሁለት ዳክዬዎች በጸጥታ ይንሳፈፋሉ ። በተረፈ ግን ጸጥ ብሏል ።

« አምና ይኸኔ ምንድን ትሰራ ነበር ? » አለች ዌንዲ ታውንሴንድ ።

እሷ አፏ እንዳመጣላት ጠየቀች ። ከፉም ፣ ደግም አላሰበች ። ግን ይህ ጥያቄ ማይክልን እንደስል ካራ ከላይ እስከ ታች ስንጥቅ አደረገው ። ምክንያቱም ባለፈው ዓመት ይኸኔ . . .

ባለፈው ዓመት በዚህ ቀን . . .



t.me/OLDBOOKSPDF

«ምን . . . ያው አሁን ከምሰራው የተለየ ምንም ነገር አል ነበረም » አላት እንደምንም ። ፊቱ ልውጥውጥ አለ ። ግንባሩ መስመር ብቻ ሆነ ። ከመቀመጫው ብድግ ብሎ—

«ትንሽ ብናወራ መልካም ነበር ። ደስ ይለኝ ነበር ። ሆኖም ካስር ደቂቃ በኋላ ስብሰባ መግባት አለብኝ ። ስለዚህ ልሂድ » አለና ፈገግ ሳይል ጨብጧት ሄደ ።

ሁኔታው ድንገት ልውጥ ማለቱን የተገነዘበችው ዌንዲ ምን ብዬ ይሆን ? ምን የሚያስከፋ ነገር ተናገርኩ ይሆን ? ስትል አሰ በች ። የለም ስለሰውየው ጠባይ ቤንን መጠየቅ ይኖርባታል። እወቅሁት ስትል ድንገት የትናየት ርቀህ እንደምትገኝ ያሳ ያሀል . . . . . .



t.me/OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ አሥራ አራት

ከአሥር ደቂቃ በኋላ በተጀመረው ስብሰባ ላይ ዌንዲም ተካፋይ እንደነበረች ሲረዳ ማይክል በጣም ተገረመ ። ዌንዲ እስብሰባው ላይ እንድትገኝ ያደረገው ቤን አብሪ ነበር ። ምክን ቱም ስብሰባው የሳንፍራንሲስኮ ሕክምና ማዕከልን ሥራ ለመ ጀመር በሚቻልበት ዕቅድ ላይ ለመነጋገር ሲሆን አስቀድሞ መነጋገርን ከሚሹ ሥራዎች አንዱ የሕንፃው የውስጥ አሠራር ንድፍ ሥራ ነው።የዚህ ባለሙያ ደግሞ ዌንዲ ታውንሴንድ ናት ።

በእርግጥ አስቀድሞ በታወቀው መሠረት መሠረታዊውን ፕላንና ንድፍ ተከትሎ ሕንፃው ይሠራል ። ግን ይህ በቂ አይ ሆንም ። ውበቱን ከፍ ለማድረግና ድንቅ የጥበብ ሥራ ለመ ፍጠር በሥነ ጥበብ ሥራዎች ማስጌጥ ያስፈልጋል ። እነዚያን የሥነ ጥበብ ሥራዎች ቤን ራሱ ወደ ሳንፍራንሲስኮ በመሄድ ሊፈልግና ሊመርጥ ወስኗል ። ስለዚህም ዌንዲ ኒውዮርክ ውስጥ የሚከናወነውን ሥራ በጥብቅ መከታተል አለባት ።

ሥራው ዛሬና ነገ ይጀመራል የሚባል ባይሆንም ስብሰ ባው የተደረገው አስቀድሞ የተቻለውን ያህል ሁኔታዎችን ለማጥናት ፣ ውሳኔዎችን ለመስጠትና ይደርሳሉ የተባሉ ችግ ሮችን ለመመልከትና ዕቅዱን አበጥሮ ለመተንተን ነው ። ይህ ዝግጅት ተደርጐ ከቆዩ ሥራው ሲጀመር የሚመጣው ችግር አነስተኛ ይሆናል ።

ስብሰባው ረጅም ግን ምንም ዓይነት ዘበዛባ የሌለበት ሲሆን በማሪዮን ሒልያርድ መሪነት ፣ በጆርጅ ኮሎዌ ረዳትነት ነበር የተካሄደው ።

ይህ ይባል እንጂ የማይክል ተሳትፎ ከነዚህ ከሁለቱ የሚ ያንስ አልነበረም ። ምክንያቱም የዚያ ፕሮጀክት ኃላፊ ራሱ



t.me/OLDBOOKSPDF

ማይክል ሒልያርድ ሆኖ ተሾሚል ። ማሪዮን ሒልያርድ የዚህን ትልቅ ፕሮጀክት ኃላፊነት ለማይክል መስጠቷ በከንቱ አልነበረም ። በመላ ሀገሪቱ የሚገኙ ታላላቅ የሚባሉ የአርኪቴክቸር ድርጅቶች ሁሉ የዚህን ፕሮጀክት ሥራ ለማግኘት ቋምጠው ነበር ። ኮተር ሂልያርድን ማሸነፍ የማይቻል ሆነና ሳያገኙት ቀሩ ። የሥራውን ሁኔታ የማይከታተል ባለሙያ ድርጅት አይኖርም ማለት ነው ። እንደሚያዋጣ ማሪዮን ሙሉ በሙሉ ታምናለች ። ይህ ደግሞ የፕሮጀክት ኃላፊ የሆነውን አርኪቴክት ስምና ዝና የሚተክል እንደሆነ ይገባታል ። ስለዚህም ኃላፊነቱን ለማይክል ሰጠችው ።

ስብሰባው ሲያበቃ ከምሽቱ አሥራ ሁለት ሰዓት ሊሆን ምንም ያህል አልቀረውም ነበር ። በዕለቱ ዌንዲ ታውንሴንድ በሀሳብ አቀራረቧ ፣ ሲያስፈልግም ማሪዮንን እስከመጋተር በመድረስ በሙያዋ ምን ያህል የበሰለች እንደሆነች አሳይታለች። ስብሰባው ሲያልቅ ድክምክም ብላ ነበር ።

ከስብሰባው ሲወጣ ቤን ትከሻዋን መታ መታ እያደረገ—

« እሰይ የኔ ልጅ ! የዛሬ ሁኔታሽ የሚደንቅ ነበር » አላት። ወዲያው ጸሐፊው ስለጠራችው ቀድሟት ሄደ ።

ዌንዲ ስለሁኔታው እያሰበች በኮሪደሩ ውስጥ ብቻዋን በመጓዝ ላይ እንዳለች ማይክል አስቆማት ። ገረማት ።

« የሥራሽን ሁኔታ ጥልቀት ላይ በጣም ተገረምኩ ዌንዲ ። እንዲህ ከሆነ በመተባበር ግሩም የሆነ ነገር እንደምንፈጥር ይታየኛል » አለ ማይክል ።

« እኔም እንደዚያ ብዬ እገምታለሁ » አለች ፣ ኩራት እየተሰማት ። ሌላ ሰው ሳይሆን ማይክል ነው'ኮ ያመሰገናት ።

« አትጠራጠሪ » አለ ማይክል ።

ድንገት ሁለቱም ዝም አሉ ፣ ጎን ለጎን እየሄዱ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ውን አልነበሩም ። እንደሷ መላ ቅጥ ያጣ ሀሳብ ያቀረቡ ፤ እንደሱ መላቅጥ ያጣውን ሀሳብ የተቀበሉ ብዙ ጥንዶች በወደቡ አካባቢ ነበሩ ።

በወደቡ አካባቢ ሲንሸራሸሩ ፣ የመጣላቸውን ሲያወሩ አመሹ። ወደ መጨረሻው ላይ በወሬ ወሬ የጋብቻ ጉዳይ ተነሳ ።

«መቼ ነው—ማለት ሚስት የማግባት ሀሳብ አለህ ? »አለችው።

ፊቱን አቅጭሞ አንገቱን በአሉታ ነቀነቀ ።

«እስከ ዘለአለም ?» አለች ።

«እስከመቼም »

«ለምን ? መጠየቅ ይፈቀድልኛል ወይስ. . . »

«ጠይቂ» አላት «እንግርሻለሁ ምክንያቱን »

«እስከመቼ ሸሽቶ ይኖራል»

«በምሣ ሰዓት ያስደነገጥኩሽ በዚያ የተነሳ ነው ። ራት አብረን እንድንበላ ያደረገኝም ይኸው ጉዳይ ነው ። አምና ፣ በዚህ እለት ...ላገባ ነበር ። እኔ...ቤን አብረ ሆነን ስንሄድ መኪናችን ተገጭታ ትልቅ የጭነት መኪና ፣ እኔና...ቤን ዳንን ። ... የዚያኛው መኪና ሹፌር እና... እሷ ግን ሞቱ» አለ ።

ይህን ሲል እንባ እሚባል አልወጣውም ፣ አላለቀሰም ። ግን ሰውነቱን አንድ ነገር የሸረካከተው ፣ የበጣጠሰው መሰለው ።

ዌንዲ በፍርሀት እና በመሳቀቅ እያየችው እንዲህ አለች።

«ማይክ ! በስማብ ! የምትነግረኝ ነገር እውን ሳይሆን ቅዠት ይመስላል! »

«ቅዠት ነበር ። አየሽ ለሶስት ቀን... አደጋው ከደረሰ በኋላ አልሰማ አልለማ ስንቃ ማለት ነፍሲን ሳውቅ...አልፋለች ። ምን ልሁን. . . እ. . . እ. . . ኔ. . . » መናገር አልቻለም ። ቃላቱ አል ወጣልህ አሉት ። ግን ጀምሮታልና መናገር አለበት ።



t.me/OLDBOOKSPDF

«ሲሻለኝ ከሁለት ሣምንት በኋላ ቦስተን ነበርኩ ... ቦስተን ነበር እምትኖረው ወደመኖሪያ ቤቷ ሄድኩ ። ግን ማንም አልነ በረም— ምንም አልነበረም ። እቃዋም ፣ ስእሎቹም ተሰርቀው ደረሰኩ ። ሰአሊ ነበረች— ነርሶች ናቸው አሉ የ...የወ...የሰረቋ ቸው ስእሎቿን...»

ዝምታ ሆነ ። ለረጅም ጊዜ ሁለቱም ፀጥ ብለው ተቀመጡ ። ከዚያ ቀጠለ—

«የቀረ ነገር አልነበረም ። የለም ። እኔም ውስጥ ማለቴ ነው» አለ ። ይሀን ብሎ ቀና ሲል የዌንዲ ፊት በእንባ ርሶ ተመለከተ ።

«ማይክል በጣም አሳዛኝ ነገር ነው ። ይህ ስለደረሰብህ በጣም አዝናለሁ» አለች እግዜር ያጥናህ እንደማለት ነበረና—ማጥናኛ ውን እራሱን በማወዛወዝ ተቀበለ። ቀጥሎ ለአንድ ዓመት ያሀል እምቢ ያለው እንባ ፈሰሰ ፣ አለቀሰ ። ዌንዲን እቅፍ ሲያደርጋት የእንባ ዘለላዎች ፊቱን እያቋረጡ ወደ አንገቱ ፈሰሱ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ አሥራ አምስት

«ማይክ የካንሳስ ሲቲውን ፕሮጀክት ስለምትመራው ሴትዮ ምን አስተያየት አለህ ... ማለት ..» አለች ዌንዲ ታውንሴንድ ።

ማይክልና ዌንዲ እዌንዲ ቤት በስተጀርባ ባለችው አትክልት ቦታ ነበሩ ። በታጣፊ ወንበር ላይ ተቀምጦ የእሁድን ጋዜጣ ይመለከት ነበረና ቀና ብሎ አየችው ። ሁለቱም የዋና ልብስ ለብሰው የኒውዮርክን ፀሐይ ይጠጣሉ ።

«ስለ ሴትዮዋ» አለች ሠሬ የመቀጠል ሙከራዋን ። አልሰማትም ። እጋዜጣው ላይ አፍጥጧል ። ጋዜጣውንም እንደማያነበው ዌንዲ ታውቃለች ።

« ማይክ »

«እ ? ምን አልሺኝ?»

«ስለ ካንሳሷ ሴትዮ እየጠየቅኩህ ነበረ »

መልስ አልሰጣትም ። እንደገና ሀሳብ ውስጥ ገባ ። ሙከራዋ ሁሉ ተስፋ የሌለው ነገር እንደሆነ ገብቷታል ። በመረበሽና በብስጭት አይን አየችው ።

« ዊስኪውን ልጨምርልህ ? » አለች ።

«እ?እ...እምን።ወደ ቢሮ መሄድ ይኖርብኛል መሰል» አለና በሷ ላይ አሳልፎ አይኑን እሆነ ባዶ ላይ ተከለ ።

«ግሩም ድንቅ ሀሳብ ነው » አለች በፌዝ ።

«ምን ማለትሽ ነው ?»

አሁን ያያት ጀመረ ። እንዲያ ሲያያት እፊቷ ላይ እንግዳ ነገር አየባት ። ምን እንደሆነ ሳያውቀው ሀሳቡ ተከፈለ ። ጥቂት ቢያጤናት ኖሮ እፊቷ ላይ ያየውን ነገር ትርጉም ሲያገኘው ይችል ነበር።



t.me/OLDBOOKSPDF

ብታውቅም ይህን ማወቋ ሰልችቷት ነበረና ። ልታስበው አቅም አጣች ። ብትችል ኖሮ ገላዋን መከልከል ነበረባት ። ብትችል ያን ለማድረግ ጊዜው አሁን ነበር ።

« ዌንዲ በጣም ታስፈልጊኛለሽ » አለ ።

ቃሉን ስትሰማው መላ አካሏን ፍትወት አቅበጠበጣት ። ግን ደግሞ ይህ መሆኑ እንዳይታወቅባት ራሷን መቆጣጠሯም አልቀረም ። ፊቷን እንዳዞረች ፣ በጀርባዋ ላይ ቀስ እያሉ ፣ እየ ደባበሱ የሚወርዱትን እጆቹን ልስላሴ ጠላች ።

« እና ፣ ልበልህ ቅድም አንተ እንዳልከው» አለች ። በጣም ታስፈልጊኛለሽ ላላት ስትመልስ ።

« ፍላጐቴን መቆጣጠር እንደማልችል ታውቂያለሽ ማለቴ ነው » አለ ።

ድምጹ እንደገላው ልስልስ ያለና የላመ ነበር ።

« ማይክል የፍላጐቴ ግለት ሳይሆን ፍቅር ነው ። ዳሩ አንተ በፍቅርና በባዶ የፍላጐት ግለት መካከል ያለውን ልዩነት አታውቀውም ። ከሷም ጋር ሳለህ እንዲሁ ነበርክ ? »

ይህን ስትል የሚዳስሷት እጆች ቀጥ አሉ ። ከንዴም ጥን ክር ሲል ተሰማት ። አደጋ አለ ። ሆኖም ራሷን ተቆጣጥራ ዝም ልትል አልቻለችም ። ልትጐዳውም ፈልጋለች ።

« እሷንም ለማፍቀር ለመውደድ ትፈራ ነበር ? ዛሬ ማን ንም መውደድ ስለሌለብህ ፣ እሷን በማጣትህ የተነሣ በደረሰብህ ሀዘን ጀርባ ተከልለህ እንድትኖር ስለረዳህ ፣ ሞቷ ችግርህን ቀላል አድርጐልሀል ልበል ? የሷ ሞት ከፍርጃም ፣ ከንትርክም ነፃ አድርጐሃል ፣ አይደለም ? »

ይህን ብላ ዞረችና ፊት ለፊት ተጋፈጠችው ። በዓይኑ ውስጥ የጥላቻ ጥንስስ ሲፈላ ተመለከተች ።

« እንዶት እንዲህ ትይኛለሽ ? እንዴት ይህን የመሰለ ነገር ደፍረሽ ትናገሪያለሽ ? » አለ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ አሥራ ስድስት

በመንገዱ ላይ አንዳች ነገር አልነበረም ። ዝር አይልም ። ይህን ሲገነዘብ የቤንዚን መስጫውን እስከ መጨረሻው ረገብ፡ው ። ጥቁር ቀለም ያለው ጋርሽ አውቶሞቢል ከነፈ ። የገጠሩ ምድርና በላዩ ላይ የተሸከመው ነገር ሁሉ እየሰፈሰፈ ያልፋቸው ነበር ። ልባቸው በደስታ ተሞላ ። በመኪና የመጓዝ ሳይሆን የመንሳፈፍ ስሜት ተሰማቸው ።

በአምስት ሰዓት አካባቢ ረፋዱ ላይ እቤቷ ድረስ መጥቶ በኦውቶሞቢሉ ከተሳፈረች በኋላ ከሳንፍራንሲስኮ ተነስተው ወደ ደቡብ ጉዞአቸውን ቀጠሉ ። ሁልጊዜም እሁድ እሁድ በመጀመሪያ እንዲሁ ይጓዛሉ ። መድረሻቸውን አያውቁትም ። ሲሰለቻቸው ወይም ሲርባቸው ከመኪናቸው ወርደው ምሳ ይበላሉ ። ካረፉ በኋላ እጅ ለእጅ ተያይዘው እየተንሸራሸሩ ፣ ስላለፈው ሕይወታቸው እያወሩ ፣ ባለፈው ስላጋጠማቸው አስቂኝ ሁኔታ እያነሱ ከልባቸው ይስቃሉ ። ሽርሽሩ ሲበቃቸው ወደ ቤታቸው ይመለሳሉ ። ይህ የተለመደ እንደ ጸሎት ሥርዓቱን ጠብቆ የሚደጋገም ነገር ነውና ለምዳዋለች ፤ ወዳዋለች ። ይህን ድርጊት ብቻ ሳይሆን ፒተርንም በተዘዋዋሪ መንገድ ማፍቀር ጀምራለች ።

ፒተር ግሬግሰን ተዝቆ የማያልቅ ችሎታ ያለው ሰው ነው ። ባንደኛው ችሎታው አካሏን እየመለሰላት ነው ። ምንም እንኳ ገና ኦፕራሲዮኑን ባይጨርስም ዛሬ የናንሲ ፊት ቁልጭ ብሎ ወጥቷል ። ፋሻው ዓይኗ አካባቢ ብቻ ሲሆን የሚገኘው ፣ ሌላውን ፊቷንም ያደረገችው ሰፊ ጥቁር መነፅር ሙሉ በሙሉም ባይሆን ሸፍኖታል ። ግንባሯ ላይ ያለውን ፋሻም ባርኔጣዋ ጋር ዶልታል ። ያም ባይሆን ከፒተር ጋር ስትሆን ይህ ሁሉ አይሰማትም ። ፒተር ይህ ሁሉ እንዳይሰማት የሚያደርግ ኃይል



t.me/OLDBOOKSPDF

አለው ። ይህን ሁሉ የሚያደርግላትን ፣ ምኞቷንና ሕልሟን እውን ያደረገላትን ፒተር ላለመውደድ ችሎታ ይኖራታልን ?

አንዲት ትንሽ ምግብ ቤት ሲያዩ መኪናቸውን አቁመው ምሳ ለመብላትና ዕረፍት ለማድረግ ወሰኑ ። ምግብ ቤቷ በፈረንሳይ የመንገድ ዳር ማረፊያና መመገቢያ ቤቶች ዕቅድ የተሠራችና የተሽሞነሞነች ነበረች ። በውስጧም የፈረንሳይ ምግቦችና ነጭ ፣ ደረቅ የወይን ጠጅ የሚሸጥባት ነበረች ። ምሳቸውን በሉ ። ነጭ ፣ ደረቅ የወይን ጠጃቸውን ጠጡ ። ይህ ደግሞ ናንሲን ያስደስታታል ። ለምዳዋለች ። እዚህ እንደመጣችበት ምሥራቃዊው ግዛት ያሉ መዝናኛዎች የሉም ። ባዛሮች በብዛት አይገኙም ። የሚያብለጨልጩ ሰማያዊ ያንገት ጌጥ መቁጠሪያዎችም አይገኙም ። ስለዚህ እንደ ሀገሩ ያገሩን መዝናኛ መቀበልና መልመድ አለባት ። አንድን ነገር መልመድ በግዴታ የሚቻል ነገር ባይሆንም በውዴታ ለምዳ ወዳዋለች ።

ይህ ብቻ ሳይሆን ናንሲ አዲስ ሰውነቷን ፣ አዲስ ገፅታዋንም ተቀብላ ወዳዋለች ። አዲስ ድምጿን በመቃኘት አዲስ እቧን መሆን ጀምራለች ።

«ፒተር ስሜን ለመለወጥ እንዳሰብኩ ነግሬሃለሁ ? » አለች ።

ይህን ያለችው ምሳቸውን በልተው ጨርሰው ወይን ጠጃቸውን እየጠጡ ሲዝናኑ ከቆዩ በኋላ ጠርሙሱን ሲያጠነፍፉት አካባቢ ነበር ። ነገሩን ከፌ አሊስን ጋር ተወያይተውበታል ። ያኔ ግን ይህን ያህልም የሚያስፈራ መስሎ አልተሰማትም ። ለፒተር ስትነግረው ዕፍረቷ በገፅታዋ ላይ ተስሎ ታዬ ። ምነው ባላነሳሁት ኖሮ ስትል አሰበች ። ግን ፒተር ዕፍረቷን ሁሉ በፍጥነት ከለላት ።

« እንዲያ ስትይ ፈፅሞ አላስገረመኝም ታውቂያሽ ። ምክንያቱም አንቺኮ የድሮዋ ናንሲ አይደለሽም ። አዲስ ሰው ነሽ ፣ ሌላ ቀንጆ ። ያሰብሽው ደስ የሚል ስም አለ ? » አለ ፒተር ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ይህን ብሎ ምርጥ ሲጋራውን አቀጣጠለ ። በፍቅር ዓይን አያት ። የሲጋራውን ሽታ መውደድ ጀምራለች ። በተለይ ከም ግብ በኋላ ሽታው ያስደስታታል ። ፒተርም ይህን የተረዳ ይመ ስላል ። ዓላማው ደግሞ ግልፅ ነው ። በሕይወት ውስጥ አንድ ነገር ከተደረገ ጥራት ያለው መሆን አለበት ። ነገሩ ለናንሲ አዲስ ስለሆነ ይህንንም እንድትለማመድ ይፈልጋል ። ከፍ ከፍ እንደ ማለት የሚያስደስት ምን ነገር ሊኖር ይችላል ?።

« ታዲያ አዲሷ ወዳጃችን ማን ትባላለች ? ስሟን ትንገ ረና » አለ ።

«ለጊዜው ሜሪ አዳምሰን የሚል ስም ነው የመጣልኝ ። እንዴት ነው ይስማማል ?»

ትንሽ አሰበና አንገቱን በስምምነት እየነቀነቀ ፣—

« መጥፎ ስም አይደለም ። እንዲያውም ወድጀዋለሁ ። ግን . . . ግን ለምንድነው ሜሪ አዳምሰንን የመረጥሽው ? »

« የናቴ ስም ፣ ማለት ከማግባቷ በፊት ሜሪ አዳምሰን ነበር ። እንዳጋጣሚ ሆኖ ዕጓለማውታን ማሳደ ፣ያው ውስጥ እወዳቸው የነበሩ መነኩሲትም ሜሪ አዳምሰን ይባሉ ነበረ »

« ኧረ በስላሴ ፣ እንዴት የሚያስደንቅ ጉድ ነው እባክሽ »

ሁለቱም በጉዳዩ ሳቁ . . . . ሜሪ አዳምሰን ። ይህን ስም ስታስበው በጣም ወደደችው ።

« ከመቼ ጀምሮ ነው ባዲሱ ስም መጠራት የምትፈልጊው?»

« እኔንጃ . . . ገና አልወሰንኩም »

« እኔ ምለው ከወደድሽው ምን ዛሬ ነገ ማለት ያስፈልጋል ። ዛሬ ፣ ከአሁን ጀምረን ለምን ሜሪ እንልሽም ? እስራዎችሽ ላይም ሜሪ አዳምሰን እያልሽ ብትፅፊ ጥሩ ነው ። አይመስልሽም ? »

ፒተር ይህን የተናገረው በከፍተኛ ስሜትና የልብ ሲቃ ነበር ። ሁልጊዜም ስለሷ ወይም ስለራሱ ሥራ ሲያነሳ የሚና ገረው በከፍተኛ ሲቃ ነበር ።



t.me/OLDBOOKSPDF

« ናንሲ እውነቱን ነው ፤ ለምን እሁኑኑ ሜሪ አትባይም ፡ እስራሽ ላይም ይህንኑ ስም አስገቢ »

« እንዴት ማለት እስራሽ ላይ ? ፎቶግራፎቹ ግርጌ ፎቶ በሜሪ አዳምስን ብዬ ልፅፍ ? »

« ይመስለኛል ። ማለት ስራሽ እኔንና ፊ እሊሰንን ብቻ እስደስቶ መቅረት የለበትም ። ትንሽ ወጣ ማለት ፤ እድማስ ሽን ማስፋት ያለብሽ መሰለኝ »

በፒተርና በናንሲ መካከል አለመግባባት እለ ቢባል የማ ይግባበብት እንደኛው ጉዳይ ይኸ ነው ። ፒተር ግሬግሰን ፤ ናንሲ ማክአሊስተር ትልቅ እንድትሆን ፤ ታዋቂ እንድትሆን ይፈ ልጋል ። ስራሽን ዓለም ሲያየው ይገባል ይላል ። ናንሲ ግን ለጊ ዜው ይህን አትሻም ። ሁሌም ይከራከራሉ ።

« እንደገና ይህን ነገር እንስተን ባንጨቃጨቅ ይሻላል » አለች ። መዳፏን «ታገድ» በሚል መልክ እያሳየችው ።

« ካልሽ ይሁንልሽ ። ለጊዜው ማለቴ ነው ። ግን ባጠቃላይ እንጋገር ካልን ይኸ የጋን መብራት ሆኖ ልቅር የምትይው ነገር አይስማማኝም ። ይህን የመሰለ ሥራ ተሠርቶ ማንም ሳያየው ይቅር ብትይኝ እሺ ማለት የሚቻለኝ አይመስለኝም ። ስራሽ መውጣት ፤ መታየት አለበት ። »

« የማይሆነውን ! »

« ስሚ ናንሲ ። ደግሜ ልንገርሽ ። አንቺ ወጥ የሆንሽ የኪነጥበብ ሰው ነሽ ። እንደፈልም ተዋናይ ይሁን እንደፎቶ ግራፈር ወይም ሌላ ፤ ስራሽም አንችም በአደባባይ መታየት አለባችሁ ። ይህ የኔ እምነት ነው ። ዕኑ ዕምነቴ ነው »

« አትልፋ ፒተር » አለችና ከወይኑ ተጎነጨች ። ከዚያም ቡዝዝ ብላ በመስኮት ወደውጭ እየተመለከተች « ቅር አይበልህ ። ግን ከእንግዲህ አደባባይ መውጣት የማይቻለኝ ሰው ነኝ »

« ለምን ናንሲ ? ለምን ? »



t.me/OLDBOOKSPDF

« ላለም ላሳየው የምፈልገውን ያህል ፥ ዓለም ሊያየኝ የሚፈልገውን ያህል አሳይቻለሁ ። አይቶኛል ። በቃኝ ። ካሁን በኋላ የሚታይ ነገር የለኝም »

« በጣም ጥሩ ! የተቻለኝን ያህል ለፍቼ ገፅታሽን የሰጠሁሽ ለካ ዕድሜ ፊክሽን እማጀት ተደብቀሽ በኔ ብቻ የሚታዩ ድንቅ ፎቶግራፎችን እንድታነሺልኝ ኖሯል ? »

« ይሀ ታዲያ በጣም የሚያምር ነገር ነው 'ንዴ ? »

« ለኔ . . . ለኔ ብቻ ቢሆን ድንቅ ዕድሌ ነው ። ላንች ግን ከዚህ የከፋ ዕጣ ሊኖር አይችልም ። ናንሲ ፥ በጣም ትልቅ ሰው ነሽ እኮ ! ተዝቆ የማያልቅ ችሎታ አለሽ ። ታዲያ ይህን ችሎታሽን መደበቁ ምን ይጠቅማል ? ስምሽ እንዲወጣ ካልፈለግሽ ሚሪ ኦዳምስን በሚለው ስም ኤግዚብሽን ማሳየት ትችያለሽ ። እንደዬ ብቻ — ለሙከራ ያህል ። አየሽ ፥ ግሬታ ጋርቦም ወደ ምናኔዋ ከመግባቷ በፊት ድንቅ ተዋናይ ተብላለችኮ ። እንዴ ብቻ ምን እንደሚሆን ለማየት ዕድልሽን ሞክሪ » አለ ፒተር በልመና ፥ በማግባባትና በመለማመጥ ድምፅ ።

ፒተር በዚህ ሁኔታ ከልቡ በነገራት ቁጥር ልቧ ይዋልላል ። ልሞክረው ? ትላለች ። በተለይ በሌላ ስም መሞከሩ አይከፋም ልበል ? አለች ። ግን እንደገና ታዋቂ መሆን ፥ እንደገና ኤግዚብሽን ማሳየት የማይሞከር ሆኖ ተሰማት ። ስትታወቅ ፥ ለከፋ ነገር ስትጋለጥ ፥ መጥፎ ነገር ሲደርስባት ታያት ። ከዚህ በፊት ይህን ሳትሆን የተጓዘችበት መንገድ ስለሆነ ወደዚያው ብትመለስ አዲስ መሆን እንደማትችል ተገንዘበች ። ብዙ ነገር እንደሚያሳስባት ማይክል አሳሰባት ።

« እሺ አስብበታለሁ » አለች ።

በዚህ ጉዳይ ላይ በተነጋገሩ ቁጥር ይህን ያህል ወደ እሺታ የቀረበ መልስ ሰጥታው አታውቅም ነበረና ደስ አለው ።

« እዎ በሚገባ አስቢበት ፥ ሚሪ » አለ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ሜሪ ብሎ በሰፊው ፈገግ አለ ። እሷም የልጅ ዕፍረት ሳቅ ሳቀች ። እና — « ካደግክ በኋላ በአዲስ ስም ስትጠራ የቀልድ የቀልድ ይመስላል » አለች ።

« ግን'ኮ ፊትሽም አዲስ ነው ። እሱም የቀልድ ይመስ ላል ? » አለና ጠየቃት ።

« ፊቴ'ንኳ አይመስለኝም ። አሁን አሁን ለምጄዋለሁ ። ዕድሜ ለፊ አሊሰንና ላንተ'ንጂ ፊቴ የራሴ ሆኖ ነው የሚሰማኝ »አለች።

« ሁልጊዜ ፣ ካሁን ጀምሮ ሜሪ እያልኩ ልጥራሽ ? »

« ደግ ። ቢያንስ ስሙ ማጠሩንና መጥበቡን ለመለካት ይረዳኛል ፣ ባደባባይ ከመልበሴ በፊት » አለች ።

ሁለቱም ደስ ብሏቸዋል ። ሁለቱም የሆነ የመደባበቅ ስሜት ይታይባቸዋል ። ሁለቱም . . . . . .

ሂሣባቸውን ከፍለው ከሆቴሉ ወጡ። መኪናው ዘንድ ሲደ ርሱ ፍሬድ አይቷቸው ሲጨፍር ተመለከቱት ። ፍሬድ በእሁድ እሁድ ሽርሽር ላይ ተካፋይ ነው። ሁሌም በምሳ ሰዓት እመኪናው ውስጥ ይጠብቃቸዋል ። ሽርሽር ሲሄዱ ግን አብሯቸው ይሄዳል። የመኪናው በር ተከፍቶለት ከወጣና የውሻ ሰላምታውን ካቀረበ ላቸው በኋላ ተከተላቸው ።

«እንዴት ነው ፣ ደከመሽ? » አለ ፒተር ፣ ለአንድ ሰዓት ያህል በእግራቸው ከተጓዙ በኋላ ።

«እንመለስ? ወይስ እንቀጥል?»

«እንመለስ ማለቱ ትንሽ ቢያሳፍርም መመለሱ አይከፋም» አለች ።

«ምን አሳፈረሽ ሜሪ? እስከ አመት ድረስ እኔና አንቺ የሩጫ ውድድር ብንጋጠም ጥለሺኝ እንደምትሄጂ እያወኩት» አለ ፒተር።

ትቀድሚኛለሽ ስላላትም፣ በአዲስ ስሟ ሲጠራት ዘላለም በዚያ ስም ሲጠራት የኖረ ያህል ስለጠራትም ተገርማ ሳቀች ። እና

«የሩጫውን ውድድር ተቀብያለሁ» አለች።



t.me/OLDBOOKSPDF

«አትጠራጠሪ ታሸንፊኛለሽ። ከኔ የምትሻይበት ነገር አለሽ»

«ምን ?»

«ወጣትነት ፣ ጥንካሬ»

«አንተስ? አንተም ገና ወጣት ነህ»

ይህን ያለችው ከልቧ ነበረና ራሱን በአሉታ እየነቀነቀ ሳቀ ባት ።

«እንዲህ አፅናኚኝ እንጂ። ምን ጊዜም ይህን አይንሽን አይ ቀይርብኝ፣ የኔዋ ተወዳጅ» አለ ።

እንዲህ ብሎ አይኑን እወዲያ ላይ ተከለ ። እንዲያ ወዲያ ወዲያ ሲያይ በፊቱ ላይ አንድ አይነት የትካዜ ጥላ ያንዣብበት ነበር ። የትካዜውን ጥላ ናንሲ ያየችው እንደ ውልብታ ብቻ ቢሆንም አይታዋለች ። የተከዘበት ምክንያቱም ገብቷታል ። የዕድ ሜው ጉዳይ ነበር ። ምንም እንኳን በመካከላቸው ያለውን የ24 ዓመት የእድሜ ልዩነት እንዳለ ባትቆጥረው ልዩነቱ ግን እንዳለ ገባት። ይግባት እንጂ አልተከፋችም። እንዲያውም የልዩነቱን መኖር የምትወደው ይመስላታል። ይህንንም ደጋግማ ለፒተር ነግራዋለች። አንዳንድ ቀን ይቀበላትና ደስ ይለዋል ። አንዳንድ ቀን ግን ይከፋ ዋል ። እንደተነገረበት እለት የባህርይ ይዞታው ይለዋወጣል ። ይህ ደግሞ ለፒተር አዲስ አይደለም ። ከዚህ በፊትም አጋጥሞታል ። ስንት ጊዜ ነው አስር ወይም ሃያ ዓመት ያህል እድሜው ዝቅ ቢል የተመኘው ?

«ናንሲ» አለ ፒተር አዲሱን ስሚን ፊዕሞ ዘንግቶ ።

«አቤት»

«ናንሲ. . . እስቲ ንገሪኝ . . . ማለት . . . አሁንም . . . ማለት እስከ ዛሬ ታስታውሺዋለሽ ? . . . ማለት ይናፍቅሻል ?»

እፊቱ ላይ የተሳለውን ጭንቀትና ስቃይ ስታይ አዘነችለት። አንገቱን እቅፍ አድርጋ በአሉታ ልትመልስለት ፈለገች፣ ለማፅ ናናት ። ግን ደግሞ ከበዳት ። ለፒተር ውሸት መንገሩ ከማንኛውም ነገር የከበደ ሆና ታያት ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ስለዚህ ጉዳይ ነግሯት አያውቅም ነበርና ናንሲ ሁለመናው ጆር ሆና ታዳምጠው ነበር። እሱም ይህን የሚናገረው አይኑን እድ ማስ ላይ ተክሎ፣ መንፈሱ በትዝታ ጎዳና ርቆ ሄዶ፣ ቅዝዝ ብሎ ነበር ።

«አሁን ለምን ተለያያችሁ?» አለች ናንሲ ።

ጥያቂውን እንደጠየቀች አልተለያዩ እንደሆንስ? የሚል ሀሳብ ብልጭ አለባት። ይህ ሐሳብ ብልጭ ሲል አፈረች። በሰው ነገር እየገ ባሁ ይሆን እንዴ? አለች፣ በሀሳቧ። ምን ይታወቃል። ስለፒተር የማ ታውቃቸው በርከት ያሉ ነገሮች ሊኖሩ ይችላሉ ። ያ ብቻ ሳይሆን መጠየቅ የማይገባተ ነገርም ሊኖር ይችል ይሆናል ። ከዚህ በፊት እንዲህ ያለ ነገር አስባ አታውቅም ነበረና ከላይ ለምን ተለያ ያችሁ ብላ ጠየቀች። ልክ ላይሆን ይችላል ። ይህን ለመጠየቅ ለመ ሆኑ እሷ ማን ናት? ምን ናት?

«ይቅርታ ፒተር እንደዚያ አይነት ጥያቄ መጠየቅ አልነበረ ብኝም» አለች ።

«ጅል አትሁኝ» አለ ፒተር፤ አይኑም እሷን ማየት፣ ሀሳቡም እሷን ማጤን እየጀመረ ።

«የፈለግሺውን ነገር ልትጠይቂኝ መብት አለሽ ! እንዳትጠ ይቂኝ የምትከለከይ ሰው አይደለሽም ። እና አየሽ ጠብ ወይም ሌላ ነገር አይደለም የለያየን ። የለያየን ሞት ነው ። ሞተች ። ካራት ዓመት በፊት ካንሰር ገደላት ።

«ከተገናኘንበት ቀን ጀምሮ ተለያይተን አናውቅም ነበር። አብዛኛውን ጊዜ አብረን ነበርን፣ ከመጨረሻዋ ቀን በስተቀር። ወደ መጨረሻው ግ አንለያይም ነበር ልልሽ እችላለሁ ። ከዚያች ቀን በስተቀር። እንደሚመስለኝ ሪቻርድም ነገሩን አውቆት ነበር ። ባሏ ግለቴ ነው። አወቀም ቀረም ዋጋ አልነበረውም ። እሷ እን ዶሁ የሁለታችንም አትሆንም ። አልሆነችም ። ከመሞት በኋላ በሚ ገባ አውቆ ነበር ይመስለኛል ። ይህን አልሽ ይህን ሰራሽ አላለም።



t.me/OLDBOOKSPDF

እንዲህ ደንገት የሚመጣበት ነገር ያስገርመዋል ። ከወራት በፊት አንድ ቀን ጧት ከእንቅልፉ ቀስቅሳ « አፁብ ድንቅ የሆነ ስሜት ሊሰማህ ከፈለክ አሁኑኑ ተነስተህ የዛሬዋን ፀሐይ አወጣጥ ተመልከት » ያለችውን አስታወሰ ።

«ናንሲ» አለና «የለም ናንሲ አይደለም ሜሪ-- ከሁን ጀምሮ ናንሲን አናውቃትም . . . ሜሪ ! ይቺ ሜሪም እንደናንሲ ደፋርና አስቸጋሪ ፍጡር ናት እንዴ ?»

«እንዲያውም ትብሳለች ። ብታውቃት ሜሪ አዳዲስ ሀሳቦችን በየደቂቃው የምታፈልቅ ነገር ናት»አለች ።

«ምንተ ያለህ ! እንግዲያስ በቃ ይቅርብኝ»አለ ።

ግን ደግሞ ይቅርብኝ ያለው ነገር እንዲቀርበት የሚፈልግ አይመስልም ነበር ። ፊቱም አይመስልም ነበር ። እመኪናው ውስጥ ከገቡ በኋላ—

«ግን ካሰበችው ትንሽ ጨረፍ ብታረግልን ? ትንሽ ?» አለ ።

አይቻልም በሚል ራሷን እየነቀነቀች ፈገግታ አሳረሰችው ። ይህ ሲሆንም ፍሬድ ውሻው በተከፈተው በር ገብቶ እንጣጥ ብሎ ጭኗ ላይ ተቀመጠ ። ፒተር መኪናውን አስነሳ ።

«እንግዲያስ እኔ አንድ ሀሳብ አለኝ ። አዲስ ዓመት እንደ ባተ ሜሪ አዳምሰን የፎቶግራፍ ትርኢት ብታቀርብ ምን ይመስልሻል ? አትስማሚም ? »

«እስማማ ይሆናል» አለች ነፃ የመሆን አዲስ ስሜት እየ ተሰማት ነበር ። «ግን መጀመሪያ ላስብበት »

« እንዴ ላስብበት . . . ምን የለም ። ቃል ቃል ነው ። ቃል እንድትገቢልኝ እፈልጋለሁ ። . . . እንዲያውም . . . » አለና ፒተር እጣፍቶ ቁልፉን ነቀለ ።

ተቀመጠበት ። ከዚያም ምን ትሆኝ ከሚል ፈገግታ ጋር እየተመለከታት « እንዲያውስ ምን አስማመነኝ ! እቤትሽ መድ

t.me/OLDBOOKSPDF

ረስ ከፈለግሽ ተስማሚ ። አይ ካልሽ እዚሁ መቅረትሽ ግድ ይሆናል ። ቃገሉ ቁልፉን ለመውሰድ ደግሞ ጉልበት ያስፈልጋል » አላት ።

ትንሽ የምታስብ መሰለችና ፤—

« እሺ ተሸንፈናል » አለች ፍሬድን እየደባበሰች « ለዛሬ ለዚህ ጉዳይ በአሸናፊነት ወጥተሃል ። ትርኢቱን ላቀርብ ተስማምቻለሁ »

« እንዲህ በቀላሉ ? » አለ የዕውነት ተገርሞ ። ብዙ ጊዜ ይህን ጉዳይ ሲያነሳ ጭራሽ የማይሞከር ነገር ነው ትለው ነበርና።

« እንዲህ በቀላሉ » አለችና የምር በሆነ ድምፅ « ግን እትርኢቱ ላይ የምገኝ ከሆነ በዚህ ሁኔታ — የሚቻል ይመስልሃል ? » ስትል ጠየቀችው ። ፊቷን እያሳየችው ።

« እሱን ለኔ ተይው ። ከዚያ በፊት አንዲት ፋሻ እፊትሽ ላይ አትኖርም » አለ ።

«ሌላው ነገር ትርኢቱን ለማቅረብ ብዙ ነገር ያስፈልጋል። ሰው ፣ አዳራሽ . . . ያንን ሳ ምን እናድርገው ? »

« እሱንም ለኔ ተይው ። አንቺ ተስማሚ ። ሌላውን ሁሉ በኔ ላይ ጣይው ። ተስማማን ? »

« አዎን ጌታዬ ። በፊርማ »

ይህን ስትል ያለውን ሁሉ በመተማመን ነው ። ታምነዋለች። ፒተር ምንም ነገር ያደርጋል ። ትርኢቱን ሊያዘጋጅ እንደሚችል ታምንበታለች ። በስራው ሁሉ ታምንበታለች ። ፊቷን በቀዶ ጥገና መያው ሊያስውበው እንደሚችል ታምንበታለች ። ለኑሮዋ ፣ ለጤናዋ ፣ ለህይወቷ ቤዛ እንደሆነ ታምንበታለች ።



t.me/OLDBOOKSPDF

«የኔ ውድ ፣ የፎቶግራፍ ትርኢቱ ከቀረበ በኋላ ለምን እደ ረኩት ብለሽ እንደማትፀፀች ርግጠኛ ነኝ» አለና ሳማት ።

መኪናውን አስነሳ ። ጉዞ ቀጠሉ ።

★ ★ ★

እቤቷ እንደገባች ወደ መኪናው እየሄዱ ሳለ ያሰበችው ነገር ትዝ አላት ። ኮመዲኖ ከፍታ የተለያዩ ንድፎችን ፣ ስዕሎችን አወጣች ። በመጨረሻ የፈለገችውን አገኘች ። አየችው ። ቃል ገብታ ነበር ። ይህን ስዕል ለማይክል እንደምትሰጠው—የሰርጋ ቸው ዕለት እንደምታበረክትለት—ቃል ገብታ ነበር ። የገፀ ምድ ርን ምስል የያዘ ሲሆን እንደኛው ዛፍ ቅርንጫፍ ላይ አንድ ልጅ ተቀምጦ የሚያሳየው ስዕል ነው ። ገና ስታየው እንባዋ ዝርግ ፍግፍ ብሎ ፊቷን አለበሰው ። ይህን ስዕል አውጥቶ ለማየት ፣ ለመጨረስ ስትፈራ ነበር ። ይህን ለማድረግ ይኸውና ዓመት ከሰ ባት ወር ፈጀባት ። አሁን ግን ደፈረች ። እንዴ ደፍራዋለች ። ገና አላለቀምና ትጨርሰዋለች ። ለፒተር ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ አሥራ ሰባት

ቃኑ ጭጋጋማና እጅግ ቀዝቃዛ ነው ። ሜሪ ማለትም ናንሲ ማክአሊስተር ወደ ፌ አሊሰን ቢሮ ስትቃረብ የባርኔጣዋን ክፈፍ ቁልቁል ሳበች ። የደማቅ ቀይ ሱፍ ካፖርቷን ኮሌታም ሽቅብ ዘረጋች ፤ ፊቷንና አንገቷን እንዲሸፍንላት ። ፍሬድ ውሻዋ እንደ ሁልጊዜው ተከትሏታል ። ለፍሬድ የተጠለቀለት የአንገት ዘለበትና መሳቢያውም ልክ ሜሪ (ናንሲ) እንደለበሰችው ካፖርት ደማቅ ቀይ ናቸው ። አንገቷን ሰበር አድርጋ ውሻውን ቁልቁል እየተመለከተች ፈገግ አለች ። መንፈሷ በፌስታ ሰፍፏል ። ደስተኛ መንፈሷ ጭጋጉና ብርዱም ሊሸፍኑትና ሊያቀዘቅዙት አልቻሉም ። ወደ ፌ ቢሮ የሚወስደውን ደረጃ በሩጫ ከወጣችው በኋላ በሩን ከፍታ ገባች ። እና ፤—

«ቤቶች ! የላችሁም እንዴ ? መጥተናል» አለች ።

ከላላ ድምጿ በሞቃቱና ምቹው ቤት ውስጥ እስተጋባ ። ወዲያው ከሌላ ክፍል መልስ መጣ ። ሜሪ ካፖርቷን አወለቀች ። ከስር የለበሰችው ቀለል ያለ ወርቅማ ጌጥ ያለው ነጭ የሱፍ ቀሚስ ነበር ። ይህን የገዛላት ፒተር ነው ።

ከዚያም በከፊል ልብ ራስዋን በመስታወት ውስጥ ተመለከተች ። ባርኔጣዋን ወደ ጐን ዘንበል አደረገችና እንደገና አየችው ራስዋን ። ምስሏን ተመልክታ ፈገግ አለች ። ደስ አላት ። መነፅር ማድረግ አቁማለች ። ምክንያቱም አይኖችዋ ላይ የነበረው ፋሻ ተነስቷል ። ፊቷ በጠቅላላ ፋሻ አይታይበትም ። ጥቂት ፋሻዎች ብቻ እግንባርዋ ላይ ይታያሉ ። እሱም ካሁን በኋላ ብዙ ጊዜ አይቆይም ። አለቀ ። እድሜ ለዘመናዊ የሕክምና ጥበብ ሜሪ (ናንሲ) ጠባሳ አይታይባትም ። አዲስ ፊት ፣ አዲስ ሰው ፣ አዲስ ስም ፣ አዲስ ሕይወት ።



t.me/OLDBOOKSPDF

«ጌመስተዋቱ ውስጥ ባየሽው ነው እንዲህ የተደሰትሽው ናንሲ ?»

ይህን ድምፅ ስትሰማ ደንገጥ ብላ ዞር አለች ። ፌ አሊሰን ነበረች የተናገረችው ። ፌ ፍቅር በተሞላ ፈገግታዋ ጥያቄውን ደገመችላት ። ራሷን በአወንታ ነቀነቀች ሜሪ ። በቃልም፣—

«አዎ ። በሱ ነው የተደሰትኩት ብዬ እስባለሁ ። የሚገርምሽ በጠቅላላ የሆንኩትን እኔነቴን ሁሉ ለምጀዋለሁ ። አንች ግን አለመድሽልኝም » አለች ።

ፊቷ ላይ መቅየምና ቋጣ መሰል ነገር ይታይባት ነበር ።

«ምን ማለትሽ ነው ፣ እንዲያ ስትይ ?» አለች ፌ አሊሰን ።

«አለስሜ ትጠሪኛለሽ ሁሌ ። ሁሌ ናንሲ ነው እኮ እምትይኝ። ናንሲ አይደለሁም ። ነበርኩ ቀረ ። አሁን ሜሪ ነኝ ። በፍርድ ቤት ፀድቆ በሕግ ሊታወቅ ምንም ያልቀረው ስሜ ሜሪ አዳምስን ነው »

«ገባኝ ። ይቅርታ »

ፌ ይህን ብላ ሁልጊዜም ሁለቱ ሲገናኙ አረፍ ብለው ወደሚጫወቱበት ምቹ ወደሆነውና ቅልል ወደሚለው ክፍል አመራች።

«ይቅርታ ፣ ሁልጊዜም ናንሲ የሚለው ስም አፌ ላይ ደርሶ ጥልቅ ይላል » አለች ፌ አሊሰን ደግማ ።

«ሁልጊዜ» አለች ሜሪ እምትወደው ወንበር ላይ እየተቀመጠች ። ግን የተበሳጨች አትመስልም ። ትንሽ ካሰበች በኋላ «እንዲህ የለመደን ነገር ማስወገድ በጣም ከባድ ነገር ሳይሆን አይቀርም ። ይመስለኛል» አለች ሜሪ። ይህን የተናገረችው ፊቷን ቅጭም አድርጋ ነበረና ፌ አሊሰን ዝም አለች ። ከዚህ ጋር አያይዛ የምታመጣውን ነገር ለመስማት ።

«ይህን ነገር ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ነው የተረዳሁት ። ሳስብ ፣ ሳስብ ገባኝ ። ብዙ ጊዜ ላስወግደው ሰሞከር አሻፈረኝ ብሎ እቦታው ላይ ሲገኝ . . . ግን አሁን ሳላራግፈው የቀረሁ አይመስለኝም » አለች ሜሪ ።

«ማይክልን ማለትሽ ነው ?»



t.me/OLDBOOKSPDF

ሜሪ እንገቷን በአወንታ ነቀነቀች እንጂ ምንም አልተና ገረችም ።

«እንዳራገፍሽው እንዴት ልትገምቺ ቻልሽ ?» አለች ፈ ።

«ወሰንኩ ። ምርጫ ጠፋ ። ወሰንኩ ። ለምን ? በይኝ ። ምክን ያቱም ያ አደጋ ከደረሰብኝ ይኸው ሁለት ዓመት መሙላቱ ነው። ዓመት ከዘጠኝ ወር……ሁለቱ ዓመት በይው ። ይህን ያህል ጊዜ ስቀ መጥ ሊፈልገኝ አልሞከረም ። እንዳሰብኩት እናቱን ብትፈልጊ እንጦረጦስ ግቢ ብሏት ወደኔ አልመጣም ። ተወኝ ። ረሳኝ ። ስለ ዚህ እኔም ልተወው ፣ ልረሳው ይገባኛል ።

«መርሳት ፣ መርሳት ቀላል አይደለማ ! በልብሽ ውስጥ ለብዙ ጊዜ ያገነንሽው ሰው እንዲህ በቀላሉ ይረሳል ብለሽ ነው ? በልብሽ ያስቀመጥሽው ጊዜ ረጂም ነው እኮ »

«እጅግ በጣም ረጂም ። ያን ያህል ጠብቄውም እንዲህ አድ ርጐኝ ቀረ ። ጣለኝ ። ረሳኝ »

«ጣለኝ . . . ረሳኝ ስትይ ስለራስሽ ምንነት ምን ይሰማሻል ?»

«ስለኔ ምንም ዓይነት መጥፎ ስሜት የለኝም ። ያጠፋ እሱ ። ያናደደኝ እሱ ። እኔ ምን አጠፋሁ ? »

«ማለቴ ባለፈው ትንሽ ራስሽን ጠልተሽ ነበር ። ለምን ከማ ሪዮን ሂልያርድ ጋር ያን ስምምነት አደረግኩ ? ስትይ ነበር ። ያ ስሜት አሁን ፈጽሞ አይሰማሽም ? »

ፈ እጉል ቁስል እየዘነቆረች እንደሆነ ገብቷታል ። ቢሆንም አለባብሶ ቢያርሱ በአረም ይመለሱ ነውና መሸፋፈኑን አልወደ ደችውም ።

«ምርጫ . . . ምንም ምርጫ አልነበረኝም» አለች ሜሪ ።

« ኖረም አልኖረም ለምን እንዲህ አደረግኩ ብለሽ ራስሽን ወቅሰሽ አታውቂም ? »

«ለማን ብዬ ? ለምን ብዬ ? ማይክል ለምን አልጠየቅኳትም ብሎ በራሱ የሚናደድ ይመስልሻል ? ሳያስብልኝ በመቅረቱ የሀ ሊና ወቀሳ እንቅልፍ ይነሳዋል ብለሽ ታስቢያለሽ ? »

t.me/OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ አሥራ ስምንት

ሜሪ አዳምስን ከሬ አሊሰን ተሰናብታ እንደወጣች በቀጥታ ወደ ዩኒየን ስኩዌር አመራች፣ በታክሲ ። እዚያም የሄደች በት ምክንያት ቲኬት ለማስቆረጥ ነበር ። በጉዞው አስቀድማ ስላሰበችበት ከሁለት ሳምንት በፊት ቲኬት ለመቁረጥ ተመዝግባ ነበር ። ስለዚህም ችግር የለባትም ። ገንዘቡን ሰጥታ ቲኬት መቀበል ብቻ ነው ።

ሜሪ ስለጉዞው ስታስብ እጅግ ደስ አላት ። ለመዝናናት ካሰበችበት ቆይታለች ። ይህ ጉዞ የመጀመሪያዋ ባይሆንም ብዙ ጊዜ ያደረገችው አይደለም ። እንዴት ነው ይህን ዓይነት ጉዞ ያደረገችው ። ከሜሪ ጋር ። በበዓል ፋሲካ ። . . . ያው ሐሳብ ረበሻት ። ማይክልን ማሰብ የለባትም ። ሐሳቡን እንደምንም ታግላ መለሰችው ።

ዩኒየን ስኩዌር እንደደረሰች ወደ ቲኬት መሸጫው ቢሮ ገባች፣

«አስቀድመሽ እንዲያዝልሽ አድርገሽ ነበር ?» አለቻት የከፍሉ ሠራተኛ ።

«አዎ ። ካሥራ አምስት ቀን በፊት»

«ስምሽን ማን ልበል ?»

«ሜሪ አዳምስ . . . ኖ ናንሲ ማክአሊስተር» አለች ሜሪ ።

ናንሲ ማክአሊስተር የሚለውን ስም ስትሰማው እንግዳ ነገር ሆነባት ። ስሟን ወደ ሜሪ አዳምስን ቀይራ በዚሁ ስትጠራ ከሁለት ወር አለፍ ይላል ። አዲሱን ስሟን ለመልመድ ስትጣጣር የውትሮውን እየረሳችው እንደሆነ ተገነዘበች ። ቲኬት ለመቁረጥ በናንሲ ማክአሊስተር የተጠቀመችው በከንቱ አልነበ



t.me/OLDBOOKSPDF

ማሰን የባሌ ዳንስ እንድትማር ፈቅዶላታል ። ትማራለች ። ይህ ደግሞ በአካሏ ላይ ምን ያህል ለውጥ እንደሚያመጣ የታወቀ ነው ። የዮጋ ልምምድም ታደርጋለች ።

ይህች ናት የዛሬዋ ሜሪ አዳምሰን ፤ የወትሮዋ ናንሲ ማክ አሊስተር ። ተለወጥኩ ፣ አዲስ ሰው ሆንኩ አለች በሐሳቧ ። ገረ ማት ። ደርሶ ንዴት ተሰማት ።

እንጦሮጦስ ! አለች በልቧ ። ማይክል ረሳኝ ። እኔም ራሴ ኩጥቂት ጊዜ በኋላ እረሳዋለሁ አለች አሁንም ባሐሳቧ ።

«አንድ መቶ ዘጠና ስድስት ዶላር ይሆናል ክፍያው»አለች የቲኬት ቢሮ ሠራተኛዋ ፣ ሜሪን ከሐሳቧ እየመለሰችና ኮምፒ ውተሩን እየተመለከተች ።

ሜሪ ቼክ ጽፋ ስትሰጣት ልጅቷ አንዴ ኮምፒውተሩን አንዴ ሜሪን ትመለከት ጀመር ። ከዚያም ሜሪን ትኩር ፣ ፈገግ ብላ ተመለከተቻት ። ሜሪ አንድ ነገር አላት ። አንዴ ካየሃት ዓይን ህን ከሷ ላይ መንቀል ያስቸግርሃል ። ማናት ? ትላለህ ፣ ይህን የሚሉ ደግሞ ወንዶች ብቻ አልነበሩም ። ሴቶችም ቢሆኑ ያው ነው ።

ፍሬድን አቅፋ (መኪና እንዳይገጨው በመፍራት) ከቲኬት መሸጫው ቢሮ ወጥታ ጉዞዋን ቀጠለች ። አንድ በጣም ትልቅ ሱፐር ማርኬት ስታይ ወደዚያው ገባች ። ምን ለመግዛት እን ደምትፈልግ ግን አታውቀውም ነበር ። ለራሴ አንድ ስጦታ እገ ዛለሁ ። ወይም ለጉዞዬ የሚያስፈልገኝ ነገር ሊያጋጥመኝ ይች ላል አለች ።

በዚያ ግዙፍ ሱፐር ማርኬት ውስጥ ካንደኛው ፎቅ ወደ ሌላው ፣ ከልብስ ክፍል ወደ ጫማ ፣ ከዚያም ወደ ጌጣጌጥ ፣ ከዚያም ወደ ሌላው እየተዘዋወረች አንዱን ዕቃ አንስታ እየጣለች ሌላ ውን አንስታ እየመረመረች ወይም እየሞከረች ብዙ ጊዜ አሳለፈች ።



t.me/OLDBOOKSPDF

« አዎ ። ላንዲት ወጣት እመቤት ስጦታ ለመግዛት አስቤ የቱን እንደምገዛ መወሰን አቃተኝ »

« ምን ዓይነት ናት እመቤቲቱ ? »

« እሳት ! እሳተ ነበልባል ናት ። »

ሜሪ በቤን ሁኔታ ሳቀች ። ቤን ምን ጊዜም ቤን ነው ። መልሱ እጥርና ቀልድ የተሞላ ነው ። አሁንስ እንዴት ነው እመቤቲቱ ቋሚ ናቸው ? ልትለው አስባ ነበር ። ግን የማይ ሞከር ነገር ማሰቧ ወዲያው ገባት ።

« ጸጉሯ ቀያቴ ሲሆን ፣ ቁመቷ እንዲህ እንቺን ታህላለች » አለ ቤን ።

ይህን ብሎ ሜሪን ከላይ እስከታች በተጠሙ ዓይኖቹ ጠጣት። ይህን ሲያደርግ ስሜቷ ተደበላለቀባት ። ስለተመኛት ። እና ግን ፍንታቸውን ስታስብ መናደድ አማራት ። ስላላወቃትና ቤን ሴት ካየ መጎምዠት ልማዱ መሆኑን ስታስብ ልትስቅበት አማራት ።

« ግን ሻንጣ ፣ ቅራቅንቦ የሚያስፈልጋት መሆኑን ርግጠኛ ነህ » አለች ።

« ይመስለኛል ። ወደ አንድ ቦታ እንድንሄድ አስቤአለሁ ። ሳታስበው እንዲሆን ስለምፈልግ ፣ ቲኬቱን እሻንጣ ውስጥ ከትቼ ላስገርማት ብዬ ነው » አለ ።

አንድ ትኬት ደብቆ ለመስጠት አምስት መቶ ዶላር መክ ፈል ይገባል ቤን ? ቤን አብሪ እንዲህ ገንዘብ በታኝ ሆነ ? እል ፍለታል ማለት ነው ።

« ዕድለኛ እመቤት ናት በለኛ »

« ዕድለኛውማ እኔ ሳልሆን አልቀርም »

«እንዴት ? ለመጋባት አስባችኋል ማለት ነው ? »

«የለም ፣ ነገሩስ ሲሥራ ነው ። የሥራ ጉብኝት አለብን»



t.me/OLDBOOKSPDF

«ያኛው ፣ ቀይ ጥብጣብ ያለው ፤ ቡናማ ከፋይ ሻንጣ ቆንጆ መሰለኝ»

«እኔም እሱ ላይ ነው ዓይኔ ያረፈው»

የሜሪን ምርጫ ተቀብሎ የሱቁን ረዳት ጠራት ።

«አመሰግናለሁ ሚስ . . .» አለ ለልጅቷ የሚገዛውን ዕቃ ካሳያትና እንዲጠቀለልለት ከነገራት በኋላ ሜሪን እያየ ።

«አዳምሰን» ስትል ስሟን ነገረችው «ምንም ምስጋና አያስፈልግም ። ምክንያቱም እኔም ደስ ብሎኛል ። ይልቅ ትንሽ ጥያቄ ሳላበዛብህ አልቀረሁምና ይቅርታ መጠየቅ ያለብኝ እኔ ነኝ መሰል ። ዓመትባል ሲቃረብ ይኸው ነኝ ። የማይሆን የማይሆን ነገር አደርጋለሁ»

«እኔም ያው ነኝ ። ብቻ የዘንድሮው ዓመት ሲያልፍ ቢከፋኝም አይፈረድብኝም ። ደስ የሚል ዓመት ነበር ። ኒው ዮርክ እንኳ ሳይቀር»

«ኒው ዮርክ ነው እምትኖረው ?»

«ከመሄድ ስገላገል ፤ አዎ ። ግን ሥራዬ ቋጭ እሚያደርግ አይደለም ። ካንዱ ወዳንዱ መዞር ነው»

ይህም ቢሆን ከማይክል ጋር አብረው እንደሚሠሩ ርግጡን የሚናገር ነገር አይደለም ። ብትጠይቀው ደስ ባላት ። ግን አትችልም ። ይህን ስታስብ በጣም ከፋት ። አመማት ። ስለሌላ ፤ የሷ ስላልሆነ ሰው መጠየቅ ስላሰኛት አመማት ። መጠየቅና ማወቅ ስትችል ባለመቻሏም አመማት ።

«ነገሩ እንኳ የጅል ነገር እንደሆነ ይገባኛል ። ግን ከዚህ ወጣ ብለን እንዳንድ ነገር ይዘን ፤ መጠጥ ቢጤ ይዘን ብንጨዋወት ? ለነገሩ እቸኩላለሁ ። አውሮፕላኑ መያዝ አለብኝ ። ግን ቅዱስ ፍራንሲስ ሆቴል ጐራ ብለን . . . »

«እኔም ቢሆን በራሪ ነኝ ። ያም ሆኖ ሐሳቡ የድርጊቱን ያህል ነው ። አመሰግናለሁ ሚስተር አቨሪ . . .» አለች ።

ፊቱ ድንገት ቅጭም አለና ፤



t.me/OLDBOOKSPDF

«ሰሜን እንዴት ልታውቂ ቻልሽ ?» ሲል ጠየቃት ።

«ደረሰኝ ሲቆርጡልህ ስምህን ሲጠሩ ሰማሁ» አለች ።

አመላለሷ ፈጣን ነበረና በጥርጣሬው ሊገፋ አልቻለም ። ይልቁንም እንዲህ ቶሎ ተገናኝተው ፡ ቶሎ በመለያየታቸው አዘነ ። በጣም ቆንጆዩ ልጅ ናት ፣ አለ በሐሳቡ ። ዌንዲን እወዳታለሁ ። ቢሆንም ከእንዲት ቆንጆዩ ልጅ ጋር አንድ ነገር መጠጣት ኃጢአት አልነበረም ።

ድንገት አንድ ሀሳብ ብልጭ አለበት ፡—

«ወዴት ነው የምትሔጂው ፣ ሚስ አዳምሰን ? »

«ወደሳንታፌ ፣ ኒው ሜክሲኮ »

ተስፋ ቆረጠ ።

«ምን ዓይነት ርጉም እጣ ነው ። እኔ ደሞ ወደ ኒውዮርክ የምትሔጂ ቢሆን ስል »

«ሻንጣ የተገዛላት እመቤት አንድ ላይ ብታዩን እጅግ ደስ እንደምትሰኝ አይጠረጠርም ነበር ። »

«እጅ ሰጠሁ ። ደግ እንግዲህ አምላክ ካለ ሌላ ጊዜ . . . »

«ሳንፍራንሲስኮ ትመጣለህ እንዴ ፣ ብዙ ጊዜ ? »

«ከዚህ በፊት'ንኳ አልነበረም ። ወደፊት ግን አይቀርም እመጣለሁ ። ማለት እንመጣለን ። የምሠራበት ድርጅት አንድ ትልቅ ፕሮጀክት አለው» አለ ። « እዚሁ ሳንፍራንሲስኮ ማለቴ ነው ። ስለዚህ ወደፊት ከኒው ዮርክ ይልቅ ይኸ ሳይሆን አይቀርም መኖሪያዩ »

«እንዲያ ከሆነ ምናልባት እንገናኝ ይሆናል »

ይህን ያለችበት ድምፅ በመጠኑ መከፋትን የሚገልፅ ነበር ። ምንም አይደለም ። ከማይከል እንጂ ከቤን ጋር ቂም የለኝም ፡ ስለዚህ አዘውትረን ብንገናኝም ክፋት የለበትም ።

የሱቅ ረዳቷ እቃው መሰናዳቱን ገለጸችላቸው ። ቤን ጨብ ጣት ፣ ጠበቅ አድርጋ ጨበጠችው ። በመገረም ቀና ብሎ አያት ፡ በለሆሳስ ፣



t.me/OLDBOOKSPDF

« መልካም የገና በዓል » አለችና በፍጥነት ካጠገቡ ተሰወረች ። ወዲያ ወዲህ ተገላምጦ ቢያይም ሊያገኛት አይችልም ።

ከቤን እንደተለያዩ ሰውነቷ ድክምክም አለ ።

ከሱቅ እንደ ወጣች ታክሲ ተሳፍራ ወደ ቤቷ ጉዞ ቀጠለች። ከዚያ በፊት ግን ፍሬድን ለእንስሳት ህክምናና ጥበቃ ድርጅት በአደራ መልክ ሰጠችው ። ምክንያቱም አያስፈልጋትም ። ጉዞዋ አለና በዚያም ላይ በርከት ያለ ቦታ ማየትና ማዳረስ አለበባትና የፍሬድ መኖር አመቺ አልነበረም ። ብቻዋን መሔድ አለባት ። ናንሲ ማክአሊስተር በሚል ስም የዱር ሰብእናዋ የምትኖርባቸውን የመጨረሻ ሳምንታት ከማንም ጋር መካፈል የለባትም ። ምስክር መኖር የለበትም ። የአንድ ሕይወት መደምደሚያ ፤ የአዲስ ሕይወት መጀመሪያ ነውና ብቸኝነት ያስፈልጋታል።

እቤቷ እንደደረሰች ተዘዋውራ ተመለከተችው ። በሩን ስትዘጋ አንድ ሀረግ ተናገረች ። ለቤን አቨሪ ፣ ለማይክል ፣ ያውቋት ለነበሩ ፣ ይወዷት ለነበሩ ፣ ታውቃቸው ትወዳቸው ለነበሩ ሁሉ ፣ « ደህና ሁኑ » የሚል ሀረግ ተናገረች ። ደረጃውን ስትወርድ እንባ ተናነቃት ። ካሜራዋንና የዕቃ ሻንጣዋን ይዛ ነበር ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ አሥራ ዘጠኝ

እረፍቷን ጨርሳ ወደ ሳንፍራንሲስኮ ስትመለስ ፒተር አየር ማረፊያ ድረስ መጥቶ እንዳይቀበላት ቃል አስገባችው ። ምክንያቱም ያለሸኚ እንደወጣች ያለተቀባይ ልትገባ ስለፈለገች ነበር ።

ጉዞውን ስትጀምር ልቧን ከብ ደት መንፈሷም ተሸብሮ ነበር። ያንለት ቤን አብረን ማግኘቷ ወዳለፈው ሕይወቷ እየተመዘዘ በመመለስ ብዙ ነገሮችን እንድታስታውስ አስገደዳት ። በዚህም የተነሳ በመጀመሪያዎቹ እለታት ከማንም ጋር ለመነጋገር ፣ ማንንም ለማዳመጥ አልተቻላትም ። ከሀሳቧ ጋር ተፋጣ ነበር ።

ያ ጉዞ ግን አብነት ስለነበረው ከጭንቀቷ ፈወሳት ። የሰላም ጊዜ አሳለፈች ። እጅግ ብዙ ነገርም ሠራች ። ወደ ሳን ፍ/ራንሲስኮ ስትመለስ ፤ ከሳንፍ/ራንሲስኮ ስትነሳ የነበረው ጭንቀት አልነበረም ። አሁን ስለቤን አብሪ ማሰብ እያስፈራትም ። ያለፈውን ሕይወቷን መለስ ብላ ለመቃኘት አትፈራም ። ይህን ያህል በመለወጥ አዲስ ሰው ሆነች ። ለመጨረሻ ጊዜ ያለፈው ሕይወቷ የሌላ የምታውቃት ሴት ሆና ታያት ።

ናንሲ ማክአሊስተር ባዕድ ሆና እሷ ሜሪ አዳምስንን ሆነች።

ሜሪ የገናንም በአል ሆነ የዘመን መለወጫን በማታውቃቸው ሰዎች መካከል ሆና አሳለፈችው ። ሰዎች በእላትን ሲያከብሩ ናንሲ እነሱን ፎቶ ግራፎች አነሳቻቸው ። በተለይ የገናን በዓል በታሆስ አካባቢ ስታከብር የበረዶ ሸርተቴ የሚጫወቱት ብዙ ነበሩና ይህን ጫወታ ለመሞከር ልቧ እጅግ ገፋፍቷት ነበር። እንዲህ ያለውን አደጋ ላይ ሊጥል የሚችል ጨዋታ ላለመሞከር ለፒተር ቃል ገብታለት ነበርና እራሷም በመፍራት ፍላጎቷን መግታት ግድ ሆነባት ።

ፒተር የገባውን ቃል አክብሮ ሊቀበላት እንዳልመጣ ስትገነዘብ ደስ አላት ። እንዲህ በማያውቅህ ሠራዊት



t.me/OLDBOOKSPDF

« ከዛሬ ጀምሮ ባርኔጣ እሚሉት ነገር የማላደርግ መሆኔን በዚህ ድርጊት አስታውቃለሁ ። »

ይህን ተናግራ ኮፍያውን ጭምድድ አድርጋ እቆሻሻ መጣያው ውስጥ ከተተችው ።

« ፈጽሞም ባርኔጣ እንደማይነካሽ ርግጠኛ ነኝ » አለ ፒተር።

« ስሜቱን ስለተረዳህልኝም ስለሌላው ሁሉ ምሥጋናዬ የላቀ ነው » አለች ሜሪ ።

የተሰማት ግን ካለችው ሁሉ የላቀ ነበር ። ፒተርን እቅፍ አድርጋ ልትስመው ፈለገች ። አላደረገችውም ። ፍላጐቷን ግን ከጠቅላላ ገፅታዋ አነበበ ። ዓይኗን ከፒተር ላይ ሳትነቅል ተመለከተችው ። በጣም እንደናፈቃት ገባት ። ከዛሬ በኋላ ፒተር ጓደኛዋ እንጂ ሀኪሟ አይሆንም ። ከፈለገች ጓደኛዋ ፣ ከፈቀደ ችለት ሁሉን ነገር ይሆናል ። ፍቅረኛዬ ሁን ብትለው ደስ ይለዋል ። ባሌ ሁን ብትለውም እንደዚሁ ። ይህ ደግሞ ከንቱ አስተሳሰብ ወይም ግምት አልነበረም ። እንደሚያፈቅራት ብትፈቅድለትና ፍቅራቸውን ለመካፈል ቢችሉ ደስ እንደሚለው ደጋግሞ ገልጾላታል ። ግን እሷ ልቧን ትጠራጠረዋለች ። በይመስለኛል ስሜት ተገፋፍታ ሳይሆንላት ቢቀር ፒተርን ማስቀየም ይሆናል ። ይህንን ደግሞ ፈፅሞ አትፈልገውም ። ስለዚህ የፒተር ጥያቄ የእሺታም የእምቢታም መልስ ሳያገኝ በውዝፍ ዶሴ ተይዞ ቀርቷል ። መዋደዳቸው ፣ መተሳሰባቸው ፣ ጓደኝነታቸው ግን አሌ የሚባል ነገር አይደለም ።

« በጣም ናፍቀኸኝ ኖሯል ፒተር » አለች ሜሪ ።

ይህን ብላ ህክምና በሚደረግላት ጊዜ እምትቀመጥበት ወንበር ላይ ተቀምጣ ሥራውን እንዲቀጥል ዝግጁ ሆነች ። ዓይኗን ገር በብ አደረገች ።

ከወንበሩ ላይ ተነስቶ ትንሽ ከተመለከታት በኋላ ፦

« ዛሬ ደግሞ ለመታከም ጥድፊያ በጥድፊያ ሆነሻል »አላት ባትለመደው ብርጩማው ላይ ፊት ለፊቷ ተቀመጠ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

« ሁለት ዓመት ሙሉ በፋሻ ስትሸፈን ፣ ፋሻ ሲላጥልህ ብታሳልፍና የመጨረሻው ቀን ቢመጣ አንተ ራስህስ ብትሆን ያንለት ለመገላገል መቻኮልህ ይቀር ነበር ? »

«አይቀርም ፣ እንዲሁ ለማለት ያህል አልኩ እንጂ ነገሩስ ይገባኛል ።... በደንብ ይገባኛል የኔ መቤት»

እግንባሯ ላይ ያለውን ፋሻ ካነሳላት በኋላ ፤

«አሁን አይንሽን መግለጥና ፊትሽን በመስታወት ማየት ትችያለሽ ፤ ሜሪ» አለ ።

ሜሪ ግን ካለችበት ላይ ንቅንቅ አላለችም ። ብዙ ዓለም አይታ መጥታለች ። ሆኖም የአዲስ እሷን ፊት ሙሉውን አታውቀውም ። አንደኛው ጕን ቢገለጥ ሌላኛው ወይ በፋሻ ተሸፍኖ ወይ ፕላስተር ተለጥፎበት ወይም ተደርቶ ነበር የምታየው ።

«በያ ብድግ በይና ወደ መስታወቱ ቅረቢ» አለ ፒተር ።

ያን አዲስ ፊት ፣ ያን ናንሲ ማክአሊስተር የነበረችውን የቀድሞ እሷን ሳይሆን ፣ ሜሪ አዳምስን የተባለችውን አዲስ እሷን ለማየት ፍርሃት ተጫናት ።

ምን ያለ የማይረባ ፍርሃት ነው አለች በሐሳቧ ።

ፍርሃቷን አሸንፋ ተነሳች ። ፊቷን በመስታወቱ ውስጥ ስታይ ፊቷ በሳቅ ቧ ብሎ ተከፈተ ። በጉንጯ ላይ ግን እንባዋ ይጉርፍ ነበር ። ይህ የስሜት ግንፈላ ተገ እስኪልላት ድረስ አልተጠጋትም ። አላነገራትም ። ያ ጊዜ የግሷ የሆነ ማንም ሊጋፋት የማይገባ ጊዜ እንደሆነ በመገንዘብ ።

«ፒተር ፣ ኧረ የፈጣሪ ያለህ ! እንዴት ቆንጆ ነው » አለች ።

«አይ አንቺ ቂል ፍጡር» አለ ፒተር በለሆሳስ እየሳቀ «እንዴት ቆንጆ ነው ሳይሆን እንዴት ቆንጆ ነኝ በይ ... ያቺ እዎ ታያት ሌላ ሰው ወይ ሌላ ነገር አይደለችም ። አንቺ ነሽ «ራስሽ ነሽ»



t.me/OLDBOOKSPDF

ዞራ እየችው ። የተናገረው ትክክል እንደሆነ በቃላት መግ ለጽ አቃታት ። ራሷን በአዎንታ ነቀነቀች ። ልክ ነው ። ሙሉ በሙሉ ተቀይራለች ። ከምታውቀው መልኳ የቀረ ቅንጣት ምል ክት የለም ። አሁን ያላንዳች ማወላወል ሜሪ አዳምሰን ነኝ ስትል አመነች ፤

«ፒተር !...» አለች ውለታ በበዛበት ድምጽ ። ሄዳ ተጠ መጠመችበት ። ተቃቅፈው ብዙ ጊዜ ቆዩ ። በመጨረሻ ፊቷን ለማየት እስኪችል ድረስ በክንዶቿ ይዞ ራቅ አደረጋት ። ፊቷ በእ ንባ ርሷል ። በጣቶቹ ጠረገላት ።

«ፒተር ... አየህ እንባየ እንኳ ፊቴን አላሟሟውም !» አለች ።

«ያ ብቻ ሳይሆን በትንሽ በትንሹ ይሁን እንጂ ፀሐይም መሞቅ ትችያለሽ» አላት ። ከዚያ በኋላ ግን ዕድሜሽን በሙሉ የፈለግሽውን ነገር ማድረግ ትችያለሽ ። ደስ ያለሽን ብትሆኚ ምንም አደጋ አይኖርም ። በነገራችን ላይ ምን ለማድረግ ነው እቅድሽ ? »

ይህን ብላ እተሽከርካሪው ወንበር ላይ ተቀምጣ ፤ እግሯ ጉንጪን ነክቶ ከራሷ በላይ እስኪሆን ሽቅብ አንስታ ከወንበሩ ጋር መሽከርከር ጀመረች ።

«አምላኬ እስቲ ይኽን ምን ትለዋለህ ? ሴትዮዋ እቢሮዬ ውስጥ ገብታ እንደ አካሏ ቢጉድል ሰው ምን ይለኛል ፡ እበ ጀህ ፤ እንኳን—ይለኝ ይሆን ?»

«አትፍራ እኔ እንደሆነ ዛሬ የመጣው ቢመጣ ጥርሴ እረገፈ ፣ እግሬ ተሰበረ ... ካሣ ምናምን እንደማልል ይገባህ ። የማከብ ረው እንጂ የምጨቃጨቅበት ቀን አይደለም»

«እንዲያም ከሆነ መልካም ። ይህ ቀን ዓመት ባልሽ መሆ ኑን መስማቴ ደሞ በጣም ደስ አሰኝቶኛል »

ፒተር ብቻ ሳይሆን ፍሬድም (ውሻው) በሆነው ነገር ደስ ያለው ይመስላል ። ይዘላል ፤ ይቧርቃል ፤ ጭራውን ይቆላል ።



t.me/OLDBOOKSPDF

የተናገርኩት ስለገባው ነው አለች ውሻውን እያሰበች ። ከዚያም ጨብጠኝ እንደማለት እጅዋን እየዘረጋችለት ፣

«አላወክም ነበር ማለት ነው ጅሉ !. ይህን ዕለት ለማክ በር ለራሳችን ጢን ያለ የምሳ ግብዣ እናደርጋለን ፒተር» አለች ።

ስሙን ከጠራችው በኋላ ሙሉ በሙሉ እያየችው ፤

«ፒተር ውለታህን ልከፍልህ የምችል አይመስለኝም ። ግን ደግሞ እስከመቃብር ከልቤ አትጠፋም ። መቼም ቢሆን የትም ቢሆን አስታውስሃለሁ ። በበድን አካሌ ነፍስ የዘራህባት አንተ ነህ» አለች ።

«አ. አ. . . እኔ ሳልሆን ሌላ ሰው ነው» አለ ፒተር ። አዎ ማሪዮን ሂልያርድ ፣ የማይከል እናት ናት ፣ ይህ ሁሉ እንዲሆን ያደረገችው ። ግን ደግሞ ሜሪ ማሪዮንን ምን ያህል እንደ ምትጠላት ስለሚያውቅ ስሟን ሊጠራ አልፈለገም ። ሌላ ሰው ብሎ ጠራት ።

ቀጥሎም . . .

«እኔ . . . እኔ በበኩሌ ግን ሜሪ—ያደረግኩልሽን ሁሉ ስላ ደረኩልሽ ደስ ይለኛል ። ለወደፊቱም ላደ . . . ላደርግልሽ የም ትፈልጊውን ሁሉ ለማድረግ ዝግጁ ነኝ» አለ ።

«ነው ? . . . ቀልድ መስሎሃል ፣ አደል ? እንዲያውም ከዛሬ እንጀምራለን ፣ ዛሬ በስድስት ሰዓት ተኩል ተገናኝተን ምሳዬን እንድታጉርሰኝ እፈልጋለሁ ። እሺ ? »

«ደስ ይለኛል»

«የት እንገናኝ ? »

አንድ በቅርብ የተከፈተ ምግብ ቤት ጠቀሰላትና ታውቀው እንደሆነ ጠየቃት ።

«በሚገባ !» አለች ።

«ይስማማሻል ? »



t.me/OLDBOOKSPDF

«አሳምሮ ። እንዲያውም ካሁን ጀምሬ ወደዚያው አካባቢ ሄጄ ሰዓቱ እስኪደርስ ፎቶ ግራፍ ሳነሳ እቆያለሁ ። ዓይን የሚገባ ነገር ከተገኘ»

«አሁን የልቤን ምኞት ነገርሺኝ ። ገበያ ሄጄ አዲስ ልብስ ስመርጥ ወይም ሌላ ብትይኝ ኖሮ ይከፋኝ ነበር»

ተሰነባብተው ተለያዩ ፣ እስከምሳ ሰዓት ።

★ ★ ★

በምሳ ሰዓት ሲገናኙ ልብሷን ቀይራ ሽክ ብላ አገኛት ።

«በእውነት ይቺ ሴት አንቺው ራስሽ ነሽ ?»

«ባለወርቅ ጫማዋ ልዕልት እነሆኝ ። እንዴት ነው ፣ አም ሮብኛል ? »

«አምሮብኛል !? እንደ ቅዱሳን አንፀባርቀሻል እንጂ ፣ ምን ማማር ብቻ ! . . . እንደፈራሁት ፎቶ ግራፍ ማነሳሳቱን ትተሽ ቀሚስ መረጣ ላይ ዋልሽ ልበል ? »

«ምን ይደረግ ትላለህ ። ሳስበው ለካ ይህ ቀን የሚከበር ፣ ፌስታ የሚደረግበት እንጂ የሚሠራበት አይደለም»

ድንገት አቅፈህ ሳማት የሚል ሐሳብ መጣበት ፣ አምግብ ቤቱ ውስጥ ያ ሁሉ ሰው እያዩ ። ሐሳቡን ገታና እጅዋን ጥብቅ አድርጎ ያዛት ።

«ውዴ ይህን ያህል ደስ ብሎሽ ስላየሁ እኔንም እጅግ ደስ አለኝ» አለ ።

«ፒተር በጣም ደስ ብሎኛል ። የዛሬዋ ቀን ለኔ ልዩ ናት ። ስለገጽታዬ ብቻ አይምሰልህ ። የዛሬ ቀን . . . ነገ የፎቶግራፍ ትርኢት የማቀርብበት ፣ ኤግዚቢሽኔ የሚከፈትበት ቀንም ስለ ሆነ . . . አዲስ ሕይወት መጀመሬም ነው ። . . . አንተም አጠገቤ እንዳለህና ድንቅ እንደሆንክ ስለማውቅ»



t.me/OLDBOOKSPDF

«ያንተ መኖር ፡ የምትለዋ ነገር ልቡን አፈካችው ።

የሰማውን አምኖ መቀበል ከበደው ። በዛበት ። ስለዚህ እንዲህ ሲል ቀለል ሊያደርገው ሞከረ ።

«ይገርምሻል ። ኤግዚቢሽን ፣ አዲስ ሕይወት . . . ከዚያ ሁሉ ነገር በታች እኔ ! የእኔስ ይሁን ፍሬድሳ ምን ያህል ነው አስፈላጊነቱ ? »

ቀልድ ነበርና ሁለቱም ከልባቸው ይስቁ ጀመር ። የምግብ ቤቱ አሳላፊ መጥቶ ምን እንደሚጠጡ ሲጠይቃቸው ፤ ሁለት ዊስኪ እንዲያመጣ ፒተር አዘዘው ፣ ወዲያው ሀሳቡን ቀየረና ፣

«የለም ሻፓኝ አድርገው » አለ ።

«ሻፓኝ ?! » አለች ሜሪ ።

«ነዋ ! እለቱን በፌስታ እናሳልፈው ብለን የለምን ?! ለፌስታ ሻፓኝ ። በዚያ ላይ ከሰዓት በኋላ ለራሴ ፈቃድ ሰጥቻለሁ ። ሥራ አልገባም »

« እውነተኛ ፌስታ ሆነ በለኛ »

«መሆን አለበት ። . . . ምናልባት . . . ማለት አንቺ ሌላ ጉዳይ ከሌለሽ »

«የምን ሌላ ጉዳይ በል ?»

«ሥራ . . . ምናልባት »

«በዛሬው ቀን !?»

ጊዜውን አብረው አሳለፉ ። በዚያ የከረምት ወራት ባህር ዳር መዝናናት ያልተለመደ መሆኑ ፒተርን ቢያስገርመውም ይህን ሀሳብ ለሜሪ ሊገልጽላት ቢሞክርም ባቀረበችው ሀሳብ መሠረት ወደዚያው ሔደው ቆዩ ።

እዚያም እስከዚያ ሰዓት ደብቃ ያቆየችውን ስጦታ አበረከተችለት ። የፎቶ ግራፍ ስጦታ ። ፒተር እጅግ ተደሰተ ።

እሜሪ መኖሪያ አፓርትማ እንደደረሱ ፣



t.me/OLDBOOKSPDF

«ለጥቂት ጊዜ አብረን እንቆይ ተጋብዘኃል» አለች። «ማለቴ የተረኝ ስጦታ አለ ። ጊዜ ካለህ እንግባ »

« እውነትሽን ነው ? »

« አትጠራጠር »

እሳሎን እንደደረሱ የስዕል መሳያ አትሮኖሷን ገጽ ወደ ፒተር አዞረችና መብራት አበራች ። አየው ሥዕሉን ። ፆ እዛፍ ላይ የተንጠለጠለና በዛፉ ቅርንጫፍ በመጠኑም የተከለለው ልጅ ያለበት የገፀ ምድር ምስል ሥዕሏ ነበር ።

«ይህን ሥዕል ሳበረክትልህ ደስ ይለኛል ። . . . ከጀመር ኩት ረጅም ጊዜ አልፏል ። . . . የጨረስኩት ግን በቅርብ ነው ። . . . ልጨርሰው የቻልኩት ለአንተ ለመስጠት ስለወ ሰንኩ ነው ። »

«ይህን ያህል . . . ?» አለ እውነት ሊሆን አይችልም በሚል ድምፅ ። በአድናቆት ተመለከታት ፣ በፍቅር አያት ።

«የእም ይህ የማይሆን ነገር ነው» አለ ። « ብዙ ብዙ ነገር ሰጥተሺኛል ፡ ይበዛብኛል»

«ፒተር እስከ ዛሬ ፎቶ ግራፍ ብቻ ነው የሰጠሁህ ። ይኽ ኛው ይለያል ፤ ፒተር ። ይኽውም የዳግም ልደቴ ማብሰሪያ ነው ። ሌላ ሰው ከሆንኩ በኋላ ቡሩሽና ቀለም እጄን የነካው ይህን ሥዕል ለመጨረስ ስል ነው ። . . . ፒተር ይህ ሥዕል ለኔ ምን ያህል እንደነበር ልነግርህ አልችልም ። ስለዚህ ነው ለአንተ ልሰጥህ የወሰንኩት ፡ እባክህ ተቀበለኝ »

አይኗ እንባ አቆረዘዘ . . . ጠጋ አላትና አቀፋት

« እንዴት ደስ የሚል ቀን ነው ። እንዴት ዋጋ የማይተመ ንለት ስጦታ ነው ። ምን ብዬ ላመስግንሽ እንደምችል አላው ቅም ። ደግነትሽ እጅግ ከበደኝ »

«ምንም ነገር ማለት አይሻህ ። ዝም ብትልም ይገባኛል» አለች አውጭ የጨለማው ጥላ እየከበደ ሲሄድ ይታያት ነበር ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ ሃያ

«ውዴ . . . እስኪ ዚፔን ዝጋልኝ» ብላ ውብ ጀርባዋን አዞረችለት «እኔ እንኳ ደስ የሚለኝ . . . ብከፍተው ነበር»

«ፒተር ! . . . እንዲህ አለ ወሬ . . . ? ! » አለች በማስጠንቀቅ መልክ ተገላምጣ እያየችው ። ሁለቱም ሳቁ ።

አለባበሷን ሲመለከት ፣ ውበቷን ሲያይ በአድናቆት ተዋጠ ። «በኋላ ምን ብሎ ነበር ብለሽ ናቂኝ ! አንድ ሰው ፎቶግ ራፍሽን ቢያይ ከምላሴ ጠጉር »

« ለምን ? »

«የተመልካች ዓይን አንቺው ላይ ያርፋል ። እዚያ ተተክሎ ይቀራል ። በቃ !»

« ምን ያህል ? »

ይህን ስትል ያለውን ነገር ፈጽሞ እንዳላመነች ገባው ። ጥር ጣሬዋ የመገረም ሳቅ አሳቀው ። እሱም በኤግዚብሽን መክፈቻ ላይ ሽክ ብሎ ለብሷል ። ቢጋቡ የሚያስቀኑ ባልና ሚስት ይሆናሉ ።

«እንዴት ነው ? ፎቶ ግራፎቹን እንደምትፈልጊው አድር ገው ሰቀሉልሽ ? ጊዜው ጠፋና ይህን'ንኳ ልጠይቅሽ አልቻል ኩም »

«ምንም ችግር የለም ። ያዘዝኩት ሁሉ እንዳዘዝኩት ሆኖ ተፈጽሟል ። እድሜ ላንተ ፣ ፒተር ። ይኸኔ ቅር ይላትና ዋ ! ብለሁቸዋል ። ወይ አንተ ወይ ጃክ ይህን ያላችሁ ይመስለኛል »

ጃክ የኤግዚብሽኑ አዳራሽ ባለቤት ሲሆን የፒተር ግሬሰን የረጂም ጊዜ ጓደኛ ነው ።

« ሁሉን ነገር ሰው ይሰራዋል ። እኔ በቃ አርቲስት ብቻ ነኝ የሚል ስሜት ይሰማኝ ጀመር »

«ሊሰማሽ የሚገባ ነው ። ይህ ትርኢት ሲያልቅ የኪነጥበብ ስራሽ ምን ያህል ዋጋ እንዳለው ያኔ ታያለሽ ። »



t.me/OLDBOOKSPDF

እንዳለውም ሆነ ። ኤግዚብሽኑ በተከፈተ ማግስት በጋዜጦች ላይ የተሰጡ አስተያየቶች በአድናቆት የተሞሉ ነበሩ ። ፒተርና ሜሪ ጧት ቁርሳቸውን በልተው ቡና እየጠጡ ጋዜጦችን ሲያነቡ በጣም ደስ አላቸው ።

«አላልኩሽም ?» አላት ፒተር ፣ ገና የመጀመሪያውን በአድናቆት የተሞላ አስተያየት ሲያነብ « አየሽ ? ኮከብ ነሽኮ »

«አንተ ደሞ ጅል ነህ ! » አለችና ጋዜጣውን አስደገፈበት ጭኑ ላይ ዘጭ ብላ ተቀመጠችበት ። ጋዜጣው ተጨማደደ ።

«እስከሚቀጥለው ሳምንት ቆይና ደሞ ሌላ ተአምር ታያለሽ ። እያንዳንዱ ፎቶግራፍ እያራባ የሚሸጥ ድርጅትና ፎቶግራፍ አሻሻጭ ከመላ ሀገሪቱ ዳር እስከዳር ስልክ እየደወለ ባያስቸግርሽ ! ቱ ! ከምላሴ ፀጉር ! »

«በቃ አዕምሮህን እንደመንሳት እያደረገህ ነው ’ኮ ፣ ውዴ ! »

ሆኖም የፒተር ግምት ሜሪ የገመተችውን ያህል ከእውነት የራቀ አልነበረም ። በሚቀጥለው ሳምንት መጀመሪያ ላይ ከተለያዩ ቦታዎች ከተለያዩ ሰዎች የስልክ ጥሪዎች ይመጡ ጀመር ። ሰኞ ዕለት ከሎስ አንጀለስ እና ከችካጐ የተለያዩ ጥሪዎች ደረሷት ። እያንዳንዱ ሰው ስልክ ደውሎ የሚያቀርብላት ጥያቄና አድናቆት አስደነቃትም ። አስደሰታትም ። ስለዚህም ስልክ በተደወለ ቁጥር አሁን ደግሞ ምን ይሉ ይሆን ? በሚል ጉጉት ስልኩን ታነሣለች ። ይህ ቀጠለ ፣ ቤን አቬሪ እስኪደውልላት ድረስ ።

ቤን አቬሪ የደወለው አንድ ማክሰኞ ቀን ወደ ማታ አካባቢ ነበር ። በዚያም ሰዓት ሜሪ ፊልሞችን ለማሳደግና ለማጠብ በማሰናዳት ላይ ነበረች ። ከተለያዩ ቦታዎች ፎቶግራፎቿን ለመግዛት የትእዛዝ ጐርፍ መጉረፍ ጀምሮ ስለነበር ከፎቶግራፍ ማጠቢያው ክፍል (ዳርክ ሩም) ለመውጣት እንኳ ጊዜ አልነበራትም ። በሥራዋ ተመስጣ እያለች ስልኩ ተንጫረረ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ሥራዋን አቋርጣ እየተጣደፈች ወጣች ። ምክንያቱም ፒተር «በዚያ ሰዓት ስብሰባ ስላለብኝ ደውዬ የት እንደምንገናኝ እነግርሻለሁ» ብሏት ነበር ። ስልኩን አንሥታ ፡—

«ሃሎ » አለች ።

«ሚስ አዳምሰን» አለ አንድ የማታውቀው ድምጽ ፡

«ነኝ» አለች ፒተር ስለመሰላት በገጽታዋ ላይ ፈክቶ የነበረው ፈገግታ ዋ እየጨለመ ።

« እ . . ከዚህ በፊት ለገና በዓል የስጦታ ዕቃዎችን ስገዛ ሚስ አዳምሰን ከምትባል ሰው ጋር ተዋውቀን ነበር ። ከሞከሺሽ ጋር ይሁን ካንቺ ጋር እርግጠኛ አይደለሁም ። የጉዞ ሻንጣዎች ስገዛ ተገናኝተን . . . » ቤን ነው ማለት ነው ። አይደለሁም ልበለው ? ለምን ?

« ከኔ ጋር ሳይሆን አልቀረም » አለች—

መዋሸት የሚያስፈልግ አልመሰላትም ።

«ማለቴ . . . እኔ . . ነው ? ማለት የማውቃት ሚስ አዳምሰን ነሻ ? »

« ነ ኝ »

« ይህንን ማረጋገጡም አንድ ነገር ነው ። ማለት ተቀራርበን ለመነጋገር ባንችልም እንተዋወቃለን ። ብቻ አሁን የደወ ልኩልሽ እንኳ የያኔ ትውውቃችንን በሚመለከት አይደለም ። የፎቶግራፍሽን ኤግዚብሽን ስላየሁ አንዳንድ ነገር እንድንነ ጋገር ስለፈለኩ ነው ። . . . ግሩም የሆነ ሥራ ነው ሚስ አዳምሰን ። እኔም ጓደኛዬ ሚስ ታውንሴንድም ኤግዚብሽኑን ዓይተን የተሰማን ስሜት ከፍተኛ ነው »

የጠራት ሴት ዕቃው የተገዛላት ሴት ትሆን ? የማወቅ ፍላጉት አደረባት ። ሆኖም መጠየቅና ማወቁ አስፈላጊ መስሎ አልተሰማትም ። ስለዚህም በረጂሙ ተንፍሳ ፡—



t.me/OLDBOOKSPDF

«ደስ ስለተሰኘችሁ እኔም ደስ ብሎኛል ፤ ሚስተር አቨሪ» አለች ።

« ስሜንም አልረሳሽም ? »

«ስሞችና የመሳሰሉ ነገሮችን አልረሳም ። አንድ ዓይነት እንነዚህን ነገሮች የማያስረሳ ተፈጥሮ አለኝ »

«መታደል ነው ። እኔ ደሞ የስም ነገር አይሳካልኝም ። ይኸ ደሞ ለሥራዬ ጥሩ ነገር አይደለም ። አንጐሌ ወንፊት ቢጤ ሆኖ ሲፈጠር ገ.ዜ ምን ማድረግ ይቻለኛል ! ወደ ፍሬ ነገሩ ልመለስና ተገናኝተን ስለሥራዎችሽ ብንነጋገር በጣም ደስ ይለ ኝ ነበር ። »

« በምን መንገድ ? » አለች ። ምን የሚያነጋግረን ነገር ተፈጠረ ደግሞ ! አለች በሐሳቧ ።

«እንዲህ ነው ሚስ አዳምሰን ። እዚህ ሳንፍራንሲስኮ ውስጥ አንድ የሕክምና ማዕከል ሕንፃ በመሥራት ላይ እንገኛለን ። በጣም ግዙፍ የሆነ ፕሮጀክት ነው ። ፕሮጀክቱን ስንቀበል ከገባናቸው ውሎች አንዱ ሕንፃውን እስከማስዋብ ያለውን ሥራ ፈጽመን ማስረከብ እንዳለብን ይገልጻል ።ያንችን ፎቶ ግራፎች ስመለከት ለዚህ ተግባር በጣም ሊያገለግሉን እንደሚ ችሉ ተረድቻለሁ ። እንዴት አድርገን በምን ሁኔታ እንደምን ጠቀምባቸው ግልጽ የሆነልን ነገር የለም ። ስለዚህም ተገናኝ ተን ይህንን ጥምር ብንወያይበት ደህና ገቢም ይኖረዋል ። ላን ቺም ቢሆን ሥራሽን ያስተዋውቅልሻል» አለ ቤን ። ይህን ሲና ገር በሙሉ ልቡ እንደነበረ ድምጹ ይናገራል ።

«ገባኝ ። . . . ግን የትኛውን ድርጅት ወክለህ እንዳነጋገር ከኝ ልትነግረኝ ትፈቅዳለህ ? » አለች ። ድርጅቱ ማን ሊሆን እንደሚችል ስለጠረጠረች ፤ ከላይ ከላይ ሊላት ያሰበውን ትን ፋሿን ቁጥር አድርጋ መጠባበቅ ጀመረች ።



t.me/OLDBOOKSPDF

«ድርጅቱ» አለ ቤን ኮራ ብሎ «የኒውዮርኩ ኮተር ሂልያርድ ነው »

«ነው ? . . . ስላሰብክልኝ አመሰግናለሁ ፣ ሚስተር አቭሪ ። ግን አይሆነኝም »

«አይሆነኝም ? ለምን ?» አለ የመደመም በሆነ ድምጽ «የምትይው አልገባኝም ?»

«በዚህ በዚህ ምክንያት ልልህ አልፈልግም ሚስተር አቭሪ ። ፍላጐቴ እንዳልሆነ ብቻ ብትረዳልኝ ይበቃል»

«ተገናኝተን ልንነጋገር ብንችል ደግ ይመስለኛል ። ማለቴ በነገሩ ላይ»

«ምንም ንግግር አያስፈልግም»

«ግን . . . እዩው ይህን ነገር አስቀድሜ ነግሬአለሁ . . . ሊ.. ሊ. . . እኔ . . . »

«ምንም ብትለኝ መልሴ አንድ ነው ። አይቻልም ። አመሰግናለሁ ፣ ደህና ሁን ሚስተር አቭሪ»

ይህን ብላ የስልኩን መነጋገሪያ በቀስታ ወደ ቦታው መለሰችው ። ሥራዋን ለመቀጠል ፊልም ማዘጋጃውና ፎቶግራፍ ማጠቢያው ጨለማ ክፍል ስትሄድ ፣ የለም ለዚህ ድርጅትስ አልሠራም — ለማይክል ሂልያርድ አገልግሎት ለመስጠት ! ምን በወጣኝ አለች ። ሚስቱ ልትሆኚ አትበቂም ብሎ አይደለም የተዋት ። እሷም ቀጣሪዬ ልትሆን ብቁነት አላይብህም ፣ ምኔም ምኔም ለመሆን ብቁ አይደለህም ። ልትለው ያስፈልጋል—ይህን አሰበች ።

የጨለማውን ክፍል በር ከፍታ ገብታ መልሳ ልትዘጋው ስትል ስልኩ የጥሪ ድምጽ አሰማ ። ቤን አቭሪ መሆን አለበት እንደገና የደወለው።ተናደደችና በሩን በርግዳ ወጥታ ወደ ስልኩ ሄደች ። መነጋገሪያውን መንጭቃ ካነሳች በኋላ ፣

«አይሆንም ማለት አይሆንም ነው ! መልሴ አንድ ነው ። ይኸን ደግሞ ቁርጥ ባለ ቃል ነግሬሃለሁ» ስትል ጮኸች ።



t.me/OLDBOOKSPDF

« የፈጣሪ ያለህ ! ምነው ምን አጠፋሁ ?» አለ ለስላሳውና ልቧን የሚያበራው የፒተር ድምጽ ።

የፒተርን ከፊል ሳቅ ያፈነው ፣ ከፊል ድንጋጤ የበረዘው ድምጽ ስትሰማ ንዶቷ ባንዴ ቀዘቀዘ ። አዕምሮዋም ርጋታን ተላበሰ ።

«ፒተር ! አስደነገጥኩህ አይል ? ይቅርታ ። አንድ ሰው ስልክ ደውሎ የማይሆን የማይሆን ነገር ነግሮኝ አይሆንም ብዬው ነበር ። እሱ መልሶ የደወለ መስሎኝኮ ነው»

«የፎቶ ግራፍ ትርኢቱን በሚመለከት ነው ?»

«አዎ ወይዚያው ነው»

«የአዳራሹ አስተዳደር የስልክ ቁጥርሽን ለማንም መስጠት አልነበረበትም ። መልዕክት ተቀብለው ላንቺ መንገር ነበረባቸው ። ያለዚያ የማንም ቦዘኔ እየተነሳ ያልሆነ ነገር ሊያደርግ ይችላል» ።

የተበሳጨ መስሎ ተሰማት ።

«ግን ደህና ነሽ አይደለም ? »

«ደህና ነኝ»

ይህን ስትል መረበሿን በድምጿ ስለተረዳ ደህና ነኝ ያለችውን አላመነም ።

«ደግ መጣሁ ፣ ከአንድ ሰዓት በማይበልጥ ጊዜ ውስጥ እደርሳለሁ ። እስከዚያ ድረስ ማንም ቢደውል ስልክ ማንሳት የለም ። ከዚያ በኋላ የሚደውለውን ሰው እኔ እንደሚሆን አደርገዋለሁ»

ሌሎች የንግግር ልውውጦች ካደረጉ በኋላ ስልኩን ዘጋች ። ግን እንደደወለና ምን እንዳበሳጫት ለፒተር አለመንገሯን ስታስበው ጥፋት እንደሠራች ተሰማት ። ፒተር ያሰበው ቦዘኔ ፣ ቀውስ እንዳስቸገራት ነው ። ቤን አቭሪ ግን ሁለቱንም አይደለም ። የሱ ጥፋት ፣ የወረወራትና የናቃት የማይከል ሂልያርድ ሠራተኛ መሆኑ ብቻ ነው ። በሌላ በኩል ደግሞ ይህን ጉዳይ ለፒ



t.me/OLDBOOKSPDF

ተር መንገርም ጥሩ እንዳልሆነ ገመተች ። የለም ጥሩ አይደለም አለች በሐሳቧ ። ይህን ጉዳይ ብትነግረው ፒተር ይበልጥ ይጨነቃል ።

የማይከል ነገር እስካሁን ከልቡናዋ አልወጣም ። በጣም ጠልቶ በመግባቱም እስከመቼም ላይወጣላት ይችላል ብሎ እን ዲያስብ ያደርገዋል ። ጥቅም የሌለውም ብላ ተወችው ። ያን ዕለት ቤን አብረ ደግሞ አልደወለም ። ይህም ተመስገን የሚያሰኝ ነበር ። ፒተር መጥቶ ከሱ ጋር ስትጨዋወት ችግሩም ፣ መሸበ ሩም ቀስ በቀስ ከሜሪ አዕምሮ እየደበዘዘና እየጠፋ ሄደ። ግን አልቀጠለም — በማግስቱ ጠዋት ቤን አብሪ ደግሞ ደወለ ።

«ሃይ ሚስ አዳምስን ። ቤን አብሪ ነኝ»

«ስማ ! ትናንት ማታ ሁሉን ነገር ተነጋግረን የጨረስን መሰ ለኝ ። ይሆንሻል ያልከው ሥራ አይሆነኝም፤አይስማማኝም አል ኩሁ ። በቃ»

«ግራ የገባኝኮ አልፈልግም አልሽ እንጂ ምን እንደማት ፈልጊ እንኳ ያወቅሽ አይመስለኝም ። ከእኔና ከጓደኛዬ ጋር ምሳ እየበላን ለምን አንነጋገርም ! አይተሸኛል ሰው ነኝ ። አል በላሽ ! መነጋገር ደግሞ ምንም ጉዳት የለውም ። ወይስ መነ ጋገሩም ሊጎዳ ይችል ይሆን ?»

ይችላል ቤን ! በጣም ሊጎዳ ይችላል ! አንተ አጠገብ መሆን ብዙ የተደበቀ ትዝታ ጉትቶ ያመጣል— በሐሳቧ ።

«አስቀድሜ ይቅርታ እጠይቃለሁ ። ግን አይመቸኝም ። ሥራ ይበዛብኛል» አለች ።

ሌላ መንገድ ቢሞክር ፍንክች ሳትል ቀረች ። ትስፋ የሌ ለው ነገር ነው በሚል መንገድ ዓይኑን አፍጦ እያንከባለለ ቂንዲ ታውንሴንድን ተመለከታት ። ኮተር ሂልያርድ ትልቅ ድር ጅት ነው ። እንደ ሜሪ ያለች ሰውን ለማስቀየም አይችልም ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ይኸ ግን በቀጥታ ከድርጅቱ ጋር ጠብ ያላት ይመስላል። ምን በደል ደረሰባት ኮተር ሂልያርድን ለምን ጠላችው ፣

«ነገስ አይመችሽም ? »

«ስማ . . . ቤን . . . ሚስተር አብሬ መቼም አይመቸኝም ። ፍላጐቱም የለኝም ። ፍላጐቱ ከሌለኝ ምንም የምንነጋገርበት ነገር የለም ። አሁን ነገሬ ግልጽ ነው ? »

«የምሥራች የሚባልለት አይደለም 'ንጂ ግልጽስ ነው» አለ ።

ጸጥታ !

«ግን» አለ ቤን «ግን ትልቅ የሙያ ስህተት የሠራሽ ይመስለኛል ። ጉዳይ አስፈጻሚ ወይም ወኪል ካለሽ ብታማክሪው ይህን እኔ የነገርኩሽን ነገር ደግሞ ይነግርሻል»

«ነበር ። ግን ወኪል ወይም ነገረ ፈጅ የለኝም ። ስለዚህም አይለኝም ። ወኪል የማያስፈልገኝ ደግሞ ከራሴ ሌላ ማንንም መስማት ስለሌለብኝ ነው»

«ከስህተቶችሽ አንዱ ይህ አስተሳሰብ መሆን አለበት በነገር ባንራራቅ ደግ ነው»

«ስላሰብክልኝ አመሰግናለሁ ። ምክንያቱም ለሌላ ሰው ማሰብ ቅንነት ነው ። ግን እንድትቸገር አያሻም ። እና እንደገና ባንደዋወል ይመረጣል»



t.me/OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ ሃያ አንድ

ቤን አብሪ ከምድር ውስጥ ባቡር ጣቢያ ወጥቶ በፓርክ አቬንዩ ወደሚገኘው ቢሮው የሚወስደውን መንገድ በእግሩ ሲፈጭ የፌብሩዋሪን (የካቲት) ቅዝቃዜ በመፍራት ኤሲ እድንጋ ዩዋ ውስጥ ተሰብስባ እንደምትገባ እሱ ደግሞ እካፖርቱ ውስጥ ለመደበቅ እንገቱ ትከሻውን እስኪነካ በመሰብሰብ ነበር ። ዝናብ ሲጥል አጓጉቶ እንደመጣ ከአየሩ ሁኔታ ተረዳ ፣ ገና ለሁለት ሰዓት ጥቂት ደቂቃ ጉዳይ ቢሆንም ቸኩሏል ። የሥራ መግቢያ ሰዓት ማለትም ሦስት እስኪሞላ ሊጠብቅ አይችልም ። ብዙ ሥራ ይጠብቀዋል ። ከሳንፍራንሲስኮ የተመለሰው ትናንት ሲሆን ከኩተር—ሂልያርድ ሥራ አስኪያጅ ከማሪዮን ሂልያርድ ጋር አራት ሰዓት ላይ ስብሰባ እንደሚኖረው ተነግሮታል ። መልካም ነገር ይዞላት እንደሚቀርብም ይተማመናል ።

በመሥሪያ ቤቱ ማረፊያ ክፍል ውስጥ ብዙ ሰዎች ተሰብ ስበዋል ። አሳንሰሮችም ጥቅጥቅ እያሉ በመሙላት ሰዎችን ወደ እየቢሮአቸው ማጓጓዝ ቀጥለዋል ። ገና ጥዋት ቢሆንም የንግድ ሥራው ዓለም መተራመሱን ጀምሯል ። ሕይወት ሬጋ ብላ በምትፈስበት ሳንፍራንሲስኮ ቆይቶ የንግድ ዓቢይ ፈለግ ወደ ሆነችው ኒው ዮርክ ሲመለስ የዚችን ከተማ ትርምስ ለሚያው ቃት ቤን አብሪ እንኳ አስደንጋጭ ሆነበት ።

የሱ ቢሮ ከሚገኝበት ፎቅ ደርሶ ሲመለከት ቀድሞት የገ ባና ሥራ የጀመረ ሰው አልነበረም ። ቢሮው ምንም እንኳ የማ ይክል ሂልያርድን ቢሮ ያህል የሰፋና እንደ ማይክል ቢሮም በልዩ ምርጫ የተሰናዳ ዕቃ ባይኖረውም ምቹና ያሸበረቀም ነው። ግርጥን ሂልያድርድ ለኩተር ሂልያርድ ቢሮዎች ምቾትን ለመ ስጠት በወጭው ላይ ወደኋላ የማትል ሥራ አስኪያጅ ናት ።



t.me/OLDBOOKSPDF

« ልልህ የፈለኩትን ነገር ገና ልትረዳልኝ አልቻልክም ይሆን በሥላሴ ? »

እነዚህ በቁጣ የጠነከሩ ቃላት ከፍሊጋው መለሱት ። ወደ አሁን አመጡት ። ከሜሪ አዳምሰን ጋር በመነጋገር ላይ እን ደሚገኝ አስታውሰው ። እውነቱን እንዲያይ ፣ ይህቺ ሜሪእንኳ ማንም እንዳይደለች እንዲረዳ አደረጉት ።

«አዝናለሁ ሚስ አዳምሰን ። ጥፋተኛ መሆኔ በደንብ ይገ ባኛል ። ሆኖም ተስፋ ያደረግኩት »

«ተስፋ ዝባንዝንኬ !—ነገርኩህ'ኮ አልፈልግም አልኩህ ፣ በዚህ ነገር ላይ ለመነጋገር ይህን ነገር አውጥቶ አውርዶ ለማ ሰብ ወይም ለኔ ምኔም ስላልሆነው የሳንፍራንሲስኮ የሕክምና ማዕከል አንዲት ቃል ለመነጋገር አልፈልግም ። በሥላሴ ይገር ሃለሁ ፣ ተወኝ » ይህቺ ተናግራ እጀሮው ላይ ደረገመችበት ። የተዘጋውን ስልክ ማነጋገሪያ በእጁ ይዞ የድል ፈገግታ ፈገገ ። ከዚያም ፣

«ይኸው አፈንዳሁትና አረፍኩ ወንድሞቼ» አለ ።

ቤን ይህን የተናገረው ለራሱ ነበር ። በሐሳብ ስለተዋጠ የቢሮውን በር ከፍቶ መቃኑን በሚዝናናት ደገፍ ብሎ የቆመው ማይክልን አላየውም ።

«እንኳን ደህና መጣህ ። ለመሆኑ ምንድነው ያፈነዳኸው ?»

ማይክ ይህን ጥያቄ የጠየቀው ይህን ያህል ለማወቅ በመ ጓጓት አልነበረም ። የጓደኛው መመለስ እንዳስደሰተው ብቻ ነበር ገጽታው የሚገልጸው ። በፊቱ ላይ ደስታው እንደጎላ ወደ ቤን ቢሮ ገብቶ በምቹው የእንግዳ መቀበያ ሶፋ ላይ ቁጭ አለ ።

«ከጉዞህ ተመልሰህ ሳይህ ደስ አለኝ»

«መመለሱስ አይከፋም ነበር ። ግን ምን ዋጋ አለው ? የሳ ንፍራንሲስኮን አየር ተለማምደህ መጥተህ የኒውዮርክን ብርድ በፍጹም ሰውነትህ አይቀበለውም»



t.me/OLDBOOKSPDF

«ለስላሳው ፍጡር ሆይ ካሁን ጀምሮ ከሞቃታማዎቹ የደቡባዊ ክፍሎች እንዳትወጣ የተቻለንን ያህል እንሞክራለን» አለ በጸሎት ድምጽ ። ከዚያ ቀጠል አድርጐ «የስልኩ ጭቅጭቅ ስለ ምን ነበር ?» ሲል ጠየቀው ።

«እሱን አታንሳው ። በዚህ የሥራ ጉብኝት ውስጥ እሾር ባዬ ውስጥ ያጋጠመኝ አንድና አስቸጋሪ የሆነ ፀጉር ! » አለ ። «ማለት ሁሉ ነገር እንደከረከሙት ሁሉ እየተስተካከለ ሲመጣ . . . እን ዳሰብነው ፡ እንደፈለግነው ሲሆን . . . ርግጠኛ ነኝ ሪፖርቱ ሲቀርብ እናትህ ተፍነክንካም አታበቃ . . . አንድ ነገር ግን አሻፈረኝ አለ። ርግጥ ነው ፤ አልሳካ ያለው ነገር ይህን ያህል ትልቅ ችግር የሚባል አይደለም ። የኔ ሃሳብ ግን ሙሉ ስኬትን ለመፍጠር ነበር ።»

«እንዴት ነው ፤ ነገሩ ምን ይሆን እያልኩ መጨነቅ ልጀምር ወይስ ?»

«አያስፈልግም ። ተሸወድኩ ልበልህ . . . እንዴት መሰለህ አንዲት አርቲስት አጋጠመችኝ። ፎቶ ግራፍ አንሺ ናት ። ማለቴ ግዙፍ ችሎታ ያላት ፍጡር . . . ማይክ እንዲህ ተራ ነገር እንዳ ትመስልህ ። ኤግዚቢሽን ታሳይ ነበር ። ኤግዚቢሽኑን ተመለከት ኩት ። ባለፈው ጊዜ በሕንፃ ማስጌጡ ሥራ ላይ ፎቶግራፎችን መጠቀም እንደሚቻል ሰብሰባ ላይ የተስማማንበትን አስታወ ስኩ ። ልቀጥራት ፈለግኩ »

« እሺ ? »

« ነገርኳት »

« መልስዋ ? »

«አንገቴ ይቆረጣልንጂ ያንተን ስራ አልነካውም አለችኝ ። እንነጋገርበት አልኳት ። አይሞከርም አለች »

«ምን ምክንያት ሰጠችህ ?—የኪነጥበብ ስራዎን ለገንዘብና ለንግድ አላውልም ነው ወይስ ሌላ ? »

«ምኑም ምኑ ሊገባኝ አልቻለም። ገና ነገሩን ሀ ብዬ ሳነሳ ጅራቷን ሸጉጣ ወደ ኋላ ማፈግፈግ ጀመረች።ሊታስጠጋኝ አልቻለችም»



t.me/OLDBOOKSPDF

እውነቱ እውነት ነው ። ዌንዲና ቤን ይፋቀራሉ ። ስራቸው አንድ ላይ በመሆኑም አንድ ላይ ይጓዛሉ ። ባለፉት ወራት በሳንፍራን ሲስኮና በሎስ አንጀለስ ሲሰሩ ባልና ሚስት ሆነው ነው ያሳለፉት ። እንዲያውም ቤን የጫጉላ ቤታችንን ጊዜ በማሳለፍ ላይ እንገኛለን እያለ ሲቀልድባት ነበር ።

« አልመለስክልኝምኮ » አለ ማይክል ።

ቢን አብረ ከሃሳቡ ብትት ብሎ ነቃ ።

«አስቀድሜ ባለመንገሬ ጅልነቴ ተሰማኝ ። መልሱ ግን ፣ አዎ ነው ። ቅር ይልሃል ማይክ ? »

ምኑ ነው ቅር የሚለኝ ? እንዲያው የኔ ነገር ገርሞኝ ነው ንጂ ምን ያህል ማየት እንደማልችል ማለት አዎ . . .

«ምን ዓይነት እንክብካቤ አደርግላት እንደነበር ዌንዲ ሳት ነግርህ አልቀረችም . . . »

ስለዌንዲ ሲናገር ድምጹ ትንሽ መረር ያለ ነበር ። ቢሆንም ቤን እንዲህ ሲል በለሆሳስ መሊሰለት ፤

« የለም ማይክ ። ዌንዲ ስላንተ ምንም ነገር ነግራኝ አታውቅም ። ካነሳችህም ደስታ የሌለህ ሰው እንደሆንክ ከመናገር አልፋ ሌላ አትጨምር ። በነገራችን ላይ የሆነው ነገር በሁለታችን መሀል ምንም ነገር ሊፈጥር አይችልም ብዬ አምናለሁ ። አይመስልህምንዴ ? »

ማይክ በአዎንታ ራሱን ነቀነቀ ።

«እንዴት መሰለህ ? » አለ ቤን «በላይህ ላይ አልተደረብኩም ፣ እዚህ ላይ እንድታምንልኝ ያስፈልጋል ። እንዲያውም የጀመርነው ካንተ ጋር መውጣት ካቋረጣችሁ ከስንትና ስንት ጊዜ በኋላ ነበር ። በነገራችን ላይ ዌንዲን ገና ካንተ ጋር ግንኙነት ሳይፈጠር ጀምሮ ልቤ ይከጅላት ነበር ። »



t.me/OLDBOOKSPDF

« በቂ ያህል የተዘጋጀሁ ይመስለኛል »

« ደህና »

«በነገራችን ላይ ለሜሪ አዳምሰን ለፎቶግራፍ እንሺቀ ደውየላት ነበር »

« ምን አለች ? »

« ሰውዬ ባትጨቀጭቀኝ ምናለ ! አለችኝ »

« የሚገርም ነገር ነው »

★ ★ ★

በስብሰባዋ ላይ ማሪዮን ሂልያርድ ከየክፍሉና ከየፕሮጀክቶቹ የመጡትን ሠራተኞች ተራ በተራ እንዲናገሩ የክፍሉን ወይም የፕሮጀክቱን ስም እየጠራች ትጠይቅ ጀመር ። የተከናወኑ ስራ ዎች ባለፈው ስብሰባ ላይ የቀረቡ ችግሮችና የተሰጣቸው መፍ ትሔ ባሁኑ የሥራ ክንዋኔ ላይ ያጋጠሙ ችግሮች ሁሉም ለስብ ሰባው ፡ ይልቁንም ለማሪዮ ከቀረቡ በኋላ በቂ መመሪያዎችና መፍ ትሔዎች ተሰጡ ።

የሳንፍራንሲስኮ የህክምና ማዕከል ፕሮጀክትን በሚመለከት ቤን አብሪና ዌንዲ እየተቀባበሉና እየተረዳዱ ራፖራቸውን አቀ ረቡ ። ራፖሩን አቅርበው እንደጨረሱ የማሪዮን ፊት በደስታ ፈካ ። በተለይም የዚህ የሳንፍራንሲስኮ ፕሮጀክት ዋና ኃላፊ ልጅዋ ማይክል ሂልያርድ በመሆኑ በዚያ ስብሰባ ላይ ከቀረቡት የሥራ አፈፃጸም ሪፖርቶች ሁሉ ይህ የሳንፍራንሲስኮው ፕሮጀ ክት ከፍተኛ ክንዋኔ እንዳደረገ ስለተረዳችና ይህም ማይክል ሂል ያርድ ጠንካራ ሠራተኛና የሥራ መሪ መሆኑን ስላስገነዘባት የማር ዮን ደስታ ጣጥፍ ድርብ ነበር ። ምክንያቱም ይህ ኮተር ሂሊያርድ የተባለ ድርጅት ዞሮ ዞሮ በማይክል እጅ መግባቱ አይቀ ርም ። የኮተር ሂልያርድን ዋና ሥራ አስኪያጅነት ዙፋን ከመው ረስ የሚተናነስ አይደለም ። የኮተር ሂልያርድ ግዝፈት ደግሞ በእድል የተገነባ ወይም ድንገት የሆነ ሳይሆን በጠንካራ ሰዎች



t.me/OLDBOOKSPDF

የሌት ተቀን ጥረት ፣ ግረትና ብርታት የተጉኘ ነው ። ማሪዮን ኮተር ሂልያርድን ለማስተዳደር ምን ያህል ኃይልና ፈቃደኛነት ፣ መስ ዋእትነት እንደሚያስፈልግ ታውቃለች ። ማይክል ስራውን በሚ ገባ ሲያከናውን የተደሰተችውም ያን ጠንካራ ሰው ወልዳ ኮት ኩታ አሳድጋ ስታየው ያሰበችው ሁሉ እንደሚሳካላት ስላወ ቀች ነው ።

«ሁሉ በወግ በወጉ ሲከናወን አንድ ትንሽ ነገር ብቻ ረበ ሸኝ» አለ ቤን አብሪ ።

በማሪዮን የገረጣ ፊት ከንብል ብሎ የነበረው ቅላት ቀነሰ፡ዶም የመሰለው ጉንጯ ወደ ቀድሞ መልኩ ተመለሰ ። ይህን ሲያዩ በዜያ ክፍል ውስጥ የተሰበሰቡ ሁሉ ትንፋሻቸው መለስ አለ ። በተለ ይም የቤን አብሪ ። ስለሰአሊዋ ነገራት ።

«ይኸን ያህል ታስፈልገናለች ? »

«በኔ ግምት በጣም ታስፈልገናለች ለናሙና ካነሳቻቸው ጥቂት ፎቶግራፎች ይገፎ መጥቻለሁ ። »

«አላነጋገርህም አለችኝ እያልክ አልነበረም ? ታዲያ ፎቶ ግራፎቹን እንዴት ልትሰጥህ ቻለች ? »

«እሷ ሰጥታኝ ሳይሆን ከትርኢት አዳራሽ ገዝቼ ነው ። የወ ጣው ገንዘብ በትክክል የወጣ ይመስለኛል ። ሆኖም ድርጅቱ ገንዘቡ የወጣበት ምክንያት በቂ አይደለም የሚል ከሆነ ገንዘቡን ከፍየ ፎቶግራፎቹን የግል ለማድረግ ፈቃደኛ ነኝ »

«እስኪ እንያቸው »

ዌንዲ ፎቶግራፎቹዋን አመጣች ፣ ፎቶግራፎቹ ታዩ ።

በጭብጥም በጊዜና በቦታ አመራረጥም የተዋጡ ነበሩ ። በፎ ቶግራፎቹ ላይ ዝብርቅርቅ ነገር አልነበረም ። ሌላ ሰው ቢያነሳ ቸው ወይ ጊዜውን ስላልጠበቀ ወይ በቦታው ላይ የሰፈሩ ነገሮች ተስማሚ ባለመሆናቸው የተነሳ ሊበላሽ ይችል ነበር ይሆን ? የሚ ያሰኙ ፎቶግራፎች ነበሩ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ማሪዮን ፍቶ ግራፎቹን በጥሞና ከተመለከተች በኋላ ቀና ብላ ቤንን ተመለከተችው ። ቤን ዝም አለ ። ቆይታ !

«እንዳልከው እንደምንም ልናግባባትና ልናሰራት ይገባል» አለች ።

«ስለተስማማን ደስ አለኝ» አለ ቤን ።

«ማይክ ? » አለች ማሪዮን ሂልያርድ «ምን ይመስልሃል ? »

ማይክል ፎቶግራፎቹን ሲመለከት አንድ ዓይነት ስሜት ተሰማው ። የሚያስደነግጥ ። ወደ ኋላ የሚመልስ ስሜት ። የት እንዳየሁት እንጃ ግን አውቀዋለሁ የሚያሰኝ ስሜት በውስጡ ይመላለስ ጀምር ። ልቡን ቁልቁል ሳበው ። ጭብጣቸው ነው ? ወይስ የሚነሳውን ነገር አመራረጥ ? ምኑን ነው የሚያውቀው ? ይህን ጥያቄ ሊመልስ ፈለገ ። ግን አልቻለም ። ፎቶግራፎቹን አትኩሮ በተመለከተ ቁጥር አእምሮው ላይ ሚዛና እየወደቀበት ሄደ። ፎቶ ግራፎቹ ጥበባዊ ኃይል እንዳላቸውም ተገነዘበ ። ስለዚህም ፣

«በጣም ድንቅ የጥበብ ሥራዎች ናቸው » አለ ።

«እኔ ግሩም የጥበብ ሥራዎች ናቸው ብያለሁ ። ያን ያህል ትልቅ ናቸው ነው እምትለኝ ? » አለች ማሪዮን ፍርጥ አድርጎ እንዲነግራት እየገፋፋችው ። በቃላት ሳይሆን አንገቱን በአ ምንታ ፅሙና በመነቅነቅ መለሰላት ።

«ታዲያ ይችን ሴት በምን ሁኔታ ነው የኛ ልናደርጋት የምንችለው ? » አለች ማሪዮን ፤ «ቤን ምን ይመስልሃል ? »

«የዚህን ጥያቄ መልስ ባውቀው እንዴት ደስ ባለኝ ነበር» አለ ቤን ።

«ግንዘብ ነው መንገዱ ። ይህ ግልፅ የሆነ ነገር ነው» አለች ማሪዮን ። ለመሆኑ ሁኔታዋ እንደምንድነው ? ተገናኝታችሁ አይተ ሃታል ? ። »

«አይቻታለሁ ። ግለት ይኸ ሁሉ ነገር ሳይሆን የገና በአል ከመዋሉ በፊት አንዳንድ የስጦታ እቃዎችን ስገዛ ድንገት ተገ ናኝተን ተነጋግረናል ። በጣም ቆንጆ ናት ። ግለት ቆንጆናኖ እን



t.me/OLDBOOKSPDF

ሳምንት ሳንፍራንሲስኮ መሄድሽ አስፈላጊ አይደለም ። እኔ ልሂ
ድና ጉዳዩን ልፈፅም እችላለሁ ። እዚህ እዋናው መሥሪያ ቤት
ቁጭ ብለሽ ይህን ያን አድርጉ ብትይን ልንረዳሽ እንችላለን ።
በቃ ፣ ይህን ያህል እሺ በይኝ »

ሳቀች እንጂ ሌላ መልስ አልሰጠችውም ። ከዚያም ብድግ
ብላ ወደ መደበኛ የቢሮ መቀመጫዋ ሄደችና ተቀመጠች ።
ስጋዋ እንደደከመ ይታያል ። መንፈሲ ግን ወደ ዱሮ ቦታው
ተመልሷል ። ሁሉንም ካየች በኋላ ፣

«አሁን በከንፈር መጠጣና በአዘንልሽ አትጫኑኝ ። ሁላ
ችሁም ማለቴ ነው ። ሂዱልኝ ። እናንተ ሥራ ከሌላችሁ—እንዲያ
ይመስለኛል ሳያችሁ—እኔ ሥራ አለብኝ ፤ ልሥራበት»

«ኢማዩ ፣ ቤት አድርሼሽ ልምጣ።እስኪ አንዳንድ ቀን ሰው
የሚልሽን እሺ በይ ! » አለ ማይክል ቆጣና ኮረፍ ብሎ ።

«ማይክል የማይቻል ነገር አታውራ ። አሁን ቀጥ ብለህ
ወደ ሥራህ ሂድ ። ያለዚያ ጆርጅን እየገፈተርክ አስወጣልኝ
እንዳልለው»

ጆርጅ ፈገግ አለ—የነገሩ መታሰብ አስገርሞት ።

«ባይሆን ሰዓት ደረሰ አልደረሰ ሳልል ለመሄድ እሞክራ
ለሁ እንጂ አሁን አይሆንም ። በተረፈ ስለመልካም አስተሳሰብ
ህና ስለሌላው ^እመሰግናለሁ ። በቃ ። ሩት ያን በር ክፈች»

ጸሐፊዋ በሩን ከፍታ እንዲወጡ መጠባበቅ ጀመረች ።
ማይክልና ቤን ወጡ ። ጆርጅ እደረጃው ላይ ቆሞ ፤

«ማሪዮን» አለ ።

«እሀ»

«ወደ ቤት መሄድ አለብሽኮ »

«ትንሽ ቆየት ብዬ»



t.me/OLDBOOKSPDF

«ደግ ፡ ከግማሽ ሰዓት በኋላ እመለሳለሁ»

ወጣ ።

ፈገግ አለች ። ሆኖም ወደራሷ ሀሳብ ስትመለስ ገና በሩ አልተዘጋም ።

የዛሬው ህልሟ የተነሳበት ምክንያት በሚገባ ታውቃታል ፡ ስለዚህ አንድ ነገር ማድረግ አለባት ። በሌላው ሌላ ምክንያት እየተነሳ እረፍት አሳጥቷታል ሀመሙ ። ሌላ መንሻ ሲጨመር ዝም ብላ ማየት አትችልም ። ለምን እንደሆነ አይገባት እንጂ ቤን አብሬ ስለሜሪ አዳምስን ሲናገር ሜሪ ማን እንደሆነች አውቃለች ። በርግጥ ናንሲ ማክአሊስተር ናት ብላለች ። ቅድም አስብሰባው ላይ በግልጥ እንደተናገረችው ወደ ሳንፍራንሲስኮ ስትሄድ ሜሪን ለማየትም ፤ ለማነጋገርም ወስናለች ። ግን ታውቃት ይሆን? ምናልባት የተደረገባት የቀዶ ጥገና ህክምና (ፕላስቲክ ሰርጀሪ) ፈጽሞ ለውጧት ሊሆን ይችላል ። ያስ ባይሆን ናንሲን በሚገባ ታስታውሳታለች እንዴ ? አይታወቅም ። ቤን አብሬ የሰጣትን የሜሪ አዳምስን አድራሻ አውጥታ ስልክ ደወለች ። ስልኩ ሶስቴ ይሁን አራቴ ሲጮህ ተሰማት ። ተነሳ ። ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት አቅሏን ስታ ወድቃ የነበረችው ማሪዮን ሂልያርድ መሆኗን ማንም ሊያምን በማይችልበት ደረጃ ረጋ ባለና ስልጣን በተሞላበት ድምጽ ፤

«ሚስ አዳምስን ። ማሪዮን ሂልያርድ ነኝ ፤ ከኒውዮርክ» ስትል ተናገረች ።

ንግግራቸው በጣም አጭር ፤ ቀዝቃዛና በመደነጋገር የተሞላ ነበር ። ማሪዮን ሂልያርድ ስለሜሪ አዳምስን በተጨማሪ ያገኘችው እውቀትም አልነበረም ። ይሁን ። ልክ የዛሬ ሶስት ሳምንት ማወቅ የሚገባትን ሁሉ ታውቃለች ። ሊገናኙ ተቀጣጥረዋል ። ማሪዮን ቀጠሮውን አጀንዳዋ ላይ ከሰፈረች በኋላ



t.me/OLDBOOKSPDF

የወንበሯን መከዳ ደገፍ ብላ ወደ ኋላዋ ተለጠጠች ። አይኖቿ ዋን ዘጋች ።

ከሚሪ አዳምሰን ጋር ከተገናኙም በኋላ ምንም ጠቃሚ ነገር ላታገኝ ትችላለች ። ሁሉም እንዳሰበችው ላይሆን ይችላል ። ወይም ሚሪ ምንም ነገር ላለመናገር ትወስን ይሆናል . . . ሆኖም ያን ቀን ትፈልገዋለች ። ልትናገራቸው ያውጠነጠነቻቸው ጥቂት ነገሮች አሉ ። ብቻ . . . ብቻ ከዚያ ወዲህ ከፋ ነገር እንዳያጋጥ ማት ። ትልቁ ምኞቷ ይህ ብቻ ነው ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ ሃያ ሁለት

ሶስት ሣምንት ሲደርስ አጭር ጊዜ ነው፣ ሲያስቡት ይር ዘም እንጂ ። የማሪዮን ሂልያርድና የሜሪ አዳምስን ቀጠሮ ደረሰ።

ከሶስት ሣምንት በኋላ እለተ ሰሉስ ።

ማሪዮን ሂልያርድ ፊይርሞንት በተባለው ሆቴል በተከራ የችው የልዩ ማዕረግ ማረፊያዋ ሳሎን ውስጥ ተቀምጣለች ። እዚያ ክፍል ውስጥ አረፍ ብሎ ወደ ውጭ ለተመለከተ ሰው ድንቅ የሆነው ወደብና ከዚያ አልፎ የሚገኘው የማሪን ካው ንቲ ውበት በእጅጉ ያስደምመዋል ። ከሌላ ሀሳብም ያወጣዋል ። ማሪዮን ሂልያርድ ግን ይህን ትእይንት ለማየት ፍላጎት አል ነበራትም ። ስለዚያች ልጅ በማሰብ ላይ ነበረች ። ምን ሆና ይሆን? ምን ትመስል ይሆን? ግሬግሰን (ፒተር) ከሁለት ዓመት በፊት ታምር አሳይሻለሁ ብሎ እንደፎከረ ተሳክቶለት ታምር ሰርቶ ይሆን? ቤን አብሪ ሜሪ አዳምስንን ሲያያት የሚያውቃት ሴት እንዳልሆነችበት ግልፅ ነው—ማይክልም ቢያያት አያስታ ውሳትም ይሆን? እሷስ እንዴት ነው ይሆን የምትኖረው? ከሌላ ወንድ ጋር ፍቅር ይዞአት ይሆን ወይስ እንደማይክል ሁሉን ነገር ትታ አንገቷን ደፍታ ውስጧ እየበገነ መኖር ቀጥላ ይሆን? ማሪዮን ሂልያርድ የቀጠሮው ሰዓት እስኪደርስ ስለ ናንሲ ማክ አሊስተር ስታስብ ልጅዋ በመሀል ገባ ። እሱም ፍቅር ያውቅ ነበር ። አፍቅሮ ነበር ። እንዲያውም አሁን እምትጠብቀው ማይ ክል ሂልያርድ በጣም ይወዳት የነበረችዋን ልጅ ነው ። ግን . . . እሷ ባትሆንስ? ካልሆነች . . . ካልሆነች ምንም ለውጥ አያመ ጣም ። እሷ ካልሆነች አንዲት የዚሁ አካባቢ ተወላጅ የሆነች ፎቶግራፍ አንሺ ናት ማለት ነው፣ ቤን አብሪ አይኑን የጣለ ባት ፎቶግራፍ አንሺ ። በቃ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

«ሚስ አዳምስን ! » ስትል ። ያየቻት ልጅ ከዚያችኛዋ ፊልም የተለየች ሆና አገኘቻት ። ድንገት ደስ ሲላት ተሰማት ።

«ሚስዝ ሂልያርድ?» አለች ሜሪ ። ትጠይቃት እንጂ በሚገባ አውቃታለች ። በርግጥ በአይኗ አይታት አታውቅም ። እሆስፒታሉ ውስጥ ስታነጋግራትም አይኗ በፋሻ ተጠቅልሎ ነበር ። አላየቻትም ። ግን ፎቶግራፉዋን አይታለች—እማይክል ቤት ። ከዚያ ወዲህም ሺ ጊዜ በህልሟ እየመጣች አስፈራርታታለች ። ማሪዮን ሂልያርድ ለሜሪ አዳምስን ቅዠት ነች ። እለም ዳርቻ ብታገኛትም አታጣትም ።

«እንደምን አለሽ?» አለች ማሪዮን ፤ እጅዋን ለሰላምታ እየዘረጋች ። እንደሚሆን እንደሚሆነው ሰላምታ ተለዋወጡ ።

«ወደ ውስጥ እንግባ» አለች ማሪዮን ።

«እሺ አመሰግናለሁ» አለች ሜሪ ።

ሜሪ በሕይወቷ ብዙ ለውጥ ያመጣችውንና በአይኑ ስጋ አይታት የማታውቀውን አዲስ ሰው ያደረገቻትን ሴትዮ ሁኔታ ለመገንዘብ ፤ ሁለቱም በየመንገዳቸው ፤ እንዳቸው የሌላውን ልብ ዘልቆ ለመመልከት ይጠናኑ ጀመር ።

ማሪዮን ይህች የምታያት ሴት ከዚያች በፎቶግራፍ ከምታውቃት ናንሲ ጋር ምንም አይነት የመልክ መመሳሰል እንደሌላት ተገነዘበች ። ለስላሳ መጠጦችንና ሻይ ልትጋብዛት ስትዘጋጅ ሁሉ ያን ያህል ገንዘብ ላወጣችላት ሰው ተጨማሪ ግብዣ ማድረጉ አስፈላጊ እንዳልሆነ ለልቧ ነገረችው ። ቢሆንም መንጋገር ያስፈልጋል ። መልኳ ቢለወጥ ድምጽዋ አይለወጥም ። ያንን የመጨረሻውን እለት ስቃይ የተሞላ የናንሲ ማክአሊስተር ድምፅ እንዲህ በቀላሉ አትረሳውም ።

«ምን ትጠጪያለሽ» አለች ማሪዮን ።

«ስለግብዣው እግዜር ይስጥልኝ ። ግን ደግሞ . . . ምንም ነገር» አለችና አቋረጠች ። ሴትየዋ ትኩር ብላ ስታያት ፤ ሜሪም



t.me/OLDBOOKSPDF

ሲትዮዋን ትኩር ብላ ስታይያት የተፈጠረው የአይን ግጭት ንግግሯን እንድታቋርጥ አስገደዳት ።

ማሪዮን የልጅቷን ውበት ፣ የለበሰችውን ልብስ ውድነት እየተመለከተች ለሕይወቷ ያስፈልጋል ተብሎ የቆረጥኩላትን ገንዘብ በልብስ ብቻ እያባከነችው ይሆን ? ስትል አሰበች ።

የልብሶችዋን ውድ መሆን ፣ ለሳንፍራንሲስኮ የአየር ጠባይ የለበሰችው ካፖርት በጣም ሞቃት ሊሆን እንደሚችልና ኒውዮርክን ታውቅ እንደሆነ ይራርባ ጠየቀቻት ።

ጥያቄው ቢበዛባትም ፣ ሜሪ የመጨረሻውን ጥያቄ ለመመለስ አሰበች ። እውነተኛውን ነገር ብትነግራት በወደደች ። ሆኖም አያስፈልግም ። ስለዚህም ፣

«ኒውዮርክን ብዙም አላውቀው ። እንዲያውም ትልቅ ከተማ ኗሪ አይደለሁም » አለች ሜሪ ።

«እኔ ሳይሽ ደሞ ትልቅ ከተማ ያገኙ ግዛት ሆና ነው የተሰማኝ» አለች ማሪዮን ።

በዚህ ሁኔታ ብዙ ተነጋገሩ ። ቀስ እያሉ ፣ እያዘገሙ ። ከብዙ ማዝገም በኋላ ማሪዮን ንግግራቸውን ወደፈሩ መምራት ጀመረች ።

«ቤን አብሬ ኮንትራት ሊሰጥሽ የፈለገው በከንቱ እንዳልሆነ ገባኝ ። ይህ እጅግ ውብ የሆነ የጥበብ ሥራ ነው ። በዚህ ሥራ ላይ ብዙ ቆይተሽበታል?» አለች ማሪዮን ፣ አስተድመው በተነጋገሩት መሰረት ናንሲ መርጣ ያመጣቻቸውን ፎቶግራፎች እየተመለከተች ።

«የፎቶ ግራፍ ሥራ ለኔ እንግዳ ነው ። ከዚህ በፊት ስእሊ ነበርኩ »

«አዎ ፣ አሁን ትዝ አለኝ ። ቤን አብሬ ነግሮኝ ነበር ። »

ማሪዮን ይህን ብላ ፎቶግራፎቹን ትመለከት ጀመር ። ለረጅም ጊዜ በፎቶግራፎቹ ውበት ተውጣ ቆየች ። ከዚያም አይኗን ሳትነቅል ፣



t.me/OLDBOOKSPDF

ልጥ ግልፅ ያደርገዋል ነገሩን ። እሱ ነው ያስተዋወቀኝ ። በዚች ከተማ ውስጥ የማያውቀው ሰው የለም »

«ፒተር ግሬሰን» አለች ማሪዮን በለሆሳስ ። ማሪዮን የራሷን ድምፅ የሰማችው እንደ ህልም ነበር ። ልትናገር አላሰበችም ፣ እንዲያ ብላ ።

ሜሪ ይህን ስትሰማ ደነገጠች ። . . . ማን ነገራት ? እንዴት ልታውቅ ቻለች ? ምናልባት ፒተር ? . . . የለም እሱ አያደርገውም ።

«ትተዋወቃላችሁ ? » አለች ሜሪ ።

«ምን . . . ከኔ ጋር ? አዎ» አለች ማሪዮን ።

ሁሉቱም ፀጥ አሉ ፡ ረጂም ለመሰለ ጊዜ ። በመጨረሻ ፡-

«እንተዋወቃለን ፡ ናንሲ ። ፒተርን አውቀዋለሁ ። ላንቺ ያደረገልሽ ህክምናም እጅግ የሚደነቅ ነው» አለች ማሪዮን ።

«ትንሽ ስሁትት ሳይፈጠር አልቀረም መሰለኝ ። እኔ ናንሲ ሳልሆን ሜሪ . . . »

ንግግሯን አልጨረሰችም ። ጉልበቷ ተሟጦ ሲወጣ ተሰማት። ባዶ ሆነች ። አጥንት አልባ የሆነች ይመስል ተልፈሰፈሰች ። እንባ አነቃት ። እንደምንም ብላ ተነሳች ። ወደ መስኮቱ ሄዳ ጀርባዋን ለማሪዮን ሰጥታ ቆመች ። እና -

«ማን . . . እንዴት ልታውቂኝ ቻልሽ ? » አለች ። የተሰበረ ድምፅ ነበር ። ማሪዮን ርግጠኛ ሆነች ። የዛሬ ሁለት አመት የሰማችው የናንሲ ማክአሊስተር ድምፅ ብቅ አለ ።

«ማን ነገረሽ ? » አለች ሜሪ ደግማ ፡ በሚያስገድድ ድምፅ ።

«ማንም አልነገረኝም ። ገመትኩ ። ግምቱ ለምን እንደመጣብኝም አላውቅም ። ሆኖም ገመትኩ ። ገና ቤን ስለሁኔታሽ ማገለፅ ሲጀምር እሷ ናት? የሚል ጥያቄ መጣብኝ ። የነገረን ነገር ሁሉ ስለአንቺ ከማውቀው ጋር ሙሉ በሙሉ ሲመሳሰል ጊዜ ነው መሰል »

«እንዲያ ከሆነ . . . » አለችና ዝም አለች



t.me/OLDBOOKSPDF

ንሽ አልሻረም ፣ ምንም ነገር አልተረሳሽም ። ወይስ የተሻለ መንገድ መርጠሻል? ብዬ እጠይቅሽ ነበር ። ሆኖም መብት ያለኝ አይመስለኝም ።»

«ልክ ነሽ ። ያን ጥያቄ ለማቅረብ ምንም መብት የለሽም ። ማይከል ሚስት አገባ ወይስ ?»

«አግብቷል» አለች ማሪዮን ።

ሜሪ ክው ብላ ደነገጠች ። ኡኡ ! ብላ ለመጮህ ፈለገች ። ድምጹን አፍና አስቀረችው ። ያ ድምፅ ከጉሮሮዋ ሳይወጣ ሟሟ።

«አዎን ፣ ሜሪ ። አግብቷል ። ሥራውን አግብቶ ትዳር መስርቷል ። የሚበላው የሚጠጣው የሚተኛው እሥራው ላይ ሆኗል። ትንፋሹ ሳይቀር ሥራው ሆኗል ።» ሜሪ ትንፋሽዋ መለስ አለ ።

«ከሥራው ላይ ንቅንቅ አይልም ። በሥራው ውስጥ ሰምጦ ዘለአለም አለሙን ሊያሳልፍ የፈለገ እስኪመስል ። አብረን እን ኖራለን ይባላል እንጂ መልኩን የማየው ከዝንተ አለም አንድ ጊዜ ነው»

የት አባሽ አንች ውሻ ! እንኳን ! አለች ሜሪ በሀሳቧ ።

«እንዲያ ካልሽ ፣ ስህተት መስራትሽን ተገንዝበሻል ማለት ነው ። ማለት በአለም ላይ ካለው ሀብትና ማንኛውም ድንቅ ነገር አብልጪ እወደው እንደነበር ታውቂያለሽ ?»

ይህን ብላ ስታበቃ በኃሳቧ ከዚሀ ፊቴ በስተቀር . . . ከፊቴ በስተቀር ! እምላኬ ምናልኩህ «በስተቀር» እንድል አደረግከኝ?

«አውቃለሁ ። አውቅ ነበር ። ግን ፍቅር ነውና ያልፋል ብዬ ገምትኩ»

«ሆን ? ግምቱ ትክክል ነበር ? ረሳኝ ?»

«እንጃ ። ምናልባት አልፎለት ይሆናል ። ስምሽን አንስቶ አያውቅም ፣ መቼም»

«በመጀመሪያ ወይም መቼም ቢሆን የት እንዳለሁ ለማወቅ ሙከራ አድርጎ ነበር ?»



t.me/OLDBOOKSPDF

ማሪዮን በአሉታ ራሷን እየነቀነቀች-

«አልሞከረም» አለች ።

ይህን ትበላት እንጂ ለማይክል ናንሲ ሞታለች እንዳለችው አልነገረቻትም ።

«ያ ከሆነ ታዲያ ለምን ጠራሽኝ ? እኔን የማየት ጉጉትሽ እንዲረካ ? . . . ፎቶግራፎች እንዳሳይሽ? . . . ለምን ? »

«እኔም ለምን እንደፈለግኩሽ አላውቅም ፣ ናንሲ ። ይቅርታ . . . ሜሪ ። ቅድም እንደነገርኩሽ ነው ። አላውቀውም ። . . . በግድ እዘኑልኝ ማለት ፣ ወይም ሆደባሻነት ይመስላል እንጂ ደጎና አይደለሁም ። መሞቻዬ ሩቅ አይደለም ። እመቃብሬ አፋፍ ላይ የቆምኩ ይመስለኛል»

ማሪዮን ይህን ብላ ወደ ሜሪ አዳምሰን ዞረች ። ያኔም ሜሪን ማሪዮን ሞቷ ስለቀረበ ምን ያህል እንዳዘነች አየች ። ሜሪን ስትመለከት ማሪዮን ለምን ነገርኳት? የሚል ብስጭት ገባት ። በዚያም አለ በዚህ ሜሪ ለማሪዮን ቅንጣት ያህል ሀዘን አልተ ሰማትም ። ማሪዮንን ለረጅም ጊዜ ትኩር ብላ ስትመለከት ከቆ የች በኋላ ፣

«እንዲህ ያለውን ነገር በመስማቴ አዝናለሁ ፣ ሚስዝ ሂል ያርድ ። ግን ደግሞ እኔም ሙት ነኝ ። ከሞትኩ ሁለት አመት ሞላኝ ። እንደሰማሁት ከሆነ አንድ ልጅሺም ሞቷል ። ሁለት ነፍስ አጥፍተሻል ማለት ነው ። የሁለት ሰው ደም አለብሽ ። እና እውነቱን መናገር ካለብኝ የሆነው ነገር ቢደርስብሽ ፣ እኔ ሳልሆን ልቤ ሀዘን ሊፀንስ አይችልም ። . . . መቼም በመንገድ ላይ ስሄድ ወንዶች አየት አድርገውኝ ፊቴ መበላሸቱን ብቻ ሳይሆን ጣረሞት መምሰሌን አይተው እንዳይሸሹኝ አድርገሽ ልኛል ። በዚህ ላመሰግንሽ ፣ ይህን ውለታ ልቆጥርልሽ ይገባኝ ነበር ። ግን አልችልም ። ብዙ ብዙ ነገር ሊሰማኝ ይገባ ነበር ብዬ አምናለሁ ። ግን ምንም አይሰማኝም ። ብቻ ልጅሽን እንዲያ እንዳደረግሽው በመገንዘብሽ በዚያ ብቻ ትንሽ ሀዘን ቢጤ ይሰ ማኝ ይሆናል ። ሌላ የለም»



t.me/OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ ሃያ ሦስት

በሆስፒታሉ ኮሪደር ውስጥ እየተጣደፈ ሲሄድ የዱማው ድምፅ ጎልቶ ይሰማ ነበር። ምን ብታስብ ነው ወደ ሳንፍራንሲስኮ ስትመጣ ብቻየን ነው የምሄድ ብላ ድርቅ ያለችው? ይህን ያህል አመት ስትኖር ረዳት አያስፈልገኝም፣ ሁሉንም ነገር ብቻየን ልወጣው እፈልጋለሁ የምትለው ለምንድነው? ይህን እያሰበ በሩን አንኳኳ። አንዲት በገጿ ላይ ምን ይፈልጋሉ? የሚል ጥያቄ የተሳለባት ነርስ በሩን ከፈተችለት።

«ማሪዮን ሂልያርድ የተኛችው እዚህ ክፍል ነው?» ሲል ጠየቃት። በነርሷ ገፅታ ላይ የተሳለው ጥያቄ አልተነሳም ነበረና «ጆርጅ ኮሉዌ እባላለሁ» ሲል ጨመረ።

ድካም፣ እርጅናና ያለመረጋጋት ስሜት በፊቱ ላይ ጎልተው ይታያሉ። እነዚህ ስሜቶች በሠራ አካላቱ ተሰራጭተው ይሰሙትም ነበር። የለም እንዲህ አይነቱ ርባና ቢስ ነገር አሁንስ ሰልችት አለኝ። ማሪዮን በዚህ ሁኔታ ልትቀጥል አትችልም። ዛሬ ሁሉንም ግልጥልጥ አድርጌ መንገር አለብኝ ሲል አሰበ። እንዳገኛት ይነግራታል። ገና ከኒውዮርክ ከመነሳቱ በፊት ይህን ውሳኔ ለማይክል ሂልያርድም ነግሮታል።

«ሚስተር ኮሉዌ?» አለች ነርሷ ስሙን ስትሰማ በገፅዋ ላይ የተሳለው ጥያቄ ወደ ፈገግታ እየተለወጠ «ስንጠባበቅ ነበር»

ማሪዮን እዚህ ሆስፒታል የገባችው ምሽቱ ላይ፣ አሥራ ሁለት ሰዓት አካባቢ ሲሆን ጆርጅ ከኒውዮርክ ተነስቶ እዚያ የደረሰው ከምሽቱ ስድስት ሰዓት አካባቢ ነበር። ይህ ደግሞ ከኒውዮርክ ሳንፍራንሲስኮ ለመድረስ የመጨረሻው ፈጣን ጉዞ ሳይሆን አይቀርም።



t.me/OLDBOOKSPDF

ነርሷን አልፎ ገባ። ማሪዮን የጆርጅን መምጣት አይታ ፈገግ ስትል ነርሷ ከክፍሉ ውስጥ ወጥታ ወደ ሠራተኞች ግረፊያ አዳራሽ ሄደች ።

«ሄሎ ጆርጅ »

«ሄሎ ማሪዮን ፤ ተሻለሽ ?»

«ከድካሙ በስተቀር አደጋውን አልፌዋለሁ ። ማለት ሀኪሞቹ የነገሩኝ እንዲያ ብለው ነው ። ኃይለኛ አልነበረም እያያዙ»

«ዛሬስ እንዲያ ሆነ ፤ ግን --- ለወደፊቱስ ? ወደፊት --»

ጆርጅ ይህን ተናግሮ በክፍሉ ውስጥ ወዲያ ወዲህ ሲንጎራደድ እርምጃው ሁሉ የአንበሳ ይመስል ነበር። ቁጣውም ለማሪዮን ግዕል ሆኖ ታያት ። ይህን ያየችው ማሪዮን ሁኔታው አስገረማት። እንደሁልጊዜው አልሳማትም ። ብዙ ነገር ሊነግራት አስቧል ማለት ነው ።

«ለወደፊቱ ፣ ወደፊት ሲሆን ይታሰብበታል ። ላሁኑ እረፍ በልና ሰውነትህን ዘና አድርገው ። እኔን ጭምር እየረበሽከኝ ነው ። የሚበላ ነገር ይቅረብልህ ? አንድ ሣንዱች እንዲያስቀምጡልህ ለነርሶቹ ነግሬአቸዋለሁ »

«መብላት አልችልም»

«አይ -- አሁን አበዛኸው ። ደሞ የምን አዲስ ጠባይ ነው ? ይህን ያህል ዘመን ስንኖር እንዲህ ስትሆን አይቼህ አላውቅም። በሽታው ያን ያህል ከባድ መስሎህ ነው ? አልነበረም ። እና በስ ላሴ ይዠሀለሁ እኔን ጨምረህ አትረብሸኝ »

«የለም የለም ፤ አትምከሪኝ ። አልፈልግም ፤ አትምከሪኝ ማሪዮን ሂልያርድ። እንደፈለኩት ልሁን ስትይ እሽ ስል ምንመጣ ? ይኸዋ በሽታ ላይ ወድቀሽ አረፍሽው ። አሁን በዛብኝ ። በቃኝ ። አልቻልኩም »

«በቃ ተስፋ ቆረጥክ?» አለች የፌዝ ፈገግታ ፈግጋ «ተስፋ ከቆረጥክ ፤ ከሰለቸህ ለምን ሥራውን ለቀህ አረፍ አትልም?»



t.me/OLDBOOKSPDF

የጆርጅ ሁኔታ የቀልድ ያህል አስደነቃት ። ሆኖም ፊቱን ወደሷ ሲመልስና ከጀመረው ሀሳብ ወደኋላ እንደማይል የሚገልፅ ገፅታውን ስታይ የቀልድ አድናቆቷ ወደ እውነተኛ አድናቆትና ድንጋጤ ተለወጠ ።

«ሥራ ልቀቅ አልሺኝ ፤ ግሪዮን ? እኔም አስቤ አሰላስዬ የወሰንኩት እሱን ነበር ። እኔም አንችም ሥራውን ለቀን በጡረታችን መኖር አለብን»

ይቀልዳል ? — የለም ከልቡ ነው ፤ አለች በሀሳቧ ።

«አትቀልድ» አለች ። ሆኖም ድምጿ የተለመደው ጥንካሬ ይጎድለው ነበር ።

«ቀልድ ? ቀልድ የለም ። እንዲያውም በዚህ አብረን በኖርንበት ሃያ አመት ውስጥ እንዲህ አይነት ጠንካራ ውሣኔ ወስኜ አላውቅም ። ሁለታችንም ከሥራ እንሰናበታለን ። ለማይክልም ይህንኑ ነግሬዋለሁ ። እግዜር ይስጠው አውሮፕላን ማረፊያ ያደረሰኝ እሱ ነበር ። ልመጣ ስላልቻልኩ በጣም አዝናለሁ ። በሥራ ተወጥሬ ነው ብሏል ። እና ተስማምተናል ። አንች ይህን አልሸፍን አሁን ዋጋ የለውም ። ተወስኖአል ፤ ያበቃ ነገር ነው»

«አበድክ ልበል ?» አለችና ከተጋደመችበት ተነስታ ቁጭ አለች ። አፈጠጠችበት ፤ በደብዛዛው ብርሃን «ልስማህና ሥራውን ትቼ ልቀመጥ እንበል ። ግን ምን ሳደርግ ልዋል ? ሹራብ ስሠራ ወይስ መጽሐፍ ሳነብ ?»

«ሹራብ ሥሪ ወይም መፅሐፍ አንብቢ ። የፈለገሽውን ብታደርጊ ከተስማማሽ ጥሩ ነው ። ሥራውን ከተውን በኋላ ግን ወዲያውኑ የምናደርገው ነገር አለ ። እኔና አንቺ እንጋባለን ። ከዚያ በኋላ እንዳፈቀድሽ መሆን ትችያለሽ ። ግልፅ ነው?»

«እንዴት ያለ ነገር ነው ባካችሁ ? ቢያንስ ቢያንስ እንድንጋባ ፈቃደኛ ነሽ ወይስ አይደለሽም ተብዬ አልጠየቅም ? ወይስ ይኸም ከዋናው ሥራ አስኪያጅ ከማይክል የመጣ ትዕዛዝ ነው» አለች ግሪዮን ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ሆኖም ድምጿ የቃላቱን ያህል መከፋትም ቁጣም አልነበረ በትም ። ስላሰቡላት ልቧ ተነካ ። ሸከሙ ቀለል አላት ። እውነትም ይበቃታል ። ብዙ ነገር አድርጋለች ። መጥፎም ጥሩም ! አኩል በኩል ። ይህን ደግሞ ተገንዝባዋለች ። አውቃዋለች ።

ከሜሪ አዳምሰን (ናንሲ ማክአሊስተር) ጋር ያንለት ያደ ረገችው ንግግር ይህን ጉዳይ ግልፅ አድርጎላታል ! የዕድሜ ልክ ተግባሯን ተመልሳ እንድታይ አድርጓታል ። ደግሞ ከፋትም ሠር ታለች ።

«የማይክልን ምርቃትም አግኝተናል» አለ ጆርጅ ። ይህን ብሎ ወደ አልጋው ሄደና እጅዋን ጨብጦ «ታገቢኛለሽ፤ ማሪዮን ?» ሲል እየፈራ ጠየቀ ። ይህን ያህል ዘመን አብረው ኖረው ሲያፍ ራት ገረመው ። እንዲያውም ማይክል «ይገባል ። ፍቅራችሁን ልታ ከብሩት ይገባል» አይነት ነገር ባይለውና ምንም ትርጉሙ ግልፅ ሆኖ ለጊዜው ባይታየው «ለጋብቻው አበረታታት» ባይለው ኖሮ ላይጠይቃትም ይችል ነበር ።

«ንገሪኝ እንጂ»

ይህን ብሎ እጅዋን ጠበቅ አደረጋት ።

ማሪዮን ሂልያርድ ቀስ ብላ ከልብ የሆነ ግን ደከም ያለ ፈገ ግታ እያሳየችውና እራሷን በአወንታ እየነቀነቀች ፤—

«ቀደም ብለን ልናስበው ይገባ ነበር ! ጆርጅ» አለችው ።

«እኔ ገና ዱሮ ነው ያሰብኩት ። ግን በጅ አትልም ስል ተውኩት» አለ ጆርጅ ።

«ደሞ ልክ ሳትሆን አትቀርም ። ያኔ ብትነግረኝ ሳይገርመኝ አይቀርም ነበር ። በጂ ማለቱን ተወው ። ጅልነ ኮ ነኝ!» አለች ።

ይህን ብላ በረጂሙ ተንፍሳ ተጋደመችና ትራሱን ደገፍ ብላ ፤—

«እንዴት አድርጌ በሕይወቴ ተጫወትኩባት!» ስትል ተፀፀተች ።



t.me/OLDBOOKSPDF

«ፈረ እንደሱ አይባልም ተይ» አለ ጆርጅ «እኔ ሳውቅሽ ሕይወትሽን በሙሉ በትጋት ፣ በአዋቂነት ፣ ቁም ነገር በመሥራት ነው ያሳለፍሺው»

እጅዋን ይዞ በፍቅር ያሻሻት ጀመር ። ለረጂም ጊዜ ሲመኘው የነበረ ነገር ነው ።

«ደሞም ያለፈ ነገር አልፏል ። ባለፈ ፋይዳ ቢስ ስህተት እየተፀፀቱ ራስን መጉዳት ጥቅም የለውም» ሲል ጨመረ ።

ይህን ስትሰማ ማሪዮን ከተጋደመችበት ተነስታ ተቀመጠችና ትኩር ብላ እያየችውና እጅዋ ድንገት ቅዝቅዝና ጥንክር እያለ ፣

«ግን . . . ግን ይኸ ፋይዳ ቢስ ያልከው ስህተት የሌሎችን ሕይወት አበላሽቶ ቢሆንስ ? . . . ልርሳህ ብለውስ የሚረሳልኝ ይመስልሃል ጆርጅ ?» አለች ።

«ምነው ማሪዮን እያወቅሽው ? የሌላ ሰው ህይወት ለማበላሸት ምን ጊዜ ኖሮሽ ?» ሲል ጠየቃት ።

በአእምሮው ውስጥ ዶክተሩ የእንቅልፍ ክኒን ወይም ህመም እንዳይሰማት የሚያደርግ መድኃኒት ሰጥቷት ይሆን ? ሲል ጠየቀ ። ያለዚያ እንዲህ አይነት ቅብጥርጥር ከማሪዮን የሚጠበቅ እንዳይደለ እየገመተ ።

«አንተ እማታውቀው ብዙ ነገር አለ ጆርጅ ። አይገባህም ነገሩ»

«ሁሉንም ማወቅ አለብኝ ?»

«ምናልባት ። ምናልባት ማወቅ ይኖርብህ ይሆናል ። ብታውቅ ደግሞ ልታገባኝ አትፈልግም ነበር ። ምናልባት »

«ፍሬ ከርስኪ ! ይህን ሀሳብ ከልብሽ አስወጭው ። ይልቅ እንዲያ ካልሽ ነገሩን የማወቅ መብት አለኝ'ኮ።ስለዚህ ያስጨነቀሽን ነገር ንገሪኝ»

ማሪዮን በሀሳብ ተውጣ አትኩራ እያየችው ለረጂም ጊዜ ዝም ካለች በኋላ ፡—

«እንጃ ! መናገር መቻሌንም እንጃ» አለች ።



t.me/OLDBOOKSPDF

«ለምን ? ለኔ ፈርተሽልኝ ፤ ይከፋዋል ይቀፈጥል ብለሽ ፈር ተሽልኝ ተሆነ እርሺው ። በዚች ዓለም ላይ ይኸ አእምሮዬን ይበ ጠብጠዋል የምለው ነገር የለኝም ። ደሞም ላንቺ መስሎሽ'ንጂ እኔ ሳስበው የምትነግሪኝ ነገር ይኸኔ የማውቀው ነው ። ስላንቺ ማላውቅው ነገር አለ ብዬ አላስብም» አለና በስጋት እየተመለ ከታት «የለም ። የልብ በሽታው ሲነሳብሽ ጊዜ ትንሽ ሳያስደነ ግጥሽና ሳያናውጥሽ አልቀረም መሰለኝ»

«በሽታው ሳይሆን ስሸሸው የነበረ ዛሬ ፊት ለፊት የተጋ ፈጥኩት እውነት ነው እንዲህ ያናወፀኝ»

«ምን?... አንድ የተለዬ ነገር አጋጥሞሽ ነበር ?» አለ ከብዙ ፀጥታና ሀሳብ በኋላ ።

ቶሎ አልመለሰችለትም ። ጠበቀ ። ቆይታ ፡—

«አዎ» ስትል ተናገረች ።

«እንዲያ ነው?» አለ — ጥያቄ ሳይሆን ገባኝ እንደማለት ። «የሆነውም ቢሆን አሁን እንርሳው ። እረፍ ማለት ያስፈልግሻል። ጉዳዩን አንስቶ መድገም አያሻም ። ይቆይልን »

ይህን ሲል ስጋቱ ይታወቅ ነበር ። ከድምጹ ፤ ከገፅታው ልብ ድካሟ እንደገና ቢነሳስ ? የሚለው ጥያቄ ይነበብ ነበር ። ስለዚህ ያጋጠማትንም ነገር አልጠየቃትም ።

«ከልጅቷ ጋር ተገናኘን» አለች ማሪዮን ።

«የምን ልጅ ?» አለ ጆርጅ ፤ ሴትዮ ምንድነው እምታወሪው በሚል ድምፅ ።

እንባዋ መውረድ ጀምሯል ።

«ስለየትኛዋ ልጅ ማለትሽ ነው?» አለ ጆርጅ እየተጨነቀ። ዝም ብላ ስታየው ቆይታ እንባዋን ገትታ ፡—

«ማይክል የወደዳት ፤ አፍቅሮ ሊያገባት የነበረችው ልጅ» አለች ማሪዮን ተስተካከላ እየተቀመጠች ።

«ታስታውሳለህ ጆርጅ ? ማይክ አደጋ የደረሰበት ቀን ማታ ትዝ ይልሀል ? ሲያነጋግረኝ እንኳ መጥቶ ። ትዝ ካለህ ያንለት ልክ



t.me/OLDBOOKSPDF

«እሷም» አለች በሀሳብ እንደሰመጠች «በርግጥ ቆንጆ ሆና ለች ። አለባበሷ ፣ አቋሟ ይኸ ቀረሽ የማትባል ቆንጆ ሆናለች ። ናት ። ግን ቁጡ ፣ መራራ ስሜት ያላትና በጥላቻ የተሞላች ሰው እንደወጣትም በግልፅ አይቻለሁ ። ቢጋቡ እንዴት አይነት ድንቅ ባልና ሚስት ይወጣቸው ነበር»

«አሁን ያ ሁሉ እንዳይሆን መሰናክሏ እኔ ነኝ ነው እም ትይው ?»

«ይህን ሁሉ ከነገርኩህ ፣ ይህን ያህል ስለሁኔታው ካወቅህ በኋላ አንተስ ቢሆን ጥፋተኛ ናት ቢሉህ አትስማማም ? . . .

«. . . ጆርጅ እውነቱን መሸሽ አያሻም ። ጥፋተኛ ነኝ ። በሁለት ፍቅረኞች መካከል መግባት አልነበረብኝም ። »

«ሳይታሰብ በደል ተፈፅሟል እንበል ። ግን ደግሞ የሁለቱ ነገር የሚሆን ከሆነ አሁንም ነገሩ የሚስተካከልበት መንገድ ይኖር ይሆናል ። ከተስተካከለ ደግሞ ያ ባይሳካ እንኳ ለልጅቷ የዋልሽላት ውለታ ቀላል አይደለም። ገላዋን መልሰሽላታል እኮ... ምናልባትም የተሻለ ኑሮ እንድትኖርም ረድተሻታል»

«ይህን ሁሉ አደረግሺልኝ አላለችም ፣ እሷ እንዲያውም በጣም ትጠላኛለች»

«ይህን እያወቀች የምትጠላሽ ከሆነ ዋጋ የላትም ። ጅል ናት ማለት ነው»

«የለም ጆርጅ ጅል አይደለችም ። መጥላቷም ትክክል ነው። ልብ ቢኖረኝ ኖሮ ደሞ ለማይክል እነግረው ነበር የሆነውን ሁሉ።»

«አሁንማ መንገር ምን ዋጋ አለው ? አሁንስ ባትነግሪው ይመረጣል—ውዴ» አለ ጆርጅ የማይክልን ቁጣ እያሰበ ። «አት ንገሪው እሺ ?»

«አይዞህ ፣ ጆርጅ» አለች ማሪዮን በሀዘን ፈገግ ብላ «ያን ያህል ደፋር አልምሰልህ ። ይህን ለሱ ለመንገር ያህል ልብ የለ ኝም ። ሆኖም ማወቁ አይቀርም ። ጊዜ ይወስዳል እንጂ ማወቁ የማይቀር ነው።ይህ እንዲሆን ደግሞ እኔም እረዳዋለሁ ። ጥፋቴን



t.me/OLDBOOKSPDF

ለመዘርዘር አቅምም ድፍረትም የለኝም ። ከተገናኙ በኋላ እሚ ስማሙ ከሆነ እሷው ትንገረው ። ያኔ ምናልባት ይቅርታ ያደርግ ልኝ ይሆናል»

«ትወኝ ብላ እምታስብ ከሆነ እሺ ብላ እምትቀበለው ይመ ስልሻል ?»

«አሱን እንጃ ! እሱ እኔንም ያጠራጥረኛል ። ግን እኔ የተቻ ለኝን ያህል እንዲገናኙ ማድረግ አለብኝ»

«እንዴት ያለው ጣጣ ...»

«አዎ እንደተበተብኩት ማፍታታት አለብኝ ። ሙሉ ላይገኝ ያሰብኩት ላይሳካ ይችላል ። ቢሆንም መሞከር አለብኝ»

«ይገርማል ። . . . ይህን ያህል ጊዜ ሁለት አመት መሆኑ ነው . . . ይህን ያህል ጊዜ በሆነ መንገድ ከልጅቷ ጋር ግንኙነት ታደርጊ ነበር ?»

«እንዲያ በፋሻ ተደግፌላ ካነጋገርኳት በኋላ አይቻት አላ ውቅም ነበር ። ለመጀመሪያ ጊዜ ያየኋት ዛሬ ነው»

«ገባኝ ፣ ዛሬስ እንዴት ልትገናኙ ቻላችሁ ?»

«የቀጠርኳትም እንድንነጋገር ያቀድኩትም ራሴ ነበርኩ ። ቤን ስለፎቶግራፉ አንሺዋ አርቲስት ሲነግረኝ ልቤ ጠረጠረ ። ጥርጣሬ እንጂ ርግጠኛ'ንኳ አልነበርኩም»

«አብራችሁ ያሳለፋችሁት ጊዜ ጭንቅ የበዛበት ሳይሆን አይ ቀርም»

«ከዚያ የባሰ ሊሆንም ይችል ነበር» አለች ድምፇ በህዘን ለስልሶና አይኗ ላይ እንባዋ ተንቀርዝዞ «የባሰ ነገር ሊመጣም ይችል ነበር ። ግን አልሆነም ። ምን ያህል እንደተሳሳትኩ ፣ ሁለት ህይወት እንዳበላሸሁ ፣ ወንጀለኛ እንደሆንኩ ብቻ ነው የተረዳ ሁት ። ያ ብቻ ነው . . .»



t.me/OLDBOOKSPDF

«ተይ እንጂ እንዲያ አትበይ ። እንዳቸውንም አልጎዳሻቸ ውም'ኮ ። በድንብ ብታስቢበት እኮ ማይክልን የበረረ መሀንዲስና የተዋጣለት ሥራ አስኪያጅ እንዲሆን አደረግሽው ፤ እሷም የተ ሟላ አካል ያላት የታወቀች ፎቶግራፍ አንሺ ነው የሆነችው ። በምንም መንገድ ይህን ሊሰጣት የሚችል ሰው አልነበረም»

«ምኑን ነው ማንም ሊሰጣት የማይችለው ? ትስፋ መቁረ ጥን ? ሀዘንን ? ግራ መጋባትን ? ምኑን ?»

«ሕንቺ የሰጠሻት ይህን ከመሰላት ደህና ሰው አይደለችም ። ማለቴ ውለታ ቢስ ናት ማለት ነው ። ሙሉ አካልን ያህል ነገር ሰጠሻት ። የሰጠሻት አዲስ ሕይወትስ ? አዲስ ዓለምስ ? ይኸ ሁሉ አይቆጠርም ? »

«አዲስ ሕይወት ። ዓዲስ አለም ። ይኸ ሁሉ ለኔ እንደሚ መስለኝ ለሷ ምንም ጣእም የለውም ። ሀያው አይደለም ። ምናል ባት ከዚህ አላት ካልከው ነገር ሁሉ ያለው ሥራዋ ብቻ ይመ ስለኛል ። በዚህ በኩል ደግሞ የሷም የማይከም ስሜት ተመሳ ሳይ ነው »

«እንዲያ ከሆነም ፡ ማለትም አንድ አይነት ከሆኑም ጥሩ ። አሁን ፈቅደሻል ። ስለዚህ ተገናኝተው አንድ ነገር ሊፈጥሩ ይችሉ ይሆናል ። ገና ልጆች ናቸው ሁለቱም ። የራሳቸውን መንገድ ይቀ ይሱ ። ስለነሱ እያሰብን የኛን ጭላንጭል ኑሮ አናበላሻት »

ይህን ብሎ ጎንበስ ብሎ ከሳማት በኋላ —

«ማሪዮን» አለ ፤ «ማሪዮን እወድሻለሁ»

አየችው ። እንደገና በፍቅርና በተሰቃይተሻል አይን እያየች

«ማሪዮን ፤ ዐፀቱን ችለሽ መቆየትሽም ይገርማል ። ምነው ቀደም ብለሽ ብትነግሪኝ ? ሀሳብ'ኮ ለሰው ሲነግሩት ይከፈላል» አለ ።

«ብነግርህ ፤ ይህንም ታደርጋለች ? ብለህ ትጠላኝ ነበር» አለች ማሪዮን ሂልያርድ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

«ማን? እኔ? እንችን? — ፍጹም የማይሆን ሀሳብ ። ያኔም ሆነ ዛሬ እንችን መውደድ እንጂ መጥላት አልችልም» አለና ትንሽ አሰበ ። ቀጥሎ ፤—

«ማሪዮን» አለ ።

አየችው ፤ አቤት እንደማለት ።

«ማሪዮን ያለፈው አልፏል ። ላሁኑ ሁለቱ የሚገናኙበትን መንገድ ቀይሺ ። የሚቻልሽን ሞክሪ ። ከዚያ በኋላ የሁለቱ ጉዳይ ነው ። አንቺ ምንም ማድረግ አትችይም ። እኔና አንቺ ብዙ አድሚ አልተረፈንም ። ያችኮ ያለችዋን የተቻለንን ያህል እንድንደ ሰትባት እፈልጋለሁ። እንጋባ ። አንድ ላይ እንኑር ፤ በሰላም ። እኔም እስከ ዛሬ የናፈቅሁት ፥ አንቺም ሠራሁት በምትይው ሀጢአት እስከ ዛሬ የተቀጣሽው በቂ ነው ። እኛምኮ በደስታ የመኖር ድርሻ አለን» አለ ጆርጅ ።

«ድርሻው ይሁን ፣ ግን እኔ የመደሰት መብት ያለኝ ይመስ ልሀል ጆርጅ ? » አለች ማሪዮን ቅዝዝ ብላ ፤ ከልቧ ።

ይህን ስትል ቅዝዝ እንዳለች ቁልቁል ሲያያት ገና ለግላጋ ወጣት ሆና ታየችው ፤ ለጆርጅ ኮሎዌ ።

«በደንብ ነዋ ! » አላት «የመኖር መብትሽን ማን ሊነሳሽ ፍቅሬ ?»

ከዚያም ፀፀቷን ሁሉ እንድትረሳ ፤ ሀጢአት የምትለው ነገር ከንቱ ሀሳብ መሆኑንና ለወደፊቱ የሚቻለውን ካደረገች በኋላ ደስ ታ'ችውን እየተሳበሱ በሰላም መኖር እንዳለባቸው ደግሞ ነገራት። ቀጥሎም ፤—

«ላሁኑ ግን ማረፍ አለብሽ ። ለጥ ። በቃ ። ለእንደዚህ ያለው በሽታ መድሐኒቱ እረፍት ነው ። እሺ ? » አለ

ወደ ላይ እያየችው ፍንድቅ ብላ ሳቀችና ፤—

«ጆርጅ ኮሎዌ እወድሀለሁ» አለችው ።



t.me/OLDBOOKSPDF

«መውደድሽ ደግ ሆነ ። ምክንያቱም ወደድሽም ጠላሽ አን ቺኑ ማግባቱ አይቀርም ነበር ። የመጣው ቢመጣ ። ገባሽ ? »

«አዎና»

ሁለቱም በደስታ ግለው በፈገግታ ይንቦገቦጉ ጀመር ።

አንድ ነርስ በሩን ቀስ ብላ ከፍታ ሀኪሙ ለማሪዮን በደንብ መተኛት እንዳለባት መግለፃቸውንና ሴሊቱ እየተገባደደ መሆ ኑን እስከትነግራቸው ሁሉንም ረስተው በፍቅር ተተብትበው አንድ ላይ ቆዩ ።

ጆርጅ ኮሎዌ እንደወጣ ማሪዮን ሂልያርድ ወደ ኒው ዮርክ ስልክ ደወለች — ከሳንፍራንሲስኮ ማለት ነው ። ጊዜው (ኒውዮ ርክ ውስጥ) እኩለ ሌሊት ቢሆንም ማይክል ስልኩን ቶሎ አላነ ሳውም ። ጠበቀች ፤ ማሪዮን ።

« ሃሎ ? » አለ ፤ እንቅልፍ የተጫጫነው የማይክል ድምፅ ።

« የኔ ሸጋ ! እኔ ነኝ » አለች ማሪዮን ።

«እማዬ ነሽ ? ደህና ነሽ ? ተሻለሽ ? » ጥያቄውን እኾነ ደው ።

«ደህና ነኝ ። አይዞህ አትስጋ ። ይልቅስ አንድ ነገር ልነግርህ ስለፈለኩ ነው የደወልኩልህ »

« ገባኝ ። ጆርጅ ነግሮኛል » አለ እያዛጋ «እንዴት ነው ፤ አሺታ ወይስ እምቢታ ? »

« እምቢታ የለም ። ሁሉንም ተቀብያለሁ » አለች ። «አሁን የጠራሁህ ለሌላ ጉዳይ ነበር» አለች ።

መልስ አልሰጣትም ። ትንሽ እንደማጉረምረም ብቻ አለ ።

«ስለዚያች ልጅ ጉዳይ» አለች ማሪዮን ።

«የቷ ልጅ ? » ማይክ እየተደናገረ ጠየቀ ።

«ፎቶግራፍ አንሺዋ ። . . . ማይክል ገና አልነቃህም'ንዴ »

«ገባኝ ። እሺ ። ምን ትሁን ? »

«ታስፈልገናለች»



t.me/OLDBOOKSPDF

«ያን ያህል !»

«በጣም ። ሆኖም እንደምታውቀው እንግዲህ እኔ የጆርጅ ሰው ነኝ ። ልጅቷን ማደኑ ያንተ ሥራ መሆኑ ነው »

«ትቀልጃለሽ እማዬ ? እኔ ያለብኝን የሥራ ውጥረት እያወቅሺው ። ቤን ይከታተል የሷን ጉዳይ»

«ቤንንማ አፍንጫህን ላስ አለችው'ኮ ። ይልቅ ስማ ። ልጅቷ ዘመናዊ ከመሆኗም በላይ የታረመችና በእውቀቷም የምትተማመን ሰው ናት ። ከማንም ኩታራ ጋር ለመነጋገር የምትፈቅድ አይመስለኝም— ከተቀጣሪዎች ጋር ማለቴ ነው»

«ገባኝ ። ግን የመቀመጫ እሾህ መስላ ነው ለኔ የታየችኝ»

«እሷ ሳትሆን አንተ ነህ እንዲያ የሆንክብኝ ። በምን መንገድ ልታግባባት እንደምትሞክር አላውቅም ። በሆነው ፣ በመሰለህ ሁሉ ብትቀርባት ደንታዬ አይደለም ። ግን እንፈልጋታለን። ለኔ ስትልም ቢሆን ይህን ነገር ዳር እንድታደርሰው እፈልጋለሁ »

«የለም ፣ የለም ዛሬ ደህና አይደለሽም ። ጊዜ እንደሌለኝ እያወቅሽ እንዲህ ስትይ» አለ። «ይልቅ ይህን ጉዳይ ብቻ እንቺ ጨርሺ ። በቃ ። »

«አላደርገውም ማይክ ፤ ደግሞ ይህን ጉዳይ አልፈፅምም የምትል ከሆነ ገና እኮ ነው ፤ ሥራውን አልለቀቅኩም'ኮ !

«ይህን ካላደረግክ አንደኛ ሥራዬን አልለቅም ፤ እዚያው እቢሮዬ ውስጥ እሞታለሁ ። ሁለተኛ—»

«በቃ በቃ!» አለ ማይክል አቋርጧት «እንዳልሽው ይሆናል »

«ልባርግ ! ቀልድ አይደለም ። ቃል ፣ ቃል ነው ። ቃልህን ከሻርክ ቃሌን እሽራለሁ ። »

« ኧረ በእግዜር ! እሺ አልኩ'ኮ አሁን ትተኛለሽ ወይስ ? »

«እተኛለሁ ። ግን ይኸ ጉዳይ ነገ ዛሬ እንደሌለው እወቅ ። ገባህ ? »

«ገባኝ ። ስሟን ማን ነበር ያልሺኝ ? »

«ሜሪ አዳምሰን»



t.me/OLDBOOKSPDF

«ሜሪ አዳምሰን ። በቃ ከነገ ጀምሮ የማገኝበትን መንገድ እፈልጋለሁ»

«ደግ . . . እግዜር ያክብርህ የኔ ቆንጆ»

«ደህና ደሪ የኔ እሮጊት ። . . . ቆይ . . . ቆይ እንኳን ለፍጥምጥሙ አበቃን ። ወሬውን ላናፍሰው ? ሙሽራው ማን እንደሆነ ልናገር ?»

«ምን ይጠየቃል ? ከጆርጅ የተሻለ ማንን ላገኝ ?—እላፍር በትም»

ሁለቱም ዘጉ ።

ማይክልንና ሜሪን ካገናኘች ፣ ሁለቱ ተዋውቀው አንድ ነገር ከመሰረቱ አእምሮዋ ሰላም ያገኛል ። ማይክ የሠራችውን ሁሉ ሲሰማ ምን ይላት ? ሆኖም ፍቅሩን የማግኘቱ ደስታ ለሷ የሚኖረውን ጥላቻ ሊቀንሰው ይችላል ። በኋላ ተፀፅታ የሠራችውን ሲያይ ይቅር ይላታል ። እንቅልፍ እያንሸራተተ . . .



t.me/OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ ሃያ አራት

ጆርጅ ኮሎዌ በፍቅር ሲሰማት ለስላሳው ሙዚቃ እንደ ገና ጀመረ ። የሠርጉ ሥነ ሥርዓት የተከናወነው በማሪዮን ሂል ያርድ ቤት ሲሆን እሷም ለዚሁ የሠርግ ቀን ሶስት ሙዚቀኞች ቀጥራ ነበር ። ለሠርጉ የታደሙት አንድ ሰባ የሚሆኑ ሰዎች ሊሆኑ ፤ የምግብ ቤቱ ክፍልም እንደ የዳንስ አዳራሽ ሆኖ ተዘጋጅቷል ። የቡፌ ግብዣው የሚከናወነው ደግሞ በዚሁ መኖሪያ ቤቱ መጻሕፍት ውስጥ ነው ። ዝግጅቱ የተከናወነ ፤ ቀኑም ተስማሚ ነበር ። የየካቲት የመጨረሻው ቀን ። ይህ ቀን ጥርት ያለ ፣ ነፋሻና ሳንካ አልባ የሆነ የኒውዮርክ ቀን ሆኗል ።

ማሪዮን ሳንፍራንሲስኮ የደረሰባትን ነገር እንደመርሳት ያለች ይመስላል ። ደሟ ግቶም ብሎ ሞልቷል ። ጆርጅ በደስታ ፈንድቋል ።

ጋዜጠኞችም በዚሁ ሠርግ ላይ ተገኝተዋል ። ታይም የተባለው ታዋቂ መጽሔት ፎቶ አንሺ ማይክልንና ማሪዮንን ፣ ባሏን ጆርጅን ፎቶ አነሳቸው።ማሪዮን በባለቤቷና በልጇዋ ታጅባ ነበር የተነሳችው ።

ማይክል ሂልያርድ እናቱን ዳረ ። ማሪዮን ሂልያርድ ካሁን ጀምሮ ፣ ማሪዮን ኮሎዌ ትባላለች ፣ የጆርጅ ኮሎዌ ባለቤት ።

ማይክል ሂልያርድ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የኮተር ሂልያርድ ባለቤት ነው ። የአንድ ግዙፍ ድርጅት (የኮተር ሂልያርድን ያዘል ግዙፍ ድርጅት) ፕሬዚዳንት መሆን ፤ ለማይክል የተሰማው ስሜት . . . ሆኖም ይህም ስሜት ቢሰማውም . . . ይህን ስሜቱን ደግሞ ማይክል ሊያብቅ አይሻም ። ፕሬዚዳንት ፣ በዚህ ዕድሜው ባለቤት ፤ በማግስቱ ታይም የተባለው በመላው ዓለም የሚሰራጭ መጽሔት የማይክልን ፎቶ በሽፋኑ ይዞ ወጣ ። ድንቅ



t.me/OLDBOOKSPDF

ብሎት ስላየችው ደስ አላት ። እንዲህ ደስ የሚለው መስሏት አያውቅም ። ብቻ ነገሩ ሁሉ አይገባትም ። ገባት አልገባት ደሞ ደንታዋ አይደለም ። ለሷ እንደሆነ ቤን አለላት ። የቤንን ያህል በፍቅር ደስ ያሰኛት ወንድ የለም ።

«እንቺም በሚቀጥለው በዖ እንዲህ ቆንጆ ሆነሽ ማየት አለብኝ ። ሙሽራ ቁንጅት ሲል የሥራ አከላቴ በደስታ ይሞላል » አለ ማይክል ዌንዲን በደስታ እያየ ።

ደስ አላት ። ዛሬ ጓደኛዋ ነው ። ትወደዋለች ። አትመኘውም ። ለጓደኛ የሚገባውን ሁሉ ግን ትመኝለታለች ።

«እህ የኛ ጀግና ፤ የሰው እጮኛ ለማማገጥ ነዋ ?»

ቤን አብሮ ነበር እንዲህ ያለው ። ቤን ሶስት መለኪያ ሻምፓኝ ይዞ ነበር የመጣው ። «በሉ ተቀጠ።ይኸው ! ሁለት መለኪያ የናንተ ነው አንሱና ጠጡ» አለ ቤን በደስታ ፈክቶ ። ቀጥሎም ፤

«በነገራችን ላይ ማይክ ምን እንደሚሻለኝ እንጃ' ንጂ ፍቅር ይዞኛል ፤ ከማሪዮን ጋር » አለ ።

«ቀለጥክ—ዛሬ ጠዋት ላንድ ጎረምሳ ዳርኳት» አለ ማይክ ። ቤን ወይኔ በሚል ሁኔታ ጣትና ጣቱን አጨሆ ደንግጦ ቀረ ። በዚህም ነገር ሶስቱም ከልባቸው ሳቁ ። ሙዚቃው የተጀመረው ገና ሰቀው ሳያበቁ ነበር ። በዚህ ጊዜ ማይክ « ሙዚቃው ጀመረ። መሔድና እናቴን ለዳንስ መጋበዝ አለብኝ ። ደንቡ እንደሚለው እኔና እሷ ዳንሱን እንከፍታለን ። ጆርጅ ይቅርታ ጠይቆ ይነጥቀኛል ። »

ይህን ብሎ ወደ ዳንሱ አዳራሽ ከገባ በኋላ ነበር እናቱን ባዲሱ የጋብቻ ስሟ ጠርቶ የጋበዛት ።

« ዛሬ በጣም ደስ ያለው ይመስላል » አለች ዌንዲ ፣ ማይክ እንደተለያቸው ።

«እንዲህ አንዳንድ ቀን እንኳ ደስ ብሎት እንየው'ንጂ » አለ ቤን ፊቱ በተመስጦ ተሞልቶ ። ከዚያም ድንገት ተመስጦን ነጥቆ ወጥቶና ከልቡ ፈገግ ብሎ ፡—



t.me/OLDBOOKSPDF

«እንቺም ዛሬ በጣም ደስ ብሎሻል » አላት

«ደሞ እኔ መቼ ከፍቶኝ ያውቃል ? ዕድሜ ላንተ 'ንጂ » አለች ከልቧ ። ለጥቂት ጊዜ ፀጥታ ሆነ ። ከዚያ በኋላ ፡—

« በነገራችን ላይ ፣ እጠይቅሀለሁ እያልኩ እየረሳሁት ። ያችን ፍቶ ግራፍ አንሺ አነጋገርካት ወይስ እንዴት አደረግክ ? » ስትል ጠየቀችው

«አላነጋገርኳትም » አለ ቤን ራሱን በአሉታ እየነቀነቀ ፤ «ማይክ ሊያነጋግራት አስቧል »

አልመሰለሽ አላት

« ማይክ ጊዜ አግኝቶ ? » አለች

ጥያቄዋ መደነቅም ነበር ።

«ጊዜ እንኳን የለውም ። ግን ማይክ ለሥራ ጊዜ ያጣል ብለሽ ነው ? እንደምንም ያብቃቃዋል ። ለዚህም ለሌላ ሌላ ሺህ ጉዳይም በሚቀጥለው ሳምንት ወደ ሳንፍራንሲስኮ ይሔዳል » አለ ቤን ።

ፀጥታ ሆነ ። ዌንዲ ማሰብ ቀጠለች ።

የለም ማይክን አላውቀውም ፣ ሁል ጊዜ አዲስ ነው ። ብቻም አይመስለኝም ። ማይክ ምን እንደሆነ 'ሚያውቀው ያለኔ ምናልባት ቤን ። ቤንም ቢሆን እንጃ ። ባት ያውቀው ነበር ማለት ይቻላል ፣ በፊት ። ግን አሁንስ ያውቀዋል ? እረ በፊትስ ቢሆን ያውቀው ነበር ? አስቸጋሪ ነገር ነው ። . . .

«መደነስ ትፈልጊያለሽ ? » አለ ቤን መለኪያውን እጠረጴዛው ላይ እያኖረና እያቀፋት ።

«መፈለግ ነው ! » አለች ደስ እያላት ።

ተያይዘው ወደ ዳንሱ አዳራሽ ገቡ ። ትንሽ እንደደነሱ— ቢያንስ ለነሱ ትንሽ የደነሱ ነው የመሰላቸው ማይክል በመካከላቸው ሲገባ እየሞከረ ።

«ተራ ይድረሰኝ'ንጂ » ፣



t.me/OLDBOOKSPDF

«እንዲህ ነኝና ! ምናለ ይደርስሀል . . . » አለ ቤን «ሰው የው ደህና ማደለህ ! ለመሆኑ ከእናትህ ጋር ልትደሰት አልነበረም እንዴ ትተኸን የሔድከው ? »

« ጆርጅን ስታይ እኔን ፈንግጣኝ ሔደች »

ሶስቱም ሳቁ ።

«ደግ አደረገች። አዋቂ ይሉሀል እንዲህ ነው» አለ ቤን እየሳቀ ።

ቤንም ወለሉን አልለቀቀ ! ማይክልም አልተመለሰ ። ሶስቱም ባንድነት መደነስ ጀመሩ ። መንገላወድ ልበለው ! ይህ የተስማት ዌንዲ በሳቅ መንከትከት ጀመረች ። ቤንና ማይክ ያን ያህል ሲደሰቱ ስታይ አደጋው ከመድረሱ በፊት የነበረው ሁኔታ በዓይነ ኅሊናዋ ታያት ። እንዲህ ነበር ማለት ነው የሚደሰቱት ስትል አሰበች ።

ዛሬ ይህ በመመለሱ ደስ አላት ። መሳቅ ጀመረች ። በመካከሉ ማይክ ቤንን በትያትራዊ ቁጣ እየተመለከተ ፡

«ስማ አቭሪ ! ከዚህ ጥፋ ብያለሁ ጥፋ ። ከእጮኛየህ ጋር ለብቻየ መደነስ እፈልጋለሁ ማለት ይግባህ » ሲል አስጠነቀቀው።

«አልሔድም ! አይቻልም ብል ምን ሊመጣ ! » አለ ቤን

«ሶስታችንም ከዳንሱ ወለል ተጠርገን እንድንጣል ታዛለች እናቴ ። ያ ደሞ ጥሩ አይመስለኝም »

በዚህ ሁኔታ ከቆዩ በኋላ ፡

« ስሙ » አለ ማይክ «ለምን ሔደን ኬክ አንበላም ? » ተስማሙ ። ኬክ ወዳለበት ሲሔዱ ቤን አቭሪ የጫማውን ሶል አየት ካደረገ በኋላ ሳታየው ዌንዲን በአውራጣቱ እያሳየና አትሰማም አሉ በሚል ሁኔታና ትያትራዊ ሹክሹክታ ፣

«ዳንስ አትችልም ይቺ ሴት ። ጫማዬን ታያለህ ? » አለው። ማይክም «የኔንም ተመልከተው ! » ሲል አጋነነ ።

«የናንተን አሳያችሁ እኔ ደሞ ነገ በእግሬ መሔዴ እማይቀር ነው » አለች ዌንዲ በማኩረፍ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

በዚህ እየተሳሳቁ እኬኩ ዘንድ ደረሱ ። ኬኩን እንስተው እየገመጡ ዳንሱን መመልከት ጀመሩ ። የተጠሩት ሀብታሞች ነበሩ ፤ ሁሉም ። በሀብታም ጋለሞቶች አንገት ላይ የተንጠለጠሉት የአንቁና የሉል ጌጦች ያበራሉ ። ልጃገረዶችም አበባ መስለዋል ።

«ትንሽ ቀደም ብሎ ይኸን ባይ ኖሮ » አለ ቤን በውሸት የፀፀት ድምጽ ልጃገረዶቹን እያየ ።

«እህሳ ! » አለ ማይክ ቀልዱን እየተከተለ ።

«እህህ ... ወደ መፀዳጃ ቤት ብቅ ብዬ የአፍንጫዬን ላብ በፑደር ላስተካክል አስቤ ነበር ። አሁን ግን እናንተ ሰዎች የምትታመኑ ሆናችሁ አልታያችሁኝም ። ይቅርብኝ » አለች ዌንዲ ።

«አይ ለዚህስ አታስቢ ። እጠብቅልሻለሁ » አለ ቤን ።

« ምን ጊዜ ኖሮህ ጌታዬ ! አንተንም የሚጠብቅ በተገኘ፤ እንኳን አንተ ሰው ልትጠብቅ »

ቤን አቨሬ « ግድየለሽም » ብሎ ብርጭቆዋን ተቀብሎ እንደማባረር አደረጋት ። ዌንዲ ወደ ወይዛዝርት ክፍል ስትሔድ ።

«ቤት ብሎ ዝም ናት ፤ አይደል ? » አለው ማይክን ።

ማይክም አድናቆቱን ከልቡ ገለጸ ። ከዚህ ቀጥሎ ቤን ማይክን በደንብ እየተመለከተ ፡

« ሁሌ ሳስበው ምንኛ ታድያለሁ እላለሁ ። ማይክ ያኔ ስንገርህ አለመቆጣትህ . . . ስለኔና ስለሷ የነገርኩህ ለት . . . » አለ ።

«ለምን እቆጣለሁ ? ! . . . ደሞም ’ኮ አየህ እኔ ለእንደዚህ ዓይነቱ ነገር ጊዜ የለኝም »

« ለወደፊቱ ግን ጊዜ እንደሚኖርህ አልጠራጠርም »

« ምናልባት ። ሆኖም ለጊዜው እናንተ ፤ እናንተ ሂዱ ፤ አግቡ ተጋቡ ። እኔ ልጄ ከባድ ሥራ ፤ ከባድ ኃላፊነት አለብኝ »



t.me/OLDBOOKSPDF

ግይከ ይሆን ያሀል ቢልም ከዚህ በፊት ይሆን የመሰለ ነገር እንደሚያስከፋው አልተከፋም ። ፈገግታ በፊቱ ላይ እንዳለ ነበር ። እንዲሁ ፈገግ እንዳለ መለኪያውን ተመለከተ ። ከዚያም ለጤና ችን በሚል ቅኝት ብድግ አድርጐ፡

«ለሁላችን ! » አለ

ሁለቱም ግጥም አድርገው ጠጡ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ ሃያ አምስት

ማይክል የእጅ ሻንጣውን ጧ እድርጎ ሲዘጋ አውሮፕላኑ የሳንፍራንሲስኮ ማረፊያውን አስፋልት ያዘ ። በመንገድ ላይም እያሰ አላረፈም ነበር ። በሳንፍራንሲስኮ ውስጥ በሚቆይበት ጊዜ ብዙ ስራ መስራት አለበት ። ብዙ ስብሰባዎች ይጠብቁታል ። የተለያዩ ሐኪሞችን ማነጋገር ፣ ጥያቄዎችን መመለስ ፡ የተለያዩ ስራዎችን መመልከት፡ አርኪቴክቶችን ማነጋገር፣ ማደራጀት ፣ መመሪያ መስጠት ። በዚያ ላይ ደሞ... ያችን ፎቶ ግራፍ እንኳ ማነጋገር፣ ማግባባት፣ ማለቂያ የለውም ። ሆኖም እንደምንም ይወጣዋል ። ለምዶታል ። ወይ የምግብ ሰዓቱን በማሳለፍ ወይ የመኝታ ሰዓቱን በመቀነስ ወይም ሌላ። ብቻ ... ይወጣዋል ።

ይህን እያሰበ በአንደኛ ደረጃ የበረራ ክፍል ከተቀመጠበት ወንበር በላይ ባለው ርብራብ ላይ አጥፎ ያስቀመጠውን ካፖርት ሲያወርድ ሆስቴስዋ አይኗን እንደጣለችበት ተገንዝቦ ፊት አልሰጣትም ። እንደሁልጊዜው ፀጥ ብሎ ወደ ውጭው በር አመራ። ሲያዩት እንዲህ አድርጎ ትቷቸው መሄዱንም እንደስራው ሁሉ ለምዶታል ።

ሰዓቱን አየ ። ከቀትር በኋላ መሆኑን ተገነዘበ ። አውሮፕላን ማረፊያው ድረስ መጥቶ የሚጠብቀው መኪና እንዳለ ያውቃል ። ምናልባትም ዛሬውኑ ስብሰባዎች ማካሄድ ይኖርበታል ። ነገ ጧት ቁርስ ላይም ስብሰባ አለው ። ከአንድ ሰዓት ጀምሮ ። የማይክል ሂልያርድ ሕይወት ይኸው ሆኗል ። ማይክል ሂልያርድ ስለስራ እንጂ ስለሌላ ነገር አያስብም ። በርግጥ ያስባል ። ስለእናቱ ያስባል ። ስለጆርጅ ኮሎዌ ያስባል ። ስለቤንና ስለዌንዲም ያስባል ። እናቱና ጆርጅ ግን የሉም ። ማጀርካ ውስጥ የሙሽርና ወቅት



t.me/OLDBOOKSPDF

እያሳለፉ አለማቸውን ይቀጫሉ ። ቢንም በቄንዲ እትና ውስጥ በሰላም ኒውዮርክ ውስጥ ይምነሽነሻል ። ሁሉም ተከባካቢ አላቸው። ስለነሱ መጨነቅ አያስፈልገም ። እሱንም ቢሆን የሳንፍራንሲስኮ ሕክምና ማእከል እያቀማጠለ ያኖረዋል ። ይሰራል . . . ከዚህ የበለጠ ምን አለ ? ስራ ሰላም ነው ።

ለማይክል ሂልያርድ ።

እንዳሰበው ሆነ። መኪና ይጠብቀዋል ። ተሳፍሮ ወደ ታላቁ ፌይርሞንት ሆቴል አመራ ። ተይዘዋል የተባሉት ሁለቱም ልዩ ክፍሎች በትክክል እንደተጠበቁ ሆነው አገኛቸው ። ሁለቱም ክፍሎች የራሳቸው ሳሎንና መኝታ ያላቸው የተሟሉ ክፍሎች ሲሆኑ ለማይክል አንዱ ክፍል በቂ እንደሆነ ግልፅ ነው ። ሁለተኛውን ልዩ ክፍል የተከራየው ለስብሰባ ሲል ነበር ። ሲያስበው በሁለቱም ውስጥ ስብሰባዎችን ማካሄድ እንደሚችልም ገመተ ፣ ባንዴ።

እቃው ተራግፎ፣ ክፍሉ ውስጥ ከገባ በኋላ ጣመኑ በሚገባ ሳይለቀው ስራ ጀመረ። ያን ለት የመጨረሻውን ጉዳይ ተነጋግሮ ሲጨርስ ከምሽቱ ሶስት ሰዓት ሆኖ ነበር ። ሌላ ጉዳይ ሲጨምር አልቻለም። ደከመው፣ ራበው። ይበቃዋል ።

እዚያው እክፍሉ ውስጥ እንዳለ ስልክ ደውሎ ብስቴካ እንዲያመጡለት አዘዘ ። ብስቴካው እስኪመጣለት አልጋው ላይ ትንጋሎ እግሩን ቡና ማቅረቢያው ጠረጴዛ ላይ ዘርግቶ ተዘረረ ።

ወዲያው «አነጋግርካት ?» የሚል ድምፅ የሰማ መሰለው። በርግጥ ድምጹን ሰምቶታል ። ግን ግዙፍ ድምፅ አልነበረም ። ድምጹን የሰማው በሀሳቡ ነበር ። ድምጹም የእናቱ ድምፅ ነበር ። ያን ያህል ጉልህ ሆኖ በመሰማቱ ገረመው ። ቀና አለ ። ክፍሉ ከሰዎች ጋር በነበረበት ጊዜ በተጨሰው የሲጋራ ጭስና በዊስኪ ሽታ ታፍኗል ።



t.me/OLDBOOKSPDF

. . . እንዲያም አለ በሀሳቡ ፤ የምበላውን ነገር እስኪያመጡልኝ ለደውልላት ። እኔንም እንዳልተኛ ይረዳኛል ።

ደወለ ።

«ሄሎ» አለች ሶስት አራቴ ስልኩ ከጮኸ በኋላ ።

«እንደምን አመሸሽ ሚስ አዳምስን። ማይክል ሂልያርድ እባላለሁ» አለ ።

ባለችበት ላይ ደንዝዛ ቀረች ። ልትጮህ ቃጣት ። ሆኖም እንደምንም ብላ ተቆጣጠረችው ። ትንፋሿንም ዋጥ አደረገች ። ይህን ሁሉ ካደረገች በኋላ ፦

«ነው? ሳንፍራንሲስኮ መጥተሃል ማለት ነው?» አለች። ይህን የተናገረችው በመጠኑ በሚቆራረጥና በጎረና ድምፅ ነበር ። ያን ድምፅ የሰማው ማይክል የተቆጣች መሰለው ። ምን አስቆጣት ! አለ በሀሳቡ ። ምናልባት በሌላ ነገር ተበሳጭታ ይሆናል ። ወይም እቤቷ ሲደውሉላት አትወድ ይሆናል ። ብቻ የሰው ጠባይ ብዙ ነው ። ያም ሆነ ያ ማይክል ደንግጦ አይደለም ።

«አዎ። ሳንፍራንሲስኮ ነው ያለሁት ። ልና ተገናኝተን አንዳንድ ነገር ብንወያይ ብዬ ነበር» አለ ማይክ።

«የለም የለም ። ምንም የምንነጋገረው ነገር የለም ። ለእናትህ ግልጹን የተናገርኩ መሰለኝ ነበር'ኮ » አለች። አልቅሺ አላት። ሰውነቷ በሙላ ትንቀጠቀጠ ፣ የስልኩን እጀታ አንደያዘች ።

«አልነገረችኝም ። ምናልባትም ረስታው ይሆናል» አለ ።

የሱም ድምፅ እንደ እሷ ድምፅ ውጥረት ይሰማበት ጀመረ።

«ካንች ጋር እንደተለያየችው ቀለል ያለ የልቧ ድካም በሽታ ስለተነሳባት ከሆስፒታል በኋላ ረስታው ይሆናል ፣ ያው ላትረሺው እንደምትችይ . . .»

«አመጣች ! » አለችና ዝም አለች ። ግን ወዲያው—



t.me/OLDBOOKSPDF

«አሁንስ እንዴት ነው ተሻላት?» ስትል ጠየቀች።

«አሁን ደህና ናት ። ከዚያም አልፎ ባለፈው ሳምንት ባል አግባታ አሁን ማጆርካ ውስጥ ትገኛለች» አለ ማይክ ።

አንድ ነገር መጥቶ እጉሮሮዋ ላይ ተሰነቀረ ። ውሻ! የኔን ሕይ ወት ብልሽትሽቱን አውጥታ ስታበቃ እሷ ተሰርጋ ትምነሽነሽ እንጂ ! አለች፣ በሀሳቧ ። ጥርሷን ማንቀራጨጭም አማራት ። ስልኩን እጆሮው ላይ ድርግም ማድረግም አሰኛት።

«ይህ እንኳ ከቁም ነገራችን ውጭ ነው» አለ የማይክል ድምፅ «እና መቼ እንገናኝ ትያለሽ ? »

«አንችልም ብዬ ነገርኩህ' ኮ »

ይህን ያለችው በፍጥነት ነበር ፣ እንትፍ ያለችበትንያህል ።

ጉዳዩ አስደንግጦት ወይም አስገርሞት አይኑን ገርበብ አደ ረገ ። ግን ብዙም አልተጨነቀም ። ጉልበት አልነበረውም፣ ደክ ሞት ነበረና ።

«እሺ ይሁን፣ተሸንፍኩ ። ላሁኑ ማለቴ ነው፣ምናልባት ሀሳ ብሽን ከቀየርሽ ፌይርሞንት ሆቴል ነኝ። ደውይልኝ»

«አልደውልም»

«ደግ»

«ደህና ደር' ሚስተር ሂልያርድ»

«ደህና ደሪ' ሚሪ አዳምሰን»

እንዴት ባንዴ ነገሩን ቁርጥ አደረገው ! ደሞም ፈፅሞ ማይ ክልን የመሰለ ነገር የለውም! የደከመ፣ ሁሉ ነገር ገደል ይግባ ብሎ የተወ ይመስላል ። በነዚህ ሁለት ዓመታት ውስጥ ምን ደር ሶበት ይሆን? ምን አጋጥሞት ይሆን?

ስልኩን ከዘጋች በኋላ ለረጅም ጊዜ ስለማይክል ብዙ ጥያቄ ዎች ጠየቀች። ስለማይክል ባያሌው አሰበች።



t.me/OLDBOOKSPDF

## ምዕራፍ ሃያ ስድስት

«ውዴ ዛሬ በጣም ፀጥ ብለሻል። ቅር የተሰኘሽበት ነገር አለ ?» አለ ፒተር ግሬግሰን ምሳ የሚበሉበትን ጠረጴዛ አሻግሮ እያየ ።

ሜሪ ምንም አልሆንኩም በሚል መንገድ ራሷን ነቅንቃ ወይን የተቀዳበትን መለኪያ እያሽከረከረች ፡—

«ምንም አልሆንኩም» አለች «ምንም አልሆንኩም ። ቅር ያለኝ ነገርም የለም ። እያሰብኩ ነው— ስለምጀምረው አዲስ ስራ። አዲስ ፕሮጀክት ሳስብ ሁሌም እንዲህ ያደርገኛል ። ከአእምሮዬ ማውጣት አልችልም »

ይህን ያለችው ስታብል ነበር ። ይህን ደግሞ እሷም ታውቀ ዋለች፣ ፒተርም ያውቀዋል ።

ነገሩ ሌላ ነበር።

ከትናንት በስቲያ ምሽት ማይክል ከደወለ ጊዜ ጀምሮ ናንሲ ዛሬን መኖር አልቻለችም ። ወደ ትናንት እየተጠለፈች ከዛሬ ሁለት ዓመት በፊት የሆነውን ሁሉ ታሰባለች ። የምታስበው ሁሉ የመጨረሻዋን ቀን ነበር።...ቢስክሌቶቻቸውን ሲነዱ፣ወደ ባዛሩ ሲገቡ ፎቶ ግራፍ ሲነሱ፣ካንዲ ፍሎስ ስትልስ ... ሰማያዊዎቹን መቁጠሪያዎች በባህሩ ዳርቻ ላይ ስትቀብራቸው፣ የገቡት ቃል . . .

ያን ለት ማታ የለበሰችው ቀሚስ፣ማይክልን ልታገባ ስትወጣ እና . . እና በመጨረሻ የማይክል እናት ድምፅ . . እሷ በፋሻ ተደግልላ ያነጋገረቻት ።

ይኸ ሁሉ ልክ እንደፊልም ባይኗ ላይ ጎልቶ ይታያት ነበር። ስንቴ ሌላ ነገር ልታስብ ሞከረች።ግን አልቻለችም ። ከዚህ ሀሳብ ልታመልጥ ኩቶ አልቻለችም ።



t.me/OLDBOOKSPDF

«ውዷ ግን . . ግን . . ደህና ነሽ?» አለ ፒተር በመጨነቅ ።

«ምን ትሆናለች ብለህ ነው? አይዞህ አትጨነቅ ። ደህና ነኝ፣ በእውነት ደህና ነኝ ። ይቅርታ ዛሬ መቼም አስጨነቅኩህ ። ምናል ባትም ደክሞኝ ይሆናል፣ በቃ» አለች ፣

ሆኖም አላመናትም ። አይቷላ የተጠናወተው የሚመስል ገፅ ታዋን ።

የተከፋ ፊቷን፣ በዓይኖቹዋ መካከል የተቋጠረ ግንባሩዋን አይቷል ።

«ከሬ ጋር በቅርብ ተገናኝታችሁ ነበር?» አለ ፒተር ።

«አልተገናኘንም ። አንድ ቀን ምሳ እጋብዛታለሁ እያልኩ አልቻልኩም።ኤግዚብሽኑ ከተከፈተ ወዲህ ስራ በዛ» አለች ። ኤግ ዚብሽኑን ስታነሳ ውለታውን በሚነግር ድምፅ ነበር የተናገረችው ፈገግ ብላ ። ከዚያም አከታትላ፡—

«ምን! እንደምታየው ከፎቶ ግራፍ ማጠቢያ ክፍል ወጥቼ አላውቅም» አለች።

«እንዲህ በጓደኝነት ግለቱ ሳይሆን እንደሐኪም አነጋግራሽ ታውቃለች ወይ? ማለቴ ነበር» አለ ።

«እንዲያውም ። አልነገርኩህም እንጂ ከገና በአል በፊት ያን ጉዳይ ጨረስን ብዬ?»

«ግን እኮ ማን እንደሆነ ውሣኔውን የሰጠው አልነገርሽኝም ። አንቺ ትሆኚ፣ እሷ »

«የወሰንኩት እኔ ነኝ ። ግን ስነግራት አልተቃወመችም » አለች ።

ፒተር የአእምሮ ሕክምና እንደሚያስፈልጋት በመጠቆሙ ናንሲ ትንሽ ቅር አላት ። ስለዚህም ሕክምናው እንደማያስፈ ልጋት በተዘዋዋሪ እንዲህ ስትል ልትነግረው ሞከረች ።



t.me/OLDBOOKSPDF

«ፒተር ምንም የመረበሽ ስሜት የለብኝም ። ድካም ብቻ ነው ። ደግሞ እሱ ይለቀኛል »

«ይሆናል ። ግን ልቤ ይጠራጠራል ። ምክንያቱም አየሽ እፊቴሽ ላይ የሆነ ነገር ይታየኛል ። . . . ማለት ከሁለት ዓመት በፊት የነበረው ነገር ፥ የሆነው ሁሉ እየመጣ የሚያስጨንቅሽ ይመስለኛል »

ይህን ሲል እየተጨነቀና ሁኔታዋን እያጤነ ነበር ። ሰምታው ሽምቅቅ ስትል ሲያይ ደነገጠ ። ራሱን ጠላ ።

«የምን ያለፈ ነገር?» አለች ሜሪ« የማይረባ ነገር አታምጣ »

«ያ ሆነ ማለት እኮ አእምሮሽ ትክክል አይደለም ማለት አይደለም። ያለ ነው። ምክንያቱም እንዲህ አይነቱ ነገር ቶሎ አይለቅም ። ቁስሉ እንዲህ በቀላሉ አይሽርም ። እስከ አስር ዓመት እስከ ሃያ አመት የሚሰቃዩ ሰዎች አሉ ፣ አደጋ ከደረሰባቸው በኋላ። ውስጥሽ ሁሌም ያስታውሳል ። ሀሳቡን አዘውትረሽ ገሸሽ ካላደረግሽው አይለቅሽም »

«አድርጌዋለሁ ፣ ለቆኛልም»

«እሱን እንግዲህ በሚገባ እምታውቂው አንቺ ነሽ ። ሆኖም አትዘናጊለት። ልትደብቂው አትሞክሪ ። ያ ከሆነ በትንሽ በትንሹ ውስጥ ለውስጥ ይጎዳሽና ሕይወትሽን ይሰንክለዋል። ችሎታሽንም ውሱን አድርጎ ያስቀረዋል ። እኔ እንኳ ይህን ያህል መናገርም አያስፈልገኝም ። ግን አንቺ መጠንቀቅ ይኖርብሻል ። ከፊ አሊሰን ጋር ያለውን ግንኙነትም ለተወሰነ ጊዜ ብትቀጥይው የሚበጅ ይመስለኛል»

ይህን ሁሉ ሲል ጉዳዩ እንዳስጨነቀው ይታወቅበት ነበር ። ይህን ብሎም ትክዝ አለ ።

«ከፊ ጋር መቀጠሉ እንኳ አያስፈልገኝም» አለች ሜሪ ።

ይህን ካለች በኋላ መልስ ሊሰጣት አልፈለገም ። መከራከር የለበትም ። ዝም ብሎ እጅዋን ይዞ ተይው እንደማለት ያህል መታ



t.me/OLDBOOKSPDF

ሙታ አደረገው። ጉዳዩን ስላነሳና ስለረበሻት ግን ይቅርታ አል ጠየቅም ። ሁኔታዋ ሁሉ ነገሩ አሳሳቢ እንደሆነ በግልፅ እንዲያይ አድርጎአታል ።

በዚህ ሁኔታ ትንሽ እንደቆዩ—

«እሺ እንግዲህ።አሁን ብንሄድ ምን ይመስልሻል?» አለ ።

ይህን ሲል ከልቡ ፈገግ እያለ ነበረና እፀፋውን ልትመል ስለት ሞከረች። ግን አልቻለችም ። ልታምንለት አትፈልግም እንጂ ግምቱ ልክ እንደሆነ ገብቷታል ። ዋሸታዋለችና ፈገግታው እንቢ አላት ።

ከምግብ ቤቱ እንደወጡ ፡

«ቤት ላድርስሽ? ሲል ጠየቃት ።

«አያስፈልግም ፤ ወደ ኤግዚብሽኑ አዳራሽ ጎራ ብዬ ጃክን ላነ ጋግረው አስቤአለሁ። የምናዘጋጃቸው ነገሮች አሉ» አለች።

«ደግ» አለ ፒተር ።

እጇን እትከሻዋ ላይ ጣል አድርጎ ወደ ፀደዩ የፀሐይ ብርሃን ገቡ። ጧት መሬቱን ሸፍኖ የነበረው ጉም በኖ ጠፍቶ ቀኑ ብሩህ ሆኗል ።

የምግብ ቤቱ የቆሙ መኪናዎች አስተናባሪ የፒተርን ጥቁር አውቶሞቢል ነድቶ እመንገዱ አስገብቶ ሲያቆማት ፒተር የእንግዳ መቀመጫውን ጋቢና በር ለናንሲ ከፈተላት ። ገብታ ተቀ መጠች። ከዚያም በወዲያኛው በር ዞሮ እንኳው መቀመጫ ወን በር ላይ ተቀምጦ መሪውን ሲይዝ ቀሚሷን እያስተካከለች ፈገግ አለች። በሀሳብ ተውጣ ። ምን ያህል እንደሚያስብላት ፣ የቱን ያህል እንደሚጨነቅላት ይገባታል ። ሆኖም ለምን እንደሚያፈ ቅራት አይገባትም ። ትጠራጠራለች። ለምን ? ትላለች። ስለፈጠረኝ ፍቅሩን ለፍጡሩ ሊሰጥ የሚገባው ዓይነት ፍቅር ይሆን ? ወይስ ፊት ስለምንሳው አላገኛትም ብሎ ስለሚያስብ ? እንጃ ።

ሆኖም ሁልጊዜም መንገድ እምትዘጋ እሷ ናት ። ይህ ሀሳብ ስላለባት ይሆናል. . . ነፃ አትሆንም፣ ከፒተር ጋር ስትሆን። እሱ ግን



t.me/OLDBOOKSPDF

በጣም መለሰ ስትል ለስለስ ባለ፣ ግን ውጫዊ ባጠነከረው ድምፅ፦

«የለም የለም፣ የፌ አሊስንን ሕክምና መከታተል አለብሽ። የገመትሽውን ያህል ቀስሉ አልዳነም ። ቆርጠሽ ካልተጋፈጥሽው ደም ሊድን አይችልም» አለ ።

አይናን ከድና አዳመጠችው

ግን እንዴት አድርጋ ትጋፈጠው ? ምን ብላ ትጋፈጠው ? ብት ጋፈጠውስ የሚድነው ነገር ምንድነው?ያለፈው ነገር ማለት ማይክ ማለትእኮ ነው ። ለማይክ ያላትን ፍቅር ደግሞ ምንስ ብላ እንዴ ትስ አድርጋ ልትረሳው ትችላለች ? ማይክ ስልክ እንደደወለላት፣ ድምጹን ስትሰማ እቅፍ አድርጋ ልትስመው ምን ያህል እንደ ጓጓች፣ እንዴት አድርጋ ትንገረው ለፒተር ? ቢያቅፋት የተመኘች ውን፣ ማይክን ያለመቸውን ምን ጉልበት አግኝታ ብታስረዳው ይገባዋል ? እንጃ . . . እንጃ . . .

«እሺ ፒተር አስብበታለሁ» አለች ፊን ማነጋገር አለብሽ አላት ።

«እንደሱ ነው የሚሻለው ። አሁን እንዴት ነው እቤትሽ ባደር ስሽ አይሻልም ? » አለ ። ተስማማች ። አደረሳት ። ከመኪናው ስት ወርድ፦

«ቤት ላስገባሽ ? » ሲል ጠየቃት ።

« አይ ተወው ። እራሴ እገባለሁ» አለች ።

ጉንጩን ሳመችው ። ዞር ብላ ሳታይ ወደ ህንፃው ገባች ።

እቤቷ እንደገባች በቀጥታ ወደ አልጋዋ አመራች ። ፍሬድ (ውሻዋ) ይዘል ፣ ጭራውን ይቆላ ፡ ምላሱን ያንቀላብጥ ነበር ። አል ጋዋ ላይ ተዘረረች ። ዘሎ አልጋው ላይ ወጣ ። ግን ጨዋታ አላስ ኛትም ነበረና ገፍታ አስወረደችው ። አልተመለሰም ።

በጀርባዋ ተዘርራ ኮርኒሱን እየተመለከተች ለረጂም ጊዜ ባሀሳብ ተውጣ ቆየች ። ብዙ ብዙ አሰበች። ሀሳቧም እግር እጅ አልነ



t.me/OLDBOOKSPDF

በረውም ። በመጨረሻ ስልኩ ተንጫረረ ። ፒተር ይሆን ? አለች በሀሳቧ ። ማንም ይሁን ደክሞኛል ፣ ወሰነች ። አላነሳውም አለች። ስልኩ መንጫረሩን ቀጠለ ። ፒተር ነው ። ደህንነቷን ሊጠይቅ መሆን አለበት ። ላንሳው ይሆን? አዎ ማንሳት አለብኝ አለች።

ስልኩ አላቋረጠም ። ተነሳች። አነሳችው ።

«ሃሎ» አለች።

«ሚስ አዳምሰን?» አለ ደዋዩ።

እምላኬ ምን አልኩህ ? ፒተር አይደለም ። ራሱ ነው። አንድ ነገር የሰራ አካላቷን ገዘፋት ። ረጅም ትንፋሽ ከሰራ አካላቷ ወጣ። እንደምንም ብላ፡—

«በስላሴ ይኸርሀለሁ ማይክ ፣ ተወኝ ! እባክህ ተወኝ !» ብላ ዘጋች ስልኩን ።

ማይክል ግራ ተጋብቶ መነጋገሪያውን በአትኩሮት ተመለከተው ። ምንድነው ? ምንነካት ? . . .

. . . ደሞስ ለምን ማይክ አለችኝ ? . . .



t.me/OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ ሃያ ሰባት

በማግስቱ ጧት ሜሪ ከድንክዬ ውሻዋ ከፍሬድ ጋር ወደ ጋለሪው (የኢግዚብሽን አዳራሹ) ስትገባ ደካከሟት ነበር ። ከፒተር ግሬግሰን ጋር ያጋጠማት አስደንጋጭ ነገር ትናንትን ደግማ እንድትኖረው አስገደዳት።ኪማይክል ሂልያርድ ጋር ለመኖር መጨረሻ የሆነችዋን ቀን በዚያች ሌሊት ከሀ እስከ ፐ አስታወሰቻት። ያንለት እሷና ማይክል ከሀርቫርድ ተነስተው በቢስክሌት ያደረጉት ጉዞ፤ የላሱት የቀመሱት . . . ሁሉንም እንደገና አደረገችው ። የገቡትንም ቃል ...

እስከ መቼም አልረሳህም ...

እስከ መቼም አልረሳሽም ...

ያችን ቀን ሺህ ዓመትም ብትኖር አትረሳትም ፡ መቶ ዓመት የኖረች ያህል ድክምክም ብሏታል ። እንቅልፍ ባይኗ ትውር ሳይል ወገግ ነበር ያለው ።

ይህም ስለሆነ የአዳራሹ ባለቤት የሆነው ጃክ ፡ ልክ እንዳያት ፡ «ሌት ተቀን ሥራ ! ምንም ረፍት ያገኘሽ አትመስይምኮ የኔ መቤት» አላት «ወይስ ከውድ ዲሬክተራችን ጋር ፓርቲ ቢጤ ወጥታችሁ አመሻችሁ ? »

ቡና ቀዳና ሰጣት ፡ ከተቀመጠች በኋላ ።

ጃክ የፒተር ግሬግሰን የቆዩ ወዳጅ ሲሆን ከናንሲ ጋር ከተዋወቁ ወዲህ እሷንም እየወደዳት መጥተዋል ።

«ሥራ ያልከው ይሻላል —እንጂ ፓርቲ አልነበረም ።

ደስም አይለኝም አለች» ሜሪ ፈገግ እያለችና የቀዳላትን ወፍራም ቡና ፉት እያለች ። ጃክ ሁሉ ነገር ከፈረንሳይ የመጣ ቢሆን ደስ ይለዋል ። ልብሱ ፡ ጫማው ፡ ባርኔጣው ። ይህ የሚጠጡት ቡና ሳይቀር የፈረንሳይ የተፈጨ ቡና አዘጋጅ የቀመመው ነው።



t.me/OLDBOOKSPDF

« ጅል የሆንሽ ልጅ » አለ ጃክ « እንቆቅ መሰል ልጅ በዚህ እድሜው መጨፈር እንዳለበት ለምን ትረሻለሽ ! »

« ሁሉም ቀስ እያለ ይደረስበታል ። አሁን እስኪ ስራዬን ልጥገበው »

ይህን ብላ ለወደፊቱ ልትሰራቸው ስላሰመቻቸው ነገሮች መግለጽ ጀመረች ። በተለይ የቅርብ እቅዷ « የሳንፍራንሲስኮ የበረንዳ ሕይወት » የሚል እንደሚሆን ገልፃለት ነገሩን በእርካታ ተቀብለው ፣ እንዲህ ሲል ፡—

« በጣም ግሩም የሆነ ሀሳብ ነው ። ከእንግዲህ ነገ ዛሬ ሳትይ እንደምትጀምሪ ተስፋ አለኝ »

ይህን አለና ቀና ብሎ ካያት በኋላ ጉዳዩን እንድታብራራለት ሊጠይቃት ሲል ፀሐፊው የቢሮውን በር ከፍታ ኧረ-ዝም-በሉ ጉድ-ነው ! የሚል የጣት ማስጠንቀቂያ አሳየቻቸው ።

«ጉዳችን ! ምናልባት አንዷ የከንፈር ወዳጅህ መጥታ ይሆን ?» አለች ናንሲ ፣ የውሸት እየደነገጠችና እያሾፈች ።

«ይሆን ይሆን ?» አለ በውሸት ድንጋጤ ።

ከዚያም ወደ ፀሐፊዋ ሄዶ እየተንሾካሾኩ ማውራት ቀጠሉ ። ናንሲ ጃክን ስታይ ጉዳዩ ምን ይሆን ስትል አሰበች ። ምክንያቱም በጃክ ገፅታ ላይ የእውነተኛ አድናቆትና ደስታ ቅይጥ ጎልቶ ይታይ ነበር ።

«እምና እንዴታ !» አላት በመጨረሻ ለፀሐፊው ። ወጣት ፀሐፊዋ ጃክ እወንበሩ ላይ ከተቀመጠ በኋላ ፡—

«የሚደንቅ ነገር ነው ። ትልቅ የምሥራች ይዤልሻለሁ » አለ ጃክ ፣ ይህን ጊዜ የቢሮው በር ተንኳኳ ።

« አንድ በጣም በጣም ታላቅ የሆነ ሰው ፎቶግራፎችሽን እንደሚፈልጋቸው በመጠቆም ሲፈልግሽ መጥቷል ፡ አለ ጃክ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ይቺ ኩሩዋና የመጣው ቢመጣ የማትደነቀዋ ሜሪ ሳትቶር በትንሹም ቢሆን በደስታ ሳትፈለቀቅ አትቀርም ሲል አሰበ ። አያት ። እሷ ያው ነበረች ፤ ፀጥ እንዳለች ። የገመተውን ያህል ቀርቶ በመጠኑ እንኳ ደስታ ፀጥታዋን አልገሰሰውም ።

«በቀጥታ ወደ መጣሁበት ቁም ነገር ልገባና ጉዳዩን ላስረዳችሁ ? » ሲል ጠየቀ ማይክል ።

«እንዴታ » አለ ጃክ ማይክልን ተከትላ ጉብታ እቢሮው ውስጥ የቆመችውን ፀሐፊ ለማይክል ቡና እንድትቀዳለት በእጁ ምልክት እየሰጣት ።

ይህን ካደረገ በኋላ ማይክልን ለማዳመጥ ተደላድሎ ተቀመጠ ። ይኸ ነገርኮ ቀላል ነገር አይደለም ። ይህን ዕድል እንደ ሚያገኝ ቢነገረው ማንኛውም የሥነጥበብ ባለሙያ ነፍሱን እስከ ማጣት እንደሚታገል ፣ እንደሚጋደል ለጃክ ግልጽ ሆኖ ታየው። ያለምንም ጥረት እንዲህ ሰተት ብሎ ሲመጣ ግን ተገረመ ።

ይበልጥ የተገረመው ግን በሜሪ ነበር ።

ማይክል የፕሮጀክቱን ዓላማ ገልያላቸው ሲያበቃ ሜሪን አያት ፣ ጃክ ደስታ ሳይሆን እፊቷ ላይ ምሬት የተቀላቀለበት ፊዝ ተመለከተ ። እንዴ ! ሲል ፣ ሜሪ ማይክን እያየች ፤

« ግን እንጃ ፣ ይኸ ነገር አሁንም ከልቤ አልገባም ። አሁንም ቢሆን መልሱ አይሆንም መሆኑን ነው » አለች ።

« ምን ? ማለት ይህን ጉዳይ ከዚህ በፊት ተነጋግራችሁበታል ማለት ነው ? » አለ ጃክ ግራ እየተጋባ ።

ማይክ ፈጠን ብሎ ይገልፅለት ጀመር ።

«አዎ» ሲል፣ « ከዚህ በፊት ማለት በመጀመሪያ የሥራውቹን ወጥነት ያየው እንዴ ባልደረባችን ነበር ። ከሱ ጋር ተነጋገሩ ። እልሆነም ። ከዚያ ከእናቴ ጋር ተገናኝተው ነበር ። ከሷ ጋር ተነጋግረው ምን እንደደረሱ አልተነገረኝም ነበር ። በሚገባ



t.me/OLDBOOKSPDF

ማለቱ ነው ። ብቻ ሁላችንም የፕሮጀክቱን ጉዳይ . . . እኔም በስልክ አነጋግሬአት ነበር ። መልሷ ጠንከር ያለ አይሆንም ሆኖ ቀይቷል ። ገፅ ለገፅ ተገናኝተን ብንነጋገር የሚሻል ስለመሰለኝ ነው ዛሬ የመጣሁት »

ምን ዓይነት ነገር ነው በሚል አስተያየት አያት ጃክ ። አንገቷን በአሉታ እየነቀነቀች

«የማይሆን ነገር ነው » አለች ።

« እኮ ለምን ? ለምን ? » አለ ጃክ እየተቁናጠረ ።

« ስለማልፈልግ »

«ቢያንስ ምክንያቱን . . . ማለት የማትፈልጊበትን ምክንያት ልትገልጭልኝ ትችያለሽ ? » አለ ማይክል በለሰለሰ ድምፅ።

እዚህ ድምፅ ውስጥ አዲስ ነገር ተሰማት ። እዚህ ድምፅ ውስጥ ማይክል ያለውን ሥልጣን የሚያውቅ ሰው እንደሆነ ተገነዘበች ። ይህን በራሱ ላይ ያለውን መተማመን ትወደዋለች ። ናፈቀት ። በዚህም ተናደደች ። ይህ ንዴት ግን የመውደድም ሆነ የናፍቆት ስሜቷን ከልቧ ሊያወጣው አልቻለም ።

« ለምን ? » አለ ማይክል ደግሞ ።

«ምናልባት ቅብጥብጥ ሰው ብሆን ይሆናል ። ቅጥየለሽ የጥበብ ሰው ብለህ ጥራኝ ብትፈልግ ። የፈለገውን ብትለኝም፣ ምክንያት ብነግርህ ባልነግርህም መልሱ አንድ ነው . . . እሺ ችላም » አለች ።

ይህን ብላ ቡናዋን ጨልጣ ሲኒዋን ካስቀመጠች በኋላ ኩት ቀመጠችበት ተነስታ እዚያው ቆማ ላፍታ ሁሉቱን ሰዎች ተራ በተራ አየቻቸው ። ከዚያም እጅዋን ዘረጋች ። ማይክልን ስትጨብጥ በዕምና ጨበጠችና ፡

« የፎቶግራፍ ሥራዎቼን ስለወደዳችሁልኝ አመሰግናለሁ ። ለሥራችሁ መቃናት ደሞ ችግር አይኖርም ። የተሻለ ሰው ልታገኙ ትችላላችሁ ። እንዲያውም በዚህ አዳራሽ ሥራዎቻቸውን



t.me/OLDBOOKSPDF

የሚያሳዩ አያሌ ሥዓሊዎችና ፎቶግራፍ አንሺዎች ስላሉ በጃክ በኩል በቀላሉ ልትገናኚዋቸው ትችላላችሁ » አለች ፡

«ሌላ ሳይሆን አንቺን ነው እምንፈልገው » አለ ማይክል።

ማይክል ይህን ሲል ግትር እንደማለት ብሎ መሆኑ በድምጹ ይታወቅ ነበር ። ቅሬታም ይሰማበት ነበርና ጃክ በይቅርታ አድርግልን አስተያየት አየው ። ሜሪ ግን ፍንክች አላለችም ። ከዚህ በፊት ያጠፋችው በቂ ነው ። ለጥቅሟ ደስታዋን ሸጣለች ። ዳግም ? — አይለምዳትም ። ስለዚህም ፡

«ይህ እንኳ አጉል ነገር መሰለኝ ፤ ሚስተር ሂልያርድ ። የልጅ ነገር ሆነ ልበል ። እኔ አይሆንም ካንተ ጋር አልሰራም ብያለሁ ። ስለዚህ ሌላ ሰው መፈለጉ ይሻላል ። ከዚህ የቀለለ ምንም ነገር ያለ አይመስለኝም » አለች ።

«እኔን ተይኝ ፡ ለድርጅቱ ከሌላ ሰው ጋርም ለመሥራት ፈቃደኛ አይደለሽም ? »

በአሉታ ራሷን ነቅንቃ ወደ በሩ አመራች ።

« ባይሆን አስቢበት ። አስበሽበት እንኳ ልትነግሪኝ አትሞክሪም ? »

ይህን ሲናገር አበሩ ዘንድ ደርሳ ነበር ። ጥያቄውን ስትሰማ ፊቷን ወደነሱ ሳታዞር ቆመች ። የምታስብ ትመስላለች ። ከፍታ በኋላ ራሷን በአሉታ ነቅንቃ በሩን ከፍታ ስትወጣ « አይሆንም አልኩ » የሚለውን ቃል ሰሙ ። ፍሬድ (ውሻዋ) አብሯት ወጣ ።

ማይክል ጊዜ አላጠፋም ። ጃክን ሳይሰናበት ከመቀመጫው ብድግ ብሎ ተከትሏት እየተጣደፈ ወጣ ። ጃክ ነገሩ ሁሉ መላ ቅጥ የጠፋው ሆኖበት ባለበት ላይ እንደተቀመጠ ቀረ ።

« እንዴ . . . ጠብቂኝ » አለ ማይክ ፡ ከአዳራሹ እንደወጣ ሜሪን እየጠራ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ለምን እንዲህ እንደሚያደርግ ራሱን አልጠየቀም ። ይህን ያህል መለማመጥ ይኖርብኛል ? አላለም ። ተከተላት ። ደረሰባት እና ጎን ጎኗን እየሔደ ፣

« አብሬሽ በእግሬ ትንሽ መጓዝ ይፈቅድልኛል ? » አላት ።
«ትርፉ ድካም ነው እንጂ ትችላለህ » አለችው ።

አንዴም ዞር ብላ አላየችውም ። ቀጥታ ፊት ለፊቷን እየተመለከተች ጉዞዋን ቀጠለች ፤ እሱም በጎን በጎንዋ ።

«ለምንድነው እንዲህ ክርር ብለሽ እምቢ ያልሽው ? የተቀየምሽበት ጉዳይ አለ ? በኔ ወይስ በሌላ ሰው ? ወይስ የሰማሽው ነገር አለ ? ስለድርጅቱ ? ወይም ስለኔ » አለ ማይክል ።

« ሰማሁ አልሰማሁ ፤ ተቀየምኩ ቀረ ልዩነት አያመጣም »

« ለምን አያመጣም ? ያመጣል ። በደምብ አድርጎ ልዩነት ያመጣል » አለና ፊት ለፊቷ ቆመ ። አቆማት ። ያዛትና ፣

« ንገሪኝ ፣ መንገር አለብሽ ። የማወቅ መብት አለኝ ። »
« መብት አለህ ? » አለችው

ሁለቱም ፊት ለፊት ተፋጠው ቆሙ ። ለዘለዓለም አለም በዚህ ሁኔታ የቆሙ ያህል ነበር ። ከዚህ በኋላ ንዴቷ ጋብ አለ ።

« ነገሩ ምስጢር ነው » አለች ።
«ደግ ፣ ግን ንክ እንዳይደለሽ ይገባኛል »

ይህን ስትሰማ ከት ብላ ሳቀችና —
«እንደሆንኩስ ማን ያውቃል ? » አለች ።

« ንክ ናት ብዬ ባምን ነገሩ ቀለል ይለኝ ነበር ። ግን ምስለሽ አልታየሽም ። አይደለሽም ። የሚታየኝ ነገር ወይ እኔን ትጠያለሽ ወይ ኮተር ሂልያርድን » አለ ።

በልቡ የማይረባ ሀሳብኮ ነው ። እኔንስ ምን አድርጌያት ፣ የት አውቄያት ? ኮተር ሂልያርድስ ምን አድርጎ ? ኮተር



t.me/OLDBOOKSPDF

ሂልያርድ ስሙን ጠብቆ ሽርና ማጭበርበር ካለበት ውል ተጠ ብቆ የሚኖር ድርጅት ነው ሲል አሰበ ። በመቀጠልም ይህ ፈጽሞ ሊሆን አይችልም ። ምናልባት ፣ አዎ ምናልባት ካንድ የቅ ርንጫፍ መሥሪያ ቤት ባልደረባ ከሆነ ሰው ጋር አንድ ግንኙ ነት ፈጥራ በዚያ ቂም ይዛ ይሆናል ። እንዲያውም እንዲያ ቢሆን ነው—አለ አሁንም በልቡ ።

« አንተን አልጠላሁም ሚስተር ሂልያርድ » አለች ቆይታ። ጉዞ ጀምረው ነበር ይህን ስትለው ።

«ግን እንዴት ያለሽ ተዋናይ ነሽ እባክሽ » አላት ፊቱ በፈገግታ ተሞልቶ ። ከተገናኙ ጊዜ ጀምሮ ይህን ማይክል አላ የችውም ፣ ይህ ያ ማይክል ነው ። ማይክል ፤ ያ የዱሮው ፣ እሷ አፓርትማ ውስጥ ወይም እሌላ ቦታ ከቤን አብሯ ጋር ነቃ ሁ ብሀ የሚጫወቱት ፣ የጫዋታ ሽር የሚችለው ማይክል ነው . . . ይህን ያለፈ ጊዜ ነገር ስታስብ ልቧ ተሸነፈ ። ማይክልን ላለማ የት ወዲያ ማየት ጀመረች ።

« ቡና ልግዛልሽ ? » አላት ።

አልችልም ልትለው አሰበች ። ግን ደግሞ ሀሳቧን ለወጠች። ሁልጊዜ ከምሰቃይ ዛሬውኑ ተስፋ ላስቆርጠው ፣ ዳግም በዚህ ጉዳይ ላይ መነጋገር የለብንም ስትል አሰበች ። ይህን አሳብም

« ይቻላል » ስትል መለሰችለት ።

ወደ ሉንዲት ኤስፕሬሶ ሄዱ ። ወፍራምና ለየት ያለ ቡና የሚጠጣባት ቤት ።

ሁለቱም ቡና አዘዙ ። ቡናው ሲመጣ ለሷ ከጨመረች በኋላ ሁለት እንኳር ስኳር የያዘውን ማቅረቢያ ሰጠችው ። ሳታ ስበው ሁልጊዜ ሁለት አንኳር እንደሚጨምር ታውቃለች ። እሱ ግን እንዴት አወቀች የሚለውን ጥያቄ አላሰበም ። ምክንያቱም ሀሳቡ እሷን በማሸነፍ ላይ ነበረና ትዝ ሳይለው ቀረ ። ስኳሩን ስለሰጠችው አመስግኖ ማስቀመጫውን እጠረጴዛው ላይ አኖረው። ቡናውን እያማሰለ ወሬ ቀጠለ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

«ፎቶግራፎችሽን ላይ አንድ ነገር ይሰማኛል ። ምን እንደሆን ግን ሊገባኝ አልቻለም ። ማለት ይኸ ነው ይኸ ልልሽ አል ችልም ። አንድ የማይገባኝ ስሜት ግን እንዳለ እርግጠኛ ነኝ ። ምንድነው ? እላለሁ ። አላገኘውም ፤ እንደ ጥንውት ቁጠረው ። ምን ማለቴ ነው ? አዲስ አይሆንብኝም ። ከዚህ በፊት ያየኋቸው፣ በደንብ የማውቃቸው ይመስለኛል ። ልትይው የፈለግሽው የሚ ገባኝ ፤ ያየሽው የሚታየኝ ይመስለኛል ። ምን ማለት ነው ታዲ ? የሆነ ትርጉም አለው ?»

እዎን ማይክል ። ደንበኛ ትርጉም አለው ። ለሥዕል እመ ርጣቸው የነበሩ ሀሳቦችን ነው ለፎቶግራፍም የምመርጣቸው ። ሥዕሎቹ ደሞ እንዳንተ የሚገቡት ሰው አልነበረም ፤ አለች በሀሳቧ ።

በቃል፤—

«አዎን ትርጉም አለው ። ፎቶግራፎቼን ሳነሳ'ኮ ሃሳቤ ወዳ ንተም እንዲደርስ ለማድረግ አስቤበት ነው » ስትል መለሰችለት።

«እሱማ ለሁሉም ሰው ነው ። እኔ'ኮ ምልሽ . . . እንዴት ብዬ ላስረዳሽ ? ልክ አንዱን ፎቶ አየሁ ልበል ። ያኔ . . . ምን ልበልሽ ያን ፎቶ በደንብ —አለ አይደለም . . . እማውቀው ይመ ስለኛል ። ብቻ ስናገረው ለራሴም የጅል ነገር ሆኖ ይሰማኛል » አለ ።

ግን ማይክል እኔን አታውቀኝም ? ሌላው ይቅር እስኪ እኒህን ዓይኖች እያቸው ። አታውቃቸውም ? በልቧ ።

እንዚህን ጥያቄዎች ልትጠይቀው አማራት ። ጸጥ ብለው ቡናቸውን ሲጠጡ ቆይተው ፤—

« በቃ በእምቢታ ልትጸና ነው የሚል ደስ እማይል ስሜት ደርሶ ተሰማኝ » አላት በመከፋት ።

ራሷን በእምንታ ነቀነቀች ፤
« ልክ ነህ አይቻልም » እያለች ።



t.me/OLDBOOKSPDF

« ችግሩ ምንድነው ? ገንዘብ ይሆን ? » አለ ።
« በፍጹም የገንዘብ ጉዳይ አይደለም »
«እኔም አልመሰለኝም »

እውነቱን ነበር « አልመሰለኝም » ያለው ። ቢመስለው ኖሮማ ገና ቅድም ያዘጋጀውን የሥራ ኮንትራት ውል አውጥቶ ያሳያት ነበር ። ውሉን አዘጋጅቶ ይዟል ። በዚያ ውል ብትስማማ አጅግ ብዙ ገንዘብ ታገኛለች ። ግን ሁኔታዋን ሲያይ የገንዘብና የውልን ነገር አለማንሳቱ የተሻለ ሆኖ አገኘው ። ይህን ጉዳይ ቢያነሳ ነገሩን ይበልጥ እንደሚያከረው ተገነዘበ ።

« እንዲህ ምርር ብለሽ እምቢ እንድትይ ያደረገሽን ነገር ባወቅኩ » አለ

«ምንም አይደለም ። አንዳንዴ ነካ ሲያደርገኝ እንዲህ ነኝ ። ያለፈ ትርዒን የምበቀለው በዚህ ሁኔታ ነው ። ሌላ ምንም» አለች ።

የልቧን ስትናገር ደነገጠች ። እሱ ግን ምንም አድናቆት ወይም ትርጉም አላሳየም ።

« እኔም የዚያ ዓይነት ነገር ሳይሆን አይቀርም እያልኩ ሳስብ ነበር » አለ ። በመካከላቸው ሰላም ነበር ። ግን ደግሞ ማይክል አንድ ዓይነት መራራነት ያለው ጣፋጭ ስሜትም ይሰማዋል ። ያ ስሜት ምን እንደሆነ ግን ሊገባው አልቻለም ።

« እማዬ በሥራሽ እጅግ ተደስታለች ። ይህ ራሱም የሚገርም ነው ። ምክንያቱም ለሆነ ላልሆነው የምትንገበገብ ሰው አይደለችም » አለ ማይክል ።

«እንዳልከው ነው እኔም እምሰማው ። አንድ ውል ስትዋዋል እንኳ ሁሉን ነገር አሳስራ ነው አሉ » አለች ናንሲ ።

« ነው ። . . . ግን እንዲያ ማድረጓም ከንቱ እንዳይመስልሽ ። ኮተር ሂልያርድን እዚህ ያደረሰችው በዚህ ጥንካሬዋ



t.me/OLDBOOKSPDF

ነው ። ግራ እኔ ምን ችግር አለብኝ? በሚገባ የተያዘች መርከብ በካፒቴንነት እንደምረከብ ነው የሆነልኝ »

« እንዴት ታድለሃል »

ይህን ስትል ድምጿ ምሬት የተሞላ ነበር ። ይህን ደግሞ ማይክል አጢኖታል ። ለምን ? ግራ ተጋባ ። ለምን ? ተቅበዘበዘ ። እና እጁን አንሳና አንገቱ ላይ ያለች ትንሽ ጠባሳ መነካካት ጀመረ ። ይሄኔ ሜሪ ድንገት ሲኒዋን አጠረጴዛው ላይ አስቀ ምጣ ቀና ብላ አየችው ። እና—

« ምን ሆንህ ነው ? » ስትል ጠየቀችው ።

« ምኑ ? » ሲል በጥያቄ መለሰላት ።

« ጠባሳው » አለችው ።

ዓይኗን ከዚያች ጠባሳ ላይ ልትነቅል አልቻለችም ። ያች ጠባሳ ምን እንደሆነች በሚገባ ታውቃለች ። ያን እለት . . .

« ምንም አይደለም ። አብሮኝ የቆየ ነው » አላት ።

« የቆየ አይመስለኝም ! በቅርብ ጊዜ የሆነ ይመስላል » አለ ችው ።

« ሁለት ዓመት ያህል » አለ እየፈረ ። « ምንም አይደለም ! ቀላል ነገር ነው ። ከጓደኞቼ ጋር ቀላል አደጋ ደረሰብንና በቃ »

ነገሩን አቃልሎ ሊያልፈው ሲፈልግ ስታይ ብልጭ አለ ባት ። ፊቱን በያዘችው ቡና ልታጠናፍረው አማራት ። የውሻ ልጅ ። ትንሽ አደጋ ይበል ! አመሰግናለሁ የኔ ቆንጆ ። አሁን ሁሉ ነገር ግልፅ ሆኖልኛል አለች በሀሳቧ ። እና . . . እና ቦርሳ ዋን አነሳች ። ተነሳች በከፋ ዓይን ቁልቁል ተመለከተችው ። ልት ዉብጠው እጅዋን ዘረጋችለት ።

« ጥሩ ጊዜ አብረን አሳለፍን ። አመሰግናለሁ ። እዚህ በምት ቆይበት ጊዜ ሁሉ መልካም እንዲያጋጥምህ እመኝልሀለሁ ። » አለች



t.me/OLDBOOKSPDF

« ምን ? ልትሔጂ ነው ? ምን መጥፎ ነገር ተናገርኩ ? » አለ ማይክል ፤ ነገሩ ሁሉ ግራ ሆኖበት ።

ኧረ የክርስቶስ ያለህ ምናይነቷ አስቸጋሪ ፍጡር ናት ያጋጠመችኝ ! አሁን ደሞ እስኪ ምን ሆንኩ ነው እምትለው ? አሰበ ። ምን ብዬ ይሆን ? ቀና ብሎ አያት ። ዓይኗን ሲያይ እዚያ ውስጥ የሚንቀለቀለውን ቁጣ ሲመለከት ደነገጠ ።

« ምን ? አጠፋሁ እንዴ ? » አለ ደግሞ ።

«እንክት አርገህ እንጂ» አለችው ።

ደንግጦ ዝም ብሎ ያያት ጀመር ።

«አየህ ፣ ስለዚህ ስለደረሰብህ አደጋ አንብቤ ነበር ። ትዝ እንደሚለኝ ከሆነ እንዲህ ቀላል ተብሎ የሚጠራ አደጋም አል ነበረም ። እነዚያ ያልካቸው ሁለት ጓደኞችህም እንደገመትኩት በጣም ነበር የተጐዱት ። ግን አንተ ጾነስተኛ አደጋ ትላለህ ። እንዲያው ለሰው ትንሽ እንኳ ልብ የለህም ? አታዝንም ማይክል ? ሁሉን ትተህ ሴትም ቀንም በቃ ስለዚህ እርጉም ሥራህ ብቻ ነው እምታስበው ማለት ነው ? »

« ምናባሽ . . . ምን ነካሽ ? ደሞስ በኔ ጉዳይ ምን ጥልቅ አደረገሽ ! ? »

« ሰው ነኝና ያገባኛል ። አንተ ግን ሰው አይደለህም »

« እብድ ነሽ »

« አይይ ! ተሳሳትክ ጌታው ። እብድ አይደለሁም ። የለም አሁን እብድ አይደለሁም »

ይህን ተናግራ እየተፈናጠረች ወጣች ። ማይክል ካለበት ንቅንቅ አላለም ነበር ። እስክትወጣ ድረስ በመገረም ዓይኑን አፍጥጦ ተመለከታት ። ካይኑ ስትሰወር ድንገት ነቃ ። ተፈናጠረና ተነሳ ። የአምስት ዶላር ኖት አጠረጴዛው ላይ ወርውሮ እንዳበደ እየሮጠ ወጣ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

እዎ መንገር ይኖርበታል ። የለም አደጋው ቀላል አደጋ አልነበረም ። ሕይወቱን የለወጠ አደጋ ነበር ። በጣም የሚወዳት ! ሕይወቱን ፍቅሩን ያጣው በዚያ አደጋ የትነሳ ነው ። ይህን ሊነግራት ይገባል —አሰበ ። ግን ይህን ለማወቅ ምን መብት አላት ? ተናደደ ። ቢሆንም . . . መንገድ ላይ ሲደርስ ታክሲው ይዟት ነጕደ ።

አልነገራትም ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ ሃያ ስምንት

ልክ እወደቡ ደርሳ የካሜራ መትከያውን ባለሶስት እግር መቋሚያ እንዳስተካከለች አንድ ሰው ቀጥ ብሎ ወደ እሷ ሲመጣ ታያት ። አረማመዱ ወደ እሷ መሆኑ አጠያየቃት ። ማን እንደሆነ አወቀች፤ ቁይታ ።

ማይክል ! ጣጣ ነው ፤ አለች በሀሳቧ ።

«አንድ ነገር ልነግርሽ ነው የመጣሁት» አለ እፊቷ ተገትሮ።

«መስማት አልፈልግም» አለችው ቀና ሳትል ።

«እሱ እንኳ ያስቸግራል ። ምክንያቱም ፈቀድሽም ቀረ እነግ ርሻለሁ ። እና ብታስቢበት ይሻላል። ስለግል ሕይወቴ የሆነ ያል ሆነ ነገር እየጎረጎርሽ ሀሳብ የመስጠት መብት የለሽም ። እንዲህ ያለህ ሰው ነህ ፤ እንዲህ አይነት ፍጡር ነህ ልትይኝ አትችይም። አታውቂኝም ፤ አላውቅሽም ። ይህን ለማለት ምን መብት አለሽ !?» አለ ።

ትናንት የተናገረችው ቃል ሌሊቱን ሙሉ እንደጥርስ ህመም ሲጠዘጥዘው ነው ያደረው። «ስለኔ ስነምግባር አስተያየትም ሆነ ፍርድ ለመስጠት የሾመሽ ማን ይሆን ? የኛ ዳኛ ! ምን መብትስ አለሽ?!» ጦፈ ።

«ምንም» አለች ረጋ እንዳለች ። « ግን ደግሞ የማየው ነገር ደስ አላለኝም »

ይህን ስትል ቀና ብላ አላየችውም ። የካሜራ ሌንስ ትቀይር ነበር ።

«ያየሽው ነገር ምን ይሆን እባክሽ ? »

«ዛጎል ። ቀንዳውጣው የሞተ በድን ቅርፊት ። ልቡ ፍቅርን የተራቆተ ፤ ስራ ፤ ስራ ብቻ የሚል ሰው። ስለማንም ደንታ የሌለው



t.me/OLDBOOKSPDF

ማንንም የማይወድ፣ ምንም የማይሰጥ ፣ ምንም ያልሆነ ባዶ ሰው። ይህንን ነው ያየሁት ። »

«አንች ውሽ ! አንች ማን ሆነሽ ፣ ምን አውቀሽ ነው ደሞ ስለኔ የውስጥ ስሜት ይህን ያህል እምታወሪው ! ለመሆኑ አንችን ሁሉን አዋቂ ያደረገሽ ማነው በይ ! » አለ ።

ዝም ብላ ካሜራዋን አዙራ የአሸዋ ኮረብታ ላይ አነጣጠ ረች።

«አንችን እኮ ነው እማናግረው! ሰሚኝ !» አለ ካሜራዋን ሊይዝ እየሞከረ ። ቀደም ብላ ፊት ለፊቱ ቆመችና አፈጠጠችበት። ከዚያም እሳት ለብሳ እሳት ጎርሳ፣—

«ለምን አትተወኝም ። ለምን እሰው ኑሮ ውስጥ ገብተህ የሰው ሰላም ትነሳለህ ?» አለችው ።

«ማ ? እኔ ? እኔ አንች ኑሮ ውስጥ አልገባሁም ። እኔ ጥቂት ፎቶግራፎችን መግዛት ብቻ ነው እምፈልገው ። በቃ ። በተረፈ ያንቺን ኑሮም ፣ ያንችን አስተያዬት አልሻም ። ፎቶግራፍ ! በቃ!»

በንዴት መንቀጥቀጥ ጀመረ። እሷ ግን አልመለሰችለትም ። እንደቆመ ትታው ሄደች። አንድ ብርድ ልብስ ላይ የተቀመጠ የወ ረቀት መያዣ ቦርሳ አነሳች ፣ ዚፑን ከፍታ ከውስጡ አንድ የታ ጠበ ፎቶግራፍ አወጣች ። እና ፣

«ፎቶ ግራፍ ነው የምትፈልገው አደል? ይኸውልህ ። ይኸን ወስደህ የፈለገህን ነገር አድርገው ። እኔን ግን ተወት አርገኝ። እሺ» ብላ ሰጠችው ።

ተቀበላት ። አላነጋገራትም ። ሄደ

ዞራ አላየችውም ። ስራዋን ቀጠለች። ስራ ፣ ስራ ፣ ስራ ። ጸሐይ ብርሃኗን ስትነሳ ካሜራው መስራት ሲሳነው ስራዋን አቆመች ።

እቤቷ እንደደረሰች እንቁላል ጠብሳ በልታ ቡና አፍልታ ከጠጣች በኋላ ወደ ፎቶግራፍ ማጠቢያ ክፍሏ ገባች።



t.me/OLDBOOKSPDF

ያንለት የተኛችው ከሌሊቱ ስምንት ሰዓት ሲሆን ነበር ።

ጧት በሁለት ሰዓት ለመነሳት ወስና ባሰደወል ሰዓቷን አስ ተካክላ ተኛች።

ባለችው ሰዓት ነቃች። ደወሉ ቀሰቀሳት ። ሰውነቷን ታጥባ ፣ ልብሷን ለባብሳ ፣ ቡናዋን እየጠጣች ጋዜጣዋን እንብባ ከቤቷ ስትወጣ ልክ ማታ ባቀደችው መሰረት ለሶስት ሰዓት ጥቂት ደቂቃ ይቀር ነበር ። ደረጃውን ስትወርድ ሁሉ የምታስበው ስለቀኑ ስራዋ ነበር።ፍሬድ ኋላ ኋላዋ ቱስ ቱስ እያለ እሷ እያሰበች ከቤት ወጡ። የውጪውን ደረጃ በመውረድ ላይ እንዳለች አንድ ደረጃ ሲቀራት ቀና ብላ ተመለከተች ። ከመንገድ ማዶ ማይክል ሂልያርድን ቆሞ አየችው። እጁን አውለበለበላት ።

አጠገቡ ባለው የጭነት መኪና ላይ በትልቅ ሰሌዳ የተለጠፈ ስእል አየች ። ተመለከተችው ። ትናንት ጧት የሰጠችው ፎቶ ግራፍ ነበር ። ወስዶ በትልቁ አትልቶ አሳጥቦ እንዳች በሚያህል ሰሌዳ ላይ ለጥፎ ይዞት መጥቷል ።

ድንገት ሳቋ መጣ ። እደረጃው ላይ ቁጭ ብላ ትንከተከት ጀመር ። ፊቱ በፈገግታ በርቶ ፣ ሰውነቱ በደስታ ተሞልቶ ወደ ተቀ መጠችበት መጣ። አጠገቧ ሲደርስ በፈገግታ እንደበራ ፣ በደስታ እንደተሞላ እደረጃው ላይ እጎኗ ተቀመጠ።

«ቆንጆ ነው? ወደደሺው ?» ሲል ጠየቃት።

«አንተ ግን የምትገርም ሰው ነህ!» አለችው ።

«ልክ ብለሻል ። ግን እንዴት ነው? ደስ አይልም?» ሲል አሁ ንም ደግሞ ጠየቃት።ደስ ይላል ብትለው እንዴት አድርጎ ይደሰት።

«እይው እስኪ ፣ አሪፍ አሪፎቹን ፎቶግራፎች መርጠን ከፊ ሉን እንዲህ በትልቁ አሳጥበን እህከምና ማእከሉ እናት ላይ ብን ስቅላቸው ጉድ አይደለም ? » አላት ።

ጉድስ ራስህ ነህ—ስትል አሰበች።

ደስ እንዳላት ሲያይ በጣም ደስ አለው ። ስለዚህም ነፃ ሆነ።



t.me/OLDBOOKSPDF

«አሁን እዚህ ምን ጎሰተን? ተነሺና አንድ ቦታ ሄደን ቁር ሰችንን እንብላ» አላት ።

ዛሬ ቆርጦ ተነስቷል ። እሺ ካያሰኛት ይች ቀን አታልፍም። ለዚህ ሲል ከሰዓት በፊት ያለውን ጊዜ በጠቅላላ ምንም ቀጠሮ አልያዘበትም ።

እሷም ብትሆን ይህንን ውሳኔውን ከሁኔታው ተረድታለች። ውሣኔው ልቧን ነክቷታል ፣ አስደንቋታል ። በዚህም ላይ ጭቅጭቅ መፍጠሩን ስሜቷ አልተቀበለውም ።

«እንሂድ» አላት ።
«እምቢ ማለት ነበረብኝ። ግን አልልህም» አለች።
«ጥሩ ዘይደሻል ። አብረን እንሂድ?» ሲል ጠየቃት ።

«በምን? በዚያ?» አለችው የጭነት መኪናውን እያሳየችው። ነገሩ አስቂኝ ሆነባት ።

«ምናለበት ። ይሄዳል እኮ » አለ ።
ተስማማች ።

አሳ አጥማጆች ወደሚመገቡት ሆቴል አመሩ ። መኪናውን እበሩ ላይ አቆሙት ። በዚያ አካባቢ የጭነት መኪና አዲስ አል ነበረምና ማንም ጉዳዬ ብሎ አላያቸውም ። ገትረውት ወደቁርስ ገቡ ። ማንም ያን ያህል ፎቶግራፍ አንስቶ ይወስዳል የሚል ፍር ሀት አልነበረባቸውምና ጠባቂ አልፈለጉም ።

ያንለት ቁርሱ ሳይቀር በሚያስገርም ሁኔታ ድንቅ ሆነላቸው። ቡናቸውን ጠጥተው እስኪጨርሱ ድረስ በመካከላቸው ጭቅጭቅ አልተነሳም ። ያኔ፡—

«አሁን ተስማማሽ አይደለም?» ሲል ጠየቀ ።

ነገሩን በጥያቄ ያቅርበው እንጂ በፊቱ ላይ የሚታየው ፈገግታ ርግጠኛነትና ኩራት አረፍተነገሩን «አሸነፍኩሽ» የሚል ስሜት ሰጥተውት ነበር ።



t.me/OLDBOOKSPDF

«በፍጹም አልተስማማሁም ፡ ሆኖም ደስ የሚል ቁደስ በሳሁ፡ ደስ የሚል ጊዜ አሳለፍኩ» አለችው ፡

«ትንሽ ውለታ ሲውሉልኝ ውለታ አነሰ ብዬ በጥፊ የምመታ ፅው አደለሁም ፡ ሆኖም ያ ሙሉ መንገዱ አይደለም»

«ሙሉው ምንድ ነው? እስኪ ንገሪኝ»

«አሃ! ስለኔ አንች መናገርሽን ፡ መፍረድሽን አቁመሽ እኔ ራሴ እንድናገር ፈቀድሽልኝ ማለት ነው ? »

ነገሩን እንደቀልድ ቢለውም በውስጡ ሽሙጥ ነበረበት ፡

«ባለፈው ቀን ያልሽው በመጠኑም ቢሆን እውነትነት አለው ፡ ለቢሮዬ ብዙ እጨነቃለሁ» አላት ፡

«ሌላ የምታስብለት ምንም ነገር የለህም? »

«በእውነት ከሆነ ሌላው ነገር ለኔ ይህን ያህልም አደለም ፡ ምናልባትም ብዙዎቹ በኑሮ ተስተካክለዋል የምንላቸው ሰዎች ካለስራ ሌላ ሕይወት የላቸው ይሆናል ፡ ጊዜም ቦታም አይገኝ ? »

«ታዲያ ይኸ ጅልነት ነው፡ በጣም ትልቅ ጅልነት ፡ ስራህን ለማሳካት ኑሮህን መስዋእት ማድረግ የለብህም ፡ ካልካቸው ትል ልቅ ሰዎች መካከል ደግሞ ኑሮንም እየኖሩ ስራቸውን በሚገባ የሚያካሂዱ ይኖራሉ»

«ካንቺ እንነሳ፡ ሁለቱንም አጣምረሽ ማድረግ ትችያለሽ ?»

«አሁን አልችልም ፡ ወደፊት ግን አይቀርም፡ ቻልኩም፡ቀረም ቢያንስ እንደሚቻል ግን አውቃለሁ»

«ምናልባትም እንዳልሺው ይሆን ይሆናል ፡ እኔም ዱሮ እንደ ማስበው አላስብ ይሆናል »

ይህን ሲላት አዘነች፡ ልቧ ለሰለሰ ፡

«ካለፉት ጥቂት ዓመታት ወዲህ ሕይወቴ እጅጉን ተለው ጧል ፡ በፊት ያተድኩት ነገር ሁሉ ከልቡናዬ ጠፍቷል ፡ መልሺ



t.me/OLDBOOKSPDF

ያን ለማሰብ ደግሞ አቅም የለኝም ። አልሞከርም ። በጭራሽ ። የሆነ ሆኖ አልተጎዳሁም ። መተኪያ የሚሆን መሳ አገኝቻለሁ» አለ ።

ለምግሉ የኮተር ሂልያርድ ፕሬዚዳንት መሆንን የመሰለ ሲል በሀሳቡ ጨመረ ። ለመናገር ግን አፈረ ።

«እሃ ገባኝ። አላገባህም ማለት ነው» አለች።

«እንዲያውም ። ጊዜም የለኝ ፤ ፍላጎትም » አለ ።

እንዲያ ነውን አለች በሀሳቧ። እንዲያ ከሆነ ባደጋ ተመካኝቶ የቀረው ጋብቻ እንኳን የቀረ ።

«ኑሮን ተቆርጦ የደረቀ ቅጠል አደረግከው ኮ» አለች ።

«ለጊዜው ለኔ እንዲያ ነው። ላንቺስ እንዴት ነው ? »

«እኔም አላገባሁም»

«ይገርምሻል ፡ እንዲያው የኔን የአኗኗር ዘዴ ታረካከሽቀለሽ እንጂ ያንችንም ሕይወት ከኔ በምንም ሁኔታ የተለዩ ሆኖ አላገኘ ሁትም ። እንደኔ በስራ የተጠመድሽ ነሽ ። እንደእኔ ብቸኛ ነሽ ። እንደእኔ በግልሽ ትንሽ አለም ውስጥ ተቀብረሽ ነው የምትኖረው ፤ ያው ነሽ ። ታዲያ እንዲህ ሆነሽ ሳለ አጉል ፍርድ ትሰነዝሪብኛ ለሽ ? ደግ ነገር አይመስለኝም» ይህን ሲናገር ድምፁ ለስላሳ ቢሆ ንም ወቀሳ ያዘለም ነበር ። ስለዚህም ተሰማት ።

«ይቅርታ አድርግልኝ ። ምናልባትም ልክ አይደለሁም ይሆ ናል» አለች።

ይህ ቢሆን ይህ ነው ብሎ ለማስረዳት ከባድ እንደሆነ ተረ ዳች ። የነገራትን ሁሉ አስታወሰች ። በማውጠንጠን ላይ እንዳለች እጁን እጅዋ ላይ ጣል ሲያደርገው ተሰማት ። በስራ አካባቢ የኮረ ንቲ ምግድ ተሰራጨባት ። እሳት ያቃጠላት ያህል መነጨቀችው ። ደነገጠ ። ግራ ተጋባ ።

«ምንነትሽን መረዳት የማይቻል አስቸጋሪ ሴት ነሽ» አለ ።

«ነኝ።ራሴ እንኳ ልናገር ብል ለመግለጽ አዳጋች የሆኑ ብዙ ነገሮች አሉ» አለች።



t.me/OLDBOOKSPDF

«አስበሽበት ብትሞክሪኝ ደግ ይመስለኛል ። ለምን ? በይኝ። የመሰልኩሽን ያህል አስፈሪ ፍጡር አይደለሁም ።»

«እንዳልሆንክም በሚገባ አውቃለሁ»

ይህን ብላ ቀና አለች ። አየችው ። ማይክል ነው ። የተሰበረው ማይክል ። የተሰበረች እሷ ። የተጣጡ ሁለት ። ያኔ ደስ እሚላት ማልቀስ ብትችል ፣ ብታነባ ፣ እሪ ብትል ነበር ። አየችው ። ተለያይተዋል ። መንገዳቸው ለየብቻ ሆኗል ።

በሕይወት እያለህ አልለይህም ፣ ይህና ሁን . . . አልለይህም —ቃል ኪዳናቸው ትዝ አላት ።

ይህ ግን ! መለያየታቸውን ፣ መንገዳቸው ለየብቻ መሆኑን ማወቋ ግን ፣ ይህና ሁን እንደማለት ነው ። በቃ . . .

«ብሄድ ይሻላል መሰለኝ—ወደ ሥራ» ኢለች ሰዓቷን አየት አድርጋ ።

«ወደ ይቻላል ተቃረብኩ ይሆን—ለድርጅታችን ትሠሪያ ለሽ ለሚለው ጥያቄዬ ? »

«አይመስለኝም—አይቻልም» -አለች ።

ይህን ሲሰማ ካሁን በኋላ የፈለገውን ቢያደርግ እሺ ሊያሰኛት እንደማይችል ገባው ። እስከዛሬ የለፋው ልፋት ሁሉ ከንቱ እንደነበረ ተገነዘበ ። በጣም ጠንካራ የሆነች ሴት ናት ። ግን ደግሞ ወዲታል ። ሁሉን ነገር ትታ ሰው ስትሆን ፣ ስትሸነፍ ምን ዓይነት ልብ እንዳላት ሲያስብ ተደነቀ ። የልቧን ንጽሕና ፣ ግርነትዋን ፣ ውስጡዋን ሲያይ ይህን ያህል ጊዜ ማንም ሰው መስጦት ፣ ሰበት የማያውቀውን ያህል እንዳቀረበችው ተገነዘበ ።

«አንድ ቀን ራት አብረን እንድንበላ ብጠይቅሽ እሺ የምትይ ይመስልሻል ፣ ሜሪ ? ማለት እንዳሸነፍሽኝ ተረድቻለሁ ። ለማጽናናት ያሀል እሺ አትይኝም ?» አለ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ፊቱ ላይ የነበረውን ነገር አይታ በለሆሳስ ሳቀች ። ከዚያም እጇን በአይዞሀ አትዘን ማጽናናት መንገድ ቸብ ቸብ ካደረገችው በኋላ ፤

«እኔም ደስ ይለኛል ። ግን አሁን አይሆንም ። በቅርብ ከከተማ መውጣቴ አይቀርም» አለች ።

ምን ዓይነት የተገረመ ነገር ነው ! አሁንም አልቻሊም ። ዙሪያ ገባውን መሸነፍ በመሸነፍ ሆነ ማለት ነው ፤ አሰበ ።

«ወዴት ነው ለመሄድ ያሰብሽው ? »

«ወደ ምሥራቅ ልመለስ አስቤአለሁ ። ለጥቂት ቀን ለግል ጉዳዩ »

ይህን የወሰነችው ድንገት ነበር ። ከማይክል ጋር እየተነጋገሩ ሳለ ። ከግማሽ ሰዓት በፊት ። ቀድሞ ማድረግ እንደሚገባት አልወሰነችም ። አሁን ግን ወሰናለች ። ፒተር እንዳላት ለማድረግ አሰባለች ። ያለፈውን ቁስል መሸፋፈን ሳይሆን ገልጦ ምን ያህል እንዳመረቀዘ ፤ እንደተመረዘ ማዩት ። ፒተር ልክ ነው ባንድ በኩል ስትል ነበር ። አሁን ግን ልክ እንደነበረ በሚገባ አረጋግጣለች ። ገልጣ ማዳን አለባት ። ገልጣ አይታ ማከም ይገባታል ። እሱ ፒተር እንዳለው ።

«በሚቀጥለው ጊዜ ሳንፍራንሲስኮ ስመጣ ስልክ እደውልልሻለሁ ወይም መጥቼ እጠይቅሻለሁ ። ያኔ ከዚህ የተሻለ ዕድል እንደሚገጥመኝ ተስፋ አደርጋለሁ »

ምናልባት አለች በሐሳቧ ። ምናልባትም ያኔ የፒተር ግሬግሰን ባለቤት ሆኜ ታገኘኝ ይሆናል ። ምናልባትም ያኔ ከበሽታዬ ተፈውሼ አልፈልግህ ይሆናል ።

ጸጥ ብለው መኪናው ወደቆመበት ሄዱ ፤ ጉን ለጉን ። ቤቷ በር ላይ አወረዳት ። ያኔም ሆነ እመንገድ ላይ ብዙ ንግ



t.me/OLDBOOKSPDF

ገር አልተለቀወጡም ። ከመኪናው ስትወርድም ብዙ አልተናገረችም ። ቁርስ ስለጋበዛት አመስግነችው ። ጨበጠችው ። ሄደች ።

አለቀለት ። ተሸነፈ ። ይህን እያሰበ ወደ ቤቷ ስትሄድ አያት ። መጠን የሌለው ኀዘን ሲወድቅበት ፣ ልቡን ሲያስ ጨንቃት ተሰማው ። አንድ ልዩ የሆነ ፣ ካለው ነገር ሁሉ የላቀ ነገር እንዳጣ ፣ እንደጠፋበት ሆኖ ተሰማው ። ምን እንደሆን ግን ፈጽሞ አላወቀውም ። የሥራ ውል ? ተወዳጅ ሴት ወይስ ጥሩ ጓደኛ ? እንጃ ። አንድ ነገር ግን ከእጁ ሾልኮ ጠፍቶበታል ። በዚህ በረጅም ጊዜ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ይህ መጠንህ የማ ይባል ብቸኝነት ተሜኘው ። መኪናውን አስነስቶ ወደ ሆቴሉ ፈረጠጠ ።

ሜሪ ስልክ በመደወል ላይ ነበረች ፣ ለፒተር ግሬግሰን ።

«መቼ አልሺኝ ? ዛሬ» አለ ፒተር ግሬንግሰን «ውዴ ዛሬ ስብሰባ አለብኝ »

«እንዲያ ከሆነ ስብሰባውን እንደጨረስክ እፈልግሃለሁ ። በጣም እፈልግሃለሁ ። ነገ መሄዴ ነው»

«የት ? ወዴት ? ለስንት ጊዜ !»
«ስትመጣ እነግርሃለሁ ። ዛሬውኑና ። ማታ »

«እሺ . . . ይሁን ። እሺ ከምሽቱ አምስት ሰዓት አካባቢ ። ግን ስብሰባውን . . . የቂል ሥራ መሰለኝ ። ሊዘገይ አይችልም»

«በፍጹም አይቻልም» አለች ።

ሁለት ዓመት ሙሉ ቆይቷል ። ያን ያህል ጊዜ ግቀየቱም ራሱን የቻለ ቂልነት ነበር ። እብደት አለች በሐሳቧ ።

«እሺ እንግዲህ እመጣለሁ »

ዘጋ ። ወዲያው ወደ አየር መንገድ ቢሮ ደወለች ፣ ቲኬት እንዲይዙላት ። ቀጥላም ወደ እንስሳት ሐኪም ደወለች ፤ ለፍሬድ ማቆያ እንዲያዘጋጅላት . . .



t.me/OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ ሃያ ዘጠኝ

ያንለት ከሰዓት በኋላ ሜሪ ፌ አሊሰንን ለማነጋገር ወደ መሥሪያ ቤቷ ሄደች ። ሜሪ ወደ ፌ መሥሪያ ቤት ከሄደች ወራት አልፈው ነበረና ወደ እንግዳ መቀበያው ክፍል ስትገባ ምንም እንዳልተቀየረና እንደ ተለመደው ምቹ እንደሆነ ተገነዘበች።

እምቹው ወንበር ላይ ተቀምጣ እግሯን ፊት ለፊቱ ዘርግታ ጣቶቿን እየተመለከተች ቀስ በቀስ ሐሳብ ውስጥ ገባች ። ሐሳቡ ጭልጥ አድርጐ ወስዷት ነበርና ፌ ስትገባ አልሰማ ቻትም ።

«እንቅልፍ እየታገለሽ ነው ወይስ እጸጥታ ቁዘማ ላይ ነሽ?»

የፌ አሊሰን ድምጽ ከሐሳቧ የመለሳት ሜሪ ፈገግ ብላ ፊት ለፊቷ በሚገኘው ወንበር ላይ የምትቀመጠው ፌን በጸጥታ ተመለከተቻት ።

«እንቅልፍም ቁዘማም አይደለም ። ዝም ብሎ ሐሳብ ነው» አለች ሜሪ ።

ፌ «ደግ» በሚል አስተያየት እያየቻት ፈገግታዋን መለሰችላት ። ሜሪ ፌን ስታይ ደስ አላት ። ይህንንም ፣

«ናፍቀሽኝ ኖሯል ባክሽ ፣ ሳይሽ በጣም ደስ አለኝ» ስትል ገለጸችላት ።

«ድንቅ ነገር ሆነሻል ልበልሽ ወይስ ከዚያም ከዚያም ስለ ምትሰሚው ሰልችቶሻል?» አለች ፌ አሊሰን በፈገግታ በርታ።

በፌ አሊሰን ፊት ላይ ያየችው ደስታ ተጋባባትና ሜሪም መሳቅ ጀመረች ። ቀጥላም «ድንቅ ነሽ መባል ምን ይሰለቻል ብለሽ» ስትል ተናገረች ። ይህን ስትል ደስ አላት ። ለፌ እሊ



t.me/OLDBOOKSPDF

ሰን ባይሆን ይህን እውነት እንኳ ሊመናገር አስቸጋሪ እንደነበር ታውቀዋለች ።

«ዛሬ ደርሺ ዱብ ስል ለምን መጣች ? የሚል ጥያቄ እን ደሚመጣብሽ መቼም የታወቀ ነው» አለች ሜሪ አዳምሰን ።

«ጥያቄው ብልጭ ብሎብኝ ነበር» ፊ ግምቷን አረጋገጠች ላት ። ፊት ለፊት ፡ ዓይን ለዓይን ግጥምጥም አሉ ። ቦግ ድር ግም ፈገግታ ተለዋወጡ ። ከዚያም ሜሪን ሐሳብ ጠለፋትና ወደ ቁዘማዋ ገባች ። ለተወሰነ ጊዜ ጸጥታ ሆነ ። ከዚያም ሜሪ ድንገት ቀና ብላ በቦዛዛ ድምጽ ፤

«ማይክልን አገኘሁት‘ኮ» ስትል ተናገረች ።
«ሊፈልግሽ መጣ ?»

«መልሱ አዎም ሊሆን ይችላል ፡ አልመጣምም ሊሆን ይች ላል ። ነገሩንኳ የፈለገው ያገኘውም ሜሪ አዳምሰንን ነው »

ቀጥላም ማይክል ለምን እንደፈለጋት ባጭሩ ነገረቻት ።
«ሦስቱም ሰዎች ይህን ያህል ለሙኑሽ ?»
«ሽንጣቸውን ገትረው»

«ደህና ምልክት ይመስላል ። በነገራችን ላይ . . . ከሦስቱ አንዱም እንኳ ማን መሆንሽን አላጤኑም ? »

«ሁለቱ ወንዶች አላወቁም ። ማሪዮን ግን አውቃለች ። እንዲያውም ማይክልን የላከችውም አውቃ ነው የሚል ግምት አለኝ»

«ለተወሰነ ጊዜ ጸጥ አሉ ። »
«ስትገናኙ ምን ስሜት ተሰማሽ ? »
«ከማን ጋር ? »
«ከማሪዮን ሂልያርድ ጋር»

«አስቀያሚ ፡ አስቀያሚ ስሜት ነበረ የተሰማኝ ። ልክ እንዳየኋት ያደረሰችብኝ ስቃይ ሁሉ ፍንትው ብሎ ታየኝ ። ጠላ ኋት»



t.me/OLDBOOKSPDF

ብሺ ።

«ምን ልበልሽ ? ያላሰብኩት ነገር አልነበረም ። የናቱ ምትክ እንድትሆን የተመኘኋት ፣ ብትወደኝ ብዬ ያለምኩዋት ፣ የማይክል ሚስት ለመሆን እምበቃ መሆኔን እንድትቀበል የጓጓሁት ። ያ ሁሉ ነገር ትዝ አለኝ»

«አሁንም የማይክል ሚስት ለመሆን አትበቂም እምትል ይመስልሻል ?»

«ያሁኑን አላውቅም ። ብቻ እንጃ ። አየሽ ያንለት እንዳየኋት ብዙው ነገሯ ተለውጦአል ። እንደመሰለኝ የፈጸመችው በደል ከብዷታል ። የተጸጸተችበት ይመሰለኛል ። ለኔ ሳይሆ ለልጅዋ ይሆናል ። እንደገመትኩት ከሆነ ማይክልም የሚመስለውን ያህል ደስተኛ አይደለም»

«ደስተኛ አለመሆኑ ሲሰማሽ ልብሽ ምን አለ ?»
«ቀለል አለኝ»

ሆኖም ለማጋነን የፈለገችውን ያህል አላጋነነላትም ቀለል ማለቱ ። እንዲያውም በጎነን የተሰበረ ድምጽ ነበረ ።

ለተወሰነ ጊዜ ጸጥታ ሆነ ።

«ቆይቼ ሳስበው ግን» አለች ሜሪ ጸጥታውን እየገሰሰች ፣ «ቆይቼ ሳስበው ግን ፣ እሱን ደላው ከፋው ለኔ ያው እንደሆነ ገባኝ ። የኔና የሱ ነገር ያበቃ ነገር ነው ፌ ። ዛሬ እሱም አያውቀኝ ፣ እኔም አላውቀው ። ሁሊታችንም በጣም ተለውጠናል ። ማን መሆኔን ቢያውቅ ሥራዬ ብሎ'ንኳ ሊያነጋግረኝ አይፈልግ ይሆናል ። እኔ ናንሲ ማክአሊስተር ያልሆንኩትን ያህል እሱም ማይክል ሂልያርድ አይደለም »

«ያን ያህል እንደተለወጠ እንዴት ልታውቂ ቻልሽ ?»

«እየሁታ ! መራራ ፣ ጥድፍድፍ ሰው ሆኗል ። ልቡ ቀዝቅዞ ሰብአዊ ስሜቱ ሞቷል ። እዚህ ሁሉ ውስጥ ምን እንዳለ . . . እንጃ ያየሁት ባህርይ ግን አብዛኛው አዲስ ነው»



t.me/OLDBOOKSPDF

«የፈለጉት የማጣት ፣ ተስፋ የመቁረጥ ፣ የጥልቅ ሀዘን ስሜት አይታይብትም ?»

«የለም አልታየኝም ። ይልቅ እኔን ስለመከዳቱ ፣ ስለመጠማቱስ ምን ይሰማሻል ? ልትይኝ የፈለግሽ መሰለኝ ። ቁም ነገሩ ይህ አይመስልሽም ?»

«እኔ እንጃ ። እኔ እንኳ ይህን አላሰብኩም። ግን እስካሁን ይህ አይነቱ ስሜት አለብሽ ማለት ነው ? በተለይም እንደከዳሽ ነው አሁንም የቆጠርሽው ?»

«እንደከዳኝ'ንጂ እንደሌላ ልቆጥረው እችላለሁ ?» አለች ኩሩር ባለ ድምፅ ! « ፊ ፣ ማይክልን እንዴት መሰለሽ እምጠላው !»

«ምን ያህል እጠላዋለሁ ብለሽ ካሰብሽ አሁንም ሀሳብሽ ሙሉ በሙሉ እሱ ላይ ነው ማለት ነው»

ናንሲ ይህ እውነት እንዳልሆን ሽንጧን ገትራ ተከራከረች ። ምን ያህል እንደምትጠላው እምርራ ተናገረች ። ይህን እያደረገች ሳለችም እንባዋ ተናነቃት ። አለቀሰች ። ፊ አሊስን ይህን ስታይ ነገሩን ለማለሰለስ ፣ ሜሪን ለማፅናናት አልሞከረችም ። ይል ቁንም የተነሳውን ነገር ፍርጥ ለማድረግ ፡-

«ናንሲ ፤ ንገሪኝ ። ማይክልን ታፈቅሪዋለሽ ወይስ ፍቅርሽን ጨርሰሻል ?» ስትል ጠየቀቻት ።

ናንሲ ብላ የጠራቻት አውቃ ነበር ። ናንሲ የፊ አሊስን ጥያቄ ለመመለስ ጊዜ ፈጀባት ። ስትመልስም ጣራ ጣራውን እያየች ሲሆን ፣ ድምጿም ደከም ያለ ነበረ ።

« ናንሲ አሁንም ታፈቅረው ይሆናል ። መቼም የናንሲ ርዝራዥ ከውስጧ አይጠፋም ። እሷ ትወደው ይሆናል ። ሜሪ ግን ማይክልን አትወደውም ። ሜሪ ማለት እኔ ነኝ ፤ ፊ ። አዲስ ህይወት ፣ አዲስ ዓለም ያለኝ ሰው ነኝ ። ልወደው አልችልም ማይክልን !»



t.me/OLDBOOKSPDF

«ለምን አትችይም ?»

«ምክንያቱም አያወደኝም ። እርሱን መርሳት አለብኝ ። ፈፅሞ መርሳት አለብኝ ። ይህን ወስኛለሁ ፤ አውቀዋለሁ ። ስለዚህ ይህን ላማክርሽ ፡ ስለማይካል ፍቅር አንስቼ አንገትሽ ስር ተወሽቄ ላለቅስ አይደለም የዛሬው አመጣጤ ። የተሰማኝን ነገር ላንድ ሰው መንገር እንዳለብኝ በመገመት ነው ። ለፒተር ብነግረው ጥሩ ነበር። ግን ይህን ለሱ መንገር ደግሞ የማይቻል መሰሎ ታየኝ ። መንፈሱን ይረብሸዋል ብዬ ገመትኩ ። ስለዚህ ቀለል እንዲለኝ ላንቺ መንገር እንዳለብኝ ገባኝ ። መጣሁ»

«መምጣትሽም ፣ መንገርሽም ጥሩ ነው ። ደስ ብሎኛል። ግን እልብ ውስጥ የሰረፀን ነገር እንዲህ በቀላሉ በታኝ ፣ ተውኩት በማለት ብቻ ማራገፍ የሚቻል አይመስለኝም ። . . . ያን ያህል ቀላል አይደለም»

«የተራገፈውኮ የዛሬ ሁለት አመት ነው ። እኔ መጭመጭ ብዬ ነውንጂ ። መጭመጭ ማለቴን ደግሞ ስከድ ነበር ። አሁን ግን ግልፅ ሆኖልኛል ። እና—»

ንግግሯን ድንገት አቋረጠችና ቀና ብላ ተቀመጠች ። ከዚያም ፊ አሊሰንን እየተመለከተች ፡—

«ነገ ለጉዳይ ወደ ቦስተን መሄዴ ነው» ስትል ተናገረች

«ለምን ጉዳይ ?»

«ሁሉን ነገር የማራገፍ ጉዳይ ። እኔና ማይክ አንድ ላይ በነበርንበት ጊዜ በጋራ የአደረግናቸው አንዳንድ ነገሮች አሉ ። እስከዛሬ ድረስ ማይክል ይመስለኛል ፣ ያስበኛል ፣ ይፈልገኛል እያልኩ የተውኳቸውን ነገሮች ማለቴ ነው ። ለፍቅራችን ሀውልት እንዲሆኑ ብዬ ነበር የተውኳቸው ። አሁን በቃ ። ሂጄ አንድ ነገር ላደርግ ወስኛለሁ»

«እምትችይ ይመስልሻል ?»

«በሚገባ» አለች ፊ አሊሰንን እንኳ ቁራጥ መስሎ በተሰማት ድምፅ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

«ከዚህ ሁሉ በፊት ማን እንደሆንሽ ፣ ማን እንደነበርሽ ሊገልጽ ይችል መንገር አትፈልጊም ?»

«ፍጹም የማይጠቅም ነገር ነው» አለች እያንገፈገፋት «አለቶ ፤ ዶቶቶ ፤ አልኩሽካ ። በቃ ። በዚያም ላይ . . . ይህን ባደርግ ለፒተርም መልካም አይሆንም» አለች የሀዘን ትንፋሽ በረጂሙ ተንፍሳ ። ተዋላም ፦

«ሬ» አለች ። «ሬ ፤ ፒተርን ላስቀይመው አልፈልግም ። ፒተር ጥሩ ሰው ነው ። የዋለልኝ ውለታ ተቆጥሮ እሚያልቅ አይደለም»

«ያም ሆነ ያ አታፈቅሪውም»፡ አለች ሬ አሲስቶ ።

«አይምስልሽ ። እወደዋለሁ»

«ታዲያ ቃል ለመግባት ፤ እወድሀለሁ ብሎ ለመንገር ችግሩ ምንድነው ?»

«ማይክል ይመስለኛል ። ማይክል በመካከላችን ገብቶ ድንቅር ይል ስለነበረ ነው ብዬ እምናለሁ»

«እሱ ቀላል ነገር ነው’ኮ ሜሪ ። ስሜትን መሸፈኛ ካልሆን በስተቀር እሱ ነገር አልቀለታል ብለናል ገና ዱሮ»

«ብቻ እንጃ» አለችና ንግግሯን አቋረጠች ፤ «ብቻ አንድ ነገር አለ ፤ ለፒተር ቃል እንዳልገባ የሚገረግረኝ ፤ ተይ የሚለኝ ። አንድ የጎደለ ነገር አለ ። ምናልባት . . . ብቻ ማይክልን ተውኩት ብልም ከልቤ አላወጣሁትም ነበር ። ከፊል ልቤ ይመጣል የሚል ተስፋ ላይ ሙጭጭ ብሎ ተጣብቆ ይሆናል ። . . . ብቻ እንጃ አንድ ልክ ያልሆነ ነገር ቢኖር ይሆናል ። ምናልባትም እኔው ራሴ እሆናለሁ»

«ልክ ያልሆነ ነገር ይኖር ይሆናል ብለሽ እንድታስቢ የሚያደርግሽ ምን ይመስልሻል ?»

«ይህንንም በትጡ አላውቀውም ። ምናልባት ፒተር ይወደኛል እንጂ አያውቀኝም የሚል ሀሳብ ሳይኖር አይቀርም በኔ በኩል ። . . . ፒተር ያውቀኛል ፤ እኔን ሜሪ አዳምስንን ማለቴ ነው ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ግን ያለፈ ህይወቴን አያውቀውም ። ባለፈ ህይወቴ የምወዳቸውን ነገሮች አያውቅም»

«አትነግረውም ? ማለት እንዲያውቅ ማድረግ አትችይም ? »

«ምናልባት እችል ይሆናል ። ግን ደግሞ ማወቅ እሚፈልግም አይመስለኝም ። መፈቀሬን እንዳውቅ ሊያደርግ ሲሞክር አየዋለሁ ። ግን ደግሞ ሙሉ እኔነቴን እንዳልሆነም እጠራጠራለሁ»

«ያን ካነሳን ብዙ ነገር ሊመጣ ይችላል»

«ልክ ነሽ ። ያም ሆኖ ግን ፒተር ደህና ሰው ነው ። በፈለግ ኩት መንገድ ብሞክር ጉዳዩ የማይሳካበት ምክንያት አይታየኝም»

«ሊሳካ የሚችለው ካፈቀርሺው ብቻ ነው»
«አፈቅረዋለሁና»

«በሱም ካመንሽበት ደህና ። ዘና ብለሽ የሚሆነው እስኪሆን ጠብቂ ። ከፈለግሺም እንዲህ እንደዛሬው ጎራ እያልሽ ልን ግከርበት እንችላለን—ወደፊት ። ለዛሬ ግን ስለማይክል ምን ፣ ምን እንደሚሰማሽ ተነጋግረን መጨረሻውን ማየቱ ነው ደጉ»

«ይህን የቦስተን ጉዞዬን ሳድርግና ሁሉን ነገር ሳራግፍ ። ከዚያ በኋላ ነፃ እሆናለሁ»

«መልካም ። ስትመለሺ ጎራ በይና ጠይቂኝ ። እንዲያ ማድ ረጉ ጥሩ አይመስልሽም ?»

«በጣም እንጂ !»
ሜሪ አዳምሰን ሁሉ ነገር ቀለል ያላት ሆና ታየች ።

ፌ አሊሰን ሰዓቷን አይታ ዩኒቨርስቲ ማስተማር ስላለባት ልትለያት መሆኑን በማሰብ የመከፋት መልክ ታየባት ። ከዚያም ፡-

«እንግዲህ እንዴት ነው እምናደርገው ? ከቦስተን እንደተመ ለስሽ ደውለሽ ቀጠሮ ብንይዝ አይሻልም ? » ስትል ጠየቀቻት ።
«ልክ እንደደረስኩ እደውልልሻለሁ »



t.me/OLDBOOKSPDF

«መልካም ። እና ደሞ ራስሽን ጠብቂ፣ እሺ ? ያለፈ ነገር እያ ስታወሱ በትዝታ መናበዝ አያስፈልግም ። ቦስተንም ሆነ የት ችግር ካጋጠመሽ ደውዪልኝ ። »

ፌ. አሊሰን ይህን ስትላት ሜሪ ተደሰተች ። እገሌ አለኝ ብሎ ማሰቡ ራሱ ትልቅ ነገር እንደሆነ ገባት ።

ያንለት ከፌ. አሊሰን ጋር ተነጋግራ ስትመለስ ሰሞኑን ከብ ዷት የነበረው ነገር ሁሉ ቀላል ሆኖ ታያት ። ስሜቷም ፈካ ። የዛሬው የፌ. አሊሰንና የሷ ንግግር የሚሰማትን ነገር ለፒተር ግሬ ግሰን ለመግለፅ መንገድ እንደጠረገላት ፣ ወ ሳኔዋንም ለመንገር ቀላል እንዳደረገላት ተገነዘበች ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ ሠላሳ

ያንለት ማታ ሜሪ አዳምሰን ለፒትር ገረገሰን ወደ ቦስተን ለመሄድ እንዳሰበች ነገረችው ።

«ቦስተን? ለምን? ምን ልትፈጥሪ፣ ሜሪ? የምትይው ነገር ፈጽሞ አልገባኝም» አለ ፒትር ።

ያንለት ፒትር ያለወትሮው ሰልችችችት ብሉት ነበር ። እንዲያውም አነጋገሩ የቁጣ ይመስል ነበር ። በመሰላቸቱም፣ ቁጣ ቁጣ ስላለውም ሜሪ አልከፋትም ። የዚህ አዲስ ባህሪ ምክንያቱ ገብቷታል ። ሰሞኑን አላረፈም ። በተለይም ያንለት ቀኑን በሙሉ ተወጥሮ እንደዋለ ታውቃለች ። አሰልቺ ስብሰባዎች፣ ይኸ ወይም ያ ነገር ። አዲስ ስለሚሰራው የህክምና ማዕከል ለመነጋገር ደግሞ ነገ ከአርኪቴክቶች ጋር ቀጠሮ አለው፤ በጧት ። ጣጣ ነው ። ያን ሁሉ ችሎ የዋለ ሰው ገና ነገም እንደማያርፍ ሲረዳ ቢደክም ቢሰለች በተለይም ያሳሰበውን ነገር ሲሰማ ቁጣ ቁጣ ቢለው ይፈረድበታል?

ለፒትርም ሆነ ለሜሪ ያልገባቸው ነገር የፒትር እዚያ ኮሚቴ ውስጥ መግባት ነው ። ምን ሊሰራ ገባ? የተሻለ ሥራ ሊሠራ ሲችል ጊዜውን ለምን ያባክናል? ገልፅ አይደለም ።

«ከመሬት ተነስተሽ ልሂድ ስትዪ በጠቅላላ እብድ መሰልሽኝ» አለ ፒትር «እብደት ነው»

«እብድም አይደለሁም፣ እብደትም አይደለም ። መሄድ ስለአለብኝ ነው ። ስለሆነም ይኸው ወስኜ ጨርሻለሁ ። . . . ፒትር ከዚህ በፊት በሕይወቴ የነበረውን ነገር ሁሉ ሙሉ በሙሉ አራግፌ ጨርሻለሁ ። አንድም ትዝታ ሳይቀር»



t.me/OLDBOOKSPDF

«እኮ እየነው እደል! … ምንም ትዝታ ሳይቀር ስላራገፍ ሽው አይደለም ትላንትና ያልደረሰ የመኪና አደጋ ያን ያህል ያስደነገጠሽና ነፍስሽን ለመግዛት ካንድ ሰዓት በላይ የወሰደ ብሽ! ሜሪ እንደባበቅ። ሙሉ በሙሉ አላራገፍሽውም።ያለፈ ትዝ ታሽን ማሰቴ ነው»

«እመነኝ አንድም ችግር አይኖርም ። አንድ ነገር እለ ፤ ካለፈው ትዝታ የተረፈ። ያንን እንደሚሆን ካደረግኩ በኋላ በቃ! ነፃ ነኝ። ከንገ ወዲያ ነፃ ሆኘ እመለሳለሁ »

«እብዶት ነው አልኩሽ! »

«በፍጹም አይደለም አልኩህ! »

ይህን ያለችው በሙሉ ልብና በተረጋጋ ድምፅ ነበረና ፒተር ግሬግሰንን ገታው ። ፒተር ሕወንበሩ ላይ ወደ ኋላው ተለ ጥጦ ተቀመጠ ። በመስልቸት በረጂሙ ተነፈሰ ። ምናልባትም እውነቷን ሊሆን ይችላል ። አውጥታ አውርዳ የወሰነችው ነገር ሊሆን ይችላል ፣ ሲል እሰበ ።

«ካልሽ ንግዲህ ደግ።ግን ምኑም አልገባኝም።ምናልባት እስ በሽበት ይሆናል ። እንዲያ እንደሚሆንም እምኛለሁ ። ግን ቦስተን ስትሄጂ የምትፈሪው ምንም ነገር የለም?»

«ምን ይነካኛል? ምንም አልሆንም ። እመነኝ»

«እምንሻለሁ የኔ እመቤት ። እንዲህ እሚያሰኘኝ ሰላላመ ንኩሽ ሳይሆን … ፣ ያ ሳይሆን … እንዲያው አንድ ነገር . . . ብቻ አንጃ ክፉ ነገር እንዲደርስብሽ አልፈልግም ። አየሽ ። አንድ ጥያቄ ልጠይቅሽ? ግን . . ጥያቄው ሙሉ በሙሉ የጅል ጥያቄ ሊሆን ይችላል?»

ክርስቶስ አውጣኝ ! አለች ሜሪ በሀሳቧ ። ያን ጥያቄ ባልጠ የቀኝ ። ዛሬ ልመልስለት አልችልም ። እሺ ወይም ፍርጥ አድ ርገሽ ንገሪኝ ቢለኝ ምን ልመልስለት ነው?



t.me/OLDBOOKSPDF

እሷ ይሆን እያሰበች ትዉኑት እንጂ እሱ ያሰበው ደግሞ ሌላ ነበር ።

«ጠይቀኝ» አለች ።

ቶሎ መልስ አልሰጣትም ። ግለትም ጥያቄውን ወዲያው አል ጠየቃትም ። አፕራሲዮን ለመሆን የምትጠባበቅ መሰላት ። ጨነቃት ።

«ማይክል ሂልያርድ እዚህ ሳንፍራንሲስኮ ውስጥ እንደሚገኝ ታውቂያለሽ?»

«እዎ» አለች ረጋ ባለ ድምፅ ።

«ተገናኝታችኋል?»

«አዎ ። ኤግዚብሽን አዳራሽ መጥቶ ተገናኘን ። ለህክምና ማዕከሉ ፕሮጀክት የውስጥ ማስጌጫ ፎቶግራፎች እንድሰራለት ጠየቀኝ ። አይቻልም ስል መለስኩለት»

«ማንነትሽን አውቋል?»

«አላወቀም»

«ለምን አልነገርሺውም?»

እስከ ዛሬ ያልነገረችውን፣ ከማይክል እናት ጋር ያደረገች ውን ስምምነት ለመንገር አመቺው ጊዜ አሁን እንደሆነ ተገነዘበች ። ግን ደግሞ እስከ ዛሬ አቆይታ ዛሬ ብትነግረው ፋይዳ የለውም ። ያለቀለት ነገር ነው ።

«ብነግረው ባልነግረው ምንም ልዩነት እንደማያመጣ ስለ ገባኝ አልነገርኩትም ። ያለፈ ነገር፣ ያለቀ ነገር ሆኗል» አለች ።

«እዚህ ነገር ላይ ... ማለት እንዲህ ስትይ ... ርግጠኛ ነሽ?»

«ርግጠኛ ነኝ ። ስለሆንኩም ነው ወደ ቦስተን እምሄደው»

«እንዲያ ከሆነ እኔም ደስ አለኝ»



t.me/OLDBOOKSPDF

ይህን ብሎ ለጥቂት ጊዜ ዝም አለ ። ገጽታው ላይ ጭንቀት ይነበብ ነበር ።

«ጉዳዩ ከማይክል ጋር የተያያዘ ነገር አለው?» አለ ቶማሎ።

«በፍጹም እንደሱ ብለህ አታስብ ። ማይክልና እኔ አፍም የለን ፤ ትውውቅም የለን ። ዛሬ ለየብቻ ነን ። የምሄደው ካለፈው ኑሮዬ ጋር የተያያዘ ጉዳይ ስላለኝ ነው ፡ ከኔ ኑሮ ጋር ብቻ ። ከዚህ በላይ ለመናገር ግን አልፈልግም»

«እኔም ንገሪኝ አልልም ። እንደፍላጎትሽ ብታደርጊ ነው ይበልጥ ደስ የሚለኝና ነው»

«እግዜር ይስጥልኝ»

ይህን ከተነጋገሩ በኋላ ፒተር ከሜሪ ጋር አልቆየም ። ብቻ ዋን መሆን የምትፈልግ መሰለው ። ስለዚህም ደህና እደሪ ብሎ ስሟት ፡ መለስ ብሎ ወጥቶ ወደ ቤቱ ሄደ ።

ያን ለት ሜሪ መንፈሷ ሁሉ ተረጋግቶ ነበር ። ስለዚህም ሌሊቱም ሰላማዊና በዕረፍታ የተሞላ ሆነ ። ጧት ተነስታ ወደ እንሰሳት መጠበቂያው ፍሬድን ወስዳ ባደራ ስታስረክብ ሁሉ መልካም እንቅልፍ መተኛቷ ይሰማት ነበር ። ወደ ቤቷ አልተ መለሰችም ። በቀጥታ ወደ አየር ማረፊያ ሄደች ። ተዘናንታ ጉዞ ዋን ቀጠለች ።

ቦስተን ከተማ የደረሰችው ከምሽቱ ሶስት ሰዓት ላይ ነበር ። ቢመሽም ያንለት ማታ ጉዳይዋን ወደምታከናውንበት ቦታ ለመ ሄድ አሰበች ። ግን ደግሞ ትንሽ እንዳበዛችውም ገባት ። ያለመ መቻኮሏ ወለል ብሎ ታያት ። ስለዚህም ጉዞዋን ሲነጋ በጠ ዋቱ ማድረግ እንዳለባት ወስና መኪና ተከራይታ አደረች ።

ቦስተን የኖረችበት ከተማ ሲሆን የምታውቃቸው ሰዎች አሉ ። ሆኖም ለማንኛቸውም ስልክ ልትደውል አልፈለገችም ። ማንንም ሄዳ ልትጠይቅ አላማረችም ። ከተማውን ተዘዋውራ ለማየት እንኳ አልከጀለችም ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ያመጣት ጉዳይ አንድ ነው ። ጧት ተነስታ ትሄዳለች ። ጉዳይዋን ፈጽማ ትመለሳለች ። የመጨረሻውን አውሮፕላንም ቢሆን ተሳፍራ ወደ ሳንፍራንሲስኮ ትመለሳለች ። ሌላ ነገር የለም ።

ራሷን አንድ ቅዱስ ተልኮ ያላት ሴት አድርጋ ቆጠረች ። ወዲያ ወዲህ ሳትል እሆቴሏ ውስጥ ተቀመጠች ። ሰው የለም ። የምታውቀው ነገር የለም ። እንዲያውም እሷ ራሷም ቦስተን ውስጥ አይደለም ያለችው ። ይህ እሚሆነው ሁሉ ህልም ነው ። ሁለት አመት ሙሉ ሳያቋርጥ ያየችው ህልም ነው ። ካሁን በኋላ ያ ህልም አይኖርም ፤ በገሃድ ። አንድ ጊዜ ብቻ ነገ ብቻ ታየዋለች ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ ሠላሳ አንድ

ጧት ወደ ቢሮው እንደገባ አውሮፕላን ጣቢያ ደውሎ ሜሪ አዳምሰንን በስልክ አነጋገራት ። መሄድ ከፈለገች መቸስ ምን ማድረግ ይቻላል በማለት እንጂ የሜሪ ወደ ቦስተን መሄድ ደስ አላሰኘውም ። እንዲያውም ምንነቱን አይወቀው እንጂ ደስ የማይል ስሜትም አሳድሮበታል ። አስጨንቆታል ።

«ዶክተር ግሬግሰን» አለች ጸሐፊው ።

«አቤት» አለ ፒተር ግሬግሰን ፤ ከሐሳቡ እየባነነ እና ቀና ብሎ እያያት ።

«ማይክል ሂልያርድ እባላለሁ የሚል ሰው ቀጠሮ አለኝ ይላል ፤ ላስገባው ? »

«አዎ አስገቢው»
«ሌሎች ሶስት ሰዎችም አብረውት አሉ»
«ሁሉንም አስገቢያቸው»

ጸሐፊዋ ስትወጣ ፒተር ማይክል ሂልያርድን ማየት እንደሚፈልግ ተረዳ ። ገና ባይኑ ሳያየው ስለማይክል ከጋዜጣ ባነበበው እና በግምት ከተረዳው በመነሳት ማይክል ገና ወጣት እንደሆነ ያውቃል ። ፒተር ሊወልደው ይችላል ። ምን ዓይነት ሐሳብ ነው ! ሜሪ ይህን የመሰለ ነገር አስባ ታውቅ ይሆን ?

አራቱ እንግዶች ወደ ፒተር ግሬግሰን ቢሮ ገቡ ። ተጨባበጡ ። ተዋወቁ ። ጊዜ አላባከኑም ። ወዲያው የመጡበትን ጉዳይ ጀመሩ ። የኮተር ሂልያርድ ግዙፍ ድርጅት በሳንፍራን ሲስኮ ለሚሠራው የሕክምና ማዕከል በተለያዩ መንገድ የሚረዱትን የሕክምና ባለሙያዎችን በማስተባበር ላይ ሲገኝ ፒተር ግሬግሰንም በዚህ የባለሙያዎች ቡድን ውስጥ እንዲገባ ለመጠየቅና ሁኔታውን ለማስረዳት ነበር የመጡት ። በሳንፍራንሲስኮ



t.me/OLDBOOKSPDF

ከሚገኙት በርካታ የሕክምና ባለሙያዎች መካከል ከዚህ በፊት አሥራ አምስቱን እንጋግረው የአዎንታ መልስ እንዳገኙና ቡድኑም ሥራውን እንደጀመረም ጸሕፈውት ።

ይህን ሁሉ ከሰማ በኋላ ፒተር ግሬግሰን አሉታዊ መልስ ሲሰጥ አዳጋች ሆነበት ። ዳሩ ሲጀመርም አሉታውን መልስ አላሰበውም ። ስብሰባውን የሚከታተለው አስቀድሞ ባሰበበት መሠረት ስለነበረ ብዙም አልተመሰጠበትም ። እሱን የመሰጠው ማይክል ሂልያርድ ነበር ።

ማይክል ሂልያርድ ።

የሚያስፈራ ጠላት አይደለም ። ወጣት ነው ። ቆንጆ ነው ። በራሱ የሚተማመን ሰው መሆኑ በግልጽ ይታያል ። ግን ክፉ ሰው አይደለም ። እንደ ጠላት አያስፈራም ።

ማይክል ሂልያርድ ።

ራሷ ሜሪን ነው ። ልክ ነው ። ብዙ የሚመሳሰሉበት ነገር አላቸው ። ድፍረታቸው ፣ ቆራጥነታቸው ፣ በራሳቸው መተማመናቸው ፣ ቀልዳቸው ፣ አዎ ቀልዳቸው ሳይቀር ተመሳሳይ ነው ። አዎ ።

ፒተር ግሬግሰን ይህን ሲረዳ ደነገጠ ። ሁሉ ነገር ድፍንፍን አለበት ። ጸጥ ብሎ ዓይኑን እማይክል ሂልያርድ ላይ ተክሎ ተቀመጠ ። ስብሰባው . . . .

አዎ ስብሰባው በመካሄድ ላይ ነበር ፣ ግን . . .

ግን ፒተር ግሬግሰን አዲስ ቃል አልሰማም ። የሁለቱን ፣ የማይክልንና የሜሪን ተመሳሳይነት ካወቀበት ጊዜ ጀምሮ ቀስ እያለ ፣ ራሱን እያለማመደ ፣ ልቡን እያዋዛ እውነቱን ሊጋፈጠው ፣ ሲሸሸው የነበረውን ነገር ሁሉ ሊመረምረው ቆረጠ ።

በስተን ። ሜሪ በስተን የሄደችው ለምንድነው ? ትዝታዋን ለመቅበር ፣ ለማራገፍ ወይስ ለማክበር ፣ ለመሳለም ?. . .



t.me/OLDBOOKSPDF

ግን እኔ ማነኝ ? ምንድነኝ ? . . . አሰበ ።

ልቡ ሜሪን መከጀል—አልፎም ማፍቀር እስከደረሰበት ጊዜ ራሱን ጠይቆት የማያውቀውን ጥያቄ ጠየቀ ።

ለመሆኑ እኔ ምንድን ነኝ ? ማነኝ ? አለ ።

የሆነው ሆነና በኒህ ሁለት ፍቅረኞች መካከል መግባት አለ ብኝ ? ፍቅራቸውን የማበላሸት መብት ማን ሰጠኝ ? አለ ።

እንዲህ እያለ ማይክን አየው።ሜሪ—ማይክል። ማይክል ሂል ያርድ የሜሪ አዳምሰን ክፋይ ነው።ሌላዋ ሜሪ ነው። ፒተር ግሬ ግሰን የሚያውቃት ሜሪን ነው። ያችን ሜሪ ፒተር አያውቃትም። ብቻ ያች አደጋው ከመድረሱ በፊት የነበረችው ሜሪ ፣ ሜሪ አልነ በረችም ። ናንሲ ማክአሊስተር ነበረች ። ፒተር ግሬግሰን ደግሞ ናንሲ ማክአሊስተርን አያውቃትም ።

ላውቃት አልፈለግኩም፣ አለ በሐሳቡ ።

አዎ ፡ እሱ ሜሪን እንጂ ናንሲን ማወቅ አይፈልግም ። ሜሪ ከፊል ፍጡሩ ናት። ያችን ያለፈ ሕይወት ያላትን፣ያችን የሚጥም ትዝታ ፣ የሚመር ትውስታ ያላትን ናንሲን አያውቃትም።ሊያው ቃት አይፈልግም ። እንኳን እሱ ሊያውቃት መፈለግ፣ እሷም እንድ ትረሳት፣ ሜሪም ሜሪን እንጂ ናንሲ ማክአሊስተርን እንደሌለች ፣ እንዳልነበረች እንድትቆጥራት ይፈልጋል ።

ግን ይህ ሁሉ ከንቱ ነበር ።

ከሜሪ አዳምሰን ሌላ፣ በሜሪ ውስጥ ናንሲም ትኖራለች።ፒተር አይቱን ጨፍኖ የለችም እያለ ቢኖር እንጂ ለካ ናንሲን ሁልጊዜ ያያት ነበር— በሜሪ ውስጥ ። ናንሲን ባየ ቁጥር ፣ ናንሲ መሆኗን መመርመርን ስለሚሸሽ ለራሱ እንኳ እንዳንዴ ጠባይዋ እንቆቅ ልሽ ይሆናል ብሎ ነበር የሚነግረው ። እንጂ ናንሲስ ሁልጊዜም በሜሪ ውስጥ ትኖር ኖሯል ። አሁን ግልፅ ሆኖ ታየው ። ተስፋ ቆረጠ ።

የማይዋጉትን ጦርነት ነበር ስዋጋ የኖርኩት ሲል አሰበ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ማሪን ሲፈጥሯት ፒተር አንድ ነገር ሞከረ። ስለዚህ ማሪ አዲስ ሰው ነበረች።ከመቃብር ሲያወጧት የፈለጋት ሴት ነበረች። በመጠኑ የዚያች ሴት ደም ነበራት። እሷ ነች እያለ እያሰባት።

ሟችቷ ፍቅረኛው እየመሰለችው።

ሊቪያ— የሊቪያን ደም በገፅታዋ ላይ ዶሉ። ምናልባትም ይህን ማድረግ አልነበረበትም ይሆናል። ይህን ማድረግ ተገቢ አልነበረም ይሆናል። ከዚህ በፊት እንዲህ ልጓሙን ለቆ ሙያውን በፈለገው መንገድ የጋለበበት ጊዜ አልነበረም። በሽተኛው እንደ ለገው፤ ወይም የበሽተኛው ቤተሰብ በሚሰጠው መመሪያ መሰረት ነበር የሚሠራው። ማሪ ግን ...

ማሪ ግን፤ ያለሱ ያለፒተር ግሬግስን ማንም አልነበረችም። ይህ ደግሞ የፈለገውን እንዲሆን ነፃነት ሰጠው። የፈለገውን እንዲሆን ነፃነት ሰጥቶት ቆዬ። አሁን ግን ያ ነፃነት ምኞት፤ ተስፋ ሆኖ ታየው።

ማይክልን ሲመለከት ...

አዎ እኔ ለካ ለማሪ የአባት ያህል ነበርኩ። ነኝ። አባቷ ነኝ አለ፤ በሀሳቡ።

ማሪ ይህን ላታውቅ ትችላለች። ሆኖም ትደርስበታለች። ይዘገያል እንጂ ትደርስበታለች።

አራቱ ሰዎች ጉዳያቸውን ፈፅመው ተነሱ። ስብሰባው ተፈፀመ። ከማይክል ጋር የመጡት ሶስት ረዳቶቹ ፒተርን ተሰናብተው ወጡ። ማይክል ግን ወደ ኋላ ቀርቶ ነበረና ሶስቱ ረዳቶች እንግዳ ማረፊያ ክፍል ውስጥ ሆነው ይጠብቁት ነበር።

ማይክል ወደኋላ የቀረው የተለየ፤ በቆይታ የሚነጋገርበት ቁም ነገር ስለነበረም አልነበረም። ከፒተር ግሬግስን ጋር ይበልጥ ለመግባባት እንዲረዳው ተልዳ ተልድ፤ ገሬ ገር ነገር ለመነጋገር ነበር።



t.me/OLDBOOKSPDF

ሆነ። ፒተርና ማይክል ቆመው ገራገሩን ሲያወሩ፣ ሲሳሳቁ ሳለ ድንገት አንድ ነገር ተፈጠረ ። ገራ ገሩ ፣ ቀልዳ ቀልዱ ወሬ ቀጥ ብሎ ቆመ ። ይህን ያመጣው የማይክል ሂልያርድ አይን ነበር ።

ከፒተር ጋር እየተጨዋወተ ሲሳቁ አይኑ በፒተር ትከሻ ዘሎ አልፎ አንድ ነገር ላይ አረፈ። አንድ ቅብ ስእል ላይ ።

ሁሉ ነገር ፀጥ አለ ።

ያን ስእል ማይክል ያውቀዋል።የሷ ነው። የናንሲ ነው ። ስት ስለው ፣ ስትጀምረው አይቶታል ። እነዚያ ነርሶች ... ወደ ቦስተን አፓርትማዋ ሄዶ እቃዋ ሁሉ እንደተወሰደ አይቶ ሲጠይቅ ሁለት ነርሶች መጥተው የሳለቻቸውን ስእሎችና አንዳንድ እቃዎቿን እንደወሰዱ ተነግሮት ነበር ። ይህን ስእል ማይክል አይረሳውም ።

በሐሳቡ « እንዴት ልርሳው ! ለሰርግህ በስጦታ መልክ አበረክትልሀለሁ ብላኝ ነበር» አለ ።

ደንዘዘ። የሚያደርገውን የሚሰራውን አያውቅም ነበር ። ስእሉ አልቋል ። ማን ጨረሰው ?

አንድ ኃይል እየጎተተ ስእሉ ወደተሰቀለበት ወሰደው ። ፒተ ርም ደንግጦ ነበርና ሊያቆመው አልሞከረም ። ሊያቆመው ቢሞ ክርም የማይቻል ነገር ነበረ ። ሊያቆመው የሚችል ኃይል ከቶ ሊኖር አይችልም ።

የሰአሊውን ፊርማ ሊያይ ተጠጋ ። እንዲያው ነው እንጂ ማን ሊሆን እንደሚችል ስሜቱ ነግሮታል ። ልቡ አውቆታል ።

ሜሪ አዳምሰን ይላል ፊርማው ።

«አ ! አምላኬ ምንድነው ? አምላኬ ሆይ ! » አለ ። ገራገሰን ትኩር ብሎ ይመለከተዋል ። ማይክል ከዚህ በላይ ለማለት የማይ ችል ሆኖ ቃየው ለፒተር ።

«ቆይ፣ እንዴት ? አ አምላኪ ምነው ! እንዴት አንድም ሰው ይህን ጉድ አልነገረኝም ? ለምን...ኮ...ማን...» .



t.me/OLDBOOKSPDF

እዚህ ላይ ጽሞ አለ ። ቅድም ስሜቱ የነገረው ፣ ልቡ ያወቀው ነገር አሁን ተስተካክሎ ፣ ጥርት ብሎ ታየው ። ልክ ነው ። ናንሲ አልሞተችም ። ናንሲ በሕይወት አለች ። ግን ተለውጣለች ። ሌላ መስላለች ። ግን በሕይወት አለች ። እስዋ ናት ። ለካ . . .

ለካ እንደዚያ አድርጋ የጠላችኝ ! ልትጠላኝ ይገባታል። ግን እሱ ምንም ጥርጣሬ አልነበረበትም ። ግን ፎቶ ግራፎቹን ሲያይ.. ለካ ወደ ሆነ እማያውቀው የአስማት አገር የሚሄደው ለዚያ ነው ። ይህ ሁሉ በሃሳቡ እንደ ጉርፍ ተዥጎደጎደ ።

ለካ !

ዓይኑን የእንባ ጭጋግ ሸፈነው ። እንባውን ዱብ ዱብ እያደ ረገ ወደፒተር ግሬግሰን ዞረ ።

ፒተር ግሬግሰን ማይክልን ሲያይ ፈራው ። ፊት ለፊት ለማ የትም አልሆነለትም ።

«ተዋት ። ለስዋ ሁሉም ነገር ተረት ሆኖአል ። ቁስሏን አት ንካባት ። ካሁን ቀደም የተሰቃየችው ይበቃታል» አለ ፒተር ።

ፒተር ይህን ያለው ከልቡ አልነበረም ። ድምጹም ይህን እውነት ቁልጭ አድርጐ ያሳይ ነበረ ። ማይክልን ካየበት ጊዜ ጀምሮ የሆነውን ነገር ሁሉ ልክ እንዳይደለ ተገንዝቧል ። እንዲያውም የት እንዳለች ልንገረው ወይስ አልንገረው የሚለው ሃሳ ብም ረብሾታል ።

«ሰው ሁሉ ዋሸኝ ግሬግሰን ። ሁሉም ሰው ውሸቱን ሞቷ ለች አለኝ» አለ ማይክል ።

አሁን እንባው ይወርዳል ።

«ሁለት ዓመት ሙሉ ! ስሜትን ተራቁቼ ፣ አለምን ረስቼ ፣ እን ደለው ሳይሆን እንደሞተር ሌትና ቀን በሥራ ተጠምጄ... ብረሳት ብዬኮ ነው !

«አልቻልኩም ። ሁለት ዓመት ሙሉ እግዜርን ምነው እኔን በገደልከኝ ! እስዋን ባተረፍካት እያልኩ ስነተርከው እና ይህን ያህል ጊዜ . . .»



t.me/OLDBOOKSPDF

«ያንተስ ? ማለት ያንተና የናንሲ ግንኙነት ምንድነው ፣ ግልፅ አድርገህ እንድትነግረኝ እፈልጋለሁ »

«ያ'ንኪ አንተን የሚያገባህ አልመሰለኝም »

«ስማ ጋግርት ...»

እንደገና በኮሌታው አንቅ አደረገው ። ፒተር እጁን አንሳ መሸነፉን ለመግለፅ ። እና ፡—

«እኔና አንተ ይህን ነገር ብንተወው ምናለበት ? ሜሪ አለች አይደለም ? መልስህን ሁሉ ከሷ ታገኛለህ ። ጥያቄህን ሁሉ እሷኑ ጠይቃት» አለና ተቀመጠ ። «እኔ እንደሆንኩ አባቷ እሆናለሁ ። እንደኔ እንደኔ ከኔም ካንተም እሷ የተሻለውን መርጣ ታደርጋለች»

«ምናልባት ይሆናል ። ግን ይህንም ቢሆን ከሷው መስማት ነው እምፈልገው ። እንዲያውም እሁኑኑ እጠይቃታለሁ ፤ እቤቷ ድረስ ሄጄ »

«ወደ ቤቷ መሄድህ እንኳ ዋጋ የለውም»

«ለምን ?»

«የለችም ። አታገኛትም»

ማይክል ግራ በመጋባት ይመለከተው ጀመር ።

«እናንተ እቢሮዬ የገባችሁት ከአየር ማረፊያ ስልክ ደውላ ልኝ ተነጋግረን እንደዘጋሁት ነው»

«የት ሄደች ? ወዴት ሄደች ደሞ አሁን ?»

ፒተር ለጥቂት ጊዜ ያህል ዝም ብሎ ቆዩ ። ልንገረው እልንገ ረው አለ ። መንገር የለበትም። ምንም ነገር መንገር አልነበረበትም።

« ወደ ቦስተን ነው የሄደችው»

ይህን ሲሰማ ማይክል ለቅፅበት ያህል አይኑን በፒተር ላይ አሳረፈ ። ፈገግታ ቢጤ ፊቱን ዳሰሰውና አለፈ ። ወደበሩ የሄደው በሩጫ ነበር ። በሩን ከፍቶ ሊወጣ አሰበና ቆመ ። ዞረ ። እንዳበባ በፈካ ፈገግታ ለፒተር ስንብቱን አቀረበ ። እና ፡—

«አመሰግንሃለሁ» አለ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ ሠላሳ ሁለት

ጉሀ ሲቀድ ከመኝታዋ ተነሳች ። ድቅስቃሱ ሁሉ ለቅቋት ፣ ሙሉ በሙሉ ሕያው ሆና ። ዝንተ ዓለም ያልተሰማት መልካም ስሜት ተሰማት ። አሁን ነፃ ናት ። ነፃ የሆነች ያህል ነው ። ተቃርባለች ። ከሁለት ሦስት ሰዓት በኋላ ሙሉ በሙሉ ነፃ ትሆናለች ። ከታሰረችበት ትፈታለች ። ያ የልጅነት ቃል ኪዳን ፣ ያ የሕፃን ጨዋታ ይሆን ያህል ጊዜ ይሠራል ! ፈቀደችለታ ። የዚያ ቃል የማሰር ኃይሉ ፣ እሷ ፈቅዳ የሰጠፈችበት ኃይል ብቻ ኖሯል ለካ ።

ቁርስ በመብላት እንኳ ልትዘገይ ፣ ልትቸገር አልፈለገችም ። በቁርስ ፋንታ ሁለት ሲኒ ቡና ጠጣች ። ከዚያም እተከራየችው መኪና ውስጥ ገብታ ጉዞዋን ቀጠለች ። መንገዱ ሁለት ሰዓት ያህል ቢፈጅባት ነው ፣ ከቦስተን እስከ ጉዳይዋ ያለው መንገድ ። አራት ሰዓት አካባቢ ትደርሳለች ። ቀትር ላይ ተመልሳ ቦስተን ትደርሳለች ። ወዲያው ወደ አየር ማረፊያ መሄድ ነው ። ወደ ሳንፍራንሲስኮ የሚጓዝ አውሮፕላን ብታገኝ . . . መሸትሸት ሲል ሳንፍራንሲስኮ ከች ነው ። ከቀናትማ ፒተር ከቢሮው ሳይወጣም ልትደርስ ትችላለች ። ያ ከሆነ ደግሞ በቀጥታ ወደ ፒተር ቢሮ ሄዳ ፤ ሳያስበው ዱብ ብላ ልታስደምመውም ትችላለች ። ምናልባትም ፒተር ፣ እሄዳለሁ ስለው እኮ በጣም ተጨንቋል ። ግን ታገሰ ።

እመንገድ ላይ ሁሉ አሁንም ሐሳቧ ወደ ፒተር ይሄድ ነበር ። ስለዚህም ከከተማው ወጥታ ገጠሩን ስትያያዘው እያለፈችው የሄደችው አንድም ነገር ትዝ አይላትም ። ስለፒተር ስታስብ አሳዘናት ። ይወዳታል ። ብዙ ውሎላታል ። እሷ ግን ምንም አላደረገችለትም ። ብትችል ብዙ ብትውልለት ደስ ይላት ነበር ። ግድየለም ። ምናልባት ከዛሬ በኋላ ሁሉ ነገር ይለወጥ ይሆናል።



t.me/OLDBOOKSPDF

ላይገናኙ ተለያይተዋል ። ረዘም ላለ ጊዜ እድንጋዩ አጠገብ ቆመች ፤ ኃይል ለማጠራቀም የፈለገች ይመስል ። በመጨረሻ ጉንበስ ብላ ድንጋዩን ለማንሳት መታገል ጀመረች ። ድንጋዩ ቀስ በቀስ መንቀሳቀስ ጀመረ ። የነበረበትን ቦታ በእንጨት ቆፈረች ። አለ ብላ ያሰበችውን እዚህ ድረስ ያመጣትን ነገር ለማግኘት ። ኢንድም ነገር አልነበረም ። ድንጋዩን ለቀቀችው ። ወደ ቦታው ተመለሰ ። ተስፋ አልቆረጠችም። በእልህና ባዶስ ጉልበት ብድግ አደረገቺው ፤ ይኸኔ ግን በጣም ስላነሳችው የፈለገችው ነገር የነበረበት ቦታ ባዶ ሆኖ ታያት ። አንድ ሰው ወስዶታል ። እኒያዩ የአንገት ጌጥ መቁጠሪያዎች አንድ ሌላ ሰው ወስዷቸዋል ። ድንጋዩን ስትለቀውና ቦታውን ሲይዝ ሰማች ፤ ድምጹን ።

« ያንችን ያልሆነ ነገር ለመውሰድ መሞከር የለብሽም ። ጌጦቹ የሌላ ሰው ናቸው ። እኔ አፈቅራት የነበረች ፥ ልረሳት ያልተቻለኝ —የሷ ናቸው »

እየችው ። ማይክል ነበር ። ዓይኖቹ በእንባ ረጥበዋል እኩለ ሌሊት ላይ ነው እዚህ ቦታ የደረሰው ። በሌሊት ልትመጣ ትችላለች ብሎ ስላሰበ ሲጠብቃት አደረ ። የምታደርገውን ነገር ስላወቀ ጊዜ አልሰጠውም ። ከሳንፍራንሲስኮ ወደ ቦስተን የበረረው አውሮፕላን በግሉ ተከራይቶ ነው ። ያን ማድረግ ባይችልም ክንፍ አውጥቶ ቢበር እንኳ አይቀርም ነበር ።

እጁን ዘርግቶ የጨበጠውን ነገር አሳያት ። ያንገት ጌጦቹ ነበሩ ። ከነአሸዋቸው ። ይህን ስታይ እንባዋ ዓይኗን ሞላው ።

«ተለያይተናል ላልል ። ላልሰናበት ቃል ገብቼ ነበር ። አላደረግኩትም » አለ ማይክል ።

« የት ነች ብለህ አልፈለግከኝም »

« ሞተች ብለው ቢነግሩኝ ምን ላድርግ »

«አለሁ ልልህ አልቻልኩም »

« ለምን ፤ »



t.me/OLDBOOKSPDF

ለምትጎዳውን ፊቴን ከለወጡልኝ መኖሬን ሳልገልጥልህ . . . ቃል ገብቼ ነበር ! ! . . . ደፍሬ ቃሌን ሰጠሁ ። ምክንያቱም አንተ ይህን ውል እንደማትቀበል ተማመንኩብህ ። ትተወኛለህ አላልኩም »

«ባውቅ እመጣ ነበር ። የገባሽልኝን ቃል ታስታውሻለሽ ? »

ዓይኖቿን ጨፍና ራሷን አቅንታ በፀሎት ስሙና ማይክል ካገኛት ጀምሮ ለመጀመሪያ ጊዜ በናንሲ ማክአሊስተር ድምፅ ተናገረች ። የማይክል ልብ በፍቅር ሲቃ ዘለለ ። በደስታ ተሞላ።

«እዚህ አለች ሎሮ የተቀበረውን ነገር እስከዘላለም ላልረሳ ቃል ገብቻለሁ ። ወይም ተምሳሌት የሆነውን ነገር» አለች።

« ረሳሽው ፡ ላትረሺው ቃል የገባሽለትን ? »

ይህን የጠየቃት እንባ እያነቀው ነበር ። ስለፒተር ግሬግ ሰንና ይህን ሁለት ዓመት ስላሳለፈቸው ጊዜም እያሰበ ።

«ሞከርኩ።በጣም በጣም ሞከርኩ ። ግን አልሆነልኝም» አለች ናንሲ ።

« አሁንስ ናንሲ ? አሁን ቃልሽን ለማስታወስ አትፈልጊም ? ቃልሽን አስታውሺ . . . »

ከዚህ በላይ ንግግሩን መቀጠል አልቻለም ። አንድ ነገር ወደሷ ገፋው ። ተንደርድሮ ሄዶ እቅፍ አደረጋት ። አጥብቆ አቀፋት ።

«ናንሲ! ኡሁ ! ናንሲ በጣም እወድሻለሁ። ሁልጊዜም እወድሻለሁ ። መሞትሽን ስሰማ እኔም የምሞት መስሎኝ ነበር ። ሞተች ብዬ ሳስብ። እኔም ሞትኩ ። ልክ እንደሰማሁ ሞትኩ» አለ ጥብቅ አድርጎ እንደያዛት ።

መልስ አልሰጠችውም ። ያሳለፈችውን የስቃይ ጊዜ አስባ ፣ ይመጣል ብላ ስትጠብቀው ያሳለፈቻቸውን ወሮች ፣ ሳምንቶች ፣ ቀኖች ፣ ሰአቶች ፣ ደቂቃና ሴኮንዶች አስታውሳ ፣ ተስፋ የቆረጠች ባቸው ቅፅበቶች ፣ ብለዋት የዛሬ ደስታዋም ተደባልቆ ስሜቷን ገፍቷት ስቅስቃ ብላ ታለቅስ ነበር።እያለቀሰችም ጥብቅ አድ



t.me/OLDBOOKSPDF

ርጋ ያዘችው። ሕፃን ልጅ አሻንጉሊቱን አጥብቆ እንደሚይዝ። ለውሰድብህ ቢሉት በጄ እንደማይል፣ እንደማይለቅ።

ብዙ ቆዩ ። በመጨረሻ ትንፋሿን እንደምንም ተቆጣጥራ ፣

«እኔም. . እወድሀለሁ። የፈለገውን ብልም አንድ ቀን እንደ ምትመጣ፣ እንደምትፈልገኝ አስብ ነበር» አለች።

«ናንሲ. . .ሚሬ . . . ስምሽ የፈለገው ይሁን» አለ ማይክል።

ሁለቱም እያነቡ ሳቁ፣ እንደ ህፃን ።

«ባለቤቴ በመሆን የመጨረሻውን አክብሮት እንድታጎናፅ ፈኝ ልለምንሽ? እንዳለፈው ሳይሆን፣ በወግ በማእረግ እንድንጋባ። በሙዚቃ ፣ በድግስ. . »

ፀጥታ። እናቱን አስታወሰ ። ሰርጓን፣ ከዚያም ገረመው። ይህን ሁሉ ያደረገች እሷ (ማሪዮን) ሆና ሳለ አልተቆጣባትም፣ ቂም አል ያዘባትም ። ለምን? ገባው። ዛሬ ሁሉን ይቅር የሚልበት ቀን ነው።

ናንሲን አገኘ። በቃው ።

ጎንበስ ብሎ አያት ። አቅፏት አደረቱ ላይ ተለጥፋ ።

«እሺ?» አለ ።

እራሷን በአሉታ ነቀነቀች ፣ በጣም ።

«አይቻልም ፣ አይሆንም፣ ሙዚቃ ፤ ድግስ፤ ዳንስ ! . . . . ይኸ ሁሉ እስኪዘጋጅ መጠበቅ አለብን እንዴ! . . .»

«እሺ?» ሲል« ታገቢኛለሽ?» ማለቱ መሆኑ ሲገባት « አዎና ለምን አላገባህም፣ አሁኑኑ እንጋባ ። መቆየት አልፈልግም ። በመ ዘግዬት አልተማመንም ። አያንዳንዷ ደቂቃ ታስፈራኛለች ። ባለ ፈው የሆነው ተመልሶ የሚሆን እየመሰለኝ እሰጋለሁ ። አንተ ትመስለኛለህ የምትጎዳው . . . እንጠብቅም »

በፀጥታ ተቀበላት ። በመላ አካላቱ መስማማቱን ገለፀላት ። አንድ ጀልባ በዝግታ እየተንሳፈፈ ቀስ ብሎ ወደ ወደቡ ተጠጋ ። ደካማይቱ ፀሐይ በስተምሥራቅ በኩል ሰማዩን በስሱ ከሸፈነው ደመና ውስጥ ለውስጥ ጉዞዋን ቀጠለች ።

ሁሉም ነገር ገባው ።



t.me/OLDBOOKSPDF

**ሲታተሙ የተዘጋጁ**

| | | |
|---|---|---|
| አበሻ | – | (አጭር ልብ ወለድ) |
| ደራጐን | – | ” |
| ፋሲል | – | ” |
| እነሱ | – | ” |
| ድንገት | – | ” |
| ወንድምጌታ | – | ” |
| ፍሪዳ | – | (መካከለኛ ..ብ ወለድ) |
| ከአድማስ ባሻገር | – | (ትርጉም ቲያትር) |
| ሲራኖ | – | ” |

**የወጡ ቀደምት ሥራዎች**

| | | |
|---|---|---|
| ሮሚዮና ጁሊዬት | – | (ትርጉም ቲያ |
| ውሽንፍር | – | ረጅም ልብ ወ |
| ጠብታ ማር | – | |
| ቃል ናቸው። | | |

ባሴ ሀብቴ ውቤ በ1946 ዓ.ም. ጐጃም፣ ብቸና፣ እነማይ፣ ጓቸማ ተወልዶ ከቆሎ ተማሪነት እንስቶ በዘመናዊ ትምህርት የሁለተኛና የሶ ትምህርቱን የተከታተለ፣ በአስተማሪነትና በሌሎች መሥሪያ ቤቶች ሲያገ ወደር የለሽ ቢባል የማይበዛበት ድንቅ አንባቢ፣ ድንቅ ዐሐፊና ሀያሲ፣ ከι ደግሞ ትሁት ቅንና ተግባቢ፣ አስተዋይ ሩህሩህ ፍቅር ሰጥቶ ፍቅር ለመቀ ታላቅ ጓደኛ፣ አገሩንና ሕዝቡን ወዳድ ሆኖ ኖሮ አብልጦ በሚወዳቸውና ሲናፍቃቸው የኖረውን ወደ እናቱ እማሆይ ዛብሽ ወርቅነህ ተመልሶ በመጨ የሕይወት ቀናቶቹ ከወላጆቹ ጋር በተወለደበት ቀዬ አሣልፎ ግንቦት 7 ቀን 1988 የተለየን የልብ ወንድማችን ነው። በሥራዎቹ ግን ዛሬም ሕያውና ከእኛ ጋር ነ

አብዱራህማን ናስር ታነ



t.me/OLDBOOKSPDF

